# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት

በዲያቆን ስሎሞን ዮሐንስ

መጋቢት 27 ቀን 2001 ዓ.ም
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

© ዲ/ን ሰሎሞን ዮሐንስ 2001 ዓ.ም

## መታሰቢያነቱ

ያለ አባት እናት፤
ያለ ግድ በውድ፤
ያለ በትር በፍቅር፤
ያለ ኩርፊያ በፈገግታ፤

ከማህፀን ጀምሮ እሁን እስካለሁበት እድሜ ድረስ
ማንኛውንም ችግር ተቋቁማ የተሸከመችኝና
የእናትነት ፍቅሯ ዘወትር የማይለየኝ
ለወላጅ እናቴ
**ለወ/ሮ ሙሉ ተገኝ**
ይሁንልኝ፡፡

## አበርክቶት

በበረከትና በፀጋ ላሳደገኝ በአገልግሎት አንደበቴን
ለከፈትኩበት ላለሁበት ደብር ለቅዱስ እግዚአብሔር አብ፤

ጊዜያቸውንና ከእግዚአብሔር የተለገሳቸውን እድሜ
በአግባቡ ተጠቅመው፤ ራሳቸውን ሳይሆን ቤተ
ክርስቲያናቸውን ለዓለም አስተዋውቀው በክብር ላረፉ
ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን፤

ቤተ ክርስቲያን የሚገባትን መብት በመጠበቅ ከጠላቶቿ
በመከላከል የተዋህዶን እምነት ጠብቀው ላስረከቡን
በድል ለኖሩና በክብር ላርፉ ነገሥታቶቻችን፤
ይህን መጽሐፍ አበረክታለሁ፡፡

## ምስጋና

ይህን መጽሐፍ እንዳዘጋጅ የረዳኝ ስፍገመገም ምርኩዝ፤
ስሰደድ ህገር፤ ሲታወክ ፀጥታ፤ ሳዝን ደስታ ለሆነኝ፤
አስቀድሞ የወደደን፤ ጠላቶቹ ሳለን የወደደን፤ ልጁን
በወደደበት መጠን የወደደን፤ የፈለገውን ነገር ሁሉ እና
የዘመናት እቅዱን በልጅ በኩል ላከናወነ
**ለቅዱስ እግዚአብሔር አብ**
ክብር ምስጋና ይግባው!
አሜን!

ወጣት አገልጋዮችን በማረበታታት የተማረው የሰው ኃይል
በቤተ ክርስቲያን ተገቢ ቦታቸውን እንዲይዙ የሚጥሩትን
ለእኔም ቤተ ክርስቲያንን እንዳገለግል የረዱኝን የአዲስ
አበባ ህገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ
**ብፁዕ አቡነ ሳሙኤልን፤**

አገልግሎቴን በማክበር ቅን ሐሳባቸውን ከተግባር ጋር
የሚለገሱኝን የማገለግልበት ቤተ ክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ
የሆኑት ክቡር አባቴን
**መልአከ ገነት ቆሞስ አባ ገ/ሥላሴ ጸባይን፤**

የዘወትር ተባባሪዬ የወልደ ነጐድጓድ
ቅ/ዮሐንስና የመካነ ጐልጐታ ቅድስት ማርያም
ቤተ ክርስቲያን ዋና ጸሐፊ
**መ/ር ሰሎሞን በቀለ ዘነበን፤**

www.ethiopianorthodox.org

በአገልግሎቴ የሚደግፈኝን ለራሴ ከማስበው
የበለጠ ዘወትር የሚያስብልኝን ወንድሜ
**ቀሲስ ተሾመ ገ/ሥላሴ**

በአሜሪካ የምትኖረው እህቴ **አስቴር ለማ**፣
ወንድሜ **ሚካኤል እሸቱ /አቢቲ/**

ጽሑፌን በትዕግሥት በመጻፍ ለአንባቢ እይታ እንዲስብ
በቂ ጊዜዋን ለግሳ ለኅትመት እንዲመች አድርጋ
የጻፈችልኝ የዘወትር ተባባሪዬ
**ሠናይት መላኩን፤**

በእግዚአብሔር ስም ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

መጽሐፉን ሳዘጋጅ ከጐኔ በመሆን በጐ
ሐሳብሽን ከተግባር ጋር የለገስሽኝን፣ ዝግጅቴ
የተሳካ እንዲሆን በጸሎትሽ በማሰብ፤ የምፈልገውን
ሁሉ በማቅረብ የተንከባከብሽኝን ክብርት እጮኛዬን
**ፍቅርተ ማርያም /አይቲን/**
እጅግ በጣም አመሰግንሻለሁ ያንቺ ማበረታታት
ለዝግጅቴ መሳካት ግብአት ሆኖኛልና::

በመጨረሻም በዚህ የምስጋና አምድ ላይ ስማቸውን
ያላነሳሁትና በጐ የሚያስቡልኝን ሁሉ በዚህ አጋጣሚ ከፍ
ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

# ማውጫ


ገጽ

መቅድም ........ 1
መግቢያ ........ 4
- ትምሕርት በኢትዮጵያ ........ 5
- ብሔራዊያን ሊቃውንት ........ 7
- ሥነ ጽሑፍ በኢትዮጵያ ........ 8
- የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እድገት ........ 10
- ሥነ ጽሑፍና ነገሥታቶቻችን ........ 12
- ታሪካዊ ቅርሶች ........ 13
- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በቅርስነት የያዘቻቸው ........ 14
- ቅርሶች ለሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ ........ 16
- በቤተክርስቲያናችን የተካሔዱ ሐዋርያዊ ተልዕኮዎች ........ 19
- ሐዋርያዊ ተልዕኮ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ........ 20
- የቤተ ክርስቲያን ኪነ ጥበባት ........ 23

**ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን** ........ 27
- በመጽሐፍ ቅዱስ ........ 27
- ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ ........ 28
- የኢትዮጵያ መልክዐ ምድር አቀማመጥ የሕዝቦቿ ጸባይ በታሪክ ሰዎችና በፈላስፎች ........ 29
- የኢትዮጵያ ጥንታዊ ግዛት ........ 31
- የኢትዮጵያ ጥንታዊ ንግድ ........ 32
- ጥንታዊው የኢትዮጵያ ወደብ አዱሊስ ........ 33
- የኢትዮጵያ የኃይል አቋም በጥንት ዘመን ........ 34
- ኢትዮጵያ በስልጣኔ ........ 35
- አክሱምና ሐውልቶቿ ........ 36
- አክሱምና ሥነ ጽሑፎቿ ........ 38
- አክሱምና ገንዘቦቿ ........ 39
- ገንዘቦቹ የተሠሩባቸው ዘመናት አከፋፈል ........ 40
- አክሱም በከርሰ ምድር ጥናት ምርምር ........ 45
- ኢትዮጵያ በሃይማኖት ........ 48



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ አንድ


- የመጀመሪያው ወርቃማ ዘመን ..... 51
- የንግሥተ ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም መሔድ ..... 52
- የንግሥተ ሳባ ከኢየሩሳሌም መመለስ የቀዳማዊ ምኒልክ መወለድ ..... 52
- ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ አባቱ ንጉሥ ሰሎሞን መሔድ ..... 53
- ቀዳማዊ ምኒልክ ኢየሩሳሌም መድረስ ..... 54
- ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ኢትዮጵያ መመለስና፤ ታቦተ ጽዮን መምጣቱ፤ የምኒልክ መንገሥ፤ ለታቦተ ጽዮን ምኩራብ-መቅደስ መሠራት ..... 55
- ንግሥተ ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም የሔደችበት ምክንያት ..... 58
- የጽዮን በዓል አከባበር ..... 59
- ቀዳማዊ ምኒልክ ያሠራው መቅደስ ..... 60


## ምዕራፍ ሁለት


- ሁለተኛው ወርቃማ ዘመን ..... 63
- በኢትዮጵያ ለተመሠረተችው ቤተክርስቲያን በር የከፈተ ሐዋርያ ..... 63


## ምዕራፍ ሦስት


- ሦስተኛው ወርቃማ ዘመን ..... 68
- አቡነ ሰላማ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያደረጉት አስተዋጽኦ ..... 72
- የአባ ሰላማ አስተዋፅኦ በውጭ ግንኙነት ..... 75
- የኢየሩሳሌምን ርስት አስጠብቀዋል ..... 75
- መንበራቸውን ዓለም አቀፋዊ ዕውቅና እንዲያገኝ አድርገዋል ..... 76
- ከኢትዮጵያ ውጭ የነበረውን የእምነት እንቅስቃሴ ተከታትለዋል ..... 77
- የአብርሃ ወአጽብሐ እረፍት፤ የአቡነ ሰላማ የስማቸው ስያሜና እረፍታቸው ..... 78


## ምዕራፍ አራት


- አራተኛው ወርቃማ ዘመን ..... 83
- የተሰአቱ ቅዱሳን መምጣት፤ የቅዱስ ያሬድ መነሣትና የተቀጸል ጽጌ አከባበር መጀመር ..... 83
- የምንኩስና አጀማመር ..... 87
- የምንኩስና መሥራች አባ እንጦንስ ..... 88
- መቃርዮስ ዘገዳመ አስቄጥስ ..... 90
- የአንድነት ገዳም መስራች አባ ጳኩሚስ ..... 91
- ስለ ልብሰ ምንኩስና ጥንታዊነትን የያዘ ምሳሌ ..... 94
- አቡነ አረጋዊ ገዳም ..... 95
- የደብረ ዳሞ ገዳም መመስረት ..... 97
- አቡነ ጰንጠልዮን ገዳም ..... 100
- ዐፄ ካሌብ ወደ የመን ለመዝመት አቡነ ጰንጠልዮንን የጸሎት እርዳታ መጠየቁ ..... 101
- የአቡነ ጰንጠልዮን ገዳም ይዞታና ገድላቸው ..... 103
- የቤተክርስቲያኑ አመሠራረት ..... 104
- በገዳሙ ውስጥ ያሉ ጥንታውያን መጻሕፍት ..... 105
- አባ ይምአታ ገዳም ..... 106
- አባ ገሪማ ገዳም ..... 107
- አባ ጽሕማ ገዳም ..... 108
- አቡነ አፍጼ ገዳም ..... 110
- አባ ሊቃኖስ ገዳም ..... 112
- አባ አሌፍ ገዳም ..... 113
- አባ ጉባ ገዳም ..... 114
- የተሰአቱ ቅዱሳን አስተዋፅኦ ..... 116
- የቅዱስ ያሬድ መነሳት ..... 117
- የቅዱስ ያሬድ ትውፊት ..... 122
- የዜማ ምልክቶች ትርጉም ..... 125
- የተቀጸል ጽጌ በዓል አከባበር መጀመር ..... 128


## ምዕራፍ አምስት


- አምስተኛው ወርቃማ ዘመን ..... 132


### ክፍል አንድ


- የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት ..... 132
- ቤተ ማርያም ..... 135
- ቤተ መድኃኔዓለም ..... 136
- ቤተ ጎልጎታ ..... 136


www.ethiopianorthodox.org

- ቤተ አማኑኤል ........ 138
- ቤተ መርቆሬዎስ ........ 138
- ቤተ አባ ሊባኖስ ........ 139
- ቤተ መስቀል ........ 140
- ቤተ ደናግል ........ 140
- ቤተ ገብርኤል ........ 141
- ቤተ ጊዮርጊስ ........ 141


### ክፍል ሁለት


- የሥነ ጽሑፍ መዳበርና፮ ሐዋርያዊ ተልዕኮ፤ እንቅስቃሴ መስፋፋት ........ 145
- በዐፄ አምደጽዮን ዘመነ መንግሥት የተተረጐሙና የተጻፉ መጻሕፍት ........ 148
- የገድላት መጻሕፍት ........ 150
- የገድላት መጻሕፍት ዓበይት ዓላማ ........ 151
- ታሪካዊና ሥነ ጽሑፋዊ ጠቀሜታቸው ........ 152
- መልክአ ........ 153
- ሐዋርያዊ ተልዕኮ መስፋፋት ........ 154


### ክፍል ሦስት


- ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ........ 159


### ክፍል አራት


- የገዳማት መስፋፋት በጣና ሐይቅ ዙሪያ ........ 167
- ዳጋ እስጢፋኖስ ........ 168
- ዘጌ ደሴት ........ 170
- መሐል ዘጌ ጊዮርጊስ ........ 171
- ኡራ ኪዳነ ምሕረት ........ 172
- ደብረ ማርያም ገዳም ........ 172
- ክብራን ገብርኤልና እንጦንስ ገዳም ........ 173
- ደብረ ሲና ማርያም ገዳም ........ 176
- ኮታ ማርያም ገዳም ........ 176
- አዝዋ ማርያም ........ 177
- ምንዳባ መድኃኔዓለም ........ 178


### ክፍል አምስት


- አባ ጊዮርጊስ ........ 179
- ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንዳይፋለስ ጠብቋል ........ 181
- ብቃት ያለው ሥነ ጽሑፍ አቅርቧል ........ 181
- በሐይቅ ምን አይነት ትምህርት ይሰጥ እንደነበር ድርሰቶቹ ምንጭ ሆነዋል ........ 183
- የአባ ጊዮርጊስ እረፍት ........ 184
- ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የአባ ጊዮርጊስ አስተዋፅኦ ........ 186


### ክፍል ስድስት


- በዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት የገባው ግማደ መስቀል ........ 188


### ክፍል ሰባት


- ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ ለቤተ ክርስቲያን ያደረገው አስተዋፅኦ ........ 193
- በዘመነ መንግሥቱ የተስፋፋው ሥነ ጽሑፍ ........ 198


### ክፍል ስምንት


- በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የተነሱ ቅዱሳን አባቶች ........ 201
- ቤተ ክርስቲያን ለቅዱሳን የምትሰጠው ክበሬታ ........ 202


## ምዕራፍ ስድስት


- ስድስተኛው ወርቃማ ዘመን ........ 209
- የዐፄ ፋሲል ዘመን ........ 209
- ዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ........ 214
- በዘመኑ የነበሩ ታላላቅ መምህራን ........ 218
- ደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ........ 220


## ምዕራፍ ሰባት


- ሰባተኛው ወርቃማ ዘመን ........ 224


### ክፍል አንድ


- በዐፄ ዮሐንስ፣ በዐፄ ምኒልክ፣ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ፣ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ........ 224
- በአገር ውስጥ የሠሯቸው ........ 224
- በውጭ ሀገር ያከናወኗቸው ........ 229


### ክፍል ሁለት


- በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ........ 231
- የዐፄ ምኒልክ አስተዋፅኦ በቅዱሳት መካናት ........ 232


www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ሦስት


- በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ........ 233
- ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ........ 234
- ሢመተ ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን ........ 236
- የቅዱሳት መካናት ይዞታ ማስጠበቃቸው ........ 237


## ምዕራፍ ስምንት


- ስምንተኛው ወርቃማ ዘመን ........ 238


### ክፍል አንድ


- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ........ 238
- ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ........ 238
- በተለያዩ ክፍለ ሀገር ያሠሯቸው አብያተ ክርስቲያናት ........ 244


### ክፍል ሁለት


- አምስተኛው የሥነ ጽሑፍ ዘመን ቅዱሳት መጻሕፍትን በማሳተም የንጉሡ ነገሥቱ ባለውለታነት ........ 245


### ክፍል ሦስት


- መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች መስፋፋትና ስብከተ ወንጌል መጠናከር ........ 251
- መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ........ 251
- የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ........ 253
- የቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ........ 254
- ስብከተ ወንጌል መጠናከር ........ 255


### ክፍል አራት


- የውጭ ግንኙነትን ማሳደግ ........ 257
- የአምስቱ እህት አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ /ስብሰባ/ በአዲስ አበባ መስተናድ ........ 260
- የጉባኤው መስተንግዶ ቅድመ ዝግጅት ........ 260


### ክፍል አምስት


- በኢኩሜኒካል ግንኙነት ባለውለታዎች ........ 268
- አስደናቂው የአቡነ ቴዎፍሎስ ንግግር ለግብጻውያን ........ 271


### ክፍል ስድስት


- የፐትርክና መንበረ መገኘት ........ 273
- ዋቢ መጻሕፍት ........ 277




በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

## መቅድም

ሰው በዚህ ዓለም ከለመኖር ወደ መኖር በአምላክ ፈቃድ የመጣው የተሠጠውን እድሜ በቁም ነገር ላይ አሳልፍት እንዲኖር ነው:: ሰው ከጊዜ ወደ ጊዜ ለመሻሻል ይጥራል መጣርም አለበት:: ትውልድ እንዴት እንደኖረና የዘመኑም እውቀት ምን እንደነበር ለማወቅ ይደክማል ማወቅም ይገባል:: የፈረሡ፣ የተቀበሩ ጥንታዊ ቤተ መንግሥቶች፣ ከተሞች እና አብያተ ክርስቲያናትን ከህብቶቻቸው ጋር፤ የወደሙትንና የዘመን ጥርስ የበላቸውን በከርሠ ምድር ጥናት (ARCHEOLOGY) እየመረመረ በዘመናት ብዛት የጠፉትን ቅርሶች ከአዲሱ ትውልድ ጋር ለማስተዋወቅ ይታገላል ትግሉም ተገቢ ነው::

ጥንታዊውን የእውቀትና የታሪክ ቅርሶች ለማየት ፍላጐት ያላቸው ሰዎች በበዙበት በዚህ ዘመን መልካም ስምና ዝና ከማትረፋቸውም በላይ:: ከጐብኝዎች የሚገኘው ገቢ ለህገር ኢኮኖሚ ግንባታ ታላቅ ድጋፍ ሆነዋል:: ስያሜውም:- «ጭስ አልባው ኢንዱስትሪ» በመባል የሚጠራው የቱሪዝም መስክ ነው:: እንግዲህ እንዲህ አይነት አሰሳ ከሚደረግባቸውና ለምርምራቸው አመርቂ ውጤት ከሚገኝባቸው የዓለማችን ጥቂት ሀገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ናት:: የህገሪቱ ሙዚየም ሆና እያገለገለች ያለችው ደግሞ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ናት::

ቀደምት አባቶች ስማቸውና ዝናቸው እየተጋነነ በክብር የሚጠሩት፤ ትውልዱም በመልካም አስተያየት ከፍተኛ ሥፍራ የሚሰጣቸው በዚህ ዓለም በመኖራቸው ብቻ ሳይሆን ለትውልድ ባቆዩት የታሪክ ቅርስ ነው:: ከእግዚአብሔር የተሠጠን እድሜ የአጭር ጊዜ እንግዳ መሆናችንን ስለሚያስገነዝበን የምንሸኘውም ባልታወቀ ጊዜ ውስጥ መሆኑን በመረዳት እውነተኛ ሀሳባችንና ሥራችን በተተኪው ትውልድ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

የማይረሳ አስመስጋኝ ቅርስ መሆን አለበት ቅርሱም ምንድን ነው? ሲባል «የእንግድነቱ ሕይወታችን የደስታ ጊዜ፣ ሙታንነታችን በሕያውነታችን ይለወጣል» ትውልዱ ይህን በእምነት ተመልክቶ ከቀደምት አባቶች የተረከበውን በዓላማ የመኖር ቅርስ ያለምንም ችግር ሊጠብቀው ይችላል።

የዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ዓላማ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባሳለፈቻቸው ዘመናት ያገኘችውን መንፈሳዊ በረከት በአጭሩ ለማስጨበጥ ነው። እነዚህ መንፈሳዊ በረከቶች ትውልድን የሚቀርፅ ስለሆነ የመጽሐፉ ርዕስ፡- «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት» በመባል ተሰይሟል። ዘመናቱንም በ8 ዋና ዋና ርዕሶች ከፍዬ አቅርቤዋለሁ። ይህ ደግሞ የአቅሜን ያህል በመጣር እኔን መሰል ወጣቶች ለማነቃቂያ፣ በዚህ ዙሪያ ጥልቅ እውቀት ላላቸው ደግሞ የበለጠ ነገር ሠርተው [ምክንያቱም እያንዳንዱ ወርቃማ ዘመን ራሱን የቻለ መጽሐፍ ሊወጣው ስለሚችል] ሌላ ፍላጋ እየባዘነና የራሱን እየጣለ የሌላውን እያንጠለጠለ የሚኖር፣ ወይም ደግሞ ወደ ብዙ ቦታ ሲሔድ ወደ ራሱ መሔድ ላልቻለ [ራሱን መፈለግ ለተሳነው] ትውልድ መታደጊያ ይሆናልና ይህን ለማስገንዘብ ፍንጭ ይሆናቸዋል ብዬ ሙሉ በሙሉ ባላስብም ያልተዳሰሰ ብዙ ነገር እንዳለ ይጠቁምልኛል በማለት ተዘጋጀ ነው።

ለቀጣዩ ትውልድ መልካም ሥራን ትቶ ከማለፍ የበለጠ የሚያስደስት ነገር የለም። ከዚህ ተቃራኒ ደግሞ አንዳንድ ሰዎች በሀሳባቸው የቤተክርስቲያኗን የአገልግሎት አቅድን ለማቋቋም ይሰለቹና ሌላው በሚሰራው ሥራ ውስጥ ድክመትን አግኝቶ ለመተቸት ይቸኩላሉ። ይህ አይነት ፀባይ ለቁም ነገር አለመታደል ነው ምክንያቱም ከጥፋት ሁሉ የበለጠ ጥፋት ቁም ነገርን ማጥፋት ነውና።

የምንመኘውን ሁሉ በቀላሉና በእውነተኛ መንገድ ለማግኘት የማይቻል መስሎ ከታየን የከበረው አዕምሮአችን የተንኮል ብቻ ምንጭ ይሆናል። እንዲህ አይነቱ የውስጥ በሽታ ለራሳችን የሚያስከትለው አንደኛው ትዝብት የነገን





ውርደት በመጭው ትውልድ ስናገኝ፣ ሁለተኛው ደግሞ በዚህ ትውልድ ላይ የሞት ፍርድ በእጻ ወስኖ ከማለፍ ይቆጠራል። ይህ አይነቱ ሕይወት እውነትን ስለማያሳየን ከእውነተኛ ሰዎች የሚፈልቀውን የመንፈስ ማርኪያና የኑሮ መደሰቻ የሆነውን «የቅን ሀሳብ ጣዕም» ሳንረዳ ከዚህ ዓለም ልናልፍ እንችላለን። ከእንዲህ አይነት ዓላማ ከሌላቸው ሰዎች የምንጠበቀው ነገር ባይኖርም የሌላውን ሕይወትና የቤተ ክርስቲያንን ህልውና እንዳያናጉ ግን ያሰጋል። ስለዚህ ለዝምታ ለቸልታ ስላልተፈጠርን፡- ባናስብም የሚያስበውን፣ ባንናገርም የሚናገረውን፣ ባንሠራም የሚሠራውን፣ ባናስተምርም የሚያስተምረውን ማወቅ አለብን።

የዚህ መጽሐፍ መረጃዎች ሁሉ በህገራዊ ሥራዎች ያተኩሩ ናቸው። ለዝግጅቴ ይጠቅማል ያልኳቸውን ከ1920 ዓ.ም ወዲህ ይህ መጽሐፍ እስከተዘጋጀበት ገዜ ድረስ የታተሙ መጻሕፍት፣ መጽሔት፣ ጋዜጦች፣ እንዲሁም በመጽሐፍ መልክ ያልተጠረዙ የታይፕ ጽሑፎችን ለማገላበጥ ሞክሬአለሁ። ከመረጃ ጋር የቀረበ ነገር ለአንባቢው የበለጠ ግንዛቤ፣ ለአቅራቢው ደግሞ የአዕምሮ ነፃነትን እንደሚሰጥ የታመነ ነው። ለዚህ ብቻ ሳይሆን ጸሐፊዎቻቸውና ጽሑፎቻቸው የሚታወቁት በምንጮቻቸው ነውና።

እንዲህ አይነት ሥራዎች ጥልቅ ጥናት እንደሚጠይቁ የታመነ ነው። ካሳተምኳቸው መጽሐፍቶች በይዘት ትልቁ ይህ ስለሆነ፡- ስህተት ቢገኝ በማረም፣ የተጣመመውን በማቃናት፣ የጐደለውን በመሙላት በተጨማሪ ካለውና ከነበረው ተዘጋጀ እንጂ፣ በየዘመናቱ የተሠሩትን ወርቃማ ታሪኮች ጐላ ያሉትን ብቻ እንዳስፈርኩ ከወዲሁ እንድትረዱኝ እያሳሰብኩ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባሳለፈችው ዘመናት ያገኘችውን መንፈሳዊ በረከት በመጠኑ እንድትነገነዘቡ የአቅሜን ያህል ደከሜ ያዘጋጀሁትን ይህን መጽሐፍ ለቤተ ክርስቲያን ክብርና ለተከታዮቿ ራስን የማወቅ መንገድ እንዲጠርግ በመመኘት በብዙ ደስታ ለንባብ ሳበረክት ራሴን ዝቅ በማድረግ ነው።

አዘጋጁ



www.ethiopianorthodox.org

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ማለት የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ማለት ነው። ሁለቱን ነጣጥለን መመልከት አንችልም። ቤተ ክርስቲያንና ኢትዮጵያ የአንድ መጽሐፍ ሁለት ገፅታዎች ናቸው። እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ በኢትዮ ጵያ የነገሡ ነገሥታት የተቀቡት በቤተ ክርስቲያናችን ስለ ነበር ቀብታ ያነገሠቻቸውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸውን የመጠበቁና የማስጠበቁን መብት ከፍተኛ ድርሻ ተወጥተ ዋል።[1] በዚህ መጽሐፍ ዝርዝር ሐሳቦች ይህን በተመለከተ ተንፀባርቋል።

ኢትዮጵያ ጥምቀተ ክርስትና በ34 ዓ.ም ከተቀበለች በኋላ፣ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብር ሃን የወንጌል ትምህርት መሠረቱ እስከ አሁን ያልተነዋወፀ ቤተ ክርስቲያን ተመስርታለች። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን[2] ከዚህ ክፍለ ዘመን ጀምራ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የማኅበራዊ ኑሮ መስራች በመሆን እርዳታዋን በዘመኑ ሁሉ ስታቀርብ ኖራለች። ክርስትና በኢትዮጵያ ያለው ንጹሕ ሃይማኖታዊ ይዘት ብቻ ሳይሆን በብሔራዊ ሕይወትም ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ተቋም ብቻ ሳትሆን የሕዝቦቿ ባሕላዊና ማኅበራዊ ሕይወትም

---

[1] በኢትዮጵያ አመራር ውስጥ ሶስት ሰዎች ጐልተው ይታዩ እንደነበር እንረዳለን እነዚህም:- ዐፄ /ንጉሡ/፣ እቴጌ /የንጉሡ ባለቤት/፣ እጨጌ ናቸው። እጨጌው ከጳጳሱ ጉን በመሆን የቤተክርስቲያኗን ሥጋዊ አስተዳደር ይመራ ነበር። እንዲሁም የመሬቱን ስሪት በሦስት የተከፈለ ሲሆን፣ ይኸውም አንደኛው ሢሶ ለነጋሢ (ለንጉሡ ወይም ለመንግሥት)፣ ሁለተኛው ሢሶ ለእነጋሢ (ለሕዝብ እርስ ለሚተዳደር ገበሬ) ሦስተኛው ሢሶ ለቀዳሲ ለቤተ ክርስቲያን መገልገያ ለካህናት መተደደሪያ በሚል ተደልድሎ ነበር።

[2] የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስንል [የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን] ማለታችን ነው። በዚህ ሀገር ያሉ እምነቶች «ኢትዮጵያ» የሚለውን ተጋርተውታል። እደ እውነቱ ከሆነ፣ በኢትዮጵያ ያሉ የካቶሊክ እምነት ተከታዮች፣ በኢትዮጵያ የሚገኙ የኘሮቴስታንት እምነት ተከታዮች መባል ይገባቸው ነበር እንጂ፣ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን፣ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን መባል የለባቸው። ምክንያቱም በሀገራችን የተመሠረተችው እንዲት ቤተ ክርስቲያን ስትሆን፣ የተቀሩት ሀገር በቀል አይደሉም።





ተጠብቆ ያለባት ናት። ስለዚህ የታሪክ ምንጭ መሆኗ ታምኖባታል። ለሥነ ጽሑፍ እድገት ለታሪካዊ ድርጊቶች አመዘጋገብ ይውል ዘንድ በግእዝ ጽሑፍ መልክና ቅርጽ የሰጠችው ይህችው ቤተ ክርስቲያን ነች። ለመግቢያ ያህል በዚህ መጽሐፍ ከምናገኛቸው ታሪኮች በመነሳት በሚከተሉት ዝርዝር ሐሳቦች መገንዘብ ይቻላል።

## ትምሕርት በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያበ ረከተችው አገልግሎት መጠኑ ቀላል አይደለም። ለምሳሌ ፀፄ ምኒልክ «ዳግማዊ ምኒልክ» ብለው በራሳቸው ስም የሰየ ሙትን ት/ቤት እስኪከፈት ድረስ የትምህርት ሚኒስቴርነቱን ሥራ ይዛ የኖረችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ናት። እነዚህ ትምህርት ቤቶች ጥንታውያን ገዳማት ናቸው።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ገዳማት ከ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ድረስ የሥነ ጽሐፍ፣ የታሪክ፣ የማኅበራዊ ሕይወት፣ የትምህርት በጠቅላላው የኪነ ጥበብ መገኛዎች ሆነው መኖራቸው የታወቀ ነው። ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚወጡት ደቀ መዛሙርት፣ ቀሳውስት መነኮሳት ብቻ ሳይሆኑ ህገራችንንም የመሩ ነገሥታትም ተገኝተውበታል። ቤተ ክርስቲያን ያቀረበቻቸው ሊቃውንት በእውቀት ብቻ ሳይሆን በታማኝነት፣ በደግነት በሃይማኖት በምግባር የጐለመሱ በመሆናቸው ለማኅበራዊ ኑሮአችን ያቀረቡት ከፍ ያለ መስዋዕትነት ከነገሥታት አንዳንዶች፣ ከቤተክርስቲያን አባቶች ደግሞ ብዙዎች በስማቸው ታቦት ተቀርጾላቸው ቤተክርስቲያን ታንጾላቸው ይታሠባሉ። እንግ ዲህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አረመኔዎችን ለማሳመን ከመጣሯና በየዘመኑ የሚነሡ ጠላቶቿን ከመከላከል በቀር በታሪኳ ውስጥ የክርስትና ሕይወቷ የተቋረጠበት ጊዜ የለም። ለዚህም ምክንያቱ:-



www.ethiopianorthodox.org

- ⇨ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በየአካባቢው መቋቋም፤
- ⇨ በችግሯ ጊዜ ጥለው የማይጠፉ አባቶችን በማፍራቷ፤[3]
- ⇨ ሕዝቡ ለአብነት መምህራንና ተማሪዎች የነፃ ትምህርት እድል በመስጠቱ፤[4]

እነዚህና በሌሎች ተዛማጅነት ባላቸው ትውፊቶች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወቷ ሳይቋረጥ ተጠብቃለች:: ይህን የሚሠለውን ኢትዮጵያዊና ኦርቶዶክሳዊ ባሕል የሚመለከት ሁሉ/እንዲህ ይላል:- «ለኢትዮጵያ ታላቁ ሐዋርያዋ ባሕሏ ነው መምህር ባይኖር ከባሕሏ ትማራለች» ሲሉ የሚመሠክሩት:: ይህ ራስን በራስ የማስተማር ባሕሏ ለዛሬው ሐዋርያዊ ተልዕኮዋ አስተዋፅኦ አድርጐላታል:: እንግዲህ አክሱም አጠገብ በቤተ ቀጢን[5] የተጀመረው የአብነት ት/ቤቶች ምንጭ ለዛሬው ዘመናዊ ትምህርት በቤተ ክርስቲያኒቱ እና በሀገሪቱ ውስጥ መስፋፋት ምክንያት ነው::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርት ከሌሎች ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናትና ከአይሁድ የትምህርት ዘይቤዎች ጋር ቀረቤታ እንዳለው ይገለጻል:: ነገር ግን ከ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት በአውሮፓም ሆነ በኢትዮጵያ ይሰጥ የነበረው የትምህርት ዓይነትና ይዘት ተመሳሳይ ሲሆን በአውሮፓ በሃይማኖት ተመሥርቶ ከሃይማኖት ጋር ይሄድ የነበረው ትምህርት ወደ ከፍተኛ ደረጃ ሲደርስ በኢትዮጵያ ግን የጥንቱ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ብቻውን ከቤተ ክርስቲያን ጋር ይገኛል::[6]

---

[3] በዮዲት ጉዲት፤ በግራኝ መሐመድ፤ በሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት፤ በደርቡሾች በኢጣሊያ ወረራ....፤ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ችግር ያደረሡ ስዎችን ተቋቁመው አጥሯ ጥብቅ መሠረቷ ጥልቅ እንዲሆን ያስቻሉ ሰማዕታትን በማፍራቷ::

[4] በዓለም ላይ የነፃ ትምህርት እድል /ስኮላር ሽፕ/ የጀመረችው ሀገራችን ናት:: ይኸውም:- በነፃ በማብላት፣ በማጠጣት፣ በማልበስ፣ ብሔራዊያን ሊቃውንትን ለሀገሪቱና ለቤተ ክርስቲያኒቱ ሕዝቡ አበርክቷል::

[5] ይህ ቦታ የአንግዶች ማረፊያና ትምህርት ቤት ነው:: ስሃገር የሚኖሩም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ስለ ኢትዮጵያ ባሕል ቋንቋ የሕዝቧ ጠባይ በተመለከተ የሚማሩባት ቦታ ናት:: ለምሳሌም:- ቅዱስ አባታችን አቡነ ሠላማ ካሣቴ ብርሃን በቀዳማዊ አልአሜዳ ዘመን ሲመጡ፤ የአክሱም ሊቀ ካህን የነበረው እንበረም ለ7 ዓመታት የኢትዮጵያን ባሕልና ቋንቋ ያስተማራቸው ሲሆን፤ ተስአቱ ቅዱሳን በዳግማዊ አልአሜዳ ዘመነ መንግሥት ሲመጡ ያረፉበትና ለአገልግሎታቸው በር ከፋች የሚሆናቸውን ቋንቋ አጥንተውበታል::

[6] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓ.ም በሚለው መጽሐፍ ውስጥ በዶክተር አግደው ጓዴ የቀረበውን ጥናት ይመለከቷል::





# ብሔራዊያን ሊቃውንት

በመምህራን በኩል የነበረውን ሕይወት ሥንመለከት፤ የጥንት መምህራን ኑሮአቸው ቀላል የሆነ የብህትውና ኑሮ ነበር:: አብዛኛዎቹ ንብረትና ጥሪት የሌላቸው ፍፁማን መናንያን ነበሩ:: እንደነዚህ ያሉ መምህራን ከትምህርታቸው ይልቅ ኑሮአቸው የበለጠ ደቀመዛሙርቶቻቸውን ወደ በጐ ነገር ይማርካል:: በእርግጥ ብዙ ጊዜ ነገሥታትና መኳንንት እንዲሁም አንድ አንድ የሴት ወይዛዝርት መምህራኑን ከደቀ መዝሙሩ ጋር እየረዱ ያለ ችግር እንዲኖሩና እንዲያስተምሩ ያደርጋሉ:: በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በርካታ ብሔራዊያን ሊቃውንት አበርክታለች::

ለምሳሌ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት መዕርግ ከሠጣቸው የቤተክርስቲያን ሊቃውንት አንዱ አለቃ አየለ አለሙ ማስታወሡ ይበቃል:: በ1867 ዓ.ም በጭልጋ አውራጃ የተወለዱት አለቃ አየለ ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሙያ ጠንቅቀው ከማወቃቸውም በላይ በማስተማር ዘመናቸው ደከመኝ ሠለቸኝ ሳይሉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን አገልግለዋል:: የዕለት ተግባራቸው ከጠዋቱ 1 ሰአት እስከ 7 ሰአት በንቃትና በትጋት አራቱን ጉባኤ በየተራ ሲተረጉሙ ይውሉ ነበር:: ሰአት ካልበቃቸው ከቀትር በኋላ ካላቸው ጊዜ ወስደው ያሟላሉ:: ይህ የከሰአት በኋላ ጊዜ ያቸው የዝግጅት ነው:: የተዛባውን ምስጢር ለማቃናት የጐደለውን ንባብ ለማሟላት ሲሉ መጻሕፍትን በመመልከት ያሳልፋሉ:: በመምህርነት እውቀት በቻ ሳይሆን:-

- ⇨ ሐብተ ጸሎት፤
- ⇨ መንኖ ጥሪት፤
- ⇨ ውሂበ ምፅዋት፤
- ⇨ ፍቅረ ቢጽ የተሠጣቸው ነበሩ::

ከደግነታቸው የተነሳ ቀለባቸውን በሚቀበሉበት ቀን ለችግረኞች አከፋፍለው በመጨረስ ባዶ እጃቸውን ወደ ቤታቸው ይገቡ ነበር:: ይህን ታላቅ ሀብት ያደነቁት ታላቁ ሊቅ ሐዲስ ተክሌ /በኋላ አቡነ ዮሐንስ/ «ሽስቃ ሽዩስ



www.ethiopianorthodox.org

*የሚደነቁት በሊቅነታቸው ብቻ አይደለም:: በጣም የሚያስገርመው በዓለም ላይ ሰለጥኛ ያለው አፍቅሮ ነዋይ እንዳት እንደጠፋላቸው ነው»* ብለዋል:: እኝህ ታላቅ ሊቅ ቤተክርስቲያንን ብቻ ሳይ ሆን ውዷ ሀገራቸውንም ጭምር በመልካም ኅሊና በጥሩ ስብዕና በማገልገላቸው በ1960 ዓ.ም በሰኔ ወር የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ማዕርግ ሰጥቷቸዋል:: በዚህም ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት የመጀመሪያው ለመ ሆን በቅተዋል:: የዕድሜ ባለፀጋ ሆነው በተወለዱ በ102 ዓመታቸው ጥር 17 ቀን 1969 ዓ.ም በጐንደር ከተማ አርፈው ሥርዓት ቀብራቸው እዚያው በመንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ተፈፅሟል::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሣቴ ብርሃን ሰላማን ያህል ታላቅ አባት ከሳለፈች 1 ሺ 600 ዓመታት አስቆጥራ ለች ሆኖም ፀሐይ ሲገባ ኮከብ እንደሚወጣ ሁሉ ቤተክርስ ቲያናችንም ደቀ መዝሙሩን በመምህሩ ወንበር ላይ በመሰ የም የተቀበለችውን የክርስትና እምነት ሳትለቅ ጥምቀቷን ሳታረክስ ቁርባኗን ሳታፈርስ እስከ አሁን ተጠብቃ ቆይታለች::

## ሥነ ጽሑፍ በኢትዮጵያ

ከጥንታዊ ትምህርቶች መካከል ሥነ ጽሑፍ ዋነኛው ነው:: ሥነ ጽሑፍ የተለያዩ ብያኔዎች አሉት በአጠቃላይ በሦስት ይከፈላል:-

1. የተጻፈ ነገር ሁሉ ሥነ ጽሑፍ ነው:: እንጨት፣ በራና /ወረቀት/ ላይ ሊጻፍ ይችላል ይህ ሥነ ጽሑፍ ይባላል::
2. ሥነ ጽሑፍ ማለት ታላላቅ መጽሐፍት ናቸው ከተጻፉትም ውስጥ ለሰው ልጅ ክፍተኛ አስተዋፅኦ ያላቸው ወይም በስፋት የሚነገሩ ሁሉ ሥነ ጽሑፍ ይባላል::
3. በፈጠራ መልክ የሚቀርብ ምናባዊ ጽሑፍ ሥነ ጽሑፍ ተብሎ ሊጠራ ይችላል::

የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ የሚባለው በምን ቋንቋ የተ ጻፈ ነው? ቢባል በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉት ናቸው:: በሳብኛና በዕርዕ /በግሪክ/ ቋንቋዎች የተጻፉ ቅርሶች አሉ:: እነዚህ ጽሑፎች ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ናቸው





አንልም:: የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ እድገት ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው::

ሥነ ጽሑፍ ዐይን ያየውን፤ ጆሮ የሰማውን፤ በአንደ በት የተነገረውን፤ በሀሳብ የመነጨውን፤ አዕምሮ በማመዛዘን የተመለከተውን፤ በርቀት አቅርቦና አጉልቶ የሚያሳይ የሥነ ጥበባት አንደኛው ክፍል ነው:: ሥነ ጽሑፍ የተገኘውና የሚ ገኘው ከትምህርት ዓለም ሲሆን፤ ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ የሰው ልጅ ያደረገውን ምርምር ጥናት ሊያገኝ የቻለው ከሥነ ጽሑፍ ዓለም መሆኑ ግልፅ ነው:: ማንኛውም ነገር በሥነ ጽሑፍ መልክ ሠፍሮ በመረጃነት ቀርቦ የሚታይ ከመሆኑም በላይ ሊቃውንት የሚደክሙበትን የምርምር ውጤት በሥነ ጽሑፍ ሕግና ሥርዓት ተመዝግቦ በመጽሐፍ መልክ ተጠርዞና ተደጉሶ እንዲነበብ ለማድረግ የሚቻለው በዚሁ አንፃር መሆኑ የታወቀ ነው:: ከዚህ የተነሳ በቤተክርስቲያን ዙሪያ ጥልቀት ርቀት ያለው ሀሳብ ለማፍ ለቅ፤ ለሰሚው ለተመልካቹና ለአንባቢው የተጣራ የተስተካከለ ሥነ ጽሑፍ ማቅረብ የሚቻለው:-

- ⇨ ብቃትና ፍፁምነት ያለው ቅዱስ አባት በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ የእግዚአብሔር አፍ ሆኖ በመናገር በማስተማር የተናገረውን ትምህርት በመጻፍ፤
- ⇨ በጥንታውያንና በዘመናውያን የሥነ ጥበባት ቋንቋዎች የተጻፉትን ደህና አድርጐ በማንበብና በመተርጐም አገናዝቦ አሳክቶ መጻፍ ሲቻል ነው::

ቅዱሳን አባቶች በከበረው አዕምሮአቸው በዳበረ እው ቀታቸው ያፈለቋቸውን ጥበባት በመጻሕፍት አምዶች ላይ ተመዝግበው ለመታየትና ለመነበብ የቻሉት በእነሡ ጥረትና ተጋድሎ ነው:: እነዚህ አባቶች የፈፀሙት ሥራ ምንም እንኳ ፈራሹ አካላቸው በሙታን ከተማ በመቃብር ለመኖር ቢገደ ድም «የጊዜው ሩጫና የሰነፎች ግልምጫ» ሳይደመስሰው የማይሞተው ስማቸው ከመቃብር በላይ ሆኖ የሚመሰገነው ወደር በማይገኝለት የሥነ ጽሑፍ ሥራቸው መሆኑን መገን ዘብ አለብን::



www.ethiopianorthodox.org

# የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እድገት

በዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ እምነት 5 የሥነ ጽሑፍ ዘመናት ተካትተዋል:: በመሆኑም አዘጋጁ የመጀመሪያ የሥነ ጽሑፍ ዘመን ብሎ ያስገባው ዐፄ ገብረ መስቀል የነበረበትን ዘመን ነው:: ይሁን እንጂ ይህ ዘመን ቅዱስ ያሬድና የተሰአቱ ቅዱሳን የጸበሩበት ዘመን እንደመሆኑ መጠን ቅዱሳት መጽሕፍት የታጻፈበትና የተተረጐመበት ወርቃማ ዘመን ነው:: ስለዚሁ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ የለም ወይ? ወደ ማለት ድምዳሜ እንዳንደርስ አስቀድሜ አሳስባለሁ:: የኢትዮጵያን ታሪክ ይህና አድርገው ያጠኑ ሊቃውንት ከዐፄ ከገብረ መሥቀል በፊት በኢዛና ዘመን ሥነ ጽሑፍ እንደነበር አረጋግጠዋል:: በንጉሥ ኤዛና ዘመን የነበሩ ሥነ ጽሑፎች በሁለት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን::

1 የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ተገኝተዋል:: የግዕዝ ቋንቋ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው በድንጋይ ላይ ነው:: ይህም:-

- ኤዛና ክርስትና ከመቀበሉ በፊትና፣
- ኤዛና ክርስትና ከተቀበለ በኋላ የተጻፉ ናቸው::

እነዚህ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ይዞታቸው የጀግንነት ሥራ፣ ድል የነሡባቸው ጦርነቶች፣ የኃያላን ነገሥታቶቻቸው ዝና፣ የአማልዕክቶቻቸው ጠባቂነት፣ ረዳትነት፣ ለሞቱ ዘመዶቻቸው ባነፁት መቃብር ላይ የሚገልፁባቸውን ስሜት አስፍረዋል:: እነዚህን መሠል የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ያጠኑት ጀርመናዊ ተወላጅ የሆኑት «ኢሎን ሊትማን» ይባላሉ::

2 በኤዛና ዘመንም ሆነ ከዚያ በኋላ በብራና ላይ የተጻፉ ሥነ ጽሑፎች አሉ:: ከእነዚህም መካከል የመጀመሪያውን ቦታ ይዞ የሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: አ4ቱ ወንጌላት በአቡነ ሠላማ ከሣቴ ብርሃን ተተርጉሞ ነበር:: ፍጻሜ ያገኘው በተስአቱ ቅዱሳን ጊዜ ነው:: የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ የትርጉም ሥራ እየሆነ የመጣው ከዚህ ጊዜ አንስቶ ነው:: ከመጀመሪያው የሥነ ጽሑፍ ዘመን በፊት በድንጋይና





በብራና ላይ የተጻፉ ሥነ ጽሑፎች መኖራቸውን ለማመልከት ነው:: ሆኖም ግን በኤዛና ዘመን በፊትና በኋላ የተተረጐሙ ሁለት መጻሕፍቶች መኖራቸው ተረጋግጧል:: እነዚህም:-

**«መጽሐፈ ቄርሎስ»** ስሙን የወረሰው በመጽሐፉ መጀመሪያ ላይ የመግቢያ ሀተታ የተመዘገበው በጸሐፊው በቄርሎስ ስም ስለሆነ ነው:: ይህ መጽሐፍ ሦስት ክፍሎች አሉት:-

- ❄ የቄርሎስ ሀተታ መግቢያ፣
- ❄ ስለ ቅድስት ሥላሴ፣
- ❄ ስለ ክርስቶስ ባሕርያት ትንታኔ፣
- ❄ መጽሐፍን ለመጻፍ ያነሳሳው ንስጥሮስንና ተከታዮቹን ለመቃወም መሆኑን ያመለክታል::

**«ሥርዓተ መነኮሳት»** የመነኮሳትን አስተዳደርና አኗኗር የሚገልፅ መጽሐፍ ነው:: የብኅትውና ሕይወት ከጀመሩት አንዱ ግብፃዊው አባ ጳኩሚስ መነኮሳት የሚተዳደሩበት ሕግ አውጥቶላቸዋል:: ይህም በዕርዕ፣ በሱረስት፣ በላቲን ቋንቋ ተጽፎ በክርስትናው ዓለም ተሰራጭቷል:: «ሥርዓተ መነኮሳት» ተብሎ ወደ ግዕዝ ተተርጉሟል:: ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምንኩስና ደንብ መሠረት የሆነ መጽሐፍ ነው:: እነዚህ ለአብነት ያህል ከመጀመሪያ የሥነ ጽሑፍ ዘመን ብዬ ከሰየምኩት ከዐፄ ገብረ መስቀል በፊት የነበሩ የትርጉም ሥራዎች ናቸው::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ጽሑፍ እዚህ ደረጃ የደረሰው ከትንሽ ነገር ተነስቶ ነው ማለት ይቻላል:: እላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት የሀገራችን የመጀመሪያዎቹ ሥነ ጽሑፍ የተገኙት በተጠረቡ የድንጋይ ሰሌዳዎች ላይ፣ በተጨማሪ በትልልቅ አሸዋማ ድንጋዮች ላይ ነው:: ሰፋ ያሉ ሙሉ ዜና የያዙ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እኩሌታ ላይ የተጻፉ የንጉሠ ነገሥት ኢዛና ሀገርን የማቅናት ዜናዎች የሚተርኩና፣ በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተቀረፁትን የተጻፉት የዐፄ ካሌብና ከልጆቻቸው አንዱ ያደረጓቸውን ዘመቻ



www.ethiopianorthodox.org

ዎች የሚናገሩ ወደ 70 ሴ.ሜ ቁመት ያላቸው የድንጋይ ስሌዳዎች ዋናዎች ናቸው::[7]

ከዚህ በተጨማሪ የአንዳንድ ነገሥታት አድራጐት የሚገልፁ በብሮንዝ /መዳብ/ እቃዎች ላይ የተጻፉ አጫጭር ጽሑፎችም በየቦታው ተገኝተዋል። እነዚህ ሁሉ በመጽሐፍ አይነት እየተሰፋፉ ወጹ ዘመናችን ለደረሰው የሥነ ጽሑፍ ሙያ የመጀመሪያ መሠረቶችና ወደ ዋናው ያደጉ ሥልጣኔ ያችን ሲሆኑ፤ እነሡን ለማጥናት የተከታተለ ሰው እየተሻሻለ በመሔድ የተለመደውን የሥነ ጽሑፍ ሙያ መረዳት ይቻላል።

## ሥነ ጽሑፍና ነገሥታቶቻችን

በዚህ ሥነ ጽሑፍ ሙያ ላይ ነገሥታትም ተሳትፈ ዋል። የዐፄ ናኦድ ልጅ ዐፄ ልብነ ድንግል በቤተ ክህነት ትምህርት እየተማሩ ያደጉ ናቸው። ያስተማራቸውም ስርፀ ድንግል የሚባል ታላቅ ምሁር ነው። ዐፄ ልብነ ድንግል በቤተ ክህነት ትምህርት የጠለቀ እውቀት ስለነበራቸው ብዙ መዝሙሮችን ደርሰዋል። ለኖህ ሐመሩን፤ ተፈስሂ ማርያምን፤ ለአዳም ፋሲካሁን፤ አርህርተ ህሊናን ደርሰዋል። በተጨማሪ በስደታቸው ጊዜ የእመቤታችንን ስብሐተ ፍቁር ደርሰዋል ተብሎ ይታመናል። ይህም:- «ኀዘና ስምዒ ውብካያ ለህገሪ ትነ ኢትዮጵያ» ስለሚል በስደታቸው ጊዜ መደረሱን ፍንጭ ይሠጥናል። ሁሉም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዛሬም በዜማ ይፀለይባቸዋል።

ከዚህ ሌላ በዘመነ መንግሥታቸው የተለያዩ መጻሕፍ ትን ከአረብኛ ወደ ግዕዝ አስተርጉመዋል። ዮሐንስ አፈወርቅ የተረጐመውን የዕብራውያንን መልዕክት በ1515 ዓ.ም እጨጌ እንባቆምና ግብፃዊው ጳጳስ አቡነ ሚካኤል ወደ ግዕዝ ተር ጉመውታል። በሁለተኛ ዓመት ንግሳቸው ገድለ ጊዮርጊስ

[7] አርኪዮሎጃዊ ቀፋሮ፤ ገጽ 34።





ወደ ግዕዝ የተተረጐመ ሲሆን፤ መጽሐፈ ሐዊ የተተረጐመ ውም በዚሁ ዘመን ነው። ይህ ንጉሥ ለሥነ ጽሑፍ ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ማድረጉን እንረዳለን። መታሰቢያውም መስከረም 5 ነው። ትልቅ የሥነ ጽሑፍ ዘመን የሚባለው የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ነው። ይህን በመጽሐፍ ውስጥ በቦታው እንመለከታለን።

## ታሪካዊ ቅርሶች

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪካውያን ቅርሶች በዓለም ዙሪያ ከሚገኙት ጥንታውያን ታሪካውያን አብያተ ክርስቲያናት ጋር በቀደምትነት፣ በስልጣኔ፣ በባህል፣ በቋ ንቋ፣ በሥነ ጽሑፍ፣ በኪነ ጥበብ በቅርስ ክምችት...፤ የመሳ ሰሉት አኩሪና አስደናቂ ነገሮች ሁሉ የበላይነት አላት። ይህ የተገኘው በቀደሙት መንፈሳውያን አባቶች ጥረት ነው። ቤተክርስቲያናችን ከተመሠረተችበት ጊዜ አንስቶ እስከ ዛሬ ህልውናቸውን ጠብቀው የቆዩና ያሉ ሳይሆኑ፤ በየክፍለ ዘመናት የመቃጠል፤ የመፍረስ እድል እየገጠማቸው ሲሆን፤ እኟዲየውም ብዙዎች ጥንታውያን ታሪካውያን የሚባሉት ገዳማቶቻችን እንደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞተው የተነሡ ናቸው።

ከዚህ ትውልድ በፊት የነበሩ ቅዱሳን አባቶች ስለ መንፈሳዊ ብቃታቸው ብቻ አይደለም የምናከብራቸው። በዘመናቸው የነበረው የኪነ ጥበባት እውቀት በቴክኖሎጂ ተራቀናል ከሚሉት የዘመናችን ጠበብት በምንም አይነት የማያንሱ መሆናቸው ነው። እነዚህ ቀደምት አባቶች እውቀ ትን፣ ጥበብን፣ ትዕግስትን፣ ፍቅርን ገንዘብ ያደረጉ ስለነበር ዋሻ ፈልፍለው፣ ድንጋይ ሰብረው፣ እንጨት ጠርበው፣ አብ ያተ ክርስቲያናትን ማነፅ፣ ከድንጋይ ከአፈር፤ ከአበባና ከቅጠል ልዩ ለዩ ህብርና መልክ ያላቸው የቀለም አይነቶች በማዘጋጀት ከፈረስ ከፍየል ከበግ ቆዳዎች እየፋቁና እየዳመጡ ብራና በማውጣት ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደየ መጽሐፍቱ ታሪክ ደግሞ ታሪካዊ ስዕሎችን በመሳል በሐረግ በማስጌጥ ዘላለማዊ ሥጦታ አበርክተው አልፈዋል።



www.ethiopianorthodox.org

ቅርሶችን በተመለከተ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰፊ መድብል ናት። ቅድመ ክርስትና ጀምሮ በኢትዮጵያ ሐውልቶችን ቀርጾ በመትከል፤ ታላላቅ ቤተ መንግሥቶችን፤ መቃብረ ነገስታቶችን በማነፅ፤ ከብረት፣ ከነሐስ፣ ከመዳብ፣ ከወርቅ፣ ከአልማዝ፣ ከመሳሰሉት ከቡራት ማዕድናት እያነጠሩ ቤተ መንግሥትን በማስዋብና በማስጌጥ ጥበብ ዳብሮባት የነበረችው የአክሱም ከተማ በይበልጥ የሥጋዊና የመንፈሳዊ ጥበብ ምንጭ የሆነው የክርስትና እምነት ከገባበት እለት ጀምሮ አቡነ ሰላማ ከእስክንድሪያ ይዘዋቸው ከመጡት ንዋየ ቅድሳት[8]፤ አይነቶችን መሠረት የደረጉ የእደ ጥበባትና የሥነ ጥበብ እውቀት በይበልጥ እያደገ እየዳበረ ስለሔደ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እፁብ ድንቅ የሚባልላቸው ሃይማኖታዊ ቅርሶች ባለቤት ለመሆን በቅታለች።

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በቅርስነት የያዘቻቸው

የክርስትና ደሴት ተብላ የምትጠራው ሀገራችን የቀደመ ታሪክ፤ የታሪክ ዘመን ቅርሶች ሙዚየም በመባል ስትታወቅ 90% ያህሉ ራስዋን ቤተክርስቲያናችንና የቤተ ክርስቲያን ቅርሶች የሚያመለክት ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በ2ሺ ዘመናት የክርስትና ታሪኳ በቅርስነት የምትጠቅሰው ከዚህ በታች ያሉትን ነው።

- ❄ የአዋጅ መንገሪያና መጥሪያ ደወልና ቃለ አዋዲ /ቃጭል/ ነጋሪት፤
- ❄ ከአብነ በረድና ከዕፅ የተቀረፁ ልዩ ልዩ ንዋየ ቅድሳት፤
- ❄ ከአለት ተፈልፍለው የታነፁ አብያተ ክርስቲያናት፤

[8] እነዚህን ንዋየ ቅድሳት ይዘው የመጡት ከ20ኛው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ አትናቴዎስ መሆኑን ገድሉን ዋቢ በማድረግ ቤተ ክርስቲያናችን ገልጻለች። ገድሉም «ከዚህ በኋላ የሊቀ ጵጵስና የክብር ልብስ አልብሶ በክቡረ መንበር ላይ አስቀመጠው የከበሩ አልባሳትን፤ ንዋየ ቅድሳትን፤ ቅዱሳት መጽሐፍትን፤ ገድላትን፤ ድርሳናትን፤ የቤተክርስቲያን ጌጣ ጌጥን፣ መስቀልን ጽንሐሕ፤ አዘጋጅቶ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ አትቴዎስ ይህን ሁሉ ንዋያተ ቅድሳት ሰጥቼሀለሁ። ነፃ ለምታደርግና የእግዚአብሔር ታቦተ ሕግ ለሆነችው ታቦተ ጽዮን አበርክት» በማለት ንዋየ ቅድሳት ሰጥቶታል። [የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲየን ትናንትናና ዛሬ፤ ገጽ 57]





- ❄ ከጥርብ ድንጋይ የታነፁ አብያተ ክርስቲያናት፤
- ❄ የቤተ ክርስቲያን ባለመጾር መስቀሎች፤
- ❄ የጳጳሳት የካህናት የእጅ መስቀሎች፤
- ❄ የቁርባን ፃህል ፅዋና እርፈ መስቀል፤
- ❄ የዝማሬ ከበሮ ፅናፅል መቋሚያ፤
- ❄ የቅዱሳት ብራና መጽሐፍት፤
- ❄ ሥዕላተ ቤተ ክርስቲያን፤
- ❄ ልብሰ ተክሕኖ ጽንሐሕ፤
- ❄ የሕጽበት ሰንና ብርት፤
- ❄ መሶበ ወርቅ ማኅተም፤
- ❄ መጐናጸፊያ፤
- ❄ ድባብ ጥላ፤
- ❄ ኩስኩስት፤
- ❄ መጫሪያ፤
- ❄ አትሮንስ፤
- ❄ ምንጣፍ፤
- ❄ መጋረጃ፤
- ❄ ቀንዲል፤
- ❄ አውድ፤
- ❄ ዘውድ፤
- ❄ ሰፌድ፤
- ❄ ጭራ፤

የወግና የባህል እቃዎች ሁሉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልባቸውና በቅርስነት ጠብቃቸው የኖሩና ያሉ ናቸው።[9] እስከ አሁን ድረስ በሰሜን ኢትዮጵያ በተደረጉት የጥናትና የምርምር ሥራዎች የአክሱም ሥርወ መንግሥትና ሥልጣኔው እስከተዳከመበት ድረስ የነበረው የታሪክ ቅርሶች አሰሳና ፍለጋ በብራና የተጻፉ መጽሐፍት በብዛት ማግኘት ባይቻልም ሌሎች የመቅደስ ኦሪት መገልገያ የነበሩ ታቦተ ጽዮን ከኢየሩሳሌም ስትመጣ በንዋየ ቅድሳትነት አብረው የመጡ በጥንታውያን ምኩራቦች አገልግሎት ይውሉ የነበሩ እነዚህም:-

[9] ዝኒ ከማሁ ገጽ 58-59፤ አክሱማዊት ፋና ወጊ ገጽ 44-45።



www.ethiopianorthodox.org

- መሶበ ወርቅ፤
- ተድባበ ወርቅ፤
- ማእጠንተ ወርቅ፤
- ተቅዋመ ወርቅ፤
- ደብተራ መንበር፤
- ደብተራ አሪት፤
- ጽንሐና መስዊያ፤
- ጽላት፤

የመሳሰሉት ሁሉ በመቅደሰ ኦሪት ያገለግሉ እንደነበር «ሥርዓተ ጽዮን ጊዜ ምፅአት» የተባለውን መጽሐፍ በመግለጽ ቦታውን ያጠኑ ሰዎች ጠቅሰዋል።[10] በዚህ መሠረት በአክሱም፣ በየሓ፣ በመጠራ፣ በአዶሊስ፣ በአጉላእ፣ በሐውዘን፣ በጉሎ መኸዳ፣ በሐውልቲ መናዞ፣ በሰግላሜን፣ በተደረገው አርኪዮሎጂዊ ምርምር ከተገኙት ጥንታዊ ቅርሶች መካከል ከላይ ከተዘረዘሩት የመቅደሰ ኦሪት ንዋያተ ቅድሳት ጥቂቶቹ ተገኝተዋል።

## ቅርሶች ለሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ

የዓለም ቱሪዝም ድርጅት ቱሪዝም ለድኅነት ቅነሳ፤ ለሥራ እድል ፈጠራ፤ እንዲሁም ለማኅበራዊ ደኅንነትት አንቀሳቃሽ ኃይል ሊሆን እንደሚችል ከመቼውም ጊዜ የበለጠ በአሁኑ ዘመን እየገለጠ ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ክፍለ ዓለም አንዷ በመሆኗ የጥንት ቅርስ ክምችት ያላት ለመሆኑ በዓለም አቀፍ ሊቃውንት በየጊዜው ትኩረት እየሳበች ያለች ሀገር ናት።[11]

ለየት ያለ መልክና ውበት ያላት፤ ደጋውና ወይና ደጋው፤ ቆላውና በረሀው፤ ተራራውና ሸንተረሩ፤ ስምጥ ሸለቆው፤ ታላላቅ ወንዞችን ንዑሳን መጋቢ ወንዞች፤ ሰፋፊና መጠነኛ ሐይቆች፤ ልዩ ልዩ የዱር አውሬዎች፤ አዕዋፍ፣ ለሀገራችን የተሠጣት የተፈጥሮ ፀጋ በተለይ የሰውን ልዩ

[10] አክሱማዊት ፋና ወጊ፤ ገጽ 44።

[11] ለምሳሌ በ1964 ዓ. ም በአፍሪካ አዳራሽ የተካሔደው የአፍሪካ አቀፍ ሀገሮች ቅድመ ታሪክና አራተኛውን ደረጃ የሊቃውንት ምርምርና ጥናት ጉባኤ ማስታወሱ ይሰቃል [አርኪዮሎጂዊ ቁፋሮ ገጽ 50]





ስሜት የሚማርኩ ናቸው። ለሥነ ጽሑፍ ደራሲዎች፤ ለቅኔ ባለሙያዎች፤ ለሰአሊዎች፤ በጠቅላላው ለኪነ ጥበብ ሰዎች ሁሉ አድናቆታዊ ስሜታቸውን በአስፈለጋቸው አይነት ለመግለፅ ያስችላቸዋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ታላቅ ቦታ ያላት፤ አስደናቂ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙባት፤ ታላላቅ ታሪካዊ ዋጋ ያላቸው የብራና መጻሕፍት የተከማቹባት፤ የእምነቷ ታሪክ ለዘመናት ያልተቋረጠባት፤ በሌላው ዓለም የጠፉ መንፈሳዊ በዓላት የሚከበሩባት፤ ሀገራችን እነዚህን ፀጋዎቿን በደንብ ብታስተዋውቃቸው ለሀገር ኢኮኖሚ ታላቅ ድጋፍ ይሆናሉ። ሌሎች ሀገሮች በቱሪዝም በኩል በሚያገኙት ገቢ የተደላደለ ሕይወትን በመምራት ላይ ይገኛሉ።

የሀገራችን ቱሪዝም ያስቀመጠልንን መረጃ ብንመለከት፤ እላይ የጠቆምኩትን ግልፅ ያደርግልናል። በአፍሪካ ውስጥ የቱሪዝም ተጠቃሚ የሆነች ሀገር ቱኒዝያ ናት። ይህቺ ሀገር በ1999 ዓ.ም 4.831 ሚሊዮን ቱሪስቶችን አስተናግዳ፤ 1.56 ቢሊዮን ዶላር ገቢ አግኝታለች። ግብፅ በ1999 ዓ.ም 4.797 ሚሊዮን ቱሪስቶችን አስተናግዳ 3 ቢሊዮን ዶላር አግኝታለች። ጐረቤት ሀገር ኬንያ በዚሁ ዓመት 894 ሺህ ቱሪስቶች ጐብኝተዋት 304 ሚሊዮን ዶላር አግኝታለች። ደቡብ አፍሪካ በ1999 ዓ.ም 6.026 ሚሊዮን ቱሪስቶች የጐበኛት ሲሆን 2.526 ቢሊዮን ዶላር ገቢ አግኝታለች።

ወደ ሀገራችን ስንመለስ ከሌሎች አንፃር ስንመለከተው ብዙ ይቀረዋል። /ሰብ ሰሃራን/ ከተባሉት ሰሜናዊ አፍሪካን ከማይጨምሩት የአፍሪካ ሀገሮች የ2002 ዓ.ም መረጃን ሳንጨምር ከ4 በላይ የዓለም ቅርሶች ያላቸው ሀገሮች ቢፈለጉ ኢትዮጵያ ቀዳሚውን ቦታ ይዛ ትገኛለች። 8 ቅርሶቿ የዓለም ተብለው ተመዝግበውላታል።[12] ይህ ሁሉ ሀብት ኖሯት እላይ

[12] ዩኔስኮ የኢትዮጵያን ቅርስ ከሚያደንቅበት ምክንያቶች አንዱ ቅርሶቻችን ስብጥር ስለሆኑ ነው። ይህም:- ሰው ሰራሽ፤ የተፈጥሮ፤ የአርኪዮሎጂ፤ ሲሆኑ። እነዚህ ሦስት የቅርስ አይነቶችን በመያዟ ሰዓለማችን እነዚህን ካሟሉ ጥቂት ሀገሮች ኢትዮጵያ አንዷ ናት።



www.ethiopianorthodox.org

ከጠቀስናቸው ሀገሮች ከእነሱ የበለጠ ሀብት እያላት ገቢዋ ይህን ይምስላል:-

የሀገራችን ቱሪዝም ቢሮ ከተቋቋመ ከ1957 ዓ.ም ጀምሮ ነው:: በዚህ መሠረት ከ1966 ዓ.ም 74 ሺ ቱሪስቶች ወደ ሀገራችን ገብተው ነበር:: ይህ ከለውጡ በፊት መሆኑ ነው:: ከለውጡ በኋላ በ1970 ዓ.ም ወደ 28 ሺ ሊወርድ ችሏል:: በ1982 ዓ.ም የቱሪስቶች ቁጥር 80 ሺ ገቢው ደግሞ 52 ሚሊዮን ብር ደርሶ ነበር:: በ1995 ዓ.ም 56.237 ሺ ቱሪስቶች ሀገራችንን ጐብኝተው 77 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል::[13] እድገት ቢኖረውም ከሌሎች አንፃር ብዙ ይቀረዋል:: ይህን ጭስ አልባው ኢንዱስትሪ ተብሎ የተሰየመውን የቱሪዝም መስክ የማይገባበት ክፍለ ኢኮኖሚ የለም::[14]

እንግዲህ በዚች በተቀደሰች ሀገር ላይ ተወልዶና አድጐ፣ በመንፈሳዊ ሀብትም በልፅጐ በዚህ ሀብት ላይ የማዘዝ ፍፁም ነፃነት አለ ለማለት የሚያስደፍረው እቦታው ድረስ ሄደን በአይን የማየት እድል ሲኖረን መሆኑን ብዙዎች ኢትዮጵያውያን አልተገነዘብነውም:: ሌላው ቀርቶ የዚህ ሁሉ ታሪክ ባለቤት የሆነችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የውጭ ሀገር ሰዎች በልዩ ልዩ መጽሐፍቶችና እትሞቻቸው ስለ ሀገር ጉብኝታቸው በሚያወጧቸው ጽሑፎች ማስጌጫ አድርገው እያተሙ መልሰው ለእኛ ሲሸጡልን፣ የሀገራችሁን ታሪክ እወቁ ሲሉን በእኛና በእነሱ መካከል ስላለው ልዩነት ከዚህ የበለጠ ምን እስተዛዛቢ ነገር አለ::

እዚህ ላይ ሳልጠቅስ የማላልፈው በቱሪስት ስም ገብተው ሀብት ዘርፈው አስዘርፈው ወደ ባህር ማዶ ያሻገሩ ሰዎች አሉ:: በእነዚህ አማካኝነት ወጥተው የአውሮፓን

[13] ይህ መረጃ የተገኘው «አዲስ ድምፅ» ጋዜጣ መስከረም 23 ቀን 1996 ዓ.ም ባወጣው እትሙ ከዚሁ ባለሙያ ጋር ከተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ላይ የተወሰደ ሲሆን፣ ከዚህ በኋላ ያለውን መረጃ ለማካተት የመረጃ እጥረት ስለገጠመኝ አልፈዋለሁ::

[14] ቱሪስቶች አየር መንገድ፣ የሚያርፉበት ሆቴል፣ ስልክ፣ ምግብ፣ የስጦታ እቃዎችን፣ የመኪና ነዳጅ...፣ ይፈልጋሉ:: ስለዚህ የማይነካው ክፍለ ኢኮኖሚ የለም::





ሙዚየሞች ያጣበቡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ንብረቶች እጣቸውን ምን ይሆን::[15]

## በቤተክርስቲያናችን የተካሔዱ ሐዋርያዊ ተልዕኮዎች

በዚህ መጽሐፍ ወደፊት እንደምንመለከተው ጐላ ጐላ ያሉ ሐዋርያዊ ተልዕኮዎች ተካሒደዋል:: በ4ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ ወደ ሀገራችን የገቡት 9ኙ ቅዱሳን አንድ ቦታ ተሰብስበው ከመኖር ይልቅ መንፈስ ቅዱስ በመደበላቸው ቦታ ተሰማርተው ወንጌል ያልደረሰበት ቦታ አስተምረዋል:: እነዚህ ቅዱሳን ወንጌልን ለማስተማር የተሰማሩበት ባዕድ አምልኮ ተስፋፍቶባቸው ወደ ነበረው በአገሪቱ ምሥራቃዊ ጠረፍ ክፍል ነበር::

ለምሳሌ:- አባ ዘሚካኤል /አረጋዊ/ በዘመኑ የፀሀይ አምልኮ ወደ ተስፋፋበት ቦታ በመሔድ በአምልኮ ባዕድ ተይዘው የነበሩትን አጥምቀው ክርስቲያን በማድረግ የደብረ ዳሞ ገዳምንና በአካባቢው ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን ሊመሠርቱ ችለዋል:: አባ ጰንጠልዮን የአካባቢውን ሕዝብ አስተምረውና አሳምነው በማጥመቅ በዘመኑ የጣኦት ቤት የነበረውን ቤተ ክርስቲያን አድርገውታል:: አባ አፍጼ የሓ ወደተባለው ቦታ ሂደው የሳባውውያን ማዕከል የነበረውን ትልቅ ቤተ ቤተ መቀደስ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲለወጥ አድርገዋል:: አቡነ ገሪማ ደግሞ ከደቡብ የመን የመጣውን

[15] ወደ ባሕር ማዶ የተሻገሩ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅርሶች በማን? በምን? ሁኔታ ወጡ የሚለውን ሥንመለከተ ቢያንስ በሦስት መንገድ ወጥተዋል:-

1. በስጦታ:- በየጊዜው በኢትዮጵያ የነገሡ ነገሥታት፣ መኳንንት፣ ከአውሮፓውያን ጋር ወዳጅነት ለመፍጠር ሲሉ ልዩ ልዩ መጽሐፍትን በስጦታ መልክ ይልኩላቸው ነበር::
2. በመገልበጥ:- ኢትዮጵያን ለማየት እድል የገጠማቸው የአውሮፓ ሰዎች ሊዘርፉ አልያም ሊወስዱ ያልቻሉትን መጻሕፍት ገልብጠው ይወስዱ ነበር:: የዳጋ እስጢፋኖስ ገድለ ስማዕት ወደ ጀርመን በርሊን የሔደው በዚህ መልክ ነበር::
3. በዝርፊያ:- አብዛኛው የቤተ ክርስትያናችን ሀብቶች ወደ ውጭ የሔዱት በዚህ አሳዛኝ ድርጊት ነው::
   [የኢትዮጵያ ታሪክ ከልብነ ድንግል እስከ ቴዎድሮስ ገጽ 7፣ ትንሣኤ ኅዳር 1975 ቁጥር 22 ገጽ 10]



www.ethiopianorthodox.org

አምልኮ መደራ በተባለው ቦታ ላይ አጥፍተው ክርስትና ሰብከውበታል። ተስአቱ ቅዱሳን በስደት እንደመምጣታቸው መጠን በአቀባበሉ ላስደሰታቸው የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ንቁ ሐዋርያዊ ተልዕኮ በማካሔዳቸው ከፍ ያለ ውለታ ፈፅመዋል። ከተስአቱ ቅዱሳን በኋላ የጐላ ሐዋርያዊ ተልዕኮ የተካሔደው በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በንጉሥ ዐምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ነው።

## ሐዋርያዊ ተልዕኮ በ21ኛው ክፍለ ዘመን

በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልዕኮዋን በሠፊው የዘረጋችበት ወርቃማ ዘመን ነው። ከአድዋ ድል በኋላ የኢትዮጵያና የቤተክርስቲያንዋ ስም በአፍሪካና በካሪቢያን ደሴቶችና በአሜሪካ በሚገባ መታወቅ ጀመረ። ስለሆነም በእነዚህ ሀገሮች ቤተ ክርስቲያን ለመመስረት የተቻለበት ጊዜ ነበር። ይህም ያስፈለገበት ምክንያት «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነፃና ጥቁር ሕዝብ ሃይማኖት በመሆኑ ነው» በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በደቡብ አፍሪካ ብዙ የክርስቲያን ነፃነት ንቅናቄዎች ነበሩ። አንዳንዶች ራሳቸውን በራሳቸው «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን» ብለው ይጠሩ ነበር።[16]

አፍሪካውያን በተለይም በካሪቢያን ደሴቶች፣ በሰሜን አሜሪካና በኢንግላንድ ነዋሪ የሆኑ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ሲያገኙ መሠረታዊ ከሆነው አፍሪካው ትውፊት ጋር የበለፀገች የራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን እንዳገኙ ይቆጥሩታል። የክርስትናቸው ሥር መሠረቱ የት እንደሆነ በፍለጋ ላይ ያሉት አፍሪካውያን የጥቁር ሕዝብ ተወላጆች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ሲያገኙ ደስ ይላቸዋል። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያኒቱ ጥንታዊ የጥቁር አፍሪካዊት ቤተ ክርስቲያን ናትና።[17]

[16] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊትና መንፈሳዊ ሕይወት ገጽ 60።

[17] ዝኒ ከማሁ ገጽ 62።





ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በእነዚህ ሀገሮች ልትወደድ የቻለችውና የተቀበሏትም፦ የሃይማኖቷ ጥንታዊነት፣ የቀኝ ገዥዎችን አላማ የማያራምድ፣[18] ባለመሆኑ ከዚህ ጋር የሀገሪቱ ታሪካዊነት የቤተ ክርስቲያኒቱ ጥንታዊነት ባሳደረባቸው መንፈሳዊ ቅንአት ተነሳስተው እናንተን እንመስል ዘንድ እንደ እናንተ እንድንሆን ኑና እርዱን በማለት ከሚያደርጉት ግብዣና ጥሪ በመነሳት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ክፍለ ዘመን በውጭ ሀገር የመሠረተቻቸው አብያተ ክርስቲያናት ከዚህ የተነሣ ነበር።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በ1965 ዓ.ም ከአሜሪካን መልስ ወደ ካሪቢያን ደሴቶች በመሔድ ይህን እውነታ አረጋግጠዋል። እነዚህም ሀገሮች በምድራቸው ላይ ለምትመሠረተው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሥሪያ ሰፋፊ ጋሻ መሬቶችን ሠጥተዋል። ዛሬም ይህ ተልዕኮ ከቅድስት አገር ኢየሩሳሌም ውጭ፡ በእንግሊዝ፣ በጀርመን፣ በአሜሪካ፣ በአውስትራሊያ፣ በካናዳ፣ በደቡብ አፍሪካ፣ በኬንያ፣ በሱዳን፣ እንዲሁም በመካከለኛው ምሥራቅ እንደ ቤሩት ሊባኖስ... ባሉ ሀገሮች ሐዋርያዊ ተልዕኮዋን በማካሔድ ላይ ትገኛለች።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ከፍተኛ የሆነ ሐዋርያዊ ተልዕኮ ፈዕማለች። ይህም የእህት አብያተ ክርስቲያናት ፓትርያርኮች የተገኙበትን ጉባኤ በ1957 ዓ.ም አስተናግዳለች። ከዓለም ዓቀፍ ጉባኤ ማለትም ከኤፌሶን ጉባኤ ወዲህ አኅጉረ ዓለም ነክ የአብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በእህትማማቾች

[18] አፍሪካውያንን እንደ ቅርጫ ሥጋ የተከፋፈሏት ምዕራባውያን ሀገርን ቀኝ ለመያዝ ከሚጠቀሙበት መንገድ አንዱ ሚሲዮናቻቸውን በመላክ ነበር። ይህን የተረዱ ዐፄ ቴዎድሮስ እንዲህ ብለው ነበር፡ «...በሚገባ አውቃለሁ የአውሮፓ መንግሥታት አንድ ሀገር ለመያዝ ሲፈልጉ መጀመሪያ ሚሲዮናውያንን ይልካሉ፤ ቀጥለውም ሚሲዮናቻቸውን የሚያጠናክር ቆንሲል ብለው ይሾማሉ፤ ከዚያ በኋላ ቆንሲሉን የሚጠብቅ ብለው የጦር ወታደሮችን ይልካሉ። እኔ እንደ ሒንዱስታን ራጃ ቂል ሆኜ እንደዚያ እንዲደረግ የምፈቅድ አይደለሁም....» ብለዋል [ዐፄ ቴዎድሮስ በጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 174] እዚህ ላይ የኬንያ መሪ የነበሩት ጆሞ ኬንያታ ያሉትን የበለጠ የሚሲዮናውያን ዓላማ ግልፅ ያደርጋል፦ «ፈረንጆች ሀገራችን ሲገቡ ወንጌል በእጃቸው መሬት በእጃችን ነበር። ትንሽ ቆይተው መሬት በእጃቸው ወንጌል በእጃችን ሆነ» ብለው ነበር።



www.ethiopianorthodox.org

አብያተ ክርስቲያናት መካከል ሲደረግ ይህ የመጀመሪያው ነው:: ከኢትዮጵያ በቀር አራቱ አብያተ ክርስቲያናት በመሐመዳውያን ተከበው የሚኖሩ ስለሆነ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለጉባኤው ታላቅ ተስፋ ሆና ተገኝታለች::[19]

ይህ ታሪካዊ ጉባኤ ብዙ ጥሩ የሆኑ ነገሮችን በውሳኔ ከማስተላለፉም በላይ ጽ/ቤቱ አዲስ አበባ ላይ፤ ጸሐፊው ደግሞ ኢትዮጵያዊ እንዲሆን ተወስኖ ነበር:: ይህ ዘመን እቅዶቹን ሁሉ በወታደራዊ መንግስት ባይከሽፍ ኖሮ በብዙ መልኩ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተጠቃሚ ያደርጋት ነበር:: ስለ ምንኩስና ሥርዓት፤ ስለ መንፈሳዊ ት/ቤት፤ ስለ ስበከተ ወንጌል፤ ዘመናዊ ዓለምና ቤተ ክርስቲያን...፤ ምን መሆን አለበት በጥልቀት ተወያይቶበታል:: በተለይ ሐዋርያዊ ተልዕኮን በተመለከተ የሚከተለውን አስተላልፏል::

*«ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ወደ ዓለም የላካቸው አባቱ እርሱን ወደ ዓለም በላከው አኳኋን ነው:: ይኸውም አብ ልጁን የሰውን ልጅ በችግሩ እንዲ መሰለው ኃጢአቱንም እንዲሸከምለት ለለ እርሱ ብሎ በመስቀል ላይ እንዲሞትለት ነው:: እንደዚሁም ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ የአገልግሎት ሥራ ለማገልገል እንጂ ሊገለገል ያልመጣውን በመጨረሻም ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጐ የሰጠ ውን ጌታ ጉልህ አድርጐ ማሳየት ነው:: ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ተግባር የደኅንነት መልዕክት ወደ ዓለም በማስተላለፍና እንዲሁም ደግ ሣምራዊ ሆና የሰባራውን ዓለም ቁስለ በማሰር የእግዚአብሔር ፍቅር በሌላው መንገድ እውነት ሆኖ ለማያገኙት ሰዎች በግልፅ እንዲረዱት በማድረግ ነው:: ይህ ከብዙዎች የቤተ ክርስቲያን ሥራዎች አንዱ ብቻ ሳይሆን ለትፈፀመው የሚገባት መሠረታዊ ተግባሯ ነው::[20]*

ይህን በጉባኤው ላይ ከተወያዩባቸው ውሳኔዎች መካከል መርጩ ያሰፈርኩት በአሁኑ ጊዜ ቅድስት ቤተ ክርስ ቲያን በበለጠ ማስፋፋት ካለባት አንዱና ዋነኛው ተግባሯ ይህ መሆን ስላለበት ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነ ቤተ ክርስ ቲያን ራሷን ለዓለም ያስተዋወቀችው በትምህርት ነው:: እንግዲህ ይህን ዘመን በትዝታ ስንመለከተው የእህት አብያተ ክርስቲያናት ትብብር ታክሎበት እስከ ዘመናችን ቢቀጥል ኖሮ ሀገር በቀል ያልሆኑ እምነቶች በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ስጋት ላይ አንወድቅም ነበር::

---

[19] ሐዲስ ሕይወት፤ ገጽ 184-192::

[20] የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤ የሰጣቸው ውሳኔዎች ገጽ 17-18





# የቤተ ክርስቲያን ኪነ ጥበባት

## ስዕላት

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከራሷ ማንነት ጋር የሚ መሳሰል የራሷ የሆነ ለዘመናት ያዳበረችው ኪነ ጥበብ አላት ከእነዚህ አንዱ ሥዕል ነው:: በቤተ ክርስቲያናችን ለሚከና ወነው መንፈሳዊ አገልግሎት ታላቅ ምስጢር የያዙ ናቸው:: ከዚህ በተጨማሪ የቃለ እግዚአብሔር መገለጫ መሣሪያ ነው:: ስለዚህ እንዲህ አይነት ኪነ ጥበባት መንፈሳዊ እንደ መሆናቸው መጠን፤ መሠራትም የሚገባው በመንፈሳውያን ስለሆነ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ስዕል የሚስሉ የቤተ ክርስ ቲያናችን ካህናት ነበሩ::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለምርምርና ጥናት የሚ ጋብዙ በርካታ ሀብቶቿ መካከል አንዱ የሆነው ስዕላተ ቤተ ክርስቲያን በታላላቅ ገዳማትና አድባራት፤ ግድግዳና ጣሪያ ላይ ተስለው የሚገኙት ጥንታውያን ስዕሎች፤ ከብዙ ዓመ ታት በኋላ ዛሬም ስናያቸው በሰው እጅ የተሳሉ አይመስ ሉም:: ይህም የቀለሙ አለመደብዘዝ፤ ከምን አይነት ንጥረ ነገሮች እንደተሠሩ ለማወቅ የዳግታል:: እነዚህ ታሪካዊ ስዕሎች ፍፁም ኢትዮጵያዊ ኪነ ጥበብ የተንፀባረቀባቸው ሲሆን፤ ይህም:- ከቀለም ዘግጅት ጀምሮ እስከ ብራና ማው ጣት ድረስ ያለውን ጉዞ የባዕድ እጅ ያልዳሰሳቸው ናቸው::

## ቅርጻ ቅርጽ

እዚህ ዘመነ ከደረሱ የጥበባት ውጤቶች ዋናው መስ ቀል ነው:: ከወርቅ ከብር፤ ከነሀስ፣ ከብረት እንዲሁም ከከበሩ ድንጋዮች ከልዩ ልዩ እፀዋት የተሠሩ የመስቀል አይነቶች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መገለጫዎች ናቸው:: በኢትዮ ጵያ ውስጥ ከ1 ሺ የበለጡ የመስቀል ቅርጽ አይነቶች ይገኛሉ:: በላያቸው ላይ እጅግ ረቂቅ የሆኑ ሐረጐችን በመ ቅረጽ፤ የክርስቶስን የማዳን ሥራ ለማንፀባረቅ ልዩ ልዩ የመ



www.ethiopianorthodox.org

ጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጫዎችን በማስቀመጥ፤ አባቶች ምን ያህል ሰፊ ትዕግስት እንደነበራቸው ሥራቸው ይመሰክራል።

በመሆኑም እያንዳንዱ ታላላቅ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ገዳማትና አድባራት ይህን የመስቀል ሥራ ከሌላው የተለየ ኅብረ መልክ ያላቸው በስማቸው የሚጠራ መስቀል አላቸው የአክሱም፤ የላሊበላ፤ የጐንደር...፤ በመባል፤ ሲጠሩ፤ መስቀሎቹን የተመለከተ ሰው የትኛው መስቀል በማን ዘመነ መንግሥት እንደተሠራ ለማወቅ የሚያስችል ምርምር ትተውልን ሄደዋል።

## ቋንቋና ሥነ ጽሕፈት

ኢትዮጵያ የሥልጣኔዋ አንዱ መገለጫ የሆነው ሥነ ጽሕፈቷ /ቋንቋዋ/ ነው። ከጌታችን ልደት በፊት 3600 ዓ.ዓ ገደማ በሰማርያ፣ በባቢሎን፣ በአሶር በእርጥብ የሸክላ ጡቦች ላይ ጽሕፈት በመቅረጽ እንደተጀመረ በመስኩ የተሠማሩ ሊቃውንት ያስረዳሉ። እንግዲህ ህገራችን በእነዚህ ጥንታውያን የሰው ልጅ ሥልጣኔ መነሻ ከሆኑ ህገሮች የምትመደብ ህገር መሆኗን እንገነዘባለን።

ኢትዮጵያ ነፃ ህገር በመሆኗ ይህን ነፃነቷን ከሚያንፀባርቁት ነገሮች አንዱ በሥነ ጽሕፈት የበለጸገ በይዘቱና በቅርፁ ብቸኛ የሆነ የራሷ ፊደል ሲኖራት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ማንኛውንም ህሳብ ለመግለፅ በራሳቸው ቋንቋ ስለሚጠቀሙ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሥነ ጽሕፈት የበለፀገ ባሕል ሊኖራት ችሏል።

ለረጅም ዘመናት ነፃነቷን ያስከበረች ኢትዮጵያ፤ የራሳቸውን መፈለግ ለተሳናቸው ሌሎች አፍሪካውያን ምሳሌ ጭምር ናት። ምዕራብ አፍሪካን በቀኝ የገዙ ፈረንሳውያን፤ በእነዚህ የአፍሪካ ህገሮች ቋንቋቸውን በመትከል ዛሬ በምዕራብ አፍሪካ መግባቢያ ቋንቋ ፈረንሳይኛ ሆኗል። ደቡብ አፍሪካን የገዙ እንግሊዛውያን በተመሳሳይ ሁኔታ ቋንቋቸውን ተክለዋል። ሰሜን አፍሪካን ወርረው የያዙ አረቦች ዛሬ





ብሔራዊ ቋንቋቸው አረብኛ ሆኗል፤ ማዕከላዊ አፍሪካን የያዙ ፖርቹጋሎች በእነዚህ ማዕከላዊ አፍሪካ ፖርቲግዝ ቋንቋ እንዲነገር አድርገዋል።

እንግዲህ ህገራችን የእነዚህ ምዕራባውያን የቀኝ አገዛዝ ቀንበር ስላላረፈባት የራሷን ኪነ ጥበብ ውጤቶቿን አክብራ በራሷ ቋንቋ የምትገለገል የአፍሪካ ብቸኛ ህገር ናት። ለዚህም ታዋቂው የፊሎሎጂ[21] ምሁሩ «ኘሮፌሰር ፓውሎ ማራሲን» እንዲህ ይላሉ፡...

> *«የዛሬ ቋንቋዎች ሁሉም ጠቃሚዎች ናቸው የዛሬውኑ ማኅበረሰብ ለማወቅ ለመረዳት ወይም ቢያንስ ያለፈውን ክፍለ ዘመን ማኅበረሰብ ታሪክ ለማወቅ ጠቃሚ ናቸው። ግዕዝ ግን እጅግ አስፈላጊ ነው። መሠረትም ነው... ያለፈውን ጊዜ ባሕል ለማጥናት እንደ ግዕዝ ያለ ቋንቋ የለም። ዐረቢኛ ለሙስሊሞች ሊጠቅም ቢችል እንኳ የግዕዝን ያህል የሥነ ጽሑፍ ሀብት አይገኝበትም፣ ስለዚህ በጣም ግልፅ ነው የትናንት ማንነትን ለማወቅ ግእዝን መማር ግድ ይላል።[22]*

እንግዲህ ህገራችን በገዛ ቋንቋዋ ተጠቅማ፤ ነገሥታቱ ባስቀረጿቸው ሳንቲሞች ላይ ጽሑፍ በማስፈር፤ ባሳነጿቸው ሐውልቶች ላይ ስሜታቸውን ባስፈለጋቸው መጠን በመግለፅ፤ በምድራችን ላይ የተመሰረተችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ደግሞ ከማንም ያልተዋሡትን ቋንቋ የበለጠ በማዳበር፤ ሥርዓተ ፊደልን ጠንቅቆ በመጠቀም፤ የታሪክ፣ የሃይማኖት፣ የፍልስፍና መጻሕፍትን በመጻፍ ዘላለማዊ ስጦታ አበርክተውልናል።

እነዚህ እስከ አሁን የተመለከትናቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መገለጫ ህብቶች ሲሆኑ በመጽሐፉ ዋና ይዘት ውስጥ ሳይካተቱ ነገር ግን ለመግቢያ ያህል ቤተ

[21] የጥንታዊ ጽሑፎች ሥነ ጥናት።

[22] ጎግል ጋዜጣ ኅዳር 5 ቀን 2001 ዓ.ም ገጽ 4።



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያኒቱን ለማስተዋወቅ የሰፈረ ነው:: እንደዚሁም ሁሉ ዝግጅቱ የተሟላ ይሆን ዘንድና አንባብያን በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ የሀገሪቱን አጠቃላይ ሁኔታ በቀጣይነት ተመልክ ተን ወደ ዋናው የመጽሐፉ ይዘት እንገባለን መልካም ንባብ::


አዘጋጁ
ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት
የሰሜን ተራራ ደብረ ሲና
ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን
ሰባኪ ወንጌል

የአዘጋጁ አድራሻ
☎ 011-127 16 09
091-186 01 13
091-170 87 80






# ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን

## በመጽሐፍ ቅዱስ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንነት በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይ በብሉይ ኪዳን ተጠቅሷል:: ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በቅ ዱሳት መጻሕፍት፣ በጥንታውያን የታሪክ ሰነዶች፣ በሥነ ፍጥረት ጥናት፣ በዓባይ ሸለቆ ዙሪያና በቀይ ባሕር አካባቢ ከታወቁ ታሪካውያን አኅጉርና ሕዝብ ጐን ተገቢ ቦታቸውን ይዘው የሚገኙ ናቸው::

በዚህ መሠረት በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ በተደጋጋሚ የተጠቀሰች ሀገር ናት:: ሙሴ የሥነ ፍጥረትን ታሪክ በተ ናገረበት በመጀመሪያው መጽሐፍ ውስጥ ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ የተከበበች መሆኗን ዘፍ. 2፥13 ገልጿል:: በመልክዓ ምድር* አቀማመጥ ከግብፅ ደቡብ መሆኗን ሕዝ 29፥19፣ ሱዳንና ግብፅን ሲያጠጡ የኖሩ የኢትዮጵያ ወንዞች አባይና ተከዜ ተገልጠዋል ኢሳ 18፥1፤ ኤር 3፥10፤ በመአድን የከበ ረችና አልማዝና ወርቋ በዓለም ተደናቂ መሆኑ ኢዮብ 28፥19፤ በንግድ ተደሳች ሀገር መሆኗ ኢሳ 43፥3፤ ይህንና ሌሎች ቀያያዥ ቃላት ስለ ኢትዮጵያ ተገልጿል:: በአጠቃላይ በመጽ ሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ41 ጊዜ በላይ ስሟ ተጠቅሷል::

ዘኁ 12፥1፤ ዘፍ. 2፥10፤ 2ዜና. 12፥4፤ 2ነገ 19፥9 ፤2ዜና 21፥16፤ አስቴ 1፥1፤ 8፥9፤ ኢሳ 11፥11፤ 37፥9፤ 43፥3፤ 45፥14፤ 20፥23፤ 20፥24፤ 20፥5፤ ኤር 38፥7፤ 38፥10፤ 18፥12፤ 39፥16፤ 46፥9 ሕዝ 30፥9፤ 30፥4፤ 38፥5፤ ኢዮ 28፥19፤ መዝ 68፥31፤ 84፥4 ዳን 10፥43፤ አሞፅ 9፥7፤ ናሆ 9፥9፤ ሰፎ 2፥12፤ የሐ. ሥራ 8፥26-42::

---

* ኢትዮጵያ 1.2 ሚሊዮን ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት ያላትና ከቀይ ባሕር ጐን በአፍሪካ አህጉር ሰሜናዊ ክፍል «የአፍሪካ ቀንድ» እየተባለ በሚጠራው ውስጥ ትገኛለች:: የኢትዮጵያ አብዛኛው ክፍል ማዕከላዊ ከፍታቸው እስከ 8000 ጫማ በሚደርቡ ገበቴ ቅርፅ በሆኑ መሰበተኛ ተራሮች /ነላቶ/ የተያዘ ሲሆን ከ12 እስከ 15 ሺህ ጫማ ከፍታ ያላቸው ትልልቅ ተራሮች ይገኙበታል:: የተቀረውም የኢትዮጵያ ግዛት በታላቁ የምሥራቅ አፍሪካ ሸለቆና በትናንሽ ቁጥር አልባ ሸለቆዎች የተሸነሸነና ዐይንን የሚስብ በልምላሜ የተከበቡ ወንዞችና ሐይቆች የተከበቡ ናቸው:: ኢትዮጵያ ወደ ምድር ወገብ የተጠጋች ብትሆንም በዓለም እጅግ ጤናማ ከሆኑ የአየር ንብረቶች የአንደኛው ባለቤት ስትሆን ብዙ የታሪክ ጸሐፊዎች ተመሳሳይ አቀማመጥ ከፍታ ካላት ከሜክሲኮ ከተማ ጋር ያነፃጽሯታል:: ሀገሪቱን ከሚከቧት ዝቅተኛ ቦታዎች በስተቀር ኢትዮጵያ በ60 እና በ80 ዲግሪ ፋራናይት መካከል የሚገኝ ተስማሚና መካከለኛ የአየር ሙቀት ያላት ሀገር ናት:: መሬቷ በአብዛኛው ለእርሻ የተመቸ በመሆኑ ከሕዝቡ 85 በመቶ አርሶ ለመኖር የሚያመች ሁኔታ በገጠር ሰፍሮ ይገኛል::



www.ethiopianorthodox.org

# ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ

ኢትዮጵያ የሚለውን ስያሜ በተለይ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትን ከእብራይስጥ ወደ ግሪክ የተረጎሙት 70 ሊቃናት ኩሽ የሚለውን ስያሜ ኢትዮጵያ በሚለው ተክተውታል። በሌሎች ሀገሮች ሥነ ጽሑፍ «ኢትዮጵያ እና አቢሲኒያ» በመባል ተገልጣለች፡፡ኢትዮጵያ የሚለው ስመ ተጸውዖ በመጽሐፍ ቅዱስ ከላይ እንዳየነው በብዙ ቦታ ይገኛል፡፡ በእብራይስጡ ቋንቋ የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያ ለማለት «የኩሽ ሀገር» ይላታል፡፡ በእብራይስጥ ኩሽ የሚለው ቃል ሦስት ነገሮችን ያመለክታል፡፡

አንደኛው የተጸውዖ ሥም መሆኑ ሲሆን፤ ከካም ልጆች መካከል አንዱ ኩሽ ይባል ነበር ዘፍ.10፥6፤ ሁለተኛው የነገድ ስም ሆኖ የሚገኝ በመሆኑ ነው፡፡ የዚህ ሰው ልጆች ነገደ ኩሽ ወይም ኩሻውያን ተብለው እንደሚጠሩ ይታወቃል፡፡ በሌላ በኩል መልከ ጠይም ወይም ጥቁር ለሆነ ሰው የተሰጠ ስያሜ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ትርጉም ግን ጠይም ሕዝቦች ሁሉ የኩሽ ዘሮች ናቸው ብሎ መናገሩ ይከብዳል፡፡ ሦስተኛውና የመጨረሻው የአካባቢ ስም ነው፡፡ መልከ ጠይም ሕዝቦች የሚኖሩበትና ከግብፅ ደቡብ እስከ ሕንድ ያለው አካባቢ መጠሪያ ስም ሆኗል፡፡ ስለዚህ ኩሽ በሁለተኛው ስም የተመለከተው ዘርዐ ትውልድ በሦስተኛው ትርጉም ይህ አይነት ዘርዐ ትውልድ የሚኖሩበት አካባቢ ስም ሆኖ ይገኛል፡፡[1]

ኢትዮጵያ በጥንት ግብጻውያን ቋንቋ ጵንጥ፤ ቶኔቶር፤ የኩሽ ሀገር እየተባለች ትጠራለች፡፡ ጱንጥ የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ካለው ፉጥ ከሚለው ስም ጋር ይመሳሰላል፡፡ ዘፍ 10፥6፡፡ ቶኔቶር ማለት ሀገር እግዚአብሔር ማለት ነው ይላሉ፡፡ ሙሴ ኦሪትን መጽሐፍ ሲጽፍ ይህቺን ሀገር «የኩሽ ምድር» እያለ መጻፉ በግብፅ ተወልዶ ያደገ እንደመሆኑ መጠን የግብፃውያንን ቋንቋ ያውቅ ስለነበር ነው እንጂ ኩሽ

1 የዛሬዋ ኢትዮጵያ ቅዱሳት መጻሕፍት የታሪክና የሥነ ጥንት ኢትዮጵያ ናት ገፅ 12፡፡





የሚለው ቃል የእብራይስጥ ቋንቋ እንዳልሆነ በሊቃውንት ታውቋል፡፡ [የኢ.ኦ.ተ.ቤ ታሪክ ገፅ 11]

ኢትዮጵያ የኩሽ ምድር ለመባል የበቃችው የኩሽ ዘሮች ስለሰፈሩባት ነው፡፡ ይህቺ ሀገር በሌላ አጠራር «የሳባ ምድር» አንዳንድ ጊዜም «አቢሲኒያ» እየተባለች ትጠራለች፡፡ ምን አልባት ይህ ስያሜ የተገኘው እነዚሁ የኩሽ ልጆች ሳባና አቢስ /ሰብታ/ ስለሰፈሩባት በስማቸው አስጠርተዋታል፡፡ በመጨረሻ ለዚች ሀገር የተሰጠው ስያሜ «ኢትዮጵያ» የሚለው ነው፡፡ በሀገራችን እንዲህ ይተረካል:- ኢትዮጲስ ሁለተኛ ሳባ የተባለው የአክሁናስ የልጅ ልጅ የቡልቃ ልጅ ነው፡፡ ኢትዮጲስ 1ኛ ከ3644-3700 ዓ.ም ከልደተ ክርስቶስ በፊት 56 ዓመት ነገሠ፡፡ ሀገሩም በስሙ ኢትዮጵያ ተባለች ይላል፡፡ ስለዚህ ኩሽ ሁለት ስም ነበረው ማለት ነው፤ እንግዲህ አቅኚዎች በአባታቸው ስም ይህችን ሀገር ኢትዮጵያ ብለዋታል፡፡

# የኢትዮጵያ መልክዐ ምድር አቀማመጥ የሕዝቦቿ ጸባይ በታሪክ ሰዎችና በፈላስፎች

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ክፈለ ዓለም በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ የምትገኝ ሀገር ስትሆን፤ በተፈጥሮ አቀማመጥ «ቀርነ አፍሪካ» [የአፍሪካ ቀንድ] እየተባለች ትጠራለች፡፡ ከጥንት ሊቃውንት መካከል ከጌታችን ልደት በፊት 8 መቶ ዓ.ዓ አካባቢ የነበረው ግሪካዊ ገጣሚ ሆሜር በግሪክ ሥነ ጽሑፍ ወይም ሥነ ግጥም ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል ተጠቅሞ የጻፈ ሲሆን፤ በፀሀይ መውጫ /ምሥራቅ/ አቅጣጫ እንደሚኖሩ በመጥቀስ የሚኖሩበትም አካባቢ የምድር ዳርቻና ፀሐያማ መሆኑን ገልጿል፡፡ ኢትዮጵያ የትኛውን ማዕዘነ ምድር አካባቢ እንደምትይዝ ለማመልከት ሞክሯል፡፡

እውቁ የግሪክ ታሪክ ጸሐፊ ቅድመ ልደት ክርስቶስ ከ400-300 ዓ.ዓ የነበረው ሐሮዶቶስ በመካከለኛው ምሥራቅ ጉዞ አድርጎ በተለይ በግብፅ ለብዙ ጊዜ የተቀመጠ መሆኑ ስለ ኢትዮጵያ ከተለያዩ ምንጮች በቂ መረጃ ለማግኘት



www.ethiopianorthodox.org

የቻለ ሰው ነበር። ከዚህ ካገኘው መረጃ በመነሳት ኢትዮጵያን በሁለት ክፍሎ ማየት ሞክሯል። አንደኛዋ ኢትዮጵያ ከግብፅ አቅራቢያ አካባቢ የምትገኘው ሲሆን፤ ሁለተኛዋ ኢትዮጵያ ደግሞ ወደ ደቡብ የተዘረጋችው የአሁኗ ኢትዮጵያ ነበረች ማለት ነው። በዚህ ጽሑፍ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩበት ሩቅ ሀገር ከግብፅ ደቡብ መለስ የሚገኝና ቀይ ባሕርን ተከትሎ የሚሔድ አካባቢ እንደነበርና የእነዚህን ኢትዮጵያውያን የኑሮ ዘዴ ሲገልፅ የእድሜ ባለፀጐችና ዓሣ ተመጋቢዎችም እንደነበሩ ያስረዳል።

ሔሮዶቶስ ከላይ እንደተመለከትነው ወደ መካከለኛው ምሥራቅ መጥቶ በተለይ በግብፅ ብዙ ጊዜ እንደመቆየቱ መጠን ከአካባቢው አዋቂዎች ጋር በመወያየት ስለ ኢትዮጵያ በርካታ ነገሮችን ለማስረዳት ችሏል። በመሆኑም በዚህ ባገኘው መረጃ መሠረት የኢትዮጵያን ወሰን ከግብፅ ደቡብ ጀምሮ እስከ ሲናምፍሮስ [ሕንድ ውቅያኖስ መዳረሻ] ድረስ እንደነበር ከዚህም ጋር ኢትዮጵያ ሁለት ክፍሎችን የያዘች አካባቢ መሆኗን ሲያመለክት፤ አንደኛዋ ከግብፅ ጋር የተጐራበተችው ኢትዮጵያ፤ ሁለተኛዋ ኢትዮጵያ ደግሞ ዓሣ ተመጋቢዎች ኢትዮጵያውያን የሚኖሩበት ወደ ደቡብ የተዘረጋችው ኢትዮጵያ [የዛሬዋ ኢትዮጵያ] በአጠቃላይ ግን አንዲት ኢትዮጵያ መሆኗን ገልጿል።

ሆሜር የተባለው የግሪክ ባለቅኔ ቀይ የሆነውን ወይን ኢትዮጵያ ብሎት ሥለሚገኝ ኢትዮጵያ ማለት ቀይ የቀይ ዳማ ቀለም ያለው ሕዝብ ማለት ነው። ይህ ሆሜር የተባለው የግሪኮች ባለቅኔና ገጣሚ እንዲህ ብሏል «የኢትዮጵያ ሕዝብ በጉልበት ኃያላን፤ በውበት የተደነቁና በጠባይ ጭምቶች ትህትናን የተሞሉ ናቸው» ሲል፤ ከ490 ዓ.ዓ ከጌታችን ልደት በፊት የነበረው ከላይ የገለጥነው ምዕራባውያን የታሪክ አባት የሚሉት ሔሮዱቱስ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንን ባነሳበት መጽሐፍ «በኢትዮጵያ እጅግ ያማሩ ሕዝቦች፤ ባለ ደምግባት ቆንጆዎች፤ ውቦች ሰዎች ያሉባት፤ ርህራሄያቸው እንደ እግዚአብሔር ነው፤ በሠፊው ሜዳ ለመንገደኞች ማለፊያ የሚሆን ድግስ እየደገሡ ያስተናግዳሉ። ምንም ቢሆን መንገደኛ የሚበላው አያጣም፤ በእድሜአቸው ከ100-130 ዓመት ይቀመጣሉ፤ ነውርና ክፉ ነገር በአገራቸው የተጠላ ነው። የጤና ምንጭ የሚሆኑ ውሆች አሏቸው ይህን በጠጡ ጊዜ ሰውነታው ይታደሳል። በህብት እጅግ ባለጠጐች ናቸው፤ ድንበሯም ከጅቡቲ ባሕር ዳር እስከ ሰናር ነጭ አባይ ድረስ ነበር። በቆላው ልዩ ልዩ አትክልት ፍራፍሬዎች ይገኙባቸ ዋል በደቡብ ቆላ ደግሞ የእጣን፣ የላስቲክ ዛፍ፣ የሰንደል እንጨት፣ ከርቤ ሌላ ብዙ ቅመማ ቅመም የሚበሉ ፍሬዎች ይገኛሉ። የከበረና የጠራ እንቁ ሉልም ዝባድም ልዩ ልዩ አይነት ሽቱ አሉበት» በማለት ተናግሯል ሲሉ አለቃ ታየ «የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ» በሚለው መጽሐፋቸው ገልፀውታል።[2]

## የኢትዮጵያ ጥንታዊ ግዛት

ጥንት የኢትዮጵያ ግዛት ከላዕላይ ግብፅ (ከደቡብ ግብፅ) አስከ ሕንድ ውቅያኖስ መዳረሻ ይደርስ ነበር። ከግብፅ ቀጥሎ (በታች) የምትገኘው ኢትዮጵያ በሰሜን ከግብፅና ሊቢያ፤ በምዕራብ ከሊቢያ ውስጣዊ ማዕዘን እንደምትዋሰን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ታዋቂ የመልከዐ ምድር ሊቆችን በመጥቀስ ገልጿል።[3] ሙሴ ባፈርኦን ቤት ይኖር ስለነበር ከፈርኦን ቤት በወጣ ጊዜ ሸሽቶ የሔደው ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ወደ ላዕላይ ግብፅ /ደቡብ ግብፅ/ ነው። ኢትዮጵያውያን ከፍ እያሉ የግብፅን ደቡብ መግዛታቸው ይልቁንም ቴቢ የተባለውን በአምልኮ ጣኦትና በሥልጣኔ የታወቀውን ሀገር በአንድ ዘመን ውስጥ ይዘው እንደነበር ይነገራል። ከ555-663 ዓ.ዓ ግብፅን በሙሉ ይገዙ የነበሩ ነገሥታት የመጨረሻዎቹ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። ዲዮዶር የተባለ የሮም ታሪክ ጸሐፊ ከግብፅ በፊት ስልጡንና ገናና መሆኗን ግብፅን ጨምሮ 18 የኢትዮጵያ ነገሥታት

[2] የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ገፅ 77፤ ሔሮዱቱስ 1ኛ መጽሐፍ መቅድሙንና 3ኛ መጽሐፍ ገፅ 14 ተመልከት።
[3] የዛሬዋ ኢትዮጵያ ቅዱሳት መጻሕፍት የታሪክና የሥነ ጥንት ኢትዮጵያ ናት። ገጽ 16




www.ethiopianorthodox.org

እንደገዟት ራሷ ኢትዮጵያ ግን በማንም ተገዝታ እንደማታውቅ እያደነቁ ጽፈዋል::[4]

## የኢትዮጵያ ጥንታዊ ንግድ

ኢትዮጵያ ጥንት ታላላቅ ከሚባሉት አገሮች የምትመደብ ሲሆን፤ በየብስም በባህርም ከገናናዎቹ የእስያ መንግሥታት ጋር ሸቀጣ ሸቀጥ እየተለዋወጡ ይነግዱ ነበር። መንግሥቷ በልብስ ፀጌጣጌጥ እንደ ምሥራቅ መንግሥታት የከበረ ነበር:: ወደ ውጭ የምትልካቸው የንግድ አይነቶች የዝሆን ጥርስ፣ እጣን፣ ከርቤ፣ ቅመማ ቅመም፣ የአውራሪስ ቀንድ፣ የጉማሬ ቆዳ፣ የኤሊ ድንጋይ፣ በሕይወት ያሉ ዝንጀሮዎች እነዚህን ወደ ሕንድ ፋርስ፣ ሮም ቻይና ወደ አረብ ሀገራት ይልኩ ነበር:: ወደ ሀገር ውስጥ ከሚገቡ ሸቀጣ ሸቀጦች መካከል የወይን ጠጅ የወይራ ዘይቶች፣ ከብርጭቆ የተሠሩ ቁሳቁሶች፣ ዋንጫዎች በያይነቱ ቀለም የተነከሩ ካባዎች የሐር ጨርቆቹ፤ የቆዳ ኮቶች የመሳሰሉትን ወደ ሀገሯ ታስገባ ነበር:: በከርሰ ምድር ያለው ሀብቷ በዓለማችን የተደነቀ እንደነበር መጽሐፈ ኢዮብ ይገልጻል 28፥19::

መንግሥቷ ይቀመጥ የነበረው በአክሱም ስለነበር አክሱም በእስያና በአፍሪካ መካከል እንደ ድልድይ በማገልገሏ ከግብፅ ከሮም ከሕንድ ከፋርስ /ኢራን/ ከቻይና ከግሪክ ሀገሮች ረዥም ዘመን የቆየ የንግድ ግንኙነት ነበራት ግሪኮች ከምስራቁ ዓለም ጋር በነበረው የንግድ እንቅስቃሴ ላይ የነበራቸው የበላይነት እየተዳከመ ሲሔድ ወደ ሕንድ በመሔድ ሸቀጦችን ከዚያ አምጥተው ለሚጠብቁት ግሪኮች የሚሸጡላቸው ኢትዮጵያውን ነበሩ:: በአሁኑ ጊዜ በደብረ ዳሞ የተገኙ የተለያዩ የሕንድ ገዥዎች ገንዘብ ይህን ያረጋግጣሉ::

ክርስትናን ለማስራጨት በጥንት ጊዜ የማይናቅ አስተዋፅኦ ያደረጉ ነጋዴዎች ናቸው:: የአክሱም መንግሥት በቅርብና በመካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች ጋር ከዚያም አልፎ ከግሪክ ጋር የቅርብ ግንኙነት ነበረው:: ወደ አክሱም የሚመጡ ነጋዴዎች ሁሉም ባይሆኑ የተወሠኑት ክርስቲያኖች ናቸው:: አዱሊስና አክሱም በተለይ ብዙ ነጋዴዎች የሚዘዋወሩባቸውም ከተሞች ነበሩ:: ለራሳቸውም ቢሆን የጸሎት ቦታና ካህን ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህ አንዳንድ ካህናትን ይዘው ሳይመጡ አልቀረም:: ይህ እንግዲህ በነጋዴዎች ቅስቀሳ እንደሆነ ያመለክታል:: ንግስተ ሳባና ንጉሥ ሰሎሞን ያስተ ዋወቀ ታምሪን የሚባል ኢትዮጵያዊ ነጋዴ ሲሆን፤ የክርስትና እምነት በበለጠ በፍሬምናጦስ አማካኝነት የተሠበከውም ወደ ፊት እንደምንመለከተው በአንድ ነጋዴ ሞት ምክንያት ነው::

## ጥንታዊው የኢትዮጵያ ወደብ አዱሊስ

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በንግዱ ዘርፍ ጥንታዊ ኢትዮጵያ ታዋቂ እንደሆነች ነው:: ይህን ንግድ የምታካሒድበት ተልቁ የባሕር በር አዱሊስ ነው:: በቀይ ባሕር ዳርቻ በምፅዋ ደቡብ ዙላ በመባል የሚታወቀው የባሕር ዳርቻ በጥንት ጊዜ አዱሊስ ይባል ነበር:: ከተማው የተቆረቆረው ከጌታችን ልደት በፊት ነው:: በዚያን ጊዜ እንደ ወደብነት የሚያገለግለው ለመላው ምሥራቅ አፍሪካ ነበር:: አገልግሎቱ ለሮማና ለግሪኩ ዓለም በመሆኑ የእነዚህ ሀገሮች ነጋዴዎች ይመጡበት ነበር:: በዚህ ምክንያት የግሪክ ቋንቋ በአክሱም መነገር ጀምሮ ነበር:: ስያሜውን ያገኘው ከግሪክ ቋንቋ መሆኑ ታውቋል «አዱሊስ» ማለት የባርያ ከተማ ማለት ነው ይላሉ:: ከተማውን የቆረቆሩት የግብፃውያንን የባርነት አገዛዝ ሸሽተው የመጡ ነጋዴዎች ስለሆኑ ነው ይህ ስያሜ የተሠጠው:: አዱሊስ ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ዋና የባህር ወደብ ሆኖ ያገለገለ ነው:: በሜዲትራንያን በምሥራቁ ዓለም መካከል ለሚካሔደው ንግድ አስተዋፅኦ ያደርጉ የነበሩት በቀይ ባሕር ዳርቻዎች ከሚገኙ ወደቦች መካከል ዋናው ይህ ወደብ ነው::[5]

---

[4] ከጣኦት አምልኮ ወደ ክርስትና ገፅ 30፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ ናፓታ መርዌ ገፅ 43::

[5] ክርስትና በኢትዮጵያ 1ኛ መጽሐፍ ገፅ 51::




www.ethiopianorthodox.org

በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ፍሬምናጦስ ወደ አክሱም የገባው በዚህ ወደብ በኩል ሲሆን፤ ይህ ወደብ በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአገራችን ለተስበከው ክርስትናም ሆነ ለሌች ህገሮች ክርስቲያኖች አስተዋፅኦ አድርጓል:: ይህም አፄ ካሌብ ወደ የመን ለመዝመት የተነሳበት የናግራን ክርስቲያኖችን የታደገበት ከዚህ ወደብ በመነሳት ነው::

በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የምርምር ቁፋሮ በዚህ አካባቢ ተካሒዷል:: በዚህ መሠረት የጥንት ቤተ ክርስቲያን ቅሪትና ንዋየ ቅድሳት ተገኝተዋል:: ከተገኙት አንዱ የሸክላ የተሸራረፈ መቅረዝ ነው:: በላዩ ላይ የግሪክኛ ጽሑፍ ተቀርጾበታል:: በተጨማሪ በአንድ ጀርመናዊ ተመራማሪ አማካኝነት የጥንት የአክሱማውያን ገንዘቦችን አግኝቷል:: አዱሊስ እስከ 8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ሲያገለግል ቆይቶ የውጭ ጠላቶች ባደረጉት የበቀል ወረራ እንዲቃጠል ተደረገ:: ከዚያ ወዲህ ሊያንሰራራ አልቻለም:: ይህን ከተማ በቁፋሮ ያገኙት በ1860 ዓ.ም ዐፄ ቴዎድሮስን ለመውጋት የመጡ የእንግሊዝ ወታደሮች ናቸው::

## የኢትዮጵያ የኃይል አቋም በጥንት ዘመን

ከጌታችን ልደት በኋላ በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው ማኒ የተባለ የፋርስ ምሁር የአክሱም መንግሥት በጊዜው ከነበሩት 4 ኃያላን መንግስታት እንደ አንዱ በመቁጠር ከፋርስ ከሮምና ቻይና ጐን አሰልፏታል:: የአክሱም ብልፅግናና ኃያልነት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው በኢዛና ዘመን ነው:: ከዚህ የተነሳ የአክሱም መንግሥትን ወዳጅነት እንጂ ጠላትነቱን የሚፈልግ ማንም አልነበረም:: በጐረቤት ሀገራት አካባቢ ያሉ ክርስቲያኖች ጠላት ሲነሳባቸው የሚያመለክቱት ወደ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት ነበር:: ለምሳሌ በየመን የሚኖሩ የናግራን ክርስቲያኖች ፊንሀስ የተባለ አይሁዳዊ ጠላት ተነስቶ ባሰቃያቸው ጊዜ ለቁስጥንጥንያ መንግሥት አቤት አሉ፤ የቁሰጥንጥንያ ንጉሥ በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ አፄ ካሌብ ጉዳዩን አሣወቀ ካሌብም በርካታ መርከቦችና የጦር ሠራዊት ይዞ ቀይ ባሕርን በማቋረጥ የናግራን ክርስቲያኖችን ነፃ አውጥቶ የፈረሡ አብያተ ክርስቲያናትና ከተሞችን በማነጽ 10ሺ የሚደርስ ሰራዊት እዚያው በመተው አብርሃም የተባለ ሹም ትቶላቸው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል:: ከዚህ የተነሳ የመን በአረቦች እስከተወረረችበት ጊዜ ድረስ የኢትዮጵያ ነበረች:: ኢትዮጵያውያን ቀይ ባሕርን በመቆጣጠራቸው ከምሥራቁ ዓለም ብቸኛ የንግድ ተጠቃሚ ለመሆን ችለው ነበር::





## ኢትዮጵያ በስልጣኔ

ስለ ኢትዮጵያ ሥልጣኔ ስናነሳ ቀዳሚውን ሥፍራ የሚይዘው የአክሱም ሥልጣኔ ነው:: አክሱም በቤተ ክርስቲያኗ ጥንታዊነት፤ በሐውልቶቿ ስመ ጥሩነት የኢትዮጵያ የታሪክና የሃይማኖት እናት ከተማ መሆኗን የማያውቅ የለም:: ሊኖርም አይገባም! ከተማዋ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1ሺ/ 2ሺ ዓ.ዓ እንደተቆረቆረች ይነገራል:: ቆርቋሪዎቹም ሁለት ሳይሆኑ አይቀሩም:: አንደኛው የከተማይቱ መሥራች በ2ሺ ዓ.ዓ የነገሠውና በሥሙ ሀገሪቱን ያስጠራው ኢትዮጲስ ነው:: መቃብሩም በምዕራብ ጫፍ በጉበድራ አካባቢ እንደሚገኝ ይታመናል:: ሁለተኛይቱ የከተማይቱ መሥራች ንግሥተ ሳባ እንደሆነች ነው:: ይህም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1ሺ ዓ.ዓ መሆኑ ነው::

አክሱም የሚለው ስያሜ ጥንተ ቃሉ:- «አኩሽም የሚል ነው፤ ትርጉሙም አ ማለት ጥንት ቀዳሚ ማለት ሲሆን፤ ኩሽ የሚለው ቃልም ኩሻውያን፤ የኩሸ ልጆች ሕዝበ ኩሽ ነገደ ኩሽ ማለት ነው፤ በዚህ መሠረት አክሱም ማለት ጥንታዊት ቀዳማዊት የነገደ ኩሽ መገኛ ከተማ የአህጉረ ኩሽ ራስ፤ እሞን ለአህጉር ኩሽ ማለት ነው» ይላሉ::[6] የከተማዋ አቀማመጥ ከአንድ ወገን እንደ ደጋን ለመጥ ካለ ኮረብታ እንደ ሠንሰለት ከሰሜን ምሥራቅ አንስቶ ወደ ሰሜን ምዕራብ በሚዘልቅ ትታቀፋለች:: ይህ እንግዲህ የኢትዮጵያ ከተሞች የአመሠራረት ወግ ነው [በአንድ በኩል ኮረብታ በሌላ በኩል የተንጣለለ

[6] መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ገጽ 219::



www.ethiopianorthodox.org

ሜዳ] የአክሱም የጥንት ስፋት ከየት እስከ የት እንደሆነ አይታወቅም፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ይቀመጥ የነበረው በአክሱም ስለነበር የተደላደለ ደረጃ ላይ ደርሶ የራሱን ገንዘብ አስቀርጾ ንግዱን ቀደም ብለን እንዳየነው በምሥራቁና በምዕራቡ ዓለም ያካሒድ ነበር።

የኢትዮጵያ ሥልጣኔ የተወለደባት አክሱም የሥልጣኔ ውጤቶቿን ተሸከማ፤ በቅርሶቿ ተሸልማ ትገኛለች። ለአክሱም ጥንታዊነትና ስልጣኔዋን የውጭ ጸሐፊ /3ኛ ወገን/ ማስረጃ አያስፈልግም። ሐውልቶቿ፤ የሥነ ጽሑፍ ውጤቶቿ፤ ሁሉ አፍ አውጥተው ይናገራሉ። ዛሬ አፈር ለብሶ የሰው እግር መርገጫ ሆኖ የሚታየው የአክሱም ከተማ እያንዳንዱ እርምጃ ቢገለጥ ቅርስ ነው። ለጥናት ለምርምር የሚመች የታሪክ ሰነዶች የሚገኙባት ጓዳ ናት። እስከ አለነበት ዘመን ድረስ አክሱም የዓለምን ሕዝብ አዕምሮ እንደገዛች /እንደሳበች/ ትገኛለች።

## አክሱምና ሐውልቶቿ

በቅርፃ ቅርፁ ረገድ ተፈጥሮ የሚያደርስባቸውን ችግሮች ሁሉ ተቋቁመው እስከ ዘመናችን ደርሰው የዓለምን አድናቆት የሚማርኩ ሐውልቶች አሏት። በአክሱም ከተማ ይኖራሉ ተብለው ከሚገመቱ ከ500 በላይ ሐውልቶች ውስጥ በአክሱምና በአካባቢዋ የሚገኙ 66 ብቻ ናቸው። እነዚህ ሐውልቶች በቁመት፣ በክብደት፣ በስፋትና በቅርፅ የተለያዩ ናቸው። የአክሱማውያን ጥበብ ተደናቂ የሚያደርገው የሐውልታቸው ሥራ ብቻ አይደለም በወቅቱ ይጠቀሙበት የነበረ የአቅጣጫ መጠቆሚያ /ኮምፓስ/፤ የርዝመት መለኪያ ሜትር የነበራቸው መሆኑም ጭምር ነው። በአጥኚዎች መሠረት የአክሱም ሐውልቶች በተለይ በሚያስደንቅ አኳኋን በጂኦሜትሪ ጥበብ ስለተቀረፁት ሰባቱ ትልልቅ ሐውልቶች ጥቂት መግለጫ።





### 1 ወድቆ የሚገኘው ትልቁ ሐውልት

33 ሜትር ርዝመት፣ 520 ቶን /5200 ኩንታል/ ክብደት፣ ከስር ስፋቱ 3.84 ሜትር፣ ጐኑ 2.35 ሜትር ወርድ ያለው ሲሆን የ13 ፎቆች ምልክት ይታይበታል። በአራቱም ማዕዘን ቅርጽ አለው።

### 2 ሐውልት ቁጥር 2

24.6 ሜትር ቁመት ያለው፣ 170 ቶን /1700 ኩንታል/ የሚመዝንና፣ ከስር ጐኑ 2.32 ሜትር ወርዱ 1.26 ሜትር ስፋት ያለው ሆኖ ወደ ላይ እየጠበበ የሚያሻቅብ መልክ አለው። በአራቱም ማዕዘን በቅርጽ ያጌጠ ነው። ይህ ሐውልት ከ65 ዓመት በፊት ጣልያን ወስዶ የመለሰው ነው።

### 3 ሐውልት ቁጥር 3

20.6 ሜትር ቁመት፣ ከስር ጐኑ 2.65 ሜትር፣ ወርዱ ደግሞ 1.18 ሜትር ስፋት ሲኖረው፣ ክብደቱ 160 ቶን /1600 ኩንታል/ ይመዝናል። ሐውልቱ ከግራና ከቀኝ በቅርጽ የተዋበ ሆኖ በጀርባው ግን ልሙጥ ነው። የ10 ፎቆች ምስል የያዘ ሲሆን በአካልም ይሁን በስዕል በአገራችን ውስጥ በስፋት የሚታወቅ ነው።

### 4 ሐውልት ቁጥር 4

ይህ ሐውልት በሰሜን ምሥራቅ ረድፍ ተተክለው ከነበሩት ታላላቅ ባለቅርጽ ሐውልቶች በአራተኛው ረድፍ ላይ ኢየሱስ ከማባለው ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ወድቆ የሚገኝ ነው። 18.2 ሜትር ቁመት፣ 56 ቶን /560 ኩንታል/ የሚመዝን ክብደት፣ ከሥር የ1.56 ሜትር ጐንና 0.76 ሜትር ወርድ ስፋት አለው። ባለ 6 ፎቅ ምስል የያዘ ሲሆን በአራቱም ማዕዘን ተመሳሳይ ቅርጽ ተሠርቶበታል።

### 5 ሐውልት ቁጥር 5

ይህ ሐውልት የንግሥተ ሳባ መዋኛ ገንዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ወድቆ የሚገኝ ሲሆን 15.8 ሜትር ቁመት፣ 75 ቶን /750 ኩንታል/ ክብደት፣ ከሥር 2.35 ሜትር ጐንና 1 ሜትር ወርድ ሲኖረው፣ በአራቱም ማዕዘን ቅርጽ የተሳለለት ነው።



www.ethiopianorthodox.org

### 6 ሐውልት ቁጥር 6

ይህ ሐውልት ከባለቅርጾቹ ሐውልቶች ትንሹ የሚባልና 15.3 ቁመት ያለው ሆኖ ግማሽ አካሉ መሬት ውስጥ ተቀብሮ የሚታይ ነው:: ከሥር 1.47 ሜትር ጐንና 0.78 ሜትር የወርድ ስፋት ያለው ሲሆን 43 ቶን /430 ኩንታል/ ክብደት ሲኖረው ባለ4 ፎቅ ምሥል የያዘና በአራቱም ማዕዘን ቅርጽ ያለበት ነው::

### 7 ሐውልት ቁጥ፫ ፯

ስድስቱ ሐውልቶች ከያዙት ቅርጽ በተለየ አኳኋን የተሠራው ይህ ሐውልት ከፊትና ከጀርባው አስደናቂ ቅርጾች የያዘ ሲሆን የመሰበር አደጋ ሳያጋጥመው በአንድ ጠፍጣፋ ቅርጽ በሌለው ሐውልት ላይ ተንተርሶ ወድቆ ይገኛል:: ይህ ሐውልት 9.78 ሜትር ቁመት አለው::[7]

## አክሱምና ሥነ ጽሑፎቿ

በቋንቋና በሥነ ጽሑፍ በኩል ግዕዝ ምንም እንኳ ሴማዊ እንደመሆኑ ከሌሎች ሴማውያን ቋንቋዎች ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዳለው ባይካድም፤ ራሱን ችሎ በጽሑፍ መቅረፅ የተጀመረው በአክሱማውያን ዘመነ መንግሥት ነው:: የኢትዮጵያ የካህናት ከተማ ተብላ ትጠራ የነበረችው አክሱም ሥነ ጽሑፏ በዘመኑ የትምህርት ዓለም ከተባለችው ከአቴና ከተማ ሥነ ጽሑፍ ጋር የሚወዳደር ነበር:: እነዚህ ጽሑፎች በቆሙት ሐውልቶቿ፤ በአንዳንድ የሸክላ እቃዎችና በአስቀረጿቸው ሳንቲሞች /ገንዘቦች/ ላይ ተጠቅመውበት ይገኛል በዚህ መሠረት በአክሱም ዘመነ መንግሥት በቂና የዳበረ ሥነ ጽሑፍ እንደነበር መረዳት ይቻላል::

[7] አክሱም የታሪክና የቅርስ ማኅደር::





## አክሱምና ገንዘቦቿ

ከዛሬ አንድ መቶ አመት በፊት በአክሱም ስለሚገኘው ጥንታውያን ገንዘቦች በሌሎች የውጭ ሊቃውንት ዘንድ ምንም አይታወቅም ነበር:: ለመጀመሪያ ጊዜ የተረጋገጠው እ.ኤ.አ. በ1840 ዓ.ም በዶክተር ኤድዋርድ ሩፕል በተባለ ጀርመናዊ ሰው አማካኝነት ነው:: ይህ ሰው ከ1831-1834 እ.ኤ.አ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለፈፀመው ጉዞ ሲተርክ አክሱም ላይ ስለተገኘው ስለ ንጉስ አፊላስና፤ አዱሊስ ላይ ስለተገኘው ስለንጉሥ ገርሰም የወርቅ ገንዘቦች ዝርዝር መግለጫ ሰጧል:: ያገኛቸውን ገንዘቦች ለትውልድ ሀገሩ ለፍራንክፈርት ከተማ ቤተ መጻሕፍት አበርክተውላቸዋል::[8]

የአክሱማውያን ገንዘቦች ተለይተው የሚታወቁበት አንድ ነገር አለ:: እርሡም መንግሥትና ሃይማኖትን ያጣመሩ ጽሑፎችና ቃላት ተቀርፀውባቸው የሚገኙ በመሆናቸው ነው:: አሁን በተገኘው የአርኪዮሎጂ ቁፋሮ የገንዘቦቹ መሥሪያ ቦታ መረጋገጡ፤ ከወርቅ የተሠሩ ገንዘቦች የአክሱም መንግሥት ከውጭ ሀገሮች ሲገናኝ እንደሚጠቀምባቸውና፤ ከመዳብና ከብር የተሠሩትን ግን ለሀገር ውስጥ መገበያያ ተብለው መሰራታቸው፤ እነዚህንና ሌሎች ምርምሮች ተካሂዶባቸዋል ምርምሩም ውጤታማ ሆኗል:: ይህም ምን ያህል ያ ዘመን ታላቅ እንደነበር ለአሁኑ ትውልድ በቂ ምስክር ይሆናሉ:: ከዚህ በተጨማሪ በከርሠ ምድር ያሉትን ማዕድናት በሚገባ ተጠቅመውባቸዋል:: ይህም ወርቅ፣ ብር፣ መዳብ፣ ነሐስን ለያይተው መጠቀማቸው ራሱ ታላቅ ሥልጣኔ ላይ እንደ ደረሱ ያስገነዝቡናል::

[8] ጥንታውያን የአክሱም ገንዘቦችና ያስቀረጿቸው ነገሥታት በአዝማች ክንፉ ኪዳኔ::



www.ethiopianorthodox.org

# ገንዘቦቹ የተሠራባቸው ዘመናት ስከፋፈል

## [1] ክርስትና ከመቀበላቸው በፊት፤

ከጌታችን ልደት በኋላ ከሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል:: በዚህ ዘመን ውስጥ በአክሱም የተሠሩ የአንድቢስ፣ የአፌላስ፣ የውሳንናስ /የውሳናስ/፣ ቀዳማዊ ዋዜባ፣ የኢዛናስ ገንዘቦች ይገኛሉ:: እነዚህ የተገኙ ገንዘቦች ምንም ዓይነት የሃይማኖት /የመስቀል/ ምልክት የሌለባቸው ከመዳብ የተሠሩ ገንዘቦች ናቸው::

## [2] ክርስትናን በተቀበሉበት ዘመን፤

ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ባለው ጊዜ ደግሞ በአክሱም የተሠሩ የኤዛና ክርስትናን ከተቀበለ በኋላ የመስቀል ምልክት የተቀረፀባቸው ገንዘቦችና ኤዛና እራሱ በደቡብ አረብ ያሠራቸው ገንዘቦች ተገኝተዋል::

## [3] በአረብ ሀገራት ስልጣኔያቸው በተዘረጋበት ዘመን፤

ከ525-700 ዓ.ም ያለውን ያጠቃልላል:: በዚህ ዘመን ውስጥ ዐፄ ካሌብና ተከታዮቹ በአክሱም ያሠሯቸው ነገር ግን ለብዙ ዘመናት ቆይ ተው ያገለገሉ የናዛናና አናኤብ ገንዘቦች ይገኛሉ:: በዚህ ዘመን ውስጥ ካሌብ፣ ነዛና በደቡብ አረብ ያሠሯቸው ገንዘቦች ተገኝተዋል::

## [4] ከአረብ ግዛት በኋላ በብቸኝነት በኖሩበት ዘመን፤

ከ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ 8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያለው ጊዜ በአክሱም ከነገሡ መካከል አለልሜርዎስ፣ እለ ገበዝ፣ ኢዮ ኤል፣ እስራኤልና፣ የትሊያ በአክሱም የሰሯ ቸው ገንዘቦች ተገኝተዋል::

## [5] ስርወ መንግሥቱ በወደቀበት ዘመን፤

ከ8ኛው እስከ አስረኛው መቶ ክፍለ ዘመን በእነዚህ ዘመናት አርማህ፣ ሐታዝ፣ ቀዳማዊ ገርስመ፣ አንድ ስሙ ያልታወቀ ንጉሥ በአክ ሱም የሠሯቸው ገንዘቦች ይገኛሉ::

እንግዲህ በአጠቃላይ በእነዚህ በከፋፈልናቸው ዘመ ናት በገንዘቦቹ ላይ በተደረጉት ጥናቶች ስለ ገንዘቦቹ አይ ነቶች ጭምር ለማወቅ ተችሏል:: የዘመኑን ስልጣኔ ለማወቅ ከመቻላችንም በላይ እላያቸው ላይ ከተቀረፁት ነገሮች አን





ጻር በቂ ሥነ ጽሑፉ እንደነበራቸው ይጠቁሙናል:: አሁን ደግሞ ከታዋቂዎቹ የአክሱም ነገሥታት መካከል የጥቂቶቹን የገንዘባቸውን መለያ አይነት፣ የተሠሩባቸው ማዕድኖችና ግራማቸውን እንመልከት::

| ያስቀረጿቸው ነገስታት | መለያ | ክብደታቸው | የተቀረጹባቸው ማዕድናት |
|---|---|---|---|
| እንድቢስ | ከአክሱም ገንዘቦች ጥንታዊ ሲሆን፣ ንጉሱ መጠምጠሚያ /ሀባኔ/ አድ ርጐ ይታያል:: ቀረጻው ቀላል ሲሆ ን፤ ለሮማውያን ነገሥታት የወርቅ ገንዘቦች የተቃረቡ ናቸው:: | 2.75፣2.67 2.62 ግራም | ወርቅ |
| አፌላስ* | በሳንቲሙ ላይ ያለው የንጉሡ መ ልክ መጠምጠሚያ ብቻ ያደረገ ነው:: አክሲል የተቀዳጀ የንጉስ መልክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚታ የው በዚህ ንጉስ ገንዘብ ላይ ነው:: | በመጀመሪያ ያስራው 0.32 ግራም ሲሆን ሌሎች ከ2.40 እስከ 2.68 ግራም የሚደርስ ነው | ወርቅ ብር መዳብ |
| ኢዛናስ | የዚህ ንጉሥ ገንዘብ የግማሽ ጨረ ቃ ምስል የያዙ፤ የመስቀል ምል ክት ያለባቸው ገንዘቦች አሠርቷል:: ይህ ንጉሥ ክርስትና ከመቀበሉ በፊ ትና ስኋላ ያስቀረጻቸው ገንዘቦች ብዙ የሚለያዩበት የየራሳቸው ምል ክት አላቸው:: | 1.70፣2.12 ገንዘቦች የጨረቃ ምስል የያዙ ሲሆን 2.07፣1.87 የሚደርሡት ደግሞ ክርስትናን ከተቀበለ በኋላ ያስቀረጿቸው ናቸው | ወርቅ ብር መዳብ |
| ኤዛና | የዚህ ንጉሥ ገንዘብ ከየመን የመጡ አሉ፤ ኤዛናስ ካሰራቸውና አክሱም ውስጥ ከተገኙ ብዙ የተሰያዩ አይ ደሉም:: በገንዘቦቹ ፊት ለፊት ላይ ከአክሊሉ በላይ ምልክቶችና ፊደ ሎች ይገኛሉ:: ኤዛና የአክሱም ትልቁ ንጉሥ ነው:: | ከየመን የመጡት ከ1.35 ወደ 1.53 ግራም ይደርሳሉ በአክሱም ያስቀረጻቸው ግን ግራማቸው አይታወቅም | ወርቅ ሆኖ መዳብ የተቀላቀለበት |
| ካሌብ** | ይህ ንጉሥ የስቀረጸው ገንዘብ በደ ቡብ አረብ በተለይ በየመን በር ከት ያሉ ሲሆኑ፤ በአክሱም የበቀረ ጻቸው ግን የተገኙት ጥቂቶች ናቸ ው:: አቀራረጻቸው እምብዛም ያ ማረ የተከናወነ አይደለም:: እላያ ቸው ላይ በጥሬ ግዕዝ «ከለበ» የሚል በፊት ለፊታቸው ላይ ያለ ሲሆን፤ በጀርባው ላይ ደግሞ «ወልደ ታዜና» የሚል የተጻፈባ ቸው አሉ:: እነዚህ የካሌብ ገንዘቦች በተለይ ከወርቅ የተሠሩ ከሮም መንግሥት ገንዘቦች ጋር የሚነጻፀሩ ናቸው:: | ከ1.30 እስከ 1.61 ይደርሳል:: መካከለኛ ሚዛናቸው ወደ 1.52 የሚቀርብ ነው እነዚህ የወርቅ ሲሆኑ፤ የመደቦቹ 0.58-0.78 እና ግራም ነው | ከወርቅና መዳብ |



www.ethiopianorthodox.org

| | | | |
|---|---|---|---|
| እለ ገበዝ | ሥሙ በነገሥታት ሥም ዝርዝር ውስጥ በ70 እና በ80ኛ ተርታ ተጠቅሶ ይገኛል በዚህ ስም የሚጠሩ ሁለት ነገሥታት አሉ:: የዚህ ንጉስ ገንዘቦች የመጀመሪያው ማለት ነው ሁለት አዱሊስ ላይ በ1924 ዓ.ም በተደረገው ቁፋሮ የተገኙ ናቸው እላያቸው ላይ «እለ ገበዝ ንጉሥ» እና «ንጉስ» የሚሉ ተፅፎ ባቸው ይገኛሉ:: | የዚህ ንጉሥ የወርቅ ገንዘቦች ወርዳቸው 16.17ı-12እና 19 ሚሊ ሜትር ሲሆን ግራማቸው 1.47 ነው | ወርቅ |
| እስራኤል | የካሌብ ሁለተኛ ልጅ ሲሆን፣ የዚህ ንጉሥ 35 የወርቅ ገንዘብ ተገኝ ቷል:: እነዚህም በ1907 ዓ.ም በአ ዱሊስ አካባቢ በተደረገው ቁፋሮ የተገኙ ናቸው:: | መጠናቸው የተለያዩ ናቸው ወርዳቸው ከ17-19ሚ. ሜትር ይደርሳል:: ክብደታቸው ከ1.45 እስከ 1.67 ዓለም የሚደርሡ ናቸው | የተገኙት በአጠቃላይ የወርቅ ገንዘቦች ናቸው |
| ዋዜና | የዚህ ንጉሥ ገንዘቦች በጀርባው መካከል የሚገኝ በመስቀል የተቀረፀ ጌጥ በወርቅ የተሠራ ሐረግ እስ በት:: በፊቱ ላይ በጥንቱ ግዕዝ «ስአሐዘበ ዘይደለ» /ለእሕዛብ ይደሉ/ ስሕዝቦች የተገባ፣ የሚል ጽሑፍ አስበት:: የንጉሡ ሥም የሚገኘው በገንዘቡ ጀርባ ነው:: የንጉሡ መልክ በላዩ ላይ መሥቀል ያለው ቀጥ ያለ ሰብል እንደ በትረ መንግሥት ይዞ ይታያል:: | የገንዘቦቹ የወርዳቸው ልክ ከ141/2 ወደ 181/2 ሚ.ሜ ይደርሣል:: ክብደታቸው ከ0.80-1.90 ግራም ይመዝናል | ወርቅ |
| አርማሕ*** | ንጉሥ አርማሕ ያስቀረጻቸው ገንዘቦች በጠቅላላው አንድ አይነት ናቸው:: በዚህ ንጉሥ ዘመን በገንዘቦች ጀርባ የወርቅ ሀረግ የማድረግ ሥራ ቀርቷል:: በዚህ ፈንታ ልዩ ልዩ መልክ ያለው መስቀል ተቀርጾ ይገኛል:: መስቀሎቹ እንደ ጉንጉን አክሊል ሆነው የተያያዙ ሁለት ስብሎች ከጽሑፎቹ ይለዩታል:: | የአርማህ ገንዘቦች ወርዳቸው በ171/2 - 22 ሚ.ሜ የሚደርሱ ሲሆን አብዛኛዎቹ ትልልቆች ናቸው ክብደታቸው ከ1.30-3.00 ግራም ይደርሳል:: | አብዛኛዎቹ የመዳብ በንሐስ ናቸው |

* የዚህ ንጉሥ ገንዘብ አይነታቸው በብዛት ስለሚገኝ ይህ ንጉሥ ረዘም ላለ ጊዜ ነግሷል ለማለት ያስደፍራል::

** የመን የተገኙት ገንዘቦች እዚያ ስተዋቸው ወታደሮች ደሞዝ መክፈያ ላይሆን አይቀርም::

*** እስከ አሁን ከተገኙት የአክሱም ጥንታዊያን ገንዘቦች መካከል በመጠናቸው ትልልቆች የሆኑ የአርማሕ ገንዘቦች ብቻ ናቸው:: የዚህ ንጉሥ ገንዘብ የሚያስገነዝበን አርማህ እስልምናን የተቀበለ ቢሆን ኖሮ ከእርሱ በኋላ የነገሡ ነገሥታት የመስቀል ምልክቱን ስምን አልተውትም? እሱ ያስቀረጻቸው ገንዘቦች ላይ በሌላ ምስል ለምን አልተተኩም? ይህም በክርስቲያኑ ንጉሥ በዓርማህ አይደለም ከእርሱ በኋላ በነገሡ ነገሥታት አልታሰበም::





ከዚህ በላይ የተገለጡት ነገሥታት ታዋቂ ስለሆኑ ብቻ አስፍሬአቸዋለሁ:: ሥማቸው ያልተገለፀ /ያልተገኘ/ የአክሱም ነገሥታቶች ገንዘብ ተገኝተዋል:: ሆኖም ግን ለአንባቢ ግልፅ እንዲሆን በማለት በዝርዝር ቀርበዋል:: አሁን ደግሞ ከአክሱም የሥልጣኔ ምልክት የሆነው እነዚህ ገንዘቦቻቸው በየትና በማን ዘንድ እንደሚገኙ ለማወቅ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል::

| ገንዘቦቹ የሚገኙባቸው ከተሞችና ሰዎች | ወርቅ | ብር | መዳብ | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| ሮም | 42 | - | 23 | 65 |
| አሥመራ | 2 | 2 | 61 | 65 |
| ለንደን | 14 | 3 | 21 | 38 |
| ቪየና | 32 | - | - | 32 |
| በርሊን | 8 | | 24 | 32 |
| ፓሪስ | 9 | 1 | 13 | 23 |
| ሌሊን ግራድ | 7 | - | 1 | 8 |
| ኒውዮርክ | 4 | - | - | 4 |
| ቦምቤ | 4 | - | - | 4 |
| ፍራንክፈርት | 2 | - | - | 2 |
| ናቪል | 2 | - | - | 2 |
| ሙኒክ | 1 | - | - | 1 |
| በአክሱም ቁፈራ | - | 2 | 15 | 17 |
| የቃው ኤል ከቢር መዝገብ | - | - | 13 | 13 |
| የሐዋራ መዝገብ | - | - | 2 | 2 |
| አንዛኒ የተሰበሰበው | 19 | 4 | 70 | 93 |
| ፓሮና " | - | 2 | 34 | 21 |
| ዳባዲ " | - | - | 21 | 11 |
| ሙኒሽኒ " | 11 | - | - | 9 |
| ኸውባለን " | - | - | 9 | 9 |
| ሌዠን " | - | + - | 8 | 8 |
| ሸሉ በርግ " | 5 | - | 1 | 6 |
| ኖወል " | 4 | - | - | 4 |



www.ethiopianorthodox.org

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ብራራ " | - | - | 4 | 4 |
| ቼኒራላ " | 2 | - | - | 3 |
| የስኒ " | - | - | 1 | 2 |
| ድሮዊን " | 2 | - | - | 2 |
| ጀምስን " | 1 | - | - | 1 |
| ሃላቪ " | 1 | - | - | 1 |
| ኤንገል " | 1 | - | - | 1 |
| እናስታሲ " | 1 | - | 1 | 1 |
| ስንዱስትሩም " | 1 | - | - | 1 |
| ዲላማን የጠቆመው | 1 | 1 | - | 1 |

በዚህ ሰንጠረዥ ያልተገለፁ በልዩ ልዩ ሊቃውንት እንዲሁም ገንዘቦችን በሚሠበስቡ ግለሰቦች እጅ ሌሎች የአክሱማውያን ጥንታውያን ገንዘቦች እንደሚገኙ የታወቀ ነው:: በመጨረሻም ገንዘባቸው በውል የተገኘ የአክሱም ነገስታቶች ስም ዝርዝርና ገንዘቦቹ ከምን መአድን የተሠሩ መሆናቸውን በቀጣዩ ሰንጠረዥ እንመልከት::

| የነገስታቱ ስም | ወርቅ | ብር | መዳብ | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| እንደቢስ | 3 | - | - | 3 |
| አፊላስ | 7 | 2 | 5 | 14 |
| የውሳናስ | 1 | - | - | 1 |
| ውሳናስ 1ኛ | 2 | 2 | - | 4 |
| ዋዜባ | 1 | - | - | 1 |
| ኤዛናስ | 16 | 2 | 3 | 21 |
| ኤዛና | 5 | - | - | 5 |
| የኤዛና ተከታዮች ስም የሌላቸው | - | 1 | 40 | 41 |
| ዋዜባስ | - | - | 15 | 15 |
| መሀየገስ | - | - | 7 | 7 |
| ያልታወቀ ንጉሥ | - | 1 | - | 1 |





| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| እና አሬዎስ | 9 | - | - | 9 |
| ያልታወቁ ነገሥታት | 3 | - | 1 | 4 |
| ኢስባኤል | 38 | - | - | 38 |
| ካሌብ | 25 | - | 3 | 48 |
| ካሌብና ተከታዮቹ | - | - | 38 | 38 |
| ኤዛና | 3 | 1 | - | 4 |
| ውሳናስ 2ኛ | 1 | - | - | 1 |
| ውሳስ | 10 | - | - | 10 |
| አናኤብ | - | 3 | - | 3 |
| አላልሚርዎስ | 1 | - | - | 1 |
| አለ ገበዝ | 3 | - | - | 3 |
| ኢዮኤል | 2 | - | 25 | 27 |
| እስራኤል | 35 | - | - | 35 |
| ዖትለያ | 2 | 1 | - | 3 |
| ዋዜና | - | - | 11 | 11 |
| አርማሕ | - | 1 | 38 | 39 |
| ሐታዝ 1ኛ | - | - | 4 | 4 |
| ገርሠም | 3 | - | 4 | 7 |
| ያልታወቀ ንጉስ የናስ | 1 | - | - | 1 |
| ሐታዝ የወርቅ | - | - | 36 | 36 |

## አክሱም በከርሰ ምድር ጥናት ምርምር [አርኪዮሎጂ]

አክሱም አሁን ከምትታየው ሌላ በምድር ውስጥ ሌላ ከተማ አላት በማለት በየጊዜያቱ ተቆፍሮ በሚወጡ ቅርሶች መሠረት በማድረግ ይገልፃሉ:: በ1910 ዓ.ም በስሜን ኢትዮጵያ በጀርመናዊ ሊቅ በኢኖ ሊትማን የተመራ ቡድን መጥቶ ነበር:: ይህ ቡድን ጸሐፊ፣ ፎቶ ግራፍ አንሺ፣ ቆፋሪ፤ ኘላንሰሪ ሆነው በአክሱምና በአካባቢዋ ባሉ ታሪካዊ ስፍራ



www.ethiopianorthodox.org

ዎች እየተዘዋወሩ ቆመውና ወድቀው ከተገኙት ሐውልት ላይ ያገኙትን:- የሳባ፣ የግሪክና፣ የግዕዝ፣ ጽሑፍ እየገለበጡ በሌ ላም በቁፋሮ ያገኙትን ለኢትዮጵያ ታሪክ ጠቃሚ የሆነ ሥራ አዘጋጅተው ደች አክሱም ኤክሴፔንዲሽን /DEUTSVUN AXUM EXPEDITION/ በተባለ በአራት ቮልዩም በጀርመን ቋንቋ አዘጋጅተው ማሳተማቸውንና ይልቁንም በአራተኛው ቮልዩም ላይ ከየሐውልቱ በቀጥታ የወሠዱትን በሳባና በግዕዝ ጽሑፍ ያስፈሩ መሆኑን ይህም ለታሪክ ጸሐፊዎች በቂ ምን ጭ ሆኖ እንደሚያገለግል ክቡር አቶ ተክለጻድቅ መኩሪያ ገልጸዋል::[9]

ከዚህ ሌላ ትልቁ የአርኪዮሎጂ ግኝት የንግሥተ ሳባና የልጇ የቀዳማዊ ምኒልክ ቤተመንግሥትና መካነ መቃብር በአክሱም ከተማ መኖሩ ነው:: በተለይ የቀዳማዊ ምኒልክ መካነ መቃብር ከተገኘ በኋላ አፅሙ ወጥቶ በጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክብር ተቀምጧል:: የንግሥተ ሳባና የኩሽ መቃብራት ግን ቦታዎቹ ተለይተው ከመታወቃቸው በቀር አልተቆፈሩም:: አፅሞቹ በዚያ እንዳሉ ናቸው ወደ ፊት በአርኪዬሎጂስቶች ተቆፍሮ ይወጣል ተብሎ ይጠበ ቃል:: አሁን በቅርብ ጊዜ ደግሞ መቃብረ ኩሽ አካባቢ የቤተ ጊዮርጊስ ተራራ ላይ ቁፍሮ ተካሒዶ፤ በቃልና በብራና መጻሕፍት ተጽፎ የሚገኘውን የአክሱምን ታሪክ የሚደግፉ ሆነው ተገኝቷል:: እነዚህ ቅርሶች የሐውልት የሸክላና የቤት መገለገያ እቃዎች፤ ከዝሆን ጥርስ የተሠሩ ጌጣ ጌጦች በብ ዛት ይገኙባቸዋል:: የአክሱም ከተማ ከርሰ ምድር ገና ያል ተመረመረ በመሆኑ ለወደፊቱ በቂ ምርምር ሲደረግ ብዙ የታሪክ ቅርሶች ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል:: እስከ አሁን የተገኘው ከ3 ፐርሰንት ያልበለጠ ነው:: በአክሱም ከተማ ለአርኪዮሎጂ ምርመራ ተብለው በሚደረጉ ጥናቶች መሠ ረት 160 የሚሆኑ አካባቢዎች የአርኪዮሎጂ ቦታዎች ተብ ለው ተለይተው የታወቁ ሲሆን እነዚህም አብያተ መንግ ሥት፣ ሐውልቶች፣ መቃብሮች፣ የጥርብ ድንጋይ ቅርሶች፣ ሌሎች ከምድር በላይና በታች የሚገኙ የታሪክ ሥፍራዎች

---

[9] የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ ናፓታ መራዌ 1ኛ መጽሐፍ ገጽ 15-16





ናቸው:: በአጠቃላይ በአክ ሱምና በአካባቢዋ የሚከተሉት ታሪካዊ አሻራዎች ጉልተው ይታያሉ::

- ✞ ከአንድ አለት ተፈልፍለው የተሠሩ እድሜያቸው ከ2ሺ ዓመት በላይ የሆኑ የድንጋይ ሐውልቶች፤
- ✞ የድንጋይ ላይ ሰሌዳዎች፤ በጥንታውያን ሳባዊ፣ ግዕዝና ግሪክ ቋንቋዎች የተጻፈባቸው ሐውልቶች::
- ✞ የዐፄ ካሌብና የዐፄ ገብረ መስቀል ቤተ መንግሥትና መካነ መቃብር ሕንፃዎች ፍራሽ፤
- ✞ የጥንታውያን ነገሥታት ሥርዓተ ንግሥ የሚፈፀምበት መናገሻ ፍርድ የሚሰጥባቸው የድንጋይ መናብርት፤
- ✞ በ350 ዓ.ም የተሠራው ጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን ህንፃ ፍራሽና፤ እንዲሁም ዛሬ ያለው በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአፄ ፋሲል የታ ነፀውና፤ በ1957 ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ያሠሩት ዘመናዊ ህንፃ ቤተክር ስቲያን፤
- ✞ የጥንታውያን ነገሥታት ዘውዶች፤ አልባሳተ መንግሥታት፤ የመሳፍ ንቶች የራስ ወርቅ፤ እንዲሁም የወርቅ አልባሳት፤ ጥንታውያን መጻሕፍት የሚገኙበት እቃ ቤትና ቤተ መዛግብት፤
- ✞ የጥንታዊው የሳባ ከተማ ህንፃዎች ፍርስራሽ፤ በ20ኛው ክፍለ ዘመን በተመራማሪዎች ተቆፍሮ የወጣው ጌታ በቤተልሔም ሲወለድ በኢት ዮጵያ ነግሶ የነበረው የባዜን መቃብር፤
- ✞ የንግሥተ ሳባ መታጠቢያና የከተማዋ ጥንታዊ የውሀ ግድብ፤ አሁን የጥምቀት በዓል የሚከበርበት ቦታ፤
- ✞ የአንበሳ ምስሎች የሚገኙበት የድንጋይ ሐውልት፤ ድንጋዮቹ እየተ ፈለፈሉ እየተጠረቡ የወጡበት የድንጋይ ተራራ፤
- ✞ ከአንድ ቋጥኝ ተፈልፍሎ የታነፀው የአባ መጣዕ ቤተ ክርስቲያን፤ የአፄ ካሌብ፤ ከተሰአቱ ቅዱሳን መካከል ደግሞ የአባ ጰንጠልዮን፤ የአባ ሊቃኖስ መካነ እረፍት የሆኑ ገዳማት፤

እነዚህን የመሣሰሉ ስልጣኔዎች አክሱም ተሸክማ አሁን ድረስ ለመረጃ ያህል እየታዩ ይገኛሉ:: በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ከአክሱም እንደሚጀምር ተመልክተ ናል፤ ይህ ሥልጣኔ አብቦ ወደፊት በዚህ መጽሐፍ በሰፊው እንደምንመለከተው ወደ ሮሐ /ላሊበላ/ ጐንደር ዘልቋል:: ሀገራችን በእምነት፣ በታሪክ፣ ሥነ ጽሑፍ፣ ቋንቋ፣ ባሕል በጠቅላላው በኪነ ጥበብ በቀይ ባሕርና በሜዲትርንያን ባሕር አካባቢ በነበሩትና ባሉት አገሮች የቅርብ ግንኙነት ነበራት:: ከእነዚህም አገሮች በእምነትና በስልጣኔ የበለፀገች፤ በቅዱሳት መጽሕፍት ትምህርት የተራቀቀች፤ የራሷ ፊደልና



www.ethiopianorthodox.org

ቋንቋ በጠቅላላው የራሷን ኪነ ጥበብ አክብራ፣ የሥነ ጽሑፍ ሥርዓትን ጠብቃ እምነቷን አፅንታ የያዘች እንዲት በተራራ ላይ የታነፀች መሠወር የማትችል ታሪካዊ ሀገር ኢትዮጵያ ናት።

## ኢትዮጵያ በሃይማኖት

ና

ሀገራችን አስቀድማ ብሉይ ኪዳንን የተቀበለች ከቤተ እስራኤል ቀጥላ በአምልኮተ እግዚአብሔር የታወቀች ሀገር ናት። በንግሥተ ሳባ አማካኝነት የብሉይ /የኦሪት/ እምነት ወደ ሀገራችን ገብቷል። ከንግሥተ ሳባ የኢየሩሳሌም ጉብኝት በኋላ ኢትዮጵያ በመንፈሳዊም ሆነ በማኅበራዊ አድገት በኩል ያገኘችው በረከት ብዙ ነው። እነዚህም:-

- የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ባለቤት፤
- የሥዩማን ካህናት አገልጋይ፤
- የታቦተ ሕግ መንበር፤
- የተደራጀ የቤተ ክህነት ሥርዓት ሀገር ለመሆን በቅታለች።

በኋላም የዓለምን ተስፋ የፈፀመው መሲሕ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመሠረተውን የክርስትና እምነት በ34 ዓ.ም ተቀብላለች። ከዚህ በኋላ በከሣቴ ብርሃን ሰላማ ፅኑ መሠረት ያለው የክርስትና እምነት በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተሠብኳል። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ነጋሪት መቺነት የወንጌልን ገፊት ቀምሳ፤ ሕገ ኦሪትን ሳትረሳ፤ ሁለቱን እየጣጣመች በክርስቶስ ደም የበቀለውን እውነተኛ ትምህርት ነው የምታስተምረው። ወደ 1 ቢሊዮን የሚጠጋ የዓለም ጥቁር ሕዝብ የታሪክ እንብርት የተቋጠረው በኢትዮጵያ ነው።

አንድ ታላቅ ሀገርና አንድ ነባር ቤተ ክርስቲያን አጣምሮ የያዘ ታሪክ ያላቸው ሕዝቦች ቢኖሩ ኢትዮጵያውያን ነን። ወንጌልንና ቤተ ክርስቲያንን የያዙ ብሉይ ኪዳንና ቤተ መቀደስ የላቸውም፤ ብሉይ ኪዳንና ቤተመቅደስ የነበራቸውም አዲስ ኪዳንና ቤተ ክርስቲያን የሏቸውም፤ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ብልጫችን እዚህ ላይ ነው! ብሉይ





ኪዳንና አዲስ ኪዳንን፤ ቤተ መቅደስና ቤተክርስቲያንን፤ ትንቢትንና ስብከትን፤ ምሳሌውንና አማናዊውን አስተባብረን ጠብቀን ይዘን መኖራችን ነው። ይህን ዘመን የማይሽረውን በሰማይም በምድርም ፍፁም ዋጋ ያለውን ህልፈትና መለወጥ የማይስማማውን ታሪክ ስላወቁና ስለተረዱ ነው ቀደምት አባቶች ቤተ ክርስቲያናቸውን ከሀገራቸው ያልለዩት።

እኛም ይህን ካመንን የታሪካችንን ባለ ዋጋነት ልንገነዘብ ያስፈልጋል። እንዲህ ከሆነ የሃይማኖትን ነገር ልናስተምር እንጂ ሊያስተምሩን መሻት የለብንም ኢትዮጵያዊ ሆኖ የቤተ ክርስቲያን ያልሆነ አለ ቢባል አይቻልም። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በፍፁም ጠላት ሊኖራት አይገባም ከየት የመጣ ኢትዮጵያዊ ነው የሷ ጠላት? ጠላቶች አሏት ቢባል እንኳ በኢትዮጵያ ምድር ያልተወለደ መሆን አለበት። ይህ ከላይ የገለፅናቸው ዋና ዋና ርዕስ ጉዳዮች ወደ መጽሐፉ ይዘት ከመግባታችን በፊት ኢትዮጵያና ኢትጵያውያንን ለማስተዋወቅ ያህል የሠፈረ ነው። በአጠቃላይ:-

## ቅድስት ሀገራችን

- የጥንት ሥልጣኔ ምንጭ፤
- ኦሪትና ወንጌልን በምድሯ ላይ ያስተናገደች፤
- ለዘመናት ያልተቋረጠ በትረ መንግሥት የተፈራረቀባት፤
- በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሴት ንግሥት /ሳባ/ ያነገሠች፤
- በሌላ ዓለም የሌሉ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናትን ያነፀች፤
- ከአፍሪካ በራሷ ቋንቋና ፊደል የምትመራ ብቸኛ ሀገር፤
- ጽላተ ሙሴና ግማደ መስቀልን በቅርስነት የያዘች፤
- በሽታዎችን ሊያጠፉ የሚችሉ ጠበል የሚፈልቅባት፤
- ጠፍተው የነበሩ መጽሐፈ ሔኖክና ኩፋሌ የተገኙባት፤



www.ethiopianorthodox.org

- ከ41 ጊዜ በላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ስሟ የተገለጠ፤
- የዓለም ጥቁር ሕዝብ የታሪክ እንብርት የተቋጠረባት፤
- የቤተ ክርስቲያን መቅረዝ የሆነ ቅዱስ ያሬድን ያስገኘች፤
- ለመጀመሪያ ጊዜ የመስቀል መልክት ያለው ሳንቲም ያስቀረጸች፤
- ለነፃነት ተምሳሌት የሆነች፤
- የባዕድ እጅ ያልዳሰሳቸው፣ ዘመናት ያልሻራቸው የኪነ ጥበባት ክምችት ያለባት፤
- መጽሐፍ ቅዱስን ምንጭ ያደረጉ ባሕል ያላት፡፡

ኢትዮጵያችን ናት!

◈◈◈◈◈◈





# ምዕራፍ አንድ

## የመጀመሪያው ወርቃማ ዘመን
[ከ1000 - 900 ዓ.ዓ]

ታሪኩ ከንግሥተ ሳባ ይጀምራል በቀድሞዎቹም ሆነ በአሁን ዘመን ትውልድ በኢትዮጵያውያን አመለካከት የዚች ንግሥት ታሪክ ከፍተኛውን ሥፍራ ይዞ ይገኛል፡፡ ከጌታችን ልደት በፊት በ1ሺ ዓመተ ዓለም የነገሠችው ንግሥተ ሳባ ብዙ ከተማዎች የነበሯት፤ ግዛቷን እያስፋፋች እግዚአብሔርንም በመፍራት በመልካም ሁኔታ ሕዝቡን ታስተዳድርና ትገዛ በነበረችበት ዘመን በእግዚአብሔር ፈቃድ ተቀብቶ በእስራኤል ላይ ነግሦ የነበረውን የሰሎሞንን ጥበብና መንፈሳዊ ኃይል ትሰማ ስለነበር ይህን ጥበብና መንፈሳዊ ኃይል በጆሮ መስማት ብቻ በቂ ሆኖ ስላላገኘችው በዓይን አይቶ መረዳት የበለጠ መሆኑን ተገነዘበች፡፡ ይህን ወሬና ዝና ያመጣላት የነበረው ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም በንግድና በመልዕክትም ይመላለስ የነበረው ታምሪን የተባለው ነጋዴ ነው፡፡ ይህ ነጋዴ በኢየሩሳሌም በሚቆይበት ጊዜያት ብዙውን ግዜ የሚያሳልፈው የንጉሡን የሰሎሞንን ስጋዊና መንፈሳዊ ጥበብ በማየት ነው፡፡ ሥርዓተ መንግሥቱን በማጥናትና በመጠበቅ የነበረው ሁኔታ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ በሚመለስበት ጊዜ እየዘረዘረ ለንግሥተ ሳባ ይነግራትና ያስረዳት ስለነበር ንግሥተ ሳባ ከዚሁ ነጋዴ በምትሰማው የሰሎሞንን ስጋዊና መንፈሳዊ ጥበብ ከንጉሡ ጋር ለመተዋወቅና ለመዛመድ ፈለገች፡፡ ለዚህም በታምሪን አማካኝነት ገፀ በረከት አስይዛ ወደ ኢየሩሳሌም ላከችው፡፡ መልዕክቱንም አድርሶ ከተመለሰ በኋላ በድጋሚ ስለ ንጉሥ ሰሎሞን አስረዳት፡፡



www.ethiopianorthodox.org

## የንግሥተ ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም መሔድ

ንግሥተ ሳባ ታምሪን የተባለው ነጋዴዋ በአይኑ ያየውንና በጆሮ የሰማውን እየዘረዘረ ካስረዳት በኋላ የጠቢቡ ሰሎሞን ዜና ማየት እንጂ መስማት ብቻ በቂ አለመሆኑን ተረዳችና ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሔድና በላከችው ገፀ በረከትና ፍመልእክት ታምሪን የተባለው ነጋዴዋ አማካኝነት ከንጉሥ ሰሎሞን ጥሪ ተደረገላት:: ምኞቷና ሀሳቧ ይሰምርላት ዘንድ መንፈስ እግዚአብሔር ልቦናዋን አነሳሳት:: ወደ ኢየሩሳሌም የመሔድ ጉዳይ አማካሪዎቿ ከወሰኑ በኋላ እርሷና ለተከታዬቿ የሚሆን ስንቅ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ በቅርብ ጊዜ እንዲዘጋጅ ታዘዘ:: ከዚህ በኋላ ጉዞዋን ቀጠለች እግዚአብሔርም መንገዱን አቀናላት ያለ አንዳች መሰናክል ተጉዛ ንጉሥ ሰሎሞን ወደ አለበት ኢየሩሳሌም ደርሳ ለታቦተ ጽዮን ክብርና ለንጉሥ ሰሎሞንም እንደሚገባ ገፀ በረከት አቀረበች 1ነገ 10÷1-13:: ንጉሥ ሰሎሞንደስ ተሰኝቶ በቤተ መንግስቱ አቅራቢያ ለእቃና ለሠራዊቷ እንደሚበቃ አድርጎ ታላቅ የሆነ ክብር ያለበት ማረፊያ ሰጣት ወዲያውም ለእርሷና ለተከታዮቿ በቂ የሆነ መስተንግዶ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ በየቀኑ ይላክላት ነበር:: አንዳንድ ጊዜ ንግሥተ ሳባ በክብር ተጠርታ እየሔደች የቤተ መንግሥቱን ሥርዓትና ሥጋዊና መንፈሳዊ ጥበቡን ትመለከት ነበር:: እርሱንም ስለ አምልኮተ እግዚአብሔር ስለ ንግሥና አስተዳደር ትጠይቀው ነበር::

## የንግሥተ ሳባ ከኢየሩሳሌም መመለስ የቀዳማዊ ምኒልክ መወለድ

ንግሥተ ሳባ ከንጉሥ ሰሎሞን ለእርሷም ሆነ ለወገኖቿ የሚጠቅመውን ሥጋዊና መንፈሳዊ ጥበብ በመስማትና በማየት በማጥናት በኢየሩሳሌም ከቆየች በኋላ ወደ አገሯ ኢትዮጵያ ለመመለስ ያላትን ፈቃድ ገልፃ ለንጉሥ ሰሎሞን ላከችበት እርሱም ይህን በሰማ ጊዜ እዚህ ድረስ መጥተሽ ሥርዓተ መንግስት ሳናሳይሽ ልትሔጂ አይገባም ብሎ መለሳት:: ከዚህ በኋላ በዚህ ተስማማች ሥርዓተ መንግስቱ በሚደረግበት ቀን ከደረሰ በኋላ ንግሥተ ሳባ በክብር ተጠርታ ሁሉን ከምታይበት ስገንት ላይ ሆና ሥርዓተ መንግስቱን ሲካሄድ አየች:: ለመሳፍንቱና መኳንቱ በጠቅላላው ለሠራዊቱ ሁሉ የተደረገውን ግብዣውን አቀራረብ በጣም አደነቀች በዚህም ወቅት ቀዳማዊ ምኒልክ ተፀነሰ:: እርሷም ወደ አገሯ ለመመለስ ያላትን ፈቃድ ጠይቃ አሳወቀች:: ንጉሥ ሰሎሞንም ለእርሷ የሚሆናትን ጌጣጌጥ አልባሳት ለመንገድም የሚሆናትን ሁሉ በሰረገላ ሆነው የሚሸኟት ታላላቅ መኳንንት ሠራዊት አዘዘ:: እሱም አጅቦ ሲሸኛት የወርቅ ቀለበቱን ከጣቱ አውልቆ ይህ ማስታወሻ ይሁንሽ የእስራኤል አምላክ ፈቃዱ ሆኖ ከአንቺ ልጅ ከሰጠኝ ይህን ምልክት ይዞ ወደ እኔ ይምጣ ብሎ በታላቅ አጀብ ሸኛት::

## ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ሰባቱ ንጉሥ ሰሎሞን መሔድ

እንደዛሬው የተጠናከረ የአየርና የየበስ መጓጓዣ በሌለበት በዚያን ጊዜ ይህን ሁሉ መንገድ አቋርጣ መንገዷን ፈፅማ ኢትዮጵያ ከመድረሷ በፊት የመን ገባች ከዚያም ተጉዛ ባሕረ ኤርትራን ተሻግራ በሐማሴን በኩል ማይበላ[1] ከተባለው ከተማ ደረሰች ከዚህም ቦታ ልጇን ወለደችው ስሙንም «እብነ መለክ» አለችው:: ይህ ስም በዘመን ብዛት ተለውጦ የዛሬውን ምኒልክ የሚለውን ስም ወለደ:: ከዚህ በኋላ በዚያን ጊዜ ሳባ ዛሬ ግን አክሱም ወደሚባለው ከተማ በገባች ጊዜ መኳንንቱን መሳፍንቱ ሠራዊቱ ሁሉ በክብር ተቀበላት:: ቀዳማዊ ምኒልክ ካደገ በኋላ አባቴ ማን ነው? እያለ ይጠይቅ ስለነበር ህያ ዓመት ሲሞላው አባትህ በእስራኤል ላይ የነገሠ የንጉሥ ዳዊት ልጅ ሰሎሞን መሆኑን ነገረችው:: ወደ አባቴ እሔዳለሁ ስላላት ታምሪን የተባለው ነጋዴዋን አስጠርታ ከንጉሥ ሰሎሞን ጋር አገናኘው ብላ ነገረችው::

---

[1] በትግረኛ ማይበላ ማለት ሴቶች ውሀ አምጡ ማለት ነው:: ንግሥቲቱ በምጥ በተያዘች ጊዜ ውሀ በማስፈለጉ ይህ ትዕዛዝ የተሠጠ ሲሆን እስከዛሬ ወንዙ ማይበላ በመባል ይታወቃል:: የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ገፅ 11 የግርጌ ማስታወሻ::




www.ethiopianorthodox.org

ይህን ትዕዛዝ ታምሪን ተቀብሎ ከንግሥተ ሳባ ለታቦተ ጽዮንና ለንጉሥ ሰሎሞን የሚሆን እጅ መንሻ ለመንገድም አስፈላጊ የሚሆነውን ሁሉ አብረውት ለሚሔዱ መኳንንትና ለመሳፍንቱ ብዙ ወጭ አድርጋ በጥብቅ አደራ ላከችው:: «ይህ ልጅ በመንግስቴ እንዲነግስ ፈቃዴ ነውና ሕገ ኦሪትን ሕገ መንግሥትንም ሥርዓተ ክህነትን አስተምረው ለበረከት ያህልም ከፊታችን አድርገን እግዚአብሔርን ለማሰብ እጅ የምንነሳበትን ሰማያዊት ከመትሆን ነገረ ታቦትን እንዲላክልን አድርግ እግዚአብሔር መንግሥትህን ይባርክ» የሚል ደብዳቤ ታምሪን ተቀበላት:: ወዲያው ልጇን ለብቻዋ አቆይታ ንጉሥ ሰሎሞን ለማስታወሻ ምን አልባት ልጁ ቢወለድ ምልክት ይሆነዋል ብሎ የሰጣትን ወርቅ ሰጠችው ይህም የእርሱ ልጅ መሆኑን በቀላሉ እንዲረዳ ነው:: ከዚህ በኋላ ልጁን አብረውት የሚሔዱ ሁሉ ተሰነባብተው ወደ ኢየሩሳሌም መንገድ ጀመሩ::

## ቀዳማዊ ምኒልክ ኢየሩሳሌም መድረስ

በብዙ ሠራዊት የታጀበው የንግሥተ ሳባ የበኩር ልጅ ኢየሩሳሌም እንደደረሰ የእስራኤል አምላክ መንገዱን አቅንቶላቸው በኢየሩሳሌም ጋዛ ወደ ምትባለዋ አገር ደረሱ:: ይህቺ አገር ንጉሥ ሰሎሞን ለንግሥተ ሳባ ማረፊያ ይሁንሽ ብሎ የሰጣት አገር ናት:: ጋዛ በዘመነ ብሉይ ኢትዮጵያውያን ወደ ኢየሩሳሌም አምልኮታቸውን ለመፈፀም ሲሔዱ ማረፊያቸው ናት ወደፊት የምናየው የጃንደርባው ታሪክ ይህን ያስታውሰናል:: ከዚህ በኋላ ንጉሥ ሰሎሞን የልጁን መምጣት በሰማ ጊዜ የጦር አዛዡን የከተማውን ሕዝብ አሰልፎ ጠበቀው የጦር አዛዡ ብንያስ ልጁን ወደ ንጉሡ እልፍኝ ይዞት ገባ:: ንጉሥ ሰሎሞንም ገና በሩቅ ሲያየው ደንግጦ ተነሳና አንገቱን አቅፎ ሳመው:: አስፈላጊውን ስጦታና አቀባበል ካደረገለት በኋላ ለመኳንንቱ ከፍ ያለ ግብዣ አደረገ:: እግዚአብሔር ስላሰበው የሰጠኝን ልጅ እዩ አላቸው:: እነሱም ይህን የወለደች እናት የተባረከች ናት እያሉ ሁሉም ሰፊ የሆነ ቃለ በረከት አቀረቡ::





ወዲያውም ልጁ ቀዳማዊ ምኒልክ አባቱ ለእናቱ የሰጣት ቀለበት ሰጠው:: እርሱም የተፈጥሮ መልኬን በአንተ ላይ አይቼ ልጄ እንደሆንክ ተረድቼአለሁ፤ ይህን ለምልክት ለምን ትሰጠኛለህ? ብሎ መልስ ሰጠው ከዚህ ቀጥሎ ታምሪን የተባለው ነጋዴ ንጉሥ ሆይ እመቤቴ ለአንተ የላከችውን መልእክት እናገር ዘንድ ፈቃድህ ይሁንልኝ ብሎ ተናገረ:: ከንግሥተ ሳባ የላከውን ደብዳቤ አነበበ «ንጉሥ ሆይ ይህ ልጄ በአገሬ ኢትዮጵያ ሥልጣነ መንግሥቱን ሙሴ የጻፋቸውን ሕግጋት፣ ሥርዓተ ክህነት አስተምረህ ላክልኝ ቢያስቸግረኝ ነው እንጂ ወደ አንተ መምጣቱን አልፈቀድኩም ነበር:: ምክንያቱም የአንተ አባትነትን ጠልቼ ሳይሆን በመንገዱ ርቀት በሀሩሩ ግለት ታሞ ይሞታል ብዬ ሰግቼ ነው:: ስለዚህ ወደ እኔ መመለሱን እንዳትከለክለው የእግዚአብሔር ማደሪያ በምትሆን በታቦተ ጽዮን ስም እማፀናለሁ» የሚል ነበር መልእክቱ:: ቀዳማዊ ምኒልክ በኢየሩሳሌም ከአባቱ ጋር የቆየው ሦስት ዓመት ሲሆን በዚሁ ዘመን መጻሕፍተ ሙሴን፣ ሕገ መንግሥት፣ ሥርዓተ ክህነትን፣ የዕብራይስጥን ቋንቋ ከሊቀ ካህናቱ ከሳዶቅ ጋር ተምሮ ወደ ኢትዮጵያ ለመሔድ ተነሳ::

## ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ኢትዮጵያ መመለስና፤ ታቦተ ጽዮን መምጣት፤ የምኒልክ መንገሥ፤ ለታቦተ ጽዮን ምኩራብ-መቅደስ መሠራት

ንጉሥ ሰሎሞን ወዲያው ሕዝቡን ሰብስቦ ይህ ልጅ ወደ አገሩ ሊመለስ ነውና የበኩር ልጆቻችሁን ከተማሩት ከካህናት ወገን አብረውት እንዲሔዱ አዘዛቸው:: ከዚህ በኋላ ሌዋውያን ተመርጠዋል:: ንጉሥ ሰሎሞን አባቱ ዳዊት «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» ብሎ ትንቢት እንደተናገረላት አሁንም ይህቺ አገር በረድኤተ እግዚአብሔር የምትጠበቅ አገር መሆኗን በዚህ ይታወቃል በማለት ለልጁ ለምኒልክ የሰጠውን በረከትና ረድኤተ እግዚአብሔር በአድናቆት ተመለከተ:: ከዚያም አያይዞ ሊቀ ካህናቱን ሳዶ



www.ethiopianorthodox.org

ቅን በቶሎ ሒድና በታቦተ ጽዮን ላይ የሚገኘውን ልብስ
(መጐናፀፊያ) አምጣ፤ የምኒልክ እናት ንግሥተ ሳባ ለታም
ሪን የላከችው ደብዳቤ በመንግሥቴ ያሉት ሁሉ ታቦተ
ጽዮንን እናስባት ዘንድ ለበረከት የሚሆን ነገር ላክልኝ
ብላኛለችና በፍጥነት ለበረከት የሚሆነውን ስጠው:: ስትሰጠ
ውም ሕገ ኦሪትን እንዲጠብቅ፤ መስዋዕት በሚሰዋበት ጊዜ
በኢየሩሳሌምና በታቦተ ጽዮን አንፃር ሁንና አቅርብ፤ ስት
ጸልይም በኢየሩሳሌም አንፃር ሆነህ ጸልይ ብሎ ሊቀ
ካህናቱም ሳዶቅ ለምኒልክ ነገረው:: የሊቀ ካህናቱ ልጅ
አዛርያስም[2] በአባቱንና በንጉሥ ሰሎሞን ፊት ለበረከት የተ
ሰጠውን ስጦታ በደስታ ተቀበለና ወደ ቤተ መቅደስ ጸሎት
ሊያደርግ ገባ፤ እግዚአብሔር ታቦተ ጽዮንን ወደ ኢትዮጵያ
እንድትመጣ ፈቃዱ ስለሆነ ለአዛርያስ በራዕይ ያነጋግረውና
በመንፈስም ያፅናናው ነበር:: አዛርያስ ወደ ኢትዮጵያ እንደ
ሚሔድ በንጉሥ ሰሎሞን ታዞ ስለነበር ይህን ቢያመለክት
አምደ እሳት ቤተ መቅደሱን በብርሃን ተከብቦ አየ::

ወዲያው ፈጥኖ ሔዶ የመንፈስ ቅዱስ ጓደኛውን
ኤልማስን ከእንቅልፉ አነቃው፤ ኤልማስም ወንድሙን አቢስን
ከእንቅልፉ ቀሰቀሰውና ሁሉም ተያይዘው ታቦተ ጽዮን ወዳለ
ችበት ቤተ መቅደስ ገብተው ከመንበሩ እግር አጠገብ ቆሙ::
በዚህን ጊዜ በቤተ መቅደሱና በዚያው ይታይ የነበረው ብር
ሃን ግሩም ነበር:: አዛርያስም እግዚአብሔር ታቦተ ጽዮንን
ይዛችሁ ሒዱ ሲለን ነው ብለው ታቦተ ጽዮንን ንጉሡ በሰጠን
መጐናፀፊያ ሸፍናችሁ ተነሱ አላቸው:: ኤልማስና አቢስም
ታቦተ ጽዮንን ይዘው ሲወጡ ከሊቀ ካህናቱ ከአዛርያስ በቀር
የሚያውቅ የለም:: እነሱም ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ወደ
ኢትዮጵያ ለመምጣት ጉዞአቸውን በመልአከ እግዚአብሔር
መሪነት በእግዚአብሔር ቸርነት ስለተቻላቸው በቅርብ ቀን
ውስጥ ጋዛ ከምትባለው ክፍለ አገር ደረሱ ከዚያም ተነስተው
ቃዴስ በርኔን ከተባለው በረሀ አደሩ:: ከዚያም ተጉዘው

[2] በሰሎሞን ዘመን የኢየሩሳሌም መቅደስ ሊቀ ካህን የነበረ ሳዶቅ 1ነገ 1 የበኩር ልጅ
ነው:: የበኩር ልጆቻችሁ ይሒዱ ስለተባለ በዚህ መሠረት አዛርያስ የሳዶቅ የበኩር ልጅ
ስለነበር እብሮ መጣ:: ታቦተ ጽዮን ከገባች በኋላ ሕገ ኦሪት በአክሱም ተጀመረ:: አዛር
ያስም የመጀመሪያው ሊቀ ካህን ሆነ:: የእርሱ ትውልድ ይህን የሹመት ማዕርግ
እየተቀበለ እስከ ክርስትና መግባት ደረሱ::





ደብረ ሲናን ወደ ኋላ አይተው በቅርብ ቀን ጉዞ በኤርትራ
የብስ ሰፈሩ::

ይህ ሁሉ ሲሆን በኢየሩሳሌም ንጉሥ ሰሎሞን ሊቀ
ካህናቱ በጠቅላላው ሕዝቡ የታቦተ ጽዮንን ወደ ኢትዮጵያ
መምጣት አላወቁም:: ሊቀ ካህናቱ ሳዶቅ የተለመደ ጸሎ
ቱን አድርሶ ወደ ቤተ መቅደሱ ገብቶ ቢመለከት ታቦተ
ጽዮንን አጣት:: በዚህን ጊዜ ደነገጠ፣ አዘነ፤ ሌዋውያን ካህና
ትም ሰምተው ደነገጡ:: ንጉሥ ሰሎሞንም ነገሩን ሰማና
ሳዶቅን አስጠርቶ ጠየቀው:: ይህን ከሰማ በኋላ ሠራዊት
ልኮ ባሕረ ኤርትራን ከተሻገሩ ተዋቸው የእግዚአብሔር
ፈቃድ ነው ካልተሻገሩ ግን ታቦተ ጽዮንን መልሷት ብሎ
ላካቸው ሠራዊቱም ሔደው አጧቸው:: ቀዳማዊ ምኒልክ
ታቦተ ጽዮን አብሯቸው ስለመጣ በጣም ደስ አለው:: ከዚህ
በኋላ ሌዋውያን ካህናት ታቦተ ጽዮንን በመጐናፀፊያ ሸፍ
ነው ባማረ ሰረገላ አድርገው ከፊትና ኋላ ሆነው እየዘመሩ
ኢትዮጵያ ገቡ:: ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ የገባችው
በፈቃደ እግዚአብሔር ነው:: ይኸውም:-

1. ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣቷ ምክንያት የሆ
ኑት ራሳቸው ነገደ እስራኤላውያን እንጂ ኢትዮጵያውያን
ባለመሆናቸው፤

2. ታቦተ ጽዮን ከቤተመቅደስ ስትወጣና ከወጣችም በኋላ
ይህን ባደረጉ ሰዎች ላይ አንዳችም መቅሰፍት ከእግዚ
አብሔር ባለመታዘዙ በእነዚህ ሊታወቅ ይችላል::

ንግሥተ ሳባም የመጡትን ሁሉ በክብር ተቀበለቻ
ቸው:: ይልቁንም ታቦተ ጽዮን አብራ መምጣቷን ስትሰማ
ለእግዚአብሔር መስዋዕት አቀረበች:: እርሷም ከኢየሩሳሌም
በመጡ ነገደ እስራኤላውያንና ከኢትዮጵያውያን ወገን ሰዎ
ችን አስመርጣ ታቦተ ጽዮንን በትጋት እንዲጠብቁ ሥርዓት
ሠርታለች:: የመንግሥቷን ሥልጣን በሙሉ ለቀዳማዊ ምኒ
ልክ አስረከበች:: ከዚህ በኋላ ሊቀ ካህናቱ አዛርያስ እንደ
ሕገ ኦሪት ሥርዓተ መንግሥት አድርሶ ቅብዐ መንግሥት
ቀባው:: ንግሥተ ሳባ መንግሥቷን ለልጇ ለቀዳማዊ ምኒልክ



www.ethiopianorthodox.org

ካስረከበች በኋላ ዛሬ ሳባ ከተባለው ቤተ መንግሥቷ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች:: መቃብሯ ለፅዮን ባሠራችው ምኩራብ አጠገብ ሆነ:: ይህ ቦታ እስከ አሁን ድረስ የንግስተ ሳባ መቃብር እየተባለ ይጠራል:: ንግሥተ ሳባ ሦስት ስም አላት፤

| •ስሟ | የተገለፀበት ቦታ |
|---|---|
| ሳባ | 1ነገ. 10÷1-10 |
| አዜብ | ማቴዎስ 12÷42 |
| ማክዳ[3] | ክብረ ነገሥት |

## ንግሥተ ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም የሔደችበት ምክንያት

- በታምሪን አማካኝነት ንጉሥ ሰሎሞን ጥሪ አድርጐላት ስለነበር ዋና ዓላማዋ ኢየሩሳሌምን ለመጐብኘት ሲሆን፤ በተጨማሪ ንጉሥ ሰሎሞን ያሠራውን ቤተመቅደስ ለመመልከት፤ በጆሮ የሰማችውን የንጉሥ ሰሎሞንን ሥጋዊና መንፈሳዊ ጥበብ በዓይኗ ለማየት::
- የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃይማኖቱ ጠንካራ ስለሆነ፤ እስራኤላውያን በሙሴ አማካኝነት የተቀበሉት የቃል ኪዳን ታቦትና አምልኮታቸውን ዓይቶ ለመረዳትና የኢትዮጵያም ሕዝብ በአምልኮተ እግዚአብሔር ፀንተው እንዲኖሩ ለማድረግ፤
- ከእስራኤል ወገን ከዳዊት ዘር ክርስቶስ ይወለዳል ተብሎ የተነገረውን ትንቢትና ምሳሌ ስለምታውቅ ከንጉሥ ሰሎሞን ለመተዋወቅ በቅርብ ለመነጋገር::
- የእሥራኤል መንግሥት አስተዳደርና አመሠራረት የቤተ ክህነቱንም ሥልጣን ለመመልከት፤
- ዋና ዓላማዋ የኢትዮጵያና የእሥራኤልን ሕዝብ አስተዋውቆና አቀራርቦ የአንድነትና የሃይማኖት ግንኙነት እንዲኖረው ለማድረግ መንፈስ እግዚአብሔር ስላነሳሳት ነው:: እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን ዲኘሎማሲያዊ ግንኙነት የጀመረችው ኢትዮጵያ መሆኗን ነው::

[3] ይህ ጎሎ ማክዳ የተወለደችበት አገር ሲሆን ንግሥት ማክዳ እየተባለች ትጠራለች:: ጎሎ ማክዳ ማለት ያማረ በረት ማለት ነው:: የአማርኛ ንግግር ሆኖ ነው እንጂ በግዕዙ (ጎል ማክዳ) ወይም ጎል ማለት ነው:: ይህ ቦታ የሚገኘው በትግራይ በቀድሞ አጋሜ በሚባለው አውራጃ ውስጥ ነው:: ሳባ የተወለደችው በከብቶች በረት አጠገብ ነው:: ስለዚህ ይህ ቦታ ጎል ማክዳ የሚባል ሆኗል::





## የጽዮን በዓል አከባበር

ታቦተ ጽዮንን ይዘው መጥተው ለመጀመሪያ ጊዜ ሐማሴን ማዕበላ ቆዩ፤ ህዳር 20 ቀን ወደ ንግሥተ ሳባ ከተማ [የዛሬዋ አክሱም] ገብተዋል:: ወዲያውኑ በማግስቱ ህዳር 21 ቀን የታቦተ ጽዮን ከጥንት ሲያያዝ በመጣው ሥርዓት በኢትዮጵያ ተከብሯል::[4] መንፈሳዊ በዓል በኢትዮጵያ መከበር የጀመረው በዚህን ጊዜ ነው:: ሌዋውያን ካህናት የእግዚአብሔርን የሕጉን ማደሪያ የሆነችውን ታቦተ ጽዮንን በዓመት በዓመት በሚያከብሩበት ጊዜ ለፅዮን የሚገባውን መዝሙር፤ በከበሮና በጽናፅል እያሸበሸቡ በዓሉን ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት ያከብሩ ነበር:: በፅዮንም ፊት እንደ የመአረጋቸው ቆመው በድርሳነ ጽዮን እንደተገለጠው «እግትዋ ለፅዮን ወህቅፍዋ» የሚለውን መዝሙር ከዳዊት እያውጣጡ ይጸልዩ ነበር:: በከበሮና በፅናፅል የእግዚአብሔር ምስጋና በአገራችን የተጀመረው ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ ከገባችበት ጊዜ ጀምሮ ነው:: ንግሥተ ሳባና ልጇ ቀዳማዊ ምኒልክ ተመካክረው ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ የገባችበት ዕለትና በኢየሩሳሌም ሳለች የምትከበርበት ዕለት እስራኤላውያን በሚያከብሯቸው በዓላት ሌዋውያኑ በከበሮና በፅናፅል እንዲዘምሩ አድርጓል:: ሌዋውያኑም ይህን ትዕዛዝ ተቀብለው በታቦተ ጽዮን ፊት የእግዚአብሔር ምስጋና ተጀመረ:: በዚህን ጊዜ በኢትዮጵያ ማህሌት ተጀመረ ማለት ይቻላል::

[4] ህዳር 21 በየዓመቱ ዛሬ የምናከብረው ከታሪክና ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ መልኩ ነው:: ታቦተ ጽዮን ዳጎንን ድል ያደረገችበት 1ሳሙ 5÷1-12፤ በዚህ የተጠቀለውን ታሪክ ለማስታወስ፤ ይህቺ ታቦት ቀዳማዊ ምኒሊክ ይዞ አክሱም የገባበትና ንግሥተ ሳባ ታላቅ በዓል አድርጋ የተቀበለችበትን፣ በኋለኛው ዘመን ክርስትና ሲስፋፋ አብርሃ ወአፅብሐ በዚችው በአክሱም ከተማ 12 ቤተ መቅደስ ያለው ቤተ ክርስተያን ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን አስደናቂ ቤተ ክርስቲያን ሠርተው ከጨረሱ በኋላ ቅዳሴ ቤቱን ያከበሩበት:: እንዲሁም በ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዮዲት ክርስትናን ለማጥፋት በተነሳች ጊዜ በእርሷ ምክንያት ታቦተ ጽዮን ዝዋይ ሐይቅ የተሰደደችበት በኋላ በአክሱም ሊቃውንት አማካኝነት የሰላሙ ዘመን ሲመጣ ተመልሳ አክሱም የገባችበትን በዚሁ በህዳር 21 ስለሆነ በእነዚህ ተደራራቢ ታሪኮች ምክንያት በየዓመቱ በደመቀ ሁኔታ ይከበራል «ህዳር ጽዮን በአክሱም ጽዮን» የሚባለው ለዚህ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

## ቀዳማዊ ምኒልክ ያሠራው መቅደስ

በሊቀ ካህኑ አዛርያስ አሳሳቢነት ቀዳማዊ ምኒልክ አዲስ ቤተ መቅደስ አሳነፀና ጨረሰ። ሥራው እንዳለቀ ታቦተ ጽዮን በአዲሱ ቤተ መቅደስ በክብር ገባች። ሌዋውያኑ ዳዊት በሠራው ሕግና ሥርዓት በየ24 ሰዓቱ እየገቡ እንዲጸልዩ አደረገ (ይህን ለመረዳት መጽሐፈ ዜና መዋዕልን ተመልከት) የቤተ መቅደሱ አሠራር እንደ ሰቀላማ ሆኖ ሞላላ ነው። ይህ መቅደሰ ኦሪት ብዙ ዘመን እንደቆየ ድርሳነ ጽዮን ይገልፃል። ከዚህ በኋላ ቀዳማዊ ምኒልክ በኢትዮጵያ ለ29 ዓመት ነግሷል። በዚሁ ዘመኑም አርፏል። ሌዋውያን ካህናት ቀዳማዊ ምኒልክን እንደ ሕገ ኦሪት የሚገባውን ሥርዓት ፈፅመው ከዚያው ከቤተ መቅደሱ አጠገብ ቀብረውታል። የቀዳማዊ ምኒልክ መቃብር የሚገኘው ከአክሱም ከተማ በምዕራብ በኩል ሲሆን ከኢትዮጺስ መቃብር የቤተ መንግሥቱ መሠረት በአፈር ተውጦ የደረጃው ክበብ ቅርፁ ይታያል። በዙሪያው የቤተ መንግሥቱ ፍርስራሽና እንዲሁም የቀድሞዎቹ ነገሥታት የወርቅ ማንጠሪያ ደንጊያዎች፣ ሐውልቶች ወድቀው ይታያሉ።

በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት (1882-1904) ዓ.ም ይኸው የቀዳማዊ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ካለበት ቦታ ላይ ታሪክ መርማሪዎች (አርኪዮሎጂስቶች) ዙሪያውን ሲቆፍሩ ከመቃብሩ ላይ በወርቅ የተሠራ የቀዳማዊ ምኒልክ ስም የተጻፈበት የጭራ መያዣና የወርቅ ቀለበት አግኝተው ለዳግማዊ ምኒልክ ሰጥተዋል። በዚሁ ዘመነ መንግሥት የቀዳማዊ ምኒልክ አፅም በቤተ መንግሥቱ አካባቢ አስፈልገው አስቆፍረው አግኝተዋል። አፅሙን ሲያወጡ የእሱና የሚስቱ ስም በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈበት የወርቅ ማሕለቅ አብረው አግኝተዋል። ይኸው አፅመ ቀዳማዊ ምኒልክ በሣጥን ሆኖ በአክሱም ቤተ መቅደስ ይገኛል።[5]

[5] ዜና ቤተ ክርስቲያን ዘኢትዮጵያ 24ኛ ዓመት ቁጥር 54-58።



የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት

የመጀመሪያው ወርቃማው ዘመን ይህን ያስታውሰናል። ለዚህ ሁሉ ታሪክ መነሻ የንግሥተ ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም መሔድና ከንጉሥ ሰሎሞን ጋር መገናኘቷ ነው። ኢትዮጵያ በዚህ ዘመን ታቦተ ጽዮንን ብቻ ሳይሆን ያገኘችው፤ «የወደደችውን ሁሉ ሰጣት» 1ነገ. 10፥13 ስለሚል በኢየሩሳሌም ያለውን ርስታችንን ያገኘነው በዚህን ጊዜ ነው።[6] ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን አገር መሆኗን በሦስት ነገሮች ማረጋገጥ ይቻላል።

1. በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ መሠረት በአብዛኛው በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስሟ ስለተጠቀሰና ስለሕዝቧም መገለፁ። ከዚህ በፊት እንዳየነው የሙሴ የጋብቻ ታሪክ ዘኁ. 12፥1፤ ንግሥተ ሳባ የእግዚአብሔርን ስም መጥቀሷ 1ነገ. 10፥9፤ በዘመነ ሐዲስ ጃንደረባው የኦሪትን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም መጓዙ፤ የሐ. ሥራ 8፥26-42፤ በዚህ ይታወቃል።

2. በባሕላዊ ማስረጃ ደግሞ፡- የሚበሉና የማይበሉ እንስሳትን በተመለከተ፤ የለቅሶ ሥርዓት፤ በሕዝቡ ዘንድ ያለው የኑሮ ሥርዓት፣ የሃይማኖት ስሜት፣ በኀዘንና በደስታ ሁኔታ ያለው፤ የበዓላት አከባበር የሴቶችና የሕፃናት ጌጣ ጌጥ ዘፀ. 32፥2፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማሕሌት ሥርዓት የካህናቱ ልብስ፣ ካባው፤ ድርቡ፣ ፅናፅሉ ከበሮው ኩፋሩ መጠምጠሚያው፣ የታቦቱ ክብር ከብሉይ ኪዳን ጋር የሚመሳሰል ከዚያም የተወሰደ ነው።[7]

3. በታሪካዊ ማስረጃ መሠረት የብሉይ ኪዳን አገር መሆኗ ይታወቃል። በአገራችን የሚታወቀው የታሪክ መጽሐፍ «ክብረ ነገሥት» እያንዳንዱን ዝርዝር ሁኔታ ዘግቦታል። እንዲሁም በአገራችን ውስጥ የኦሪት መስዋዕት ይሰዋባቸው የነበሩ አብያተ መቅደስና ምኩራባት ተገኝተዋል፤ የተገኙትን በዚህ ሰንጠረዥ መልክ ተቀምጧል።

[6] የታሪክ መስታወት ገፅ 16።
[7] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገፅ 16።



www.ethiopianorthodox.org

| በትግራይ የተገኙ | በአማራ ሳይንት | በጐጃም | በደቡብ |
|---|---|---|---|
| አክሱም ጽዮን ሮሀ ሀውዜን[8] | ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም | መርጡለ ማርያም በባሕር ዳር ጣና ቂርቆስ | ብርብር ማርያም |

በዚያን ጊዜ የተጠቀሰችው ኢትዮጵያ የአሁኗ ኢትዮጵያ አይደለችም እንዳይባል፤ በአሁኑ ጊዜ ስለጥንታዊት ኢትዮጵያ በአጠቃላይ የተነገረው ሁሉ ቅሪት በመገኘት የሚታየውና ለመታወስም የሚቻለው በአሁኗ ኢትዮጵያ ካለው የባሕል፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት ሁኔታዎችና ይዘቶች ጋር ተገናዝቦ እነዚህ ሁሉ በሌላው ዓለም (በጐረቤት አገሮች) የማናያቸው ሲሆኑ፤ እነዚህ ሁሉ በአሁኗ ኢትዮጵያ የምናያቸው፤ የምንዳስሳቸው እውነታዎች ናቸው:: ስለዚህ የዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ አሁን ያለችው ራሷ መሆኗን በዚህ ይታወቃል::

እነዚህን የመሳሰሉ ቦታዎች ጥንት የኦሪት መስዋዕት ይቀርብባቸው የነበሩ ቦታዎች ሲሆኑ ዛሬ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ስጋውና ክቡር ደሙ ይፈተትባቸዋል:: ለዚህ ነው ወንጌልና ቤተክርስቲያን ያላቸው፤ ኦሪትና ቤተ መቅደስ የላቸውም፤ ኦሪትና ቤተ መቅደስ የነበራቸው እስራኤላውያን (አይሁድ) ዛሬ አዲስ ኪዳንና ቤተ ክርስቲያን የላቸውም የምንለው::

❋❋❋❋❋❋

[8] የመጀመሪያው ከድንጋይ የተፈለፈለ መቅደስ አሪት የተገኘው በትግራይ ሀውዜን ከተማ ውስጥ ነው:: የኢትዮጵያ ስልጣኔ ገፅ 39::





# ምዕራፍ ሁለት

## ሁለተኛው ወርቃማ ዘመን
## [ከ34-300 ዓ.ም]

## በኢትዮጵያ ለተመሠረተችው ቤተክርስቲያን በር የከፈተ ሐዋርያ

ለአገራችን ለኢትዮጵያ ንጉሥ ሰሎሞን በሳባ አማካኝነት የሰጣት ከንጉሥ ቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ በእስራኤል ርስት እንደ ነበራት ተመልክተናል:: ንጉሥ ሰሎሞን ለንግሥተ ሳባ የሰጣት ቦታ በኢየሩሳሌም ከቤተ መቅደስ አጠገብ ያለው ርስት ነው:: የኢትዮጵያ የታሪክና የቅድስና ይዞታ የሚገኘው ጌታችን ከተሰቀለበት ቀራንዮ ጋር ተያይዞ ነው:: ይህ ዴር ሡልጣን (የመንግሥት ይዞታ) የተባለው ከንጉሥ ሰሎሞን ጀምሮ ኢትዮጵያውያን በእንግድነት ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ የሚጠቀሙበት ቦታ ሆኗል::[1] ለዚህ ነው አሁን በታሪኩ ውስጥ የምንመለከተው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ[2] የኦሪት እምነቱን ሊፈፅም ወደ ኢየሩሳሌም ሔዶ በጋዛ በኩል ሲመለስ ቅዱስ ፊሊጶስ ያገኘው:: ንጉሥ ሰሎሞን ለእናታችን ንግሥተ ሳባ «ጋዛን» ሰጥቷት ነበርና እስከ ንግሥት ህንደኬ ድረስ ይህ ቦታ በኢትዮጵያውያን ነገሥታት እጅ

[1] ኢትዮጵያውያን ከቀደምት እስራኤላውያን ጋር የታሪክና የባሕል የእምነት ቁርኝት ስለነበራቸው እንዲሁም ጥንታዊ በዓላትን በማክበር ረገድ የጋራ ባሕል ስለነበር፤ በቋንቋና በይትበሀሎች ላይ የሚገናኙ እውነታዎችም ስለሚገኙ የኢትዮጵያ የመንግሥት ልዑካንና ምዕመናን በየጊዜው ወደኢየሩሳሌም እየሄዱ በአውደ ምኩራቦች እየተገኙ ሕገ ኦሪትን ይሰሙና የተለያዩ በዓላትን ያከብሩ ነበር::

[2] «ጃን» ማለት ጥንተ ቃሉ ሲተነተን ንጉሥ፣ ትልቅ፣ ክቡር፣ ንዑድ፣ እንደ ዝሆን የገዘፈ ማለት ነው:: ጃን-ሆይ፣ ጃን-ሰዩም የሚል ቅጽልና ስያሜ እየተሰጣቸው ላይ ላዩን የመንግሥትን መዋቅር ሲመሩ የነበሩትን እናስታውሳለን:: «ጃንደረባ» የሚለው ቃል በጥንት ጊዜ ማዕረጉ የሚሰጠው የቤተ መንግሥትን ሀብትና ንብረት የሚጠብቅ በነገሥታቱ ዘንድ ተአማኒነት ያለው የቤተ መንግሥቱ ተወላጆች የሚቆጣጠር የሚንከባከብ ባለሟል ብርቱ ምሥጢረኛ የበላይነት ማዕርግ የነበረው መሆኑን ሲያመለክት ቆይቷል:: በኋላ ግን ይህ ቃል ለስልብ ወንዶችና የዘር መዝሪያቸው ሕፁው ለሆኑ የቤት አሽከሮች ተሰጠ:: /ፍንጭ ፍተሻ ገጽ 5/



www.ethiopianorthodox.org

ስለቆየ ይህ ጃንደረባ በኢትዮጵያ ከነበረው ሥልጣን ሌላ በጋዛ ተሹሞ ይኖር እንደነበር የጻፉ አሉ::[3]

በሐዋርያት ሥራ ላይ ቅዱስ ሉቃስ በመዘገበልን መሠረት «የንግሥት ህንደኬ ባለሟል በገንዘቧ ላይ የሠለጠነ ይለዋል:: ምን አልባት ይህ ሥልጣን የንግሥቲቱ እንደ አሁኑ ገንዘብ ሚኒስቴር ሳይሆን አይቀርም:: «ህንደኬ» ማለት የመዓረግ ስም ነው:: ዋና ስሟ ጌርሳሞት ትባላለች ምክንያቱም በክብረ ነገሥት ህንደኬ (ቅንደኬ) የተባሉ ነገሥታት 7 ያህል ይገኛሉ:: ህንደኬ ማለት በዚያን ጊዜ የሴቶች ነገሥታት የክብር ስም ሳይሆን አይቀርም:: የመጨረሻዋ ንግሥት ህንደኬ የአክሱምና የኑብያ ንግሥት የነበረችው በሐዋርያት ሥራ የተመዘገበችዋ፤ ጃንደረባው በተጠመቀበት ቅዱስ ማቴዎስ በሰሜኑ አካባቢ ባስተማረበት ዘመን የነበረችዋ ናት::[4] የጃንደረባው ጉዞ የተካሔደው በ34 ዓ.ም. አካባቢ ነው:: ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው ከወገናችን ሐዋርያ የተመረጠልን ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪካ የሚያኮራ ታሪክ የተፈፀመበት ወርቃማ ዘመን ነው:: ይህ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ:-

- ቅዱሳት መጻሕፍትን እያነበበ የተገኘ፤
- በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጓዘ፤
- ትህትና የነበረው ባለሥልጣን፤
- በፈቃዱ የተጠመቀ፤
- በነገረ ድኅነተ ዓለም የተደሰተ ቅዱስ ሰው ነው::

እንግዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት ጃንደረባ ሕገ ወንጌልን ተቀብሎና ተጠምቆ ወደ ኢትዮጵያ መመለሱ ተረጋግጧል:: ይሁን እንጂ ጃንደረባው ይህን ክርስቲያናዊ ትምህርት ለቤተ መንግሥቱና ለሕዝቡ ማስተማሩ ወይም መስበኩን መገመት አያዳግትም:: ስለዚህ ይህ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ሕገ ወንጌልን ከጥምቀት ጋር የተቀበለ ቀዳሚ ሐዋርያ አድርገን መቀበል ግድ ይላል::

[3] ነቅዐ ንፁህ ዜና ሐዋርያት ገፅ 51::
[4] መጽሔተ አሚን ገፅ 78::





በንግሥቲቱ ቤተ መንግሥት ሥርዓተ ኦሪት እና ሥርዓተ ሐዲስ በጋራ ያለ ተቃውሞ ይተገበር ነበር:: በጊዜው በአክሱም የነበሩ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች ትምህርቱን ያለ ተቃውሞ ተቀብለውታል ከአንዳንድ አክራሪ አይሁዳውያን በቀር:: ቅዱስ ጳውሎስ እንኳ የተቀበለውን የክርስትና እምነት ከኢየሩሳሌም ውጭ በአንጾኪያና በግሪክ ከተሞች ሲያስተምር ተቃውመውት ነበር:: ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ግን ኦሪትን የሚያጠፋ ትምህርት አመጣህ ብለው እንደ ሐዋርያት አልገደሉትም:: *«ስለ ኢትዮጵያ ክርስቲያን መሆን ኢትዮጵያውያን የሚያምኑት ዓለም የሐዋርያትን ደም እንደውሃ ሲያፈስ ኢትዮጵያ ግን የአንድም ሐዋርያ ደም ሳታፈስ የሚመራኝ የሰምና ምራኝ በማለት ክርስትናን እንደተቀበሉ ነው::»* የሆኖ ሆኖ ከፍሬምናጦስ በፊት ክርስትና በኢትዮጵያ ለመኖሩ የሚያጠራጥር አይደለም::[5] ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ግብረ ሐዋርያትን ወይም የሐዋርያት ሥራን በተረጐመበት ድርሳኑ ስለ ርዕደተ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር «በቅድስት አገር (ኢየሩሳሌም) ጽርሐ ጽዮን ኢትዮጵያውያንም ከአይሁድ ጋር በዓለ ሃምሳን ለማክበር አብረው ነበሩ»:: በማለት ዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ገልጸዋል::[6]

ይህ ወርቃማ ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሲታይ ከመጀመሪያ ጀምሮ ሐዋርያዊ ተልዕኮ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ወደን ፈቅደን መቀበላችንን ያመላከተ ነው:: የክርስትናና የሕገ ኦሪት ርክክብ የተፈጸመበት ሁኔታ ያለምንም ጸብና ክርክር ሲሆን የሂደቱ ሌላው ባሕርይ የሐዋርያዊ ተልዕኮ ውጤት የሆነው በኢትዮጵያ የክርስትና እምነት ወደ ሕዝብ የወረደው ከነገሥታቱና ከእንደራሴዎች ቀጥሎ በተዋረድ መሆኑን ይህ ታሪክ ያስገነዝበናል:: ሲጠበቅ የነበረው ተስፋ አብሳሪ እንጂ እንደሌሎች ሀገሮች የነበረውን ሥርዓትና እምነት ሰብሮና ጥሶ የገባ ባለመሆኑ እንደ ለማዳ እንስሳ በመቀላቀሉ የተለየ ባሕርይ ባለቤት ያደርገዋል:: በመሆኑም ክርስትና በኢትዮጵያ ሲሰበክ ከአቀባይም

[5] Panorama of the Ethiopia church pag. 3
[6] ዝኒ ከማሁ



www.ethiopianorthodox.org

ሆነ ከተቀባይ ወገን በኩል የጠፋ ሕይወት የፈሰሰ የሰው ደም አልነበረም።

ከጃንደርባው ጥምቀት ጀምሮ እስከ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ያለ ጥምቀት በእምነት መቆየቷ ወደ ፊት ለምናየው ለአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ስብከት የተመቻቸ መንገድ ሆኖለታልና፡ በዚህ ወርቃማ ዘመን ዓለም ክርስቲያኖችን ሲጨፈጭፉ በተለይ የሮም ቄሳሮች እነኔሮን፣ ዲዮቅልጢያኖስ፣ ትራጃን... ግፍ በተሞላ እጃቸው ምስኪን ክርስቲያኖችን ደማቸውን ሲያፈሱ ኢትዮጵያ ያለ ጥምቀት ክርስትናን ታስፋፋ ነበር።

ክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ እና በሮም ንጉሠ ነገሥት ወይም በመካከለኛው ምሥራቅ እና በአውሮፓ እንዴት እንደተሰበከ ሲመረመር በሮም ንጉሠ ነገሥት ዘንድ ክርስትና የተሰበከውና ተቀባይነትን ያገኘው በተራው ሕዝብ ሆኖ ወደ መኳንንቱና ወደ ነገሥታቱ ሊደርስ የቻለው 300 ዓመታት ያህል ዘግይቶ ነው። በኢትዮጵያ ግን በተቃራኒው ክርስትና በመጀመሪያ የተሰበከውና ተቀባይነትን ያገኘው በነገሥታቱና በቤተ መንግሥቱ አካባቢ ነበር።

ክርስትና በመጀመሪያ በምዕራቡ ዓለም በነገሥታቱ ዘንድ ተቀባይነትን ባለማግኘቱ ክርስቲያኖች ስቃይና ስደት ይደርስባቸው ነበር። በኢትዮጵያ ግን ክርስትና መጀመሪያ በነገሥታቱና በንጉሣዊያን ቤተሰብ ዘንድ ተቀባይነትንና ድጋፍን ስላገኘ በቀላሉ ወደ ተራው ሕዝብ ደርሶ ለመስፋፋት ችሏል። በምዕራቡ ዓለም የክርስትና ሃይማኖት የመንግሥትን ድጋፍ ያገኘውና መንግሥትን ሃይማኖት ሊባል የቻለው ከ300 ዓመታት በላይ ክርስቲያኖች ከባድ ስቃይና ስደት ከደረሰባቸው በኋላ ሲሆን በኢትዮጵያ ግን ክርስትና ከመጀመሪያው አንስቶ ሕጋዊ የመንግሥት ሃይማኖት ሆኖ ነው የጀመረው።[7] የጃንደረባው ዘመን ለአሁን ዘመን ትውልድ ያተረፈለት ነገር ቢኖር፡-

7 የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ በምድር ላይ /ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ/ 1ኛ መጽሐፍ ገጽ 162





1. ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ሀገሪቱ አስቀድማ መተዋወቋን አስረድቷል።[8]

2. ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን አገር መሆኗን፤ ጃንደረባው በኦሪቱ ሕግ መሠረት በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ሔዷልና፣ ይህም የወንጌልን ገፈት ቀምሳ ሕገ ኦሪትን ሳትረሳ የኖረች አገር መሆኗን።

3. የነገረ መለኮት ትምህርት ወደ ምዕራቡ ዓለም ከመድረሱ በፊት በ34 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ መድረሱንና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እውነተኛውን ምንጭ መያዟን ያስገነዝበናል።

4. «በእግዚአብሔር ልጅ አምናለሁ» ብሎ በመጠመቁ ይህን ታላቅ ዶግማ ለዓለም ክርስቲያኖች አስተዋውቋል፤ የክርስትና መሠረታዊና ዋናው ነገር ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ማመን ሲሆን ይህ የጃንደረባው ቃል በዮሐ.3፥16 የተጠቀሰውን የመጽሐፍ ቅዱስ መክፈቻ ቁልፍ የተባለውን ጥቅስ ያስረዳል።

5. ታላላቅ የጥንት ታሪክ ጸሐፊዎች ሰፊ ቦታ የሰጡት ይህ የጃንደረባው ጥምቀት እነሩፊኖስ «ጃንደረባው ለወገኖቹ ሐዋርያ ሆነ» በማለት የተናገሩ ሲሆን፤[9] ከእኛው ወገን ሐዋርያ ተመርጦልን ክርስትናን በአገራችን እንዲመሠረት ሆኗል። የዚህ ወርቃማ ዘመን ለዛሬው ለኢትዮጵያ ትውልድ ቀርቶ ለመላው አፍሪካ የሚያኮራ ነው ያልነው ለዚህ ነበር።

8 ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ መጽሐፍ ቅዱስን በምን ቋንቋ ያነብ እንደነበር በቀላሉ መናገር አይቻልም። ይህንን በደንብ ያጠኑ የመጽሐፍ ቅዱስ የትርጉም ባለሙያዎች ሲገልጹ «...የግሪክኛ ቋንቋ በኢትዮጵያ በተለይም በአክሱም ቤተ መንግሥት አካባቢ በሰፊው ይነገር ነበርና ጃንደረባው ያነበበበት ቋንቋ ከዕብራይስጥ ቋንቋ ይልቅ በአመዛኙ በግሪክኛ የተተረጐመውን የሰብአ ሊቃናት ትርጉም ይመስላል።» /በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግእዝ ቋንቋ ገጽ 17/

9 የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አባት እየተባለ የሚጠራው አውሳብዮስ ደግሞ ጃንደርባው ከተጠመቀ በኋላ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ወንጌል ስለመስበኩ የሚከተለውን ጽፏል መልእክተ እድሀና ለየቀኑ ሩቅ ወደሆኑት ሀገሮች ሁሉ እየተስፋፋ ሳለ ፈቃደ እግዚአብሔር በሴትዋ /ንግሥተ ህንዳኬ/ ትመራ የነበረችው ሀገር ከኢትዮጵያ ባለስለጣኖች አንዱን አመጣ ይህ ሰው በእስራኤላውያን ቀጥሎ ከወንጌላዊው ቅዱስ ፊልጶስ የመለኮታዊውን ቃል ምስጢር ለመቀበል ቀዳማዊ ነበር። ከዓለም ምዕመናን ቀዳምያት /የመጀመሪያ ፍሬ/ ነበር። ይህ ሰው /ጃንደርባው/ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ሕይወትሰጭ የሆነውን የክርስቶስን ሰዎች መካከል መመላለስ የምታሳውቀውን ወንጌል ለመስበክ የመጀመሪያው ሰው እንደሆነ ታምኗል «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» የሚለው ስለ ኢትዮጵያውያን እውነተኛ እምነትና እምልኮ የተነገረውን ትንቢት በእርሱም ምክንያት ተግባራዊ ፍፃሜን አግኝቷል «አውሳብዮስ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ 2ኛ መጻሐፍ ገጽ 13 ጠቅሰው ሊቃውንት አሰረድተዋል የኢ.ኦ.ተ.ቤ በ2ሺ ገጽ 13»



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ሦስት

## ሦስተኛው ወርቃማ ዘመን

[ከ300 - 360 ዓ.ም.]

**«ዘንቱሰ ብዕሲ መምህርነ**
**ዘተፈነወ ውስተ ምድር ይክስት ብርሃነ»**
***«ብርሃንን ይገልጥ ዘንድ ወደ አገራችን የተላከ***
***ይህ ሰው መምህራችን ነው»***
**(ቅዱስ ያሬድ ድጓ)**

መረጲዎስ የተባለ ግሪካዊ የጢሮስ ነጋዴ [የጠቢባን አለቃና አገር ጐብኝም ነው ይሉታል] በእስክንድርያና በህንድ እየዞረ ይነግድ ነበር:: ይህ የጢሮስ ወይም የሶርያ ነጋዴ በኃላፊነት ሰብስቦ ያስተምራቸው የነበሩ ሁለት ክርስቲያን ልጆች አስከትሎ ወደ ህንድ ለመጓዝ ቀይ ባሕርን አቋርጦ በኢትዮጵያ ጠረፍ በምትገኘው በቀድሞው የወደብ ከተማ በነበረችው አዱሊስ ላይ ሲደርስ ሞተ:: የዚህ ሰው አሟሟት ጀልባውን ወደ ወደቡ አስጠግቶ ሳለ በዚያ አካባቢ ያሉ ሰዎች በጀልባይቱና በተሳፋሪዎች ላይ አደጋ ጥለው እቃቸውን ዘርፈው ሜሬጲዎስና የጀልባይቱን ቀዛፊዎች እዚያው ገደሏቸው:: አብረውት የነበሩት ሁለት ልጆች ፍሬምናጦስና ኤዴስዮስ ተርፈው በአንድ ዛፍ ጥላ ሥር ሆነው ሲፀልዩና መጽሐፍ ሲያነቡ የአዱሊስ ሰዎች አገኟቸው:: ልጆቹን ለሀ ማሴን ገዥ ለነበረው ባሕረ ነጋሽ አስረከቧቸው::

ባሕረ ነጋሹም የአክሱም ንጉሥ ለነበረው ለቀዳማዊ አላሜዳ ወስዶ ሰጣቸው:: እነሱም ወደ ንጉሡ ቀርበው የደረሰባቸውን ሁሉ ነገሩት:: ንጉሡም በደረሰባቸው ችግር አዝኖ በቤተ መንግሥቱ እንዲያድጉ አዘዘ:: ፍሬምናጦስ በእድሜና በትምህርት የበሰለ ስለነበር የንጉሡ ልጅ ሞግዚትና አስተማሪ ሆነ:: ይህ የንጉሥ ልጅ ኢዛና መሆን አለበት:: ይህም ሕፃኑን አልጋ ወራሽ በክርስትና እምነት እየኮተኮተ ለማሳደግ ረድቶታል:: ኤዴስዮስ ግን የግምጃ ቤት ኃላፊ አድርጎታል::





እነዚህ ሁለት ወጣቶች እየዋሉ እያደሩ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ታማኝነትን ተሰሚነትን እያገኙ ሔዱ፤ የአገሩንም ባሕልና ቋንቋ በደንብ አጠኑ::[1]

ቀዳማዊ አላሜዳ ሊሞት በተቃረበበት ጊዜ ልጆቹ /ኢዛና ሳይዛና/ ለአካለ መጠን አልደረሱምና መንግሥቱን በሞግዚትነት እቴጌይቱን አደራ አላት ሁለቱ ወጣቶች ማለት ፍሬምናጦስና ኤዴስዮስን ወደ ፈለጉበት እንዲሔዱ ለቀቃቸው:: ነገር ግን በእቴጌይቱ ልመና ወደ አገራቸው መሔዳቸው ቀርቶ ልጆቿ እስኪያድጉ ድረስ በአስተዳደር በኩል ሲመክሯት ቆዩ:: እነዚህ የንጉሡ ልጆች የ12 ዓመት ሕፃናት ስለነበሩ እናታቸው ንግሥት ሶፍያ (አህይዋ) የልጆቿ ሞግዚት በመሆን የመንግሥቱን ሥልጣን በመቀዳጀት በባልዋ ተተክታ ታስተዳድር ጀመር:: ልጆቿም በእነፍሬምናጦስ የክርስትና ትምህርት ተኮትኩተው አደጉ::

ኢዛናና ሳይዛና ለአካለ መጠን ደርሰው ሙሉ በሙሉ የንጉሠ ነገሥትነታቸውን ሥልጣን ያዙ:: እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ በመሆን በመንፈሳዊ ጥበብ እየተመሩና እየተራቀቁ የእግዚአብሔርን ሕልውና ለሕዝቡ እያስተዋወቁ ለ15 ዓመታት ኢትዮጵያን አስተዳደሩ:: ፍሬምናጦስ በአክሱም ሲኖር የቤተመንግሥቱ አማካሪ ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል በጃንደረባው የተሰበከውን የክርስትና ሃይማኖት በሚገባ የሚስፋፋበትን መንገድ ይፈልግ ነበር:: ምክንያቱም በጊዜው የነበሩ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ሃይማኖት እንጂ ምስጢራትን የሚፈፅሙ ካህናት የሏቸውም ነበር:: ይህን ለማሟላት ጳጳሳት ያስፈልጋል:: ከዚህ ጋር ፍሬምናጦስ ለመጀመሪያ ጊዜ የክርስቲያን ቤተ ጸሎት ለውጭ አገር ሰዎች (ለነጋዴዎች) ለማሠራት ችሏል:: ዝግጅቱ መስመር እንደያዘለት ሲያይ የሚያስተምርና የሚያጠምቅ ጳጳስ ለማስመጣት አስፈላጊ መሆኑን ማስረዳት ጀመረ:: በኋላ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ጳጳሳት እንዲያመጣላቸው

[1] በጊዜው የነበረው የአክሱም ሊቀ ካህን እንበረም ለ7 ዓመታት ያህል የግዕዝን ቋንቋና የሕዝቡን ባሕል አስጠንቷቸዋል::



www.ethiopianorthodox.org

በዚያን ጊዜ በአፍሪካ የክርስትና ማዕከል ወደ ሆነችው ወደ እስክንድርያ ፍሬምናጦስን ላኩት:: ኤዴስዮስ ግን ቤተሰቦቹን ለመጠየቅ (አገሬ ናፈቀኝ) ብሎ ስንብት ጠይቆ ወደ ትውልድ አገሩ ሄደ:: በዚያም ካህን ሆኖ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ሲያገለግል ኖረ::

ፍሬምናጦስ ግን ጉዞውን ወደ ግብፅ እስክንድርያ አደረገ:: ይህም በ325 ዓ.ም. ገደማ ነው:: ፍሬምናጦስ እስክንድርያ እንደደረሰ የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ባለሥልጣኖችን አላገኛቸውም:: ይህ የሆነው በዚያን ጊዜ ክብር ይግባውና! ወልድ ፍጡር ነው ብሎ የተነሳው አርዮስን ለማውገዝ ወደ ኒቂያ ሔደው ስለነበር ነው::[2] ከዚያ እስኪመለሱ ድረስ ፍሬምናጦስ ከአንድ ዓመት በላይ ቆየ:: በጊዜው 19ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ እና ጉባኤ ኒቂያን በሊቀ መንበርነት የመራው እለእስክንድሮስ ስላረፈ በመንበሩ ቅዱስ አትናቴዎስ ተተካ:: ይህም አርዮስን አውግዘው ጸሎተ ሃይማኖትን አርቅቀው ከተመለሱ በኋላ ነው:: ፍሬምናጦስ የመጣበትን ጉዳይ በመንበሩ አዲስ ለሆነው ለ20ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ለቅዱስ አትናቴዎስ በዝርዝር አቀረበ::

ቅዱስ አትናቴዎስ ጉዳዩን አውጥቶ አውርዶ የአገሩን ባሕልና ቋንቋ የሚያውቅ ሌላ የተሻለ ሰው እንደማያገኝ ስለተረዳ ፍሬምናጦስን ራሱን ሹሞ ወደ ኢትዮጵያ ላከው:: ቅዱስ ፍሬምናጦስ ከቅዱስ አትናቴዎስ የተቀበለውን ከፍተኛ ማዕረግ ተጐናፅፎ ወደ ኢትዮጵያ በሚገባበት ወቅት ሁለቱ ወንድማማች ነገሥታት፣ መኳንንት ሕዝቡ በታላቅ ደስታና ክብር በአክሱም ከተማ ተቀበሏቸው:: እዚህ ላይ ማስታወስ ያለብን ፍሬምናጦስ ሶርያዊ እንደመሆኑ መጠን ጵጵስና ለመቀበል ወደ ሶርያ በመሔድ ፈንታ ወደ እስክንድርያ በመሔዱ ነው:: በእርግጥ በጂኦግራፊ አቀማመጧ ኢትዮጵያ ለግብፅ ቅርብ መሆኗ ይታወቃል::

[2] የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ምዕራፍ 6 ገፅ 105-116 ይመለከቷል::





የዚያን ጊዜ ወገን ለማብዛት ሳይሆን የወንጌል መልእክት ለማዳረስ ነበር ትልቁ ጥረት፤ ይህን ለማፍረስ ፍሬምናጦስ የዘር ስሜት አላሸነፈውም:: አቡነ ሰላማ ወደዚህ ከመጣ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ እነዚህን ነገሥታት በማጥመቅ ኢዛናን «አብርሃ»* ሳይዛናን «አፅብሐ»** ተብለው ተጠሩ:: ከእነሱ በኋላ በኢትዮጵያ የነገሡ ነገሥታት አለማዊ ስማቸውን እየቀየሩ በክርስትና ስማቸው እንዲጠሩ አይነተኛ ምክንያት ሆነዋል:: እነዚህ ነገሥታት ስማቸውን ከቀየሩ በኋላ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሥነ ጽሑፍ ውስጥ የሚታወቁት በዚሁ ስም ነው:: ግን ኢዛና የመንግሥት ሥራውን በተመለከተ የተወልን የድንጋይ ጽሑፍ ያንኑ የቀድሞውን ስሙን ነው የሚጽፈው:: በተጨማሪ ክርስትናን በኢትዮጵያ በማስፋፋት ረገድ «ዳግማዊ ቆስጠንጢኖስ» ተብሏል::

አቡነ ሰላማ ከቅዱስ አትናቴዎስ የተቀበሉትን ጵጵስና ብቻ አይደለም ይዘው ወደ ኢትዮጵያ የገቡት፤ በኒቂያ ላይ የፀደቀውን የወልድን በመለኮቱ ከአብ ጋር እኩል መሆኑን የሚያምን መግለጫ ጭምር ነው:: በመንግሥት ደረጃ የኒቂያን ጉባኤ ውሳኔ የተቀበለ የአክሱም መንግሥት ብቻ ነው:: እንደ አሪቱ ሥርዓት ሊቀ ካህን የነበረው እንበረም አቡነ ሰላማ ወንጌልን አስተምረው ስላሳመኑት በክርስትና መስፋፋቱ ረገድ ሊተባበራቸው ችሏል:: የኤጲስ ቆጶስነት ማዕረግ ስጥተውት ስለነበር ከእርሳቸው በታች አድርገው ስለሾሙት ሥራቸው ይበልጥ እየተቃናላቸው ሔደ:: ነገሥታቱም አብርሃ ወአፅብሐ ከአቡነ ሰላማ ጐን በመሆን ሥሩ የጠለቀውን የክርስትና እምነት በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ እገዛ አድርገዋል:: ከ34 ዓ.ም. ጀምሮ ክርስትና በኢትዮጵያ የገባበት ዘመን ቢሆንም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመችው ወይም ክርስትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት የሆነው በ328 ዓ.ም ነው::

* አብርሃ ማለት አበራ
** አጽብሐ ማለት አነጋ



www.ethiopianorthodox.org

# አቡነ ሰላማ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያደረጉት አስተዋጽኦ

- ***መካሪ አበነፍስ:-*** በሀገር ውስጥ በሕዝቡ የኑሮ አቀማመጥ ይዞታ አለመመቸት በአቡነ ሰላማ ጊዜ ብዙ ጥሩ ነገሮች ተደርገዋል:: ከእነዚህም አንዱ በየቀበሌው አንዳንድ ቄስ መካሪ እንዲሆን መደረጉ ሲሆን፤ ይህም መጽሐፍ አንብቦ ለማይጠቀም ሕዝብ ቀርቶ ለአዋቂና ለተማረም የሚጠቅም መልካም ድርጊት ነው:: በጊዜ ብዛት መካሪው ቄስ ስለ ነፍስ ጉዳይ የአባት ያህል ይመክራልና አበ ነፍስ (የነፍስ አባት) ተብሎ ይጠራ ጀመር:: በኋላም ስለ ኃጢአት ኑዛዜ በመቀበል ንስሐ የሚሰጥ (የንስሐ አባት) ተባለ እስከ አሁን ይህ አጠራር ተጠብቆ ይገኛል::
- **አበ ልጅ (የክርስትና አባትና እናት):-** አበ ልጅ ማለት የሚጠመቀውን ሕፃን በእግዚአብሔር መንገድ እየመራ የሚያስተምረው እንደ ዋስ እንደ ተያዥ ሆኖ በቤተክርስቲያን ፊት መቀበሉን የሚያረጋግጥ ምእመን ነው:: ይህ ባሕል ከመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋር አብሮ ተመስርቷል:: አሁን ግን መንፈሳዊ ሥርዓቱን ለቆ የወገን ማደራጃ ሆኗል::
- ***የጽዋ ማኅበራት ማቋቋም:-*** የመጀመሪያዋ የፅዋ ማኅበር በኢትዮጵያ ማለት ነው ማኅበረ ጽዮን ትባላለች:: የተመሠረተችውም በ347 ዓ.ም. አካባቢ ነው:: አቡነ ሰላማ ማኅበረ ሐዋርያት ብሎ ከማቋቋም ይልቅ በኢትዮጵያ መዲና በአክሱም ዙሪያ ይኖር የነበረው ሕዝብ ታቦተ ጽዮንን ይወድ ስለነበር የእመቤታችን ፍቅር ስላለው ወንጌልን ለመስበክ፤ የእግዚአብሔርን ቃል ለማዳረስ ያመች ዘንድ ማኅበረ ጽዮን ብሏታል::

እንደታሰበውም ብዙ የወንጌል ማኅበር ለማቋቋም ተቻለ:: በጽዮን ስም የተቋቋመው ማኅበር ተግባሩም ሆነ ዓላማው በቅ/ጳውሎስ አማካኝነት የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ያቋቋሙት የወንጌል ማኅበርን ይመስላል:: በቆሮንቶስ ተቋቋሞ የነበረው ማኅበር የወንጌል ትምህርት ከተሰጠ በኋላ በክርስቲያኖች የተዘጋጀው የፍቅር ምግብ ለእያንዳንዱ ይታደ





ላል:: ይህ ብቻ አይደለም በዚያን ጊዜ ወንጌል እንዲስፋፋ፤ የተቸገሩት እንዲረዱ በማለት የገንዘብ አስተዋጽኦ እያደረጉ በቅዱስ ጳውሎስ እጅ ወደ ኢየሩሳሌም ይልኩ ነበር:: በአክሱም የተቋቋመችው ማኅበረ ጽዮን ይህን የተከተለ ስለሆነ:-

- ስብከተ ወንጌል ለማስፋፋት፤
- አብያተ ክርስቲያን በየቦታው ለማሠራት፤
- የቅዱሳንን በረከትን ለመሳተፍ፤
- ድሆችን ለመርዳት የተቋቋመች የአገራችን የመጀመሪያዋ የጽዋ ማኅበር ናት::

- ***የአብያተ ክርስቲያናት መታነፅ:-*** አብርሃ ወአጽብሐ ክርስትናን ከማስፋፋት ጋር የሚፀናበትንም መንገድ በማበጀት አስተዋፅኦ አድርገዋል:: ከዚህም ጋር በአቡነ ሰላማ አሳሳቢነት ለመጀመሪያ ጊዜ የአክሱም ጽዮንን ቤተ ክርስቲያን አንፀዋል:: ይኸውም «ገበዘ አክሱም» በመባል ይታወቃል:: ይህ ማለት እዚህ ገበዘ አክሱም ማለት «ካቴድራል» ከሚለው ጋር ተመሳሳይነት አለው:: ቤተ ክርስቲያኑ በጣም ትልቅ ሲሆን 12 ቤተ መቅደስ ያለው በ5 ክፍሎች የተከፋፈለ ነው:: የዚህ ቤተ ክርስቲያን አሠራር በዓለም ላይ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ነው:: በዓለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የታነፀው በዚህ ዘመን ነው ማለት ይቻላል::

ቤተ ክርስቲያን በፊሊጲስዮስ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ተሠራ ይነገራል:: የኢየሩሳሌሙ ኤጲስ ቆጶስ የነበረው ያዕቆብ በኢየሩሳሌም 7 አብያተ ክርስቲያን እንዳሠራ ይተረካል፤ በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በቁስጥንጥንያ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የተከለ ሲሆን የእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ምንነት (አሠራራቸው) ሊታወቅ ስላልቻለ ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም ላይ የተሠራችው ቤተ ክርስቲያን አብርሃ ወአፅብሐ ያሠሩት የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ሆና ተገኝታለች፤ ምክንያቱም የአክሱም ጽዮን አሠራር በጽሑፍ ተጽፎ ሲነገር ተረትም ነው ሲባል ቆይቶ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአርኪዮሎጂ ስለተገኘ እውነተኝነቱ ተረጋግጦለታል::



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተክርስቲያን በዓለም ላይ የታነፀው በአክሱም ጽዮን ሲሆን ዘመኑም በ349 ዓ.ም. ነው::[3] እላይ የጠቀስናቸው አብያተ ክርስቲያናት በአርኪዮሎጂ እስኪገኙ ድረስ ቀዳሚውን ቦታ የምትይዘው አክሱም ጽዮን ናት::

- **የቅዱሳት መጻሕፍት መተርጐም:-** በአቡነ ሰላማ ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍት ከግሪክ (70 ሊቃናት) መጽሐፍ ወደ ግዕዝ ተተርጉሟል:: አቡነ ሰላማ ለቤተክርስቲያናችን ካበረከቷቸው ታላላቅ ሥራዎች አንደኛው የቅዱሳት መጻሕፍት መተርጐም ነው:: በተለይ ወንጌላት በዚሁ ዘመን እንደተተረጐው ይነገራል:: የትርጉሙ ሥራ ይበልጥ ፍፃሜ ያገኘው በተስአቱ /9ኙ/ ቅዱሳን ነው::

- **የሥነ ፊደል ሥራ መስተካከል:-** የጥንቱ ግዕዝ ዛሬ እንደሚነበበው ከካብዕ እስከ ሳብዕ ያለው ድምፅ በፊደል አልነበረም:: ግን ግዕዙን ብቻ አናጋሪ አድርጐ ይነበብ ነበር:: ለምሳሌ:- «ሐወለተ አከሰመ» ሐውልተ አክሱም ማለት ነው:: በዚህ ሁኔታ መጻሕፍትን ለመተርጐም አስቸጋሪ ስለሆነ አቡነ ሰላማ ከኢትዮጵያ ብሔራውያን ሊቃውንት ጋር ተመካክረው በጥንታዊ ፊደል ቅርፅ መሠረት ከካብዕ እስከ ሳብዕ ያሉትን ድምፅ ሰጭ ከሆኑት ከዕብራይስጥ፣ ከግሪክ፣ ሳይቀር ተረጐሙበት:: ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ጽሕፈት እንደ አሁኑ አረብኛ ከግራ ወደ ቀኝ ነበር የሚጻፈው:: አባ ሰላማ ግን ከቀኝ ወደ ግራ እንዲጻፍ አድርገዋል::[4] [በተጨማሪ መዝገበ ፊደል የሚለውን የኪ.ወ.ክ መጽሐፍ መቅድሙን ተመልከት::]

አቡነ ሰላማ በቅድሚያ ክርስትና ማስፋፋቱን የጀመሩት ከባለሥልጣኖቹ ነበር:: ከነገሥታቱ (አብርሃ ወአፅብሐ) በኋላ ወደ ባለሥልጣኖቹ መሔዱ ወሳኝነት አለው ምክንያቱም ባለሥልጣኑን የሚከተሉት ብዙ ሰዎች ይኖሩታል:: በዚህ ዓይነት ለፈጣን መስፋፋት ከላይ ወደታች መውረዱ ጥቅም ነበረው:: ስለዚህ በቅርብ ጊዜ ክርስትናን በብዙ

[3] ክርስትና በኢትዮጵያ ክፍል 1 ገፅ 66::

[4] ትንሣኤ ሐምሌ 1972 ቁጥር 34 ገፅ 8-9::





የኢትዮጵያ ቦታዎች ተስፋፍቷል ለማለት ይቻላል:: ነገር ግን የስፋቱን አድማስ ለመወሰን አይቻልም:: በአቡነ ሰላማ ጊዜ ክርስትና ከየት እስከየት እንደተሰበከ አስቸጋሪ ነው:: እርግጠኛው ግን የአክሱም መንግሥት ክርስትናን እንደተቀበለ ነው::

## የአባ ሰላማ አስተዋፅኦ በውጭ ግንኙነት

## የኢየሩሳሌምን ርስት አስጠብቀዋል

በአቡነ ሰላማ አማካኝነት አብርሃ ወአፅብሐ ለቆስጠንጢኖስ ደብዳቤ ጽፈው ነበር:: ይህ ደብዳቤ ዋና ፍሬ ሃሳቡ *«በኢየሩሳሌም ዳር ሁሉጣን የሚባል ቦታ ንጉሥ ሰሎሞን ለእናታችን ለንግሥተ ሳባ እንደሰጣትና ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የሕህዛብ ነገሥታት ኢየሩሳሌምን እስካጠፏት ድረስ በአባቶቻችን በኢትዮጵያውያን ነገሥታት እጅ እንደነበር ከታሪክ አይታችሁ ሽማግሌዎችም ጠይቃችሁ እንድትመልሱልን እንለምናችኋለን»* የሚል ነበር::

በ70 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም በጥጦስ ጠፍታ ስለነበር ይህ የእኛ ይዞታ ጠፍቶ ነበር ማለት ነው:: ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ የኢትዮጵያ ነገሥታት አብርሃና አፅብሐ የላኩትን መልዕክት አይቶ፣ ከታሪክ ተመልክቶ ከሽማግሌዎቹም ተረድቶ የእናቱን የእሌኒን ምክር ሰምቶ በደስታ እሺ አለና በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያን የታሪክ ርስት በቆስጠንጢኖስ ንጉሥ እና በንግሥት እሌኒ ትዕዛዝ እንደ ቀድሞው ለኢትዮጵያውያን ርስት ሆነ::

በጎልጎታ እሌኒ መስቀሉን አስቆፍራ (አስጠርጋ) ካዘጋጀች በኋላ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል የተቀበረበት ቦታ ለኢትዮጵያውያን ሰጥታለች:: ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያውያን በዴር ሱልጣን ቤት ሰርተው ተቀመጡ:: ይህ የሆነው በአቡነ ሰላማ መልካም አሳቢነት ነው:: እንግዲህ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ኢትዮጵያን እንደ ተወለዱባት ቆጥረው ይህን የመሰለውን ብሔራዊ ሥራ ሰርተዋል::



www.ethiopianorthodox.org

## መንበራቸውን ዓለም አቀፋዊ ዕውቅና እንዲያገኝ አደረገዋል

በኒቂያ የተሠበሰቡ አባቶች አርዮስንና ትምህርቱን አውግዘው ብቻ አልተለያዩም። ቤተክርስቲያንን ለማሳደግና ለማስፋፋት አንድነቷንም ለመጠበቅ የሚያስችሉ ውሳኔዎችን አሳልፈዋል። ለአንዲት ቤተክርስቲያን ህልውና መጠበቅ የተማከለ ቅዱስ ሲኖዶስ አስፈላጊ እንደሆነ በማመን ነው። በዚህ መሠረት በዚያን ዘመን በሮም ቄሣር ግዛት ሥር የነበሩትን በታሪክና ተያያዥ ትውፊታዊ አቋማቸው ተጠሪና ቋሚ አባላት የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ። እነዚህም 4ቱ ታላላቅ መናብርት ይባላሉ።

1. በምዕራቡ የሮም ቄሣር መንግሥት ግዛት ውስጥ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በሮማ መንበር ሥር፤
2. በደቡብ የሮማ የቄሣር መንግሥት ግዛት ውስጥ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በእስክንድርያ መንበረ ሥር፤
3. በሰሜኑ የሮማ ቄሣር መንግሥት ግዛት ሥር ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በኤፌሶን መንበር ሥር፤
4. በምሥራቁ የሮማ ቄሣር መንግሥት ግዛት ሥር ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በአንጾኪያ መንበር ሥር፤

እንዲጠቃለሉ ሲወሠን፤ ከሮም ግዛት ውጭ በራሳቸው ነፃ መንግሥት የሚተዳደሩ ለምሳሌ እንደ ኢትዮጵያና የፋርስ አብያተ ክርስቲያናት ምን ይሁኑ? የሚል ጥያቄ በኒቂያ ጉባኤ ተነስቶ እንደነበር ሊቃውንት የናገራሉ። በዚህ መሠረት ከሮም መንግሥት ግዛት ውጭ ክርስትናን የተቀበሉ እላይ የገለጥነው ራሳቸውን ችለው በተቋቋሙ መናብርት ደረጃ ሊቀ ጵጵስና እኩል እንዲሆን ወይም በዚህ ሁኔታ የሚታወቁ መናብርት ሊቀ ጳጳስና በአቅራቢያቸው ካለው /ከ4ቱ በአንዱ/ የበላይ ተመልካችነት ሥር እንዲሆኑ ተወሰነ።

በሚያስደንቅ ሁኔታ የክርስትና እምነት በአጭር ጊዜ በቅዱስ አባታችን በአቡነ ሰላማ እየተስፋፋ ባለችው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከላይ በተጠቀሠው በአንዱ ውሳኔ መሠ





ረት የቅርብ ተመልካቿ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ሆነ፤ እንዲህ አይነቱ በየአብያተ ክርስቲያናቱ መካከል የተደረገውን ትውፊታዊ ስምምነት ጥቅምት ዘጠኝ በሚነበበው ሥንክሳር ላይ ፍንጭ ይሠጠናል።በተመሣሣይ ሁኔታ በእስክንድርያና በኢትዮጵያ መካከል የተደረጉት ስምምነትና ቅኖና እንዲህ ይላል:- «ሊቀ ጳጳስ ተብሎ የሚጠራው /የሚታወቀው/ ይህ ኢትዮጵያዊ ባለ መንበር በሊቀ ጵጵስና ማዕርግና ደረጃ /በ4ቱ መናብርተ ሊቀ ጵጵስና ልክ ማለት ነው/ መከበር ይገባዋል» [ፍትሐ ነገ. አንቀጸ 4]

እንግዲህ ያን ጊዜ በአባ ሰላማ አማካኝነት ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ጵጳስና ማዕርግ መሠረታቸው ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት መንበር እኩል እንደነባር እንረዳለን። ይህም በአክሱም ላይ ብቻ ተወስኖ /ታውቆ/ እንዳይቀር በሌሎች ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት መንበር በኩል እውቅናን እንዲያገኝ አባ ሰላማ ታላቅ ጥረት አድርጓል።

## ከኢትዮጵያ ውጭ የነበረውን የእምነት እንቅስቃሴ ተከታተለዋል

በመንግሥት ደረጃ የኒቂያን የጉባኤ ውሳኔ የተቀበለው የኢትዮጵያ ንጉሥ ብቻ ነው። ይህም በአባ ሰላማ አማካኝነት ነው መቀመጫውን ቁስጥንጥንያ ያደረገውና መላ የሮምን ግዛት በተደላደለ ሁኔታ ሲመራ የነበረው ቆስጠንጢኖስ ሲሞት በምትኩ ልጅ ቁንስጣ በሥልጣነ መንግስቱ ተተክቶ ሲገዛ /337-361 ዓ.ም/ በኒቂያ ጉባኤ ውሳኔ ተቀባዮች ላይ ስደትን አስጀመረ። ይህ ስደት አትናቴዎስን እንዲጋዝ ሲያደርግ፤ አርዮስን ግን ወደ አገልግሎቱ እንዲመለስ ተጠራ።

በቅዱስ አትናቴዎስ ምትክ በምእመኑ ፈቃድ ሳይሆን በጉልበት አርዮሳዊ አባ ጊዮርጊስን የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ አድርጉ ሾመ። በዚህ መሠረት ወደ ኢትዮጵያ ነገሥታት አብርሃ ወአፅብሀ ደብዳቤ ልከዋል። ይህ ደብዳቤ በቅዱስ አትናቴዎስ ተሹሞ የመጣውን አባታችንን አባ ሰላማን ሽረው



www.ethiopianorthodox.org

አርዮሳዊ ቴዎፍሎስ በመንበሩ እንዲቀመጥ ቁንስጣ ጠይ ቋል::[5]

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ገና ባልጠነከረችበት በዚ ህን ጊዜ በደገኛ ሐዋርያዋ በአባ ሰላማ ብርታትና አርቆ አስተዋይነት ቀደም ብላ የኒቂያን የእምነት መግለጫ መቀ በልዋ በኋላም በአታላይነቷ የአርዮስን ኑፋቄና መልእክተኛ ውን ቴዎፍሎስ ሕንዳዊ በመጣባት እግሩ ተመልሷል:: በውጭ አብያተ ክርስቲያኖች ውስጥ በቅዱሳት መጽሕፍት አተረጓጎም የታዩትን ክስተቶች፣ ጠንካራና ደካማ ጐን፣ ገንቢና አፍራሽ፣ ተልዕኮአቸውን ለመከታተል አባ ሰላማ ንቁ ነበር:: ይህን መንፈሳዊ ቅንአትን የሚያነሳሳ የአባ ሰላማን ታሪክ የተመለከተ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ጥንታውያን አባ ቶች ገና የአርዮስን የትምህርት በሽታ ከርፋቱና ኮምጣጣነቱን አውቀው ወደ ሀገር ሳያስገቡ ከውጭ የደፉትን አተላ ዛሬ ትውልዱ ሲገታው ስንመለከት ኢትዮጵያዊ ናቸው ለማለት ይከብደናል:: ስለዚህ ቅዱስ አባታችን ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የውጭውን የእምነት እንቅስቃሴ በሚገባ ተከታትሏል::

## የአብርሃ ወአጽብሐ ዕረፍት፤
## የአቡነ ሰላማ የስማቸው ስያሜና ዕረፍታቸው፤

ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደ ረጉ እነዚህ እኑያነ ነገሥታት አብርሃ ወአፅብሐ የአክሱም ቤተክርስቲያንን በሚያስደንቅ ሁኔታ ሠርተው ከጨረሱ በኋላ ቀጣዩን ቤተ ክርስቲያን ያሠሩት የእናታቸው የንግሥት ሶፍያ አገር በሆነው በሁለት አውላሎ አውራጃ ዓይባ ገማድ በሚባለው ቦታ ነበር:: ይህ ታሪካዊ ቤተክርስቲያን በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተሠራ ሲሆን ከአንድ አለት ተፈልፍሎ የተሠራ እስከ ዛሬ በስማቸው የሚጠራ ገዳም ነው::[6]

[5] የኢትዮጵያ ታሪክ 1ኛ መጽሐፍ ገጽ 310፤ የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ታሪክ ገጽ 24-25

[6] ታሪክ ነገሥት አብርሃ ወአፅብሐ ገፅ 14-15::





የመቅደሱን ሥራ ከፈፀሙ በኋላ በወርቅ በእንቁ ያጌ ጡት ነበር:: አምዶቿ እንደ አርዘሊባኖስ ቀጥ ብለው የቆሙ ናቸው:: ሌት ከቀን የሚያበራ ብርሃን የሚሰጡ እንቁ የተ ሠሩ 48 መስኮቶች ነበሩት:: እንደ ፀሐይ የሚያበራ እና የአዕማዱ ቁጥር 42 ይደርሳሉ:: መቅደሱን ለ4 ከፍለውት ነበር፤ ይህ አስደናቂ ቤተክርስቲያን እንደ አክሱም ቤተ ክርስቲያን በ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አደጋ ደርሶበታል:: ሙሉ በሙሉ ባይፈርስም ቅኔ ማህሌቱና መንበሩ ፈርሷል:: በአስደናቂ ጥበብና በንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሠሩ ሐረጎች በእሳት ጋይተው ምልክታቸው ይታያል:: ይህ ሁሉ ጥፋት የደረሰው በዮዲት ጉዲት ነው:: የአብርሃ ወአፅብሐ ገዳም እንዲህም ሆኖ ውበቱና አስደናቂነቱን አላጣም:: የዓለም ቱሪ ስቶች እየዩ ያደንቁታል:: ይህም የዓለም ታላላቅ ሥራ ዎች እንደ አንዱ ሆኖ በዓለም የቅርስ መዝገብ ተመዝግቧል:: በኢትዮጵያም የሚገኙ ታላላቅ ቅርሶች አንዱ ነው::[7]

ንጉሥ አብርሃ በሕይወተ ሥጋ የነበረበት ዘመን ሃምሳ ሁለት ዓመት ነው:: አምስት ዓመት በእናት በአባቱ ቤት፤ ሰባት ዓመት በቤተ መቅደስ፤ አስራ አምስት ዓመት በሕገ ኦሪት ሕዝቡን በማስተዳደር፤ አስራ አምስት ዓመት ወንጌልን በማስተማር፤ አሥር ዓመት ከወንድሙ ከአፅብሐ ተለይቶ በምድረ ትግራይ በአጠቃላይ ሃምሳ ሁለት ዓመት ቆይቷል:: ከዚህ በኋላ ጥቅምት አራት ቀን አርፏል:: ወንድ ሙም አፅብሐ ወንድሙ ባረፈበት ጥቅምት አራት ሞቷል:: የሕይወት ዘመኑ ስልሳ አምስት ዓመት ነው:: ይኸውም አምስት ዓመት ከእናት ከአባቱ ቤት፤ ሰባት ዓመት በቤተ መቅደስ፤ አስራ አምስት ዓመት በሕገ ኦሪት ነግሶ ሕዝቡን በማስተዳደር፤ አስራ አምስት ዓመት በሕገ ወንጌል፤ የኢት ዮጵያን ሕዝብ በማስተማር በማሳመን፤ በማጥመቅ፤ አሥር ዓመት ከወንድሙ ተለይቶ በሸዋ አገር ቤተ መንግሥቱን የረር በማድረግ፤ አስራ አምስት ዓመት ወንድሙ ከሞተ በኋላ በጠቅላላ ስልሳ አምስት ዓመት ነው::[8] የሁለቱም መቃብር ዛሬ በገርአልታ በሚታወቀው ገዳማቸው አፅማ

[7] ዝኒ ከማሁ ገፅ 14::

[8] ዝኒ ከማሁ ገፅ 33::



www.ethiopianorthodox.org

ቸው ሳይፈርስ ይገኛል፡፡ የመጀመሪያዎቹ የኢትዮጵያ ቅዱሳን ሲሆኑ መታሰቢያቸው ጥቅምት አራት ቀን ነው፡፡

በአፍሪካ ውስጥ ታላላቅ መምህራን የነበሩባቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ሲጠፉ በኢትዮጵያ ለተቋቋመችው ቤተ ክርስቲያን ግን ማንኛውንም ችግር አልፋ እስከ ዛሬ በመቆየትዋ ወንጌሉንም አፅንታ በመገኘትዋ ከብፁዕ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ትምህርቷን ሳታጨልም ለመጀመሪያዋ ሐዋርያ ለአባታችን አቡነ ሰላማ የትጋታቸውን የፍቅር አገልግሎታቸው ፍሬ መሆኗን ሲያስደንቅ ይኖራል፡፡ ከዚህ በመነሳት ነው ፍሬምናጦስ ከሚለው የግል መጠሪያ ስማቸው በተጨማሪ «ሰላማ» እና «ከሳቴ ብርሃን» የሚል ስም የተሰጣቸው በውጭው ቤተክርስቲያን እስከ ዛሬ የሚጠቀሙት ስም በቀድሞው ፍሬምናጦስ ነው፡፡ የስሙ ስያሜ:-

| ስያሜ | ምክንያት |
|---|---|
| ሰላማ | ይህ ስያሜ በክርስቶስ መስቀልና ደም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ስለተፈፀመው የእርቅ ሥራ ለሕዝበ ኢትዮጵያ አብሳሪ መሆኑን ያመለክታል፡፡ «በመስቀሉ ደም ሰላምን አደረገ» እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ፡፡ ቆላ. 1፥20 በአባ ሰላማ አማካኝነት ወደ ክርስቶስ በመቅረባቸው፣ የከበደ ሸክማቸው የቀለለላቸው ሁሉ ሰላም በማግኘታቸው «ሰላማ» ብለዋቸዋል፡፡[9] |
| ከሣቴ ብርሃን | ብርሃነ ወንጌልን ለኢትዮጵያ ስላበሩ፣ በብርሃነ ትምህርታቸው የተደሰቱ በጨለማ ውስጥ ኖረው በእርሳቸው አማካኝነት ብርሃነ ወንጌል የበራላቸው ምዕመናን «ከሣቴ ብርሃን» በማለት ሰይመዋቸዋል፡፡ ቅዱስ ያሬድም በድጓው ላይ «ብርሃንን ይገልጥ ዘንድ ወደ አገራችን የተላከ ይህ ሰው መምህራችን ነው» ብሏል፡፡[10] |

በመልካም አባትነታቸው ያስቡላቸው ስለነበር ፍቅራቸው ተስምቷቸው «አቡነ» ብለዋቸዋል፡፡ እንደ እስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ግን ቄሱ አቡነ ሲባል ጳጳሱ ደግሞ አምባ (አባ) ይባላል፡፡ ለምዕመናን ከጳጳሱ ይልቅ ቄሱ ይቀርባልና፡፡ ከሣቴ ብርሃን ሰላማም በፍፁም ትህትና ሁልጊዜ ከምእመናን ጋር የቅርብ ግንኙነት ያደርጉ ነበርና አምባ በማለት ፈንታ አቡነ ብለዋቸዋል፡፡ ፍሬምናጦስ እነዚህ ስሞች የተሰጧቸው በአሚነ ክርስቶስ ከወለዷቸው ልጆቹ ከምእመናን ብቻ ነው፡፡[11]

[9] ትንሣኤ ሐምሌ 1972 ዓ.ም ቀጥር 34 ገፅ 8፡፡

[10] ዝኒ ከማሁ ገጽ 8፡፡



የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት

በእውነቱ ለአንድ ትጉ ሐዋርያ የሚገባ ስም ነው፡፡ «አንዲት ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት ናት መባል የሚገባት እንደ ጌታዋ በዚህ ዓለም የእግዚአብሔርን ሥራ ተግታ ስትሠራ ነው» የሚባለው ለዚህ ነው፡፡ ክርስትና በኢትዮጵያ ውስጥ እስከ አሁን ድረስ የቆየው በትምህርት የተገኘን እውቀት ቁጭ ብሎ በማወጅ ሳይሆን እንደ አቡነ ሰላማ በመሰሉ ሐዋርያ እውነተኛውን ሕይወት እየኖሩ ቤተ ክርስቲያንን ከእነሙሉ ሥርዓቷ ባቆዩን አባቶች ነው፡፡

አባታችን አቡነ ሰላማ የተሸከሙት መንፈሳዊ ኃላፊነት በትክክል ለመወጣታቸው በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሥነ ጽሑፍ ብቻ ሳይሆን የተመሠከረላቸው ምዕራባውያንም ጭምር መስክረዋል፡፡ በቅዱስነትም ደረጃ ይከበራሉ፡፡ የሮማ ካቶሊክ ኦክቶበር 27 የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ኖቬምበር 30 መታሰቢያቸውን ያከብራሉ፡፡ የኮፕት (የግብፅ) ቤተ ክርስቲያን ስንክሳር በዓሉን አይሰራላቸውም፡፡ አቡነ ሰላማ በእጃቸው ይይዙት የነበረው መስቀልና በግሪክኛ የቀደሱበት መጽሐፍ በጥንታዊቷ ተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይገኛል፡፡ አቡነ ሰላማ በእግዚአብሔር ፈቃድ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያ ከመሆናቸውም በላይ ብዙ በረከቶችን ስላስገኙላት በዓመት ሁለት ጊዜ ሐምሌ 26 እና ታህሳስ 18 ቀን ቅዱስ አባት ብላ ታከብራለች፡፡ በስማቸውም ቤተ ክርስቲያን አንፃለች፡፡ በትግራይ አገረ ስብከት ብቻ በአቡነ ሰላማ ስም ሦስት አብያተ ክርስቲያናት አሉ፡፡ መካነ መቃብራቸው ግን ከሦስቱ አንዱ በሆነው አምባ ከበሮ በሚባል በገመድ ብቻ በሚወጣበት አምባ ላይ በተንቤን አውራጃ ነው፡፡ ቅዱስ አባታችን አቡነ ሰላማ:-

[11] ክርስትና በኢትዮጵያ ክፍል 1 ገፅ 47፡፡



www.ethiopianorthodox.org

- መሠረቱ ያልተናወጸ ቤተ ክርስቲያን በስብከታቸው የመሠረቱ፤
- ቅድስናቸው በጥንት አብያተ ክርስቲያናት የተመሠከረ ላቸው፤
- የወንጌልን ብርሃን በመላው ኢትዮጵያ ዞረው ያበሩ፤
- በክርስቶስ መስቀል ዳግኘውን ሰላም ለኢትዮጵያውያን ያስተዋወቁ፤
- ሐዋርያዊ ግዴታቸውን በሚገባ የተወጡ፤
- በኢየሩሳሌም ላለው ርስታችን በነበሩበት ዘመን መፍትሔ ያስጡ፤
- የአርዮስን ትምህርት በመጣበት ቦታ የመለሱ፤
- መንበራቸውን በዓለም አቀፍ ዕውቅና ያካተቱ፤
- ለህገሪቱ ጭምር የሥነ ፊደል ሥርዓት የዘረጉ፤
- ህገራችን በራሷ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስን እንድታገኝ የተረጎሙ፤
- ሐዋርያዊ ሕይወት ያላቸው ታላቅና ቅዱስ የቤተ ክርስ ቲያናችን አባት ናቸው።





# ምዕራፍ አራት

## ሶስተኛው ወርቃማ ዘመን
[ከ480 - 600 ዓ.ም]

## የተስዐቱ ቅዱሳን መምጣት፤ የቅዱስ ያሬድ መነሳትና፤ የተቀጸለ ጽጌ በዓል አከባበር መጀመር

አብርሃና አፅብሐ ከሞቱ ወዲህ እስከ ካሌብ ድረስ የመቶ ዓመት ልዩነት አለ። የቁስጥንጥንያ ግዛት ከትልቁ ቆስጠንጢኖስ ወዲህ የክርስትና ሃይማኖት በጣም እየተስፋፋ ሔዶ ነበር። ዳሩ ግን በትልቁ ቴዎዶስዮስና በተከታዮቹ ዘመነ መንግሥት ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ቀሳውስት በበረከቱ መጠን እርስ በራሳቸው መለያየት ተከሰተ፤ በችግሩና በስደቱ ዘመን በኔሮን፣ በእነ ዲዮቅልጢያኖስ ጊዜ የነበራቸው ኅብረትና አንድነት በአሁኑ ማለት (በ451 ዓ.ም. አካባቢ) በምቾቱ ጊዜ ጠፋና የቁስጥንጥንያው ከእስክንድ ርያው፤ የእስክንድርያው ከሮማው ቤተ ክርስቲያን በአዲስ ሃሳብ ተለያዩ ይልቁንም ለክርስቶስ 1 አካል 2 ባሕርያት አሉት የሚል አዲስ ክህደት ተከሰተ፤ ይህ ብቻ አይደለም የሥልጣን የዘር ችግር ታከለበት፤ በዚህና በመሳሰሉት ነገሮች ብዙ ሁከትና ፍጅት አስከተለ። ጳጳሳቱና ቀሳውስቱ የጊዜውን መንግሥት ተለጥፈው በሙግቱ ቀንቷቸው በተደላደሉበት ሰዓት ይህን የሁለት ባህርይ ትምህርት ለተራው ሕዝብ ጭምር እንዲደርስ አብልጠው ጣሩ። ይሁን እንጂ በዚህ መካከል እነ ዲዮስቆሮስ፣ ያዕቆብ ዘእልበረዳኢ የመሰሉ የተዋሕዶ አባቶች መነሳታቸው ይታወቃል። ስለዚህ አንድ ባሕርይ በተዋሕዶ የሚሉ ያላቸው ምርጫ መሰደድ ነበር።

በዚህ ምክንያት በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ 9 መነኮሳት ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ መጡ። በዚህን ጊዜ በኢትዮጵያ ነግሦ የነበረው ዳግማዊ አልአሜዳ ነበር። እነዚህ መነኮሳት የስደታቸው ምክንያት በጉባኤ ኬልቄዶን



www.ethiopianorthodox.org

- መሠረቱ ያልተናወጸ ቤተ ክርስቲያን በስብከታቸው የመሠረቱ፤
- ቅድስናቸው በጥንት አብያተ ክርስቲያናት የተመሠከረ ላቸው፤
- የወንጌልን ብርሃን በመላው ኢትዮጵያ ዞረው ያበሩ፤
- በክርስቶስ መስቀል የተገኘውን ሰላም ለኢትዮጵያውያን ያስተዋወቁ፤
- ሐዋርያዊ ግዴታቸውን በሚገባ የተወጡ፤
- በኢየሩሳሌም ላለው ርስታችን በነበሩበት ዘመን መፍትሔ ያሰጡ፤
- የአርዮስን ትምህርት በመጣበት ቦታ የመለሱ፤
- መንበራቸውን በዓለም አቀፍ ዕውቅና ያካተቱ፤
- ለሀገሪቱ ጭምር የሥነ ፊደል ሥርዓት የዘረጉ፤
- ሀገራችን በራሷ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስን እንድታገኝ የተረጎሙ፤
- ሐዋርያዊ ሕይወት ያላቸው ታላቅና ቅዱስ የቤተ ክርስ ቲያናችን አባት ናቸው።

❁ ❁ ❁ ❁





# ምዕራፍ አራት

## ሁለተኛው ወርቃማ ዘመን
[ከ480 - 600 ዓ.ም]

### የተስዓቱ ቅዱሳን መምጣት፤ የቅዱስ ያሬድ መነሳትና፤ የተቀጸል ጽጌ በዓል አከባበር መጀመር

አብርሃና አፅብሐ ከሞቱ ወዲህ እስከ ካሌብ ድረስ የመቶ ዓመት ልዩነት አለ። የቁስጥንጥንያ ግዛት ከትልቁ ቆስጠንጢኖስ ወዲህ የክርስትና ሃይማኖት በጣም እየተስፋፋ ሔዶ ነበር። ዳሩ ግን በትልቁ ቴዎዶስዮስና በተከታዮቹ ዘመነ መንግሥት ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ቀሳውስት በበረከቱ መጠን እርስ በራሳቸው መለያየት ተከሰተ፤ በችግሩና በስደቱ ዘመን በኔሮን፣ በእነ ዲዮቅልጢያኖስ ጊዜ የነበራቸው ኅብረትና አንድነት በአሁኑ ማለት (በ451 ዓ.ም. አካባቢ) በምቾቱ ጊዜ ጠፋና የቁስጥንጥንያው ከእስክንድ ርያው፤ የእስክንድርያው ከሮማው ቤተ ክርስቲያን በአዲስ ሃሳብ ተለያዩ ይልቁንም ለክርስቶስ 1 አካል 2 ባሕርያት አሉት የሚል አዲስ ክህደት ተከሰተ፤ ይህ ብቻ አይደለም የሥልጣን የዘር ችግር ታከለበት፤ በዚህና በመሳሰሉት ነገሮች ብዙ ሁከትና ፍጅት አስከተለ። ጳጳሳቱና ቀሳውስቱ የጊዜውን መንግሥት ተለጥፈው በሙግቱ ቀንቷቸው በተደላደሉበት ሰዓት ይህን የሁለት ባህርይ ትምህርት ለተራው ሕዝብ ጭምር እንዲደርስ አብልጠው ጣሩ። ይሁን እንጂ በዚህ መካከል እነ ዲዮስቆሮስ፣ ያዕቆብ ዘእልበረዳኢ የመሰሉ የተዋሕዶ አባቶች መነሳታቸው ይታወቃል። ስለዚህ አንድ ባሕርይ በተዋሕዶ የሚሉ ያላቸው ምርጫ መሰደድ ነበር።

በዚህ ምክንያት በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ 9 መነኮሳት ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ መጡ። በዚህን ጊዜ በኢትዮጵያ ነግሦ የነበረው ዳግማዊ አልአሜዳ ነበር። እነዚህ መነኮሳት የስደታቸው ምክንያት በጉባኤ ኬልቄዶን



www.ethiopianorthodox.org

የተከሰተውን አዲስ ትምህርት በመቃወማቸው በቢዛንታይን ነገሥታት ስቃይ ስለፀናባቸው ነው። ቢዛንታይን የሚባለው በቁስጥንጥንያ የአንድ መንደር ስም ነው። ነገሥታት የሚወለዱበት መንደር ስለሆነ መላው የታናሽ እስያ ቢዛንታይን እየተባለ ይጠራል።[1] በዚህም ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ንጉሡ አቀባበል በማድረግ ተቀበላቸው በኋላም በሰላም እንዲኖሩ ፈቀደላቸው። ቲያረፉትም በአክሱም ቤተ ቀጢን በሚባለው ሥፍራ ነው። ይህ ቤተ ቀጢን የእንግዶች ማረፊያ ወይም ት/ቤት ሳይሆን አይቀርም። ተሰአቱ ቅዱሳን ስማቸውና የስማቸውም ትርጉም፤ የመጡበትን አገር እንደሚከተለው እናያለን።

| | |
|---|---|
| አቡነ አረጋዊ ዘሮም | አረጋዊ ማለት ያረጀ ሽማግሌ ማለት ነው፤ በእድሜ ልጅ ሲሆኑ እንደአዋቂ ቁም ነገርን ይሠሩ ስለበር ነው። |
| አቡነ ጰንጠሌዎን ዘሮም | ጰንጠሌዎን ማለት በግሪክ ቋንቋ ይመስላል ልብስ ማለት ነው። |
| አቡነ ይምአታ ዘቆስያ | ይምአታ ማለት ማታ የመጣ ማለት ሲሆን ከተሰአቱ ቅዱሳን ዘግይተው መጨረሻ ስለመጡ የተሰጠ ስያሜ ነው። |
| አቡነ ገሪማ ዘሮም | ገሪማ ማለት ግሩም የሆነ የሚያስገርም ትምህርትና ሥራ የሚሠራ ማለት ነው። |
| አቡነ ፅህማ ዘአንፆኪያ | ፅህማ ማለት ጢማም ወይም ባለ ጽህም ማለት ነው። |
| አቡነ አፍጼ ዘእስያ | አፈ አፄ ወይም አፈ ዕፄ አፈ ንጉሥ ማለት ነው። |
| አቡነ ሊቃኖስ ዘቁስጥንጥንያ | ሊቃኖስ ማለት የሶሪያ ቋንቋ ይመስላል። ሊቅ፣ በጣም የተማረ ማለት ነው። ሊቀ ሊቃውንት እንደማለት ነው። |
| አቡነ አሌፍ ዘቄሳርያ | አሌፍ ማለት በዕብራይስጥ ፊደል አንደኛ መጀመሪያ የተገኘ /የመጣ/ ማለት ነው። |
| አባ ጉባ ዘኪልቅያ | ጉባ ማለት በአማርኛ ቋንቋ የተሰየመ ነው። ተራራ የሚያህል ትልቅ ግርማው የሚያስፈራ ማለት ነው። |

[1] የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገፅ 167 የግርጌ ማስታወሻ።





የተሰአቱ ቅዱሳን ስም ከግዕዝና ከአማርኛ ቋንቋ የተሰየመ ነው።[2] እነዚህ ቅዱሳን ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ዝም ብለው አልተቀመጡም። ለሥራቸው በር ከፋች የሆነውን ቋንቋ፣ የሕዝቡን ባሕል ጠንቅቀው ካወቁ በኋላ በአንድ ላይ አንድ አካባቢ ከመኖር ይልቅ መንፈስ ቅዱስ በመደበላቸው ቦታ ማስተማርን መረጡ። መንፈሳዊ ዓላማቸውንም ለማሳካት የአክሱም ነገሥታት እርዳታና ድጋፍ አልተለያቸውም ነበር። የተሰአቱ ቅዱሳን ሐዋርያዊ ተልዕኮአቸውን በ5 መመደብ ይቻላል።

1. ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ማፅናት፤
2. መጽሐፍትን መተርጎም፤
3. ወንጌልን ማስፋፋት፤
4. ገዳማትን መትከል፤
5. ሥርዓተ ምንኩስናን ማደራጀት ናቸው።

እነዚህ ሥራዎቻቸው ወቅታቸውን እየጠበቁ ተፈጽመዋል። በዚህ በኩል የመጀመሪያ ሥራቸው ባዕድ አምልኮ የሚፈፀምበትን ቦታ ሕንፃ ቤተክርስቲያን እንዲሠሩ አድርገዋል። የቤተ ክርስቲያን አሠራራቸው ሞላላ ሆኖ መንበሩ በምሥራቅ አቅጣጫ ክብ እንዲሆን አደረጉ፤ ይህ ዓይነቱ አሠራር የሶሪያን እቅድ የተከተለ ነው። አንዳንድ ፍርስራሾች መሠረታቸው እየተቆፈረ ወጥቷል። ቅዳሴ በዜማና በንባብ እንዲፈፀም ያደረጉት እነሱ ናቸው። የሚያስፈልጉትን ጸሎቶች ምንባቦችን ተርጉመዋል። ራሳቸውም ደርሰዋል።

ሁለተኛው በመጽሐፍ መተርጐም በኩል አስተዋጽኦአቸው በጣም የላቀ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ በአቡነ ሰላማ የተጀመረውን የመጽሐፍ ቅዱስን የመተርጐም ሥራ ተከፋፍለው ከፍፃሜ አድርሰውታል። ይህም ለግዕዝ ሥነ ጽሑፍ መስፋፋት በጣም ጠቅሟል። እንዲያውም የመሠረት ድንጊያ ነው ማለት ይቻላል። የቤተክርስቲያንን እምነት የሚያጠናክር ጽሑፎችን ለምሳሌ የቄርሎስንና የሌሎችን የታወቁ አበው ተግሳፅና ድርሰት ወደ ግዕዝ እየተረጐሙ ለየአድባ

[2] እስከ ማዕዜኑ ተሐነክሱ በክሌሆን ጌጋያቲክሙ ገፅ 46-47። መፅሔተ አሚን ገፅ 64።



www.ethiopianorthodox.org

ራቱና ለገዳማቱ እንዲዳረሱ አድርገዋል:: በዚህ መሠረት ይህ የተስአቱ ቅዱሳን ዘመንና የቅዱስ ያሬድ የተነሳበት የአፄ ገ/መስቀል ዘመን «የመጀመሪያው የሥነ ጽሑፍ ዘመን» በመባል ይታወቃል::

በሦስተኛ ደረጃ ወንጌልን አስፋፍተዋል:: በአንድ አገር ወንጌል ተሰበከ ሲባል በአንድ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ክርስቲያን ሆነ ማለት አይደለም:: ክርስትና በአባ ሰላማ ተሰብኳል ሲባል መላው ኢትዮጵያ ወንጌል ደረሰ ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ነው:: ስለዚህ ከአባ ሰላማ በፊትም ሆነ በኋላ የቤተ ክርስቲያን ዜጐች የመሆን እድል ያልገጠማቸው ኢትዮጵያውያን ነበሩ:: አሁንም አሉ:: ስለዚህ አገራችን ክርስትናም ባዕድ አምልኮ የሚከተሉ ሰዎች ነበሩባት:: በዚህ መሠረት በአገራችን አንዳንድ ክርስትና ያልተዳረሰባቸው ቦታዎች ስላሉ እግዚአብሔር በሚያውቀው እነዚህ 9 መነኮሳት ለአገራችን መምህርነት መጥተዋል ማለት ነው:: በዚህ መሠረት የክርስቶስን ወንጌል በሚገባ አስተምረዋል:: ሐዋርያዊ ግዴታቸውንም ተወጥተዋል::

በአራተኛ ደረጃ ገዳማትን መትከል ነው:: ቅዱሳን አባቶች በአትን መስርተው የመናንያን ማኅበር እንዲስፋፋ የአምልኮ ቦታ ይኖራቸዋል:: የተስአቱ ቅዱሳን ገዳማዊ አመራር ይህን ሥርዓት የተከተለ ነው:: ተስአቱ ቅዱሳን ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማትን ከመትከላቸውም ሌላ በስማቸው እስከ አሁን ድረስ የሚጠሩ ገዳማት አሏቸው በአሁኑ አጠራር ገዳማቸው በክልል 1 ውስጥ ይገኛሉ::

በአምስተኛ ደረጃ ሥርዓተ ምንኩስናን አደራጅተዋል:: ምንኩስና በግብፅ በረሀ በሲና የተጀመረ አንድ ጠንከር ያለ የክርስትና ሕይወት አኗኗር ነው:: የመጀመሪያ ዎቹ መነኮሳት ተራ ምእመናን ነበሩ:: ብቻ ለገዳሙ ቅዳሴ አገልግሎት የሚያገለግሉ ከመካከላቸው አንዳንዶችን ለቅስና መአርግ ይሾማሉ:: ምንኩስናን ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡት ተስአቱ ቅዱሳን ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል አቡነ አረጋዊ ትልቅ ተግባር ያከናወኑ ሲሆን፤ የምንኩስና ሥርዓት ጀማሪ ከሆኑት ከአቡነ





እንጦንስ አራተኛ ትውልድ ናቸው:: ይኸውም አቡነ አረጋዊም ይህን በኢትዮጵያ አስፋፍተዋል:: ይህን በራሳቸው ታሪክና በሐዋርያዊ ተግባራቸው ላይ እንመለከታለን:: ከዚህ በመቀጠል የምንኩስና አጀማመር መግለፅ ስላለበት ወደዚህ እንሔዳለን::

## የምንኩስና አጀማመር

ምንኩስና ወደፊት በምናያቸው ሦስት ቅዱሳን አባቶች ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህን ሕይወት የተከተሉ የእግዚአብሔር ሰዎች ነበሩ:: መነኮሰ ማለት ዘርኀቀ እምዓለም [ከዓለም የራቀ] ማለት እንደሆነ የታወቀ ነው:: ከአዳም ጀምሮ 7ኛው ትውልድ ሄኖክ አካሔዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ ምንም በስብበ ዓለም የኖረ ቢሆንም በፈቃደ እግዚአብሔር ተነጥቋል ዘፍ. 5÷24፣ ዕብ. 11÷5::

ቴሴብያዊ ኤልያስም የሔኖክን አዲስ ሕይወት አብነት አድርጐ በድንግልና (በምንኩስና) ጾዋሚ ተሀራሚ ሆኖ ዝናም ለዘር፣ ጠል ለመከር፣ እንዳይሰጥ ምድር የተከሉባትን እንዳታፀድቅ እያወገዘ በመንፈሳዊ ግርማ ታፍሮ ተከብሮ ከኖረ በኋላ እንደ ሄኖክ በአፍራሰ እሳት (በእሳት ሰረገላ) ወደ ሰማይ አርጓል 2ነገ. 2÷11:: ሆኖም ለመአስባን ሥርዓተ ምንኩስና የሠራላቸው ሄኖክ፤ ለደናግል ሥርዓተ ምንኩስና ጀምሮ የሰጣቸው ኤልያስ መሆኑን መረዳት ይገባል:: እንደዚሁም የእግዚአብሔር አገልጋይ /ካህን/ ሆኖ ጠጉሩን ሳይላጭ፣ ጥፍሩን ሳይቆርጥ ጠጅ ሳይጠጣ በስንዴና በወይን እየስታኮተ የኖረና ርዕሰ ባሕታውያን በመሆኑ የመልከጼዴቅ ታሪክ ለዚሁ ማስረጃ እናደርገዋለን ዘፍ. 14÷8-23፤ ዕብ. 7÷1-5::

በዘመነ ብሉይ ይህን ከተረዳን በዘመነ ሐዲስ ዮሐንስ መጥምቅም እነኤልያስን አብነት በማድረግ ሰላሳ ዘመን በገዳም ተወስኖ የግመል ፀጉር ለብሶ ወገቡን በጠፈር መታጠቂያ ታጥቆ የወይን ጠጅ ሳይጠጣ በግብረ ምንኩስና ፀንቶ



www.ethiopianorthodox.org

ኖሯል ማቴ. 3÷4፣ ሉቃስ 1÷15:: ሥርዓተ ምንኩስና አን ዲህ በመንፈስ እግዚአብሔር እየተመራ ከዚህ ከደረሰ በኋላ ጌታችን የማስተማር ተግባሩን ሲጀምር እንዲህ ብሏል «ስለ ስሜ ቤቱን፣ ወንድሞቹን እህቶቹን፣ አባት እናቱን፣ ሚስቱን ልጆቹን እና እርሻውን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል:: የዘላለም ሕይወትን ይወርሳል» ማቴ. 19÷29::

የሰው ፀጋው ልዩ ልዩ ስለሆነ የተቻለው በድንግልና መንኩሶ እንደ ኤልያስ እያገለገለ ያልተቻለው እንደ ሔኖክ ቤት ሠርቶ ሚስት አግብቶ ልጆች ወልዶ በፈሪሃ እግዚአ ብሔር አሳድጎ በዚህ ዓለም ከኖረ በኋላ ይመነኩሳል:: 12ቱ ሐዋርያትና 72ቱ አርድዕት ከመአስባን ካገቡትና ከደናግል የመረጣቸው ለዚህ ጭምር ነው:: ወደፊት እንደ ምናየው በዘመነ ሊቃውንት የበለጠ ምንኩስና ሕይወት የታየበት ዘመን ነው:: ማዕርገ ምንኩስና እንዲህ ደምቆ በእግዚአብሔር ፈቃድ እየተመራ የመጣ ሲሆን ምንኩስና ከአምላክ ሕግ የተ ለየ ተጀምሮ የማይፈፀም ከንቱ የሆነ ሰው ሠራሽ ጽድቅ ነው ብሎ መንቀፍ አይገባም::

## የምንኩስና መሥራች አባ እንጦንስ

የመጀመሪያው ገዳም መሥራች የአባ እንጦንስ የሕ ይወት ታሪክ በታላቁ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ቅዱስ አት ናቴዎስ በሚገባ ጽፎታል:: ይህም (ከ251-356) ዓ.ም መሆኑ ነው:: ይህ በግብፃዊው አባ እንጦንስ ግብፅ ውስጥ የተጀመ ረው የብህትውና ኑሮ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ለመላው የክርስቲያኑ ዓለም ያበረከተችው መንፈሳዊ ስጦታ (በረከት) ነው:: አባ እንጦንስ ግብፅ ውስጥ በምትገኝ ቆማ በተባለች መንደር ውስጥ ከደጋግና ሀብታም ቤተሰቦች በ251 ዓ.ም. ተወለደ:: ከወላጆቹ እረፍት በኋላ እድሜው 20 ዓመት ሲሆን አንድ ቀን ቤተ ክርስቲያን ለአምልኮ ሲሔድ በማቴ ዎስ ወንጌል 19÷21 የተጻፈው ሲነበብ ሰምቶ ልቡ ስለተነካና የንባቡ መልእክትም የወደፊት ሕይወቱን የሚመለከት ሆኖ ስላገኘው ወደ ቤቱ ሲመለስ ከወላጆቹ ወርሶ የነበረውን





ርስቱን ለድሆችና ለጐረቤቶቹ አከፋፍሎ ከመፀወተ በኋላ ዓለም በቃኝ ብሎ መነነ::

በግብፅ በረሀ በብህትውና ተወስኖ ለ85 ዓመታት በጾም በጸሎት አጋንንትን በመዋጋትና የተለያዩ ተአምራትን በመፈፀም የእጅ ሥራዎችን በመሥራት አምላኩን እያገለገለ ኖረ:: የሕይወት ታሪኩን የጻፈለት የእስክንድርያው ፓትርያ ርክ ቅዱስ አትናቴዎስም አባ እንጦንስ ወደ ነበረበት ገዳም ሔዶ ለተወሰነ ጊዜ አብሮት በመቆየት ሥርዓተ ምንኩስናን ተምሯል:: ታላቁ ቆስጠንጢኖስም በጸሎቱ እንዲያስበው ለአባ እንጦንስ የልመና ደብዳቤ መላኩ ይነገራል::

አባ እንጦንስ የምነና ኑሮውን ከጀመረበት ጊዜ አን ስቶ እስከ አረፈበት ጊዜ ድረስ በነበረበት ወቅት ከሚኖር በት ዋሻ ሁለት ጊዜ ብቻ ወጥቶ ከምዕመናን ጋር ለጥቂት ጊዜ እንደቆየ ወደ በአቱ ተመልሷል:: ይኸውም መጀመሪያ የወጣው በንጉሥ መክስምያኖስ ትዕዛዝ ስደትና ስቃይ የደረሰባቸውን ክርስቲያኖች ለማፅናናት በ311 ዓ.ም. ሲሆን፤ ለሁለተኛ ጊዜ የወጣው ደግሞ አርዮሳውያን በአትናቴዎስ ላይ በተነሱበት ወቅት ለአትናቴዎስና ለኒቂያ ጉባኤ ውሳኔ ዎች ያለውን ፅኑ ድጋፍ ለመግለፅ በ338 ዓ.ም. ነበር::

የቅዱስ እንጦንስ የብህትውና የብቃት ዝና ከሰሙ ክርስቲያኖች መካከል አንዳንዶቹ እሱ ወደሚኖርበት በረሀ ሄደው በአካባቢው በሚገኙ ዋሻዎች ውስጥ በየግላቸው የምነና ኑሮ ይኖሩ ጀመር:: ምንም እንኳ ኑሮአቸው ለየግል ቢሆንም የአባ እንጦንስ ተከታይ የነበሩ ባህታውያን ተራርቀው ከመ ኖር ይልቅ እሱ በሚኖርበት ዋሻ አካባቢ ሰብሰብ ብለው መኖራቸው አልፎ አልፎ በዘላን ዘራፊዎች በገዳማቱና በራሳ ቸው ላይ ከሚደርስባቸው አደጋዎች በመከላከል ለመዳን አስ ችሏቸዋል:: ከመካከላቸው እቅመ ደካማ የሆኑትን የታመሙ ትን ለመርዳት ችለዋል::

አባ እንጦንስ በራዕይ በእግዚአብሔር መልአክ በታዘ ዘው መሠረት የመነኮሳቱ ልብስ ነጭ ፈረጂያና (ቀሚስ)



www.ethiopianorthodox.org

ቆብ፣ መታጠቂያቸው ከቆዳ የተሠራ ሰቅ እንዲሆን ወስኖ ሲሠራበት ኖሯል:: መነኮሳቱ በየግላቸው ሆነው ሲፀልዩ፣ ሲጾሙ፣ ሲሰሩ ከሰነበቱ በኋላ ከቅዳሜ እኩለ ሌሊት ጀምሮ እስከ እሁድ ምሽት ድረስ ቅዱስ እንጦንስ ከሚኖርበት ዋሻ ዙሪያ ተሰብስበው ከሱ ጋር የማኅበር ጸሎትና አምልኮ ይፈ ፅሙ ነበር:: ይህ ዓይነቱ የብሕትውና ኑሮ በኋላ በአባ ጳኩ ሚስ እንደተመሠረተው የአንድነቱ ኑሮ ቀጥሎ ባሉት የኢትዮጵያ ዘመናት (ለ1 ሺ 600) ዓመታት ለአገራችን ይሾሙ የነበሩት የግብፅ ጳጳሳት የሚመረጡት ከቀይ ባሕር 40 ኪ.ሜ. ርቆ ይገኝ የነበረው ከዚሁ ከአባ እንጦንስ ገዳም ነው::[3] አባ እንጦንስ በ356 ዓ.ም. አርፏል:: እረፍቱ ጥር 22 ቅዳሴ ቤቱ ሐምሌ 22 ይከበራል::

## መቃርዮስ ዘገዳመ አስቄጥስ

ግብፅ ውስጥ በ300 ዓ.ም. አካባቢ ከደጋግ ሰዎች ተወለደ:: ለአካለ መጠን እንደደረሰ ወላጆቹ ሚስት አጬ ለት:: ሆኖም በፈቃደ ሥጋ አልተዋወቁም:: ብላቴናዋም ታማ ሳለ ለሱባኤ ወደ አስቄጥስ በረሀ[4] ሂዶ ይህቺ ቦታ ለተከታዮችህ ተሰጥታለች የሚል መልዕክት ራዕይ አየ:: እንደተመለሰም ብላቴናይቱንና ወላጆቹ በተከታታይ ስለ ሞቱ ህብቱን ለነዳያን መፅውቶ ወደ መንፈሳዊ ተግባራት ተሠማራ:: በምዕመናን ተመርጦ በቅስና ተመድቦ ያገለግል ነበር:: በዚህን ጊዜ ከአንድ ጓደኛዋ የፀነሰች ልጃገረድ ጓደኛዋን ላለማጋለጥ ስትል የደፈረኝ አባ መቃርስ ነው በማለቷ በወላጆቿና በአካባቢው ነዋሪዎች መንገላታትና ውርደት ደርሶበታል:: ታሪኩ እንደሚለው መላዕክት ሰውን መስለው ደግ ሰውነቱንና ንፅህናውን መስክረዋል:: እንዲሁም የተጠቀሰችው ነፍስ ጡር ምጥ ለ4 ቀናት ያህል ስለ ፅናባት በመጨረሻ ህቁን አውጥታለች::

[3] የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለ3ኛ ጊዜ ተሻሽሎ የታተመ ገፅ 87-89::

[4] መነኮሳት በኅብረት እየሠሩ በኅብረት እየተመገቡ፣ በኅብረት እየጸለዩ የሚኖሩበት ገዳም በሥርዓተ መቃርስና ጳኩሚስ እንደሚመራ ሲታወቅ፡ ሥራ ሥርን ቅጠላ ቅጠልን እየ ተመገቡ ተበታትነው የሚኖሩ መነኮሳት የሚኖሩበት ገዳም ደግሞ አሥቄጥሳዊ ይባላል:: አሥቄጥስ ማለት «የልብ_ሚዛን» ማለት ነው:: ይህ ቦታ ለግብፅ ገዳማት ዋና ማዕከል የሆነና ታላላቅ ቅዱሳን አባቶች የወጡበት የበረከት ማዕከል ነው::





ከዚህ በኋላ አባ መቃርዮስ ቀደም ሲል አይቶት የነበረውን ራዕይ አስታውሶ መንኖ ወደ አስቄጥስ በረሀ በመሔድ ገዳመ አስቄጥስን መሠረተ:: አባ እንጦንስም ወደ ገዳሙ እየሔደ ይጐበኘው ነበር:: እንዲሁም ከአባ እንጦንስ ሥርዓተ ምንኩስናን ይጠይቅ ነበር:: የእስክንድርያው 24ኛ ፓትርያርክ ቅዱስ ቄርሎስ ከአባ መቃርዮስ ተምሯል:: በቄሳር ቫሌንቲዮስ (Vialentius) ተሹሞ የነበረው አርዮሳዊ ጳጳስ ሊስዮስ (Lucius) አባ መቃርዮስን ወደ አርዮሳዊ እምነት ለማስለወጥ ጥረት አድርጐ ስላልተሳካለት በሮምና በቁስጥንጥንያ መካከል ትገኝ ወደ ነበር አንዲት ስሟ ያልተጠቀሰ ደሴት አግዞት ነበር::

አባ መቃርዮስ በግዞት ላይ በነበረበት ሰዓት የደሴ ቲቱ ንጉስ ልጅ ከያዛት 7 ርኩስ መንፈስ በሙሉ ስላወጣ ላት ንጉሡና የደሴቲቱ ሰዎች ወደ ክርስትና እምነት ለመመለስ ችለዋል:: የጣአቱ ቤተ መቅደስ ፈርሶ በላዩ ላይ ቤተ ክርስቲያን ተሠራ:: ይኸውም ቤተ ክርስቲያን በጌታች ንና በድንግል ማርያም፣ በሊቃነ መላዕክት ስዕል ያጌጠ እና ከወርቅ፣ ከእንቁ የተሠራ ነበር:: አባ መቃርዮስ በ390 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ ሲሆን የኮኘት ቤተ ክርስቲ ያን ፓትርያርክ አባ ብንያም /623-663/ ዓ.ም አስቄጥስ ገዳም በስሙ የተሠራውን ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቤቱን ከቦ ታው ድረስ በመሔድ አከብሯል:: የእኛ ቤተ ክርስቲያን ስንክሳርም መታሰቢያውን ይሠራለታል::[5]

## የአንድነት ገዳም መስራች አባ ጳኩሚስ

በአባ እንጦንስ ዘመን ለውትድርና ተገዶ የነበረው አባ ጳኩሚስ የውትድርናን መራራነት ከተመለከተ በኋላ በአባ እንጦንስ አማካኝነት የተመሠረተው የምንኩስና ሕይ ወት በጣም ከመረዳቱም በላይ ከተጠቀሰው ቦታ በበኩሉ አንድ ገዳም መስርቷል:: የመነኮሳትን የአንድነት ኑሮ የመ ሠረተው አባ ጳኩሚስ ግብፅ ውስጥ ኤስና በተባለች መንደር

[5] ዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ሕይወት በቤተ ክርስቲያን ገፅ 238::



www.ethiopianorthodox.org

ከአረማውያን ወገን ከነበሩ ቤተሰቦች በ290 ዓ.ም. ተወለደ። ካደገ በኋላ በቆስጠንጢኖስ ዘመን ለወታደርነት ተመልምሎ አገልግሏል። ከውትድርና አገልግሎት ላይ ሳለ በተመለከተው በክርስቲያኖች ጀግንነት፣ ቸርነት፣ እንግዳ ተቀባይነት ተስቦ (ልቡ ተነክቶ) ስለነበር፤ የአገልግሎቱን ግዳጁን እንደፈፀመ በ313 ዓ.ም. ወደ ሲቪልነት ተመልሶ ሲኖር የክርስትናን ትምህርት ተቀብሎ ተጠመቀ። ከዚህ በኋላ የአባ እንጦንስ ደቀ መዝሙር ወደነበረው አባ ፓላሜኖን ወደ ተባለው መናኝ ዘንድ ሔዶ ስለ ብህትውና ኑሮ እና ሥርዓት ሲማር ከቆየ በኋላ በ320 ዓ.ም. በአባይ ወንዝ አጠገብ ከሚገኝ ታቤኒስ ከተባለው ቦታ ገዳም መሠረተ።

በብህትውና ለመኖር ወደ ገዳሙ ሔደው ለተሰበሰቡት መነኮሳት በማኅበር እንዲኖሩ የሚረዱና መነኮሳት ለኑሮአቸው የሚገቡ ሕጎችን አወጣላቸው። አባ ጳኩሚስ በመሠረተው ማኅበራዊ በሆነው የምንና ኑሮ ለመሳተፍ ብዙ ሰዎች ስለሔዱ በሕይወት ሳለ ዘጠኝ የወንድና ሁለት የሴት ገዳማትን መስርቶ ባዘጋጀው የመነኮሳት ሕጎች መሠት ይተዳደሩ ጀመር። በዚህ አኳኋን አባ ጳኩሚስ በ346 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ብዙ ገዳማት ተመስርተው በውስጣቸውም ቁጥራቸው የበዛ መነኮሳት በብህትውና ይኖሩ ነበር። አባ ጳኩሚስ የመሠረተው የማኅበራዊ የብህትውና ኑሮ መንገድ ከታቤኒስ ወደ ሌሎች ገዳማት ተዛምቶ በተግባር ላይ ውሏል። እንዲሁም ያዘጋጀው ሥርዓተ መነኮሳት በታላቁ ባስልዮስ በቤኔዲክትና በካስያን ጽሑፎች (ሥራዎች) ላይ ታላቅ ተፅእኖ አድርጓል። የዚህም በአባ ጳኩሚስ የተዘጋጀው ሕግ ዋነኛው ቅጂ ሲጠፋ ወደ ላቲን የተተረጐመው እስከ ዛሬ ድረስ አለ። በሕጉ ውስጥ ከተጠቀሱትም ዋና ዋናዎቹ ጥቂቶች እንደሚከተሉት ናቸው።

በማኅበራዊ ብህትውና ኑሮ የሚኖረው እያንዳንዱ መነኩሴ በየእለቱ ቀንና ሌሊት ሊሠራቸው (ሊፈፅማቸው) የሚገቡ ተግባሮች ተዘርዝረዋል። ይኸውም መነኮሳት ጠዋትና ማታ አብረው እንዲጸልዩ፣ በአንድነት እንዲሠሩ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲያጠኑና በቁም ጽሕፈት እንዲጽፍ፤





ገቢና ወጭያቸው አንድ ላይ እንዲሆን፣ በአንድነት እንዲመገቡ፣ ልብሳቸውም አንድ ዓይነት እንዲሆን እነዚህን የመሳሰሉትን ማኅበራዊ ኑሮ ነክ ሕጎች አወጣላቸው። በዚህ አኳኋን መነኮሳቱ የዕለት ምግባቸውን የሚያገኙት እየሠሩ ነበር። እነዚህን ሕጎች በመተላለፍ የማያከብሩ መነኮሳት ላይ የሚወሰዱት ለዘብ (ቀለል) ያሉ የቅጣት ዓይነቶች ተዘጋጅተዋል። እንዲሁም ማንኛውም እውነተኛ መነኩሴ ሊፈፅማቸው ከሚገቡ ተግባሮች ዋና ዋናዎች የድንግልና ኑሮ፣ ንፅህናን እግዚአብሔርን በሙሉ ልብ ማፍቀርና ማምለክ፣ ድህነትና ታዛዥነት ናቸው።

ቀደም ሲል በአባ እንጦንስ ከተመሠረተው ከመጀመሪያው ከብቸኝነት የብሕትውና ኑሮ ይህ በአባ ጳኩሚስ የተዘጋጀው የማኅበራዊ የብሕትውና ኑሮ ያሳየው ታላቅ ለውጥ መነኮሳት ከዋናው ከአምልኮተ እግዚአብሔር ተግባራቸው በተጨማሪ የተለያዩ ሥራዎችን በትጋት እንዲሠሩ፣ እንዲማሩ የሚያዝ ሕግ ነው። ማንኛውም ሰው በብህትውና ለመኖር ወደ ገዳማቱ ሲሔድ እዚያ እንደደረሰ በአባልነት አይቀበሉትም ነበር። ከ1-3 ዓመታት ለሚሆን ጊዜ የሰውየው ጠባይ ከተመረመረና ፈቃደኝነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ሥርዓተ ምንኩስና ተፈፅሞለት የገዳሙ አባል የመሆን ፈቃድ ያገኛል። በዚህ አኳኋን አባ ጳኩሚስ በመሠረተው የማኅበራዊ የብሕትውና ኑሮ ውስጥ መሃይምነት ፈፅሞ ጠፍቶ ነበር።

የእስክንድርያው ፓትርያርክ አትናቴዎስ ከአባ እንጦንስ ምንኩስና እንደተማረ ሁሉ እንዲሁም የቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ ዮሐንስ አፈወርቅ ቲቢድያ በተባለው አባ ጳኩሚስ በመሠረተው ገዳም ውስጥ ከ337-381 ዓ.ም. ድረስ በብሕትውና ቆይቷል። ታላቁ ባስልዮስ በግብፅ ገዳማት በብህትውና ከቆየ በኋላ ወደ ቁስጥንጥንያ ሔዶ በአባ ጳኩሚስ የብሕትውና ሥርዓት መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜ በቢዛንታይን ገዳማትን መስርቷል። የግሪክና የሩስያ አብያተ ክርስቲያናት የሚገለገሉባቸውን የመነኮሳት መተዳደሪያ ሕግ አዘጋጀላቸው እንግዲህ አባ ጳኩሚስ የመሠረተው የአንድ



www.ethiopianorthodox.org

ነት ገዳም ተቀባይነትን አግኝቷል ማለት ነው። አባ ጳኩሚስ ብዙ ሲያገለግል ከኖረ በኋላ በግንቦት 14 ቀን አርፏል።[6]

## ስለ ልብሰ ምንኩስና ጥንታዊነትን የያዘ ምሳሌ

(1) የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት በውስጥ እጀ ጠባብ፣ በላይ እጀ ሠፊ ከዚህ በኋይ ደግሞ እንደ መብርህያት ያለ ይደርብ ነበር። ይህንን ለብሶ አፍአዊ መስዋዕት ይሰዋና አፍአዊ ኃጢአትን ያስተሰርይ ነበር። መነኮሳትም እንዲህ ያለ ልብሰ ምንኩስና ለብሰው ውስጣዊ መስዋዕትን ይሰውና ውስጣዊ ኃጢአትን ያስተሰርያሉ።

(2) እስራኤላውያን ከግብፅ በወጡ ጊዜ ኩፌት ደፍተው በሎታ ይዘው ዝናር ታጥቀው ጫማ አዝበው እንደተነሱ መነኮሳትም እንዲህ ያለ ልብሰ ምንኩስና ለብሰው በምናኔ ወይም በሞት ከዚህ ዓለም ይለያሉ።

(3) ሥጋውያን አርበኞች ኩፌት ደፍተው፣ ዝናር ታጥቀው፣ ጋሻ ጦር ነጥቀው ሥጋዊ ጠላታቸውን ድል ነሥተው በመጡ ጊዜ ነገሥታት፣ መኳንንት፣ ካባ ላንቃ ያለብሷቸዋል ይሸልሟቸዋል። መነኮሳትም ልብሰ ምንኩስና ለብሰው ረቂቅ ጠላታቸውን ድል በነሱ ጊዜ ሥላሴ የብርሃን ካባ ላንቃ ያለብሷቸዋል።[7]

እንግዲህ እነዚህ 3 ቅዱሳን መነኮሳት የመሠረቱት ያደራጁት የምንኩስና ሕግና ሥርዓት በአገራችን በሰፊው ተስፋፍቷል። ይህም በዚህ ወርቃማ ዘመን በምንመለከታቸው በተሰአቱ ቅዱሳን አማካኝነት ነው። እነዚህ ዘጠኝ መነኮሳት ታሪካቸውንና የመሠረቱትን ገዳም ይዞታ እንደ ሚከተለው እናያለን።

[6] የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ በሉሌ መላኩ ገፅ 87-94።

[7] መርሐ ምእመናን ገፅ 26-27።





## አቡነ አረጋዊ ገዳም

አቡነ አረጋዊ ትውልዳቸው ሮም ሲሆን አባታቸው በሮም ከነገሡ ነገሥታት አንዱ ነበር። ስሙ ይስሐቅ ይባላል። እናታቸው ደግሞ አድና ትባላለች። በክርስቲያናዊ ሕይወታቸው የፀኑ ከመሆናቸውም በላይ እግዚአብሔርን የሚፈሩ በቅድስናቸውም የታወቁ ቅዱሳን ነበሩ። ሁለቱም ሁለት ልጆች ነበሯቸው። ከእነዚህም አንዱ ቴዎድሮስ ሁለተኛው ገብረ አምላክ ይባላሉ። ገብረ አምላክ የተባሉ አቡነ አረጋዊ ናቸው። አቡነ አረጋዊ ሦስት ስም ነበራቸው አንደኛው በወላጆቻቸው የወጣላቸው ገብረ አምላክ የሚባለው ነው፤ ሁለተኛው በመነኩሱበት ወቅት አባ ጳኩሚስ ያወጡላቸው ዘሚካኤል የሚል ሲሆን፤ ሦስተኛው ደግሞ ከመንፈሳዊ ሥራቸው የተነሳ 8ቱ ጓደኞቻቸው «አረጋዊ» ብለው የሰየሟቸው ስም ነው። ይህ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመጠሪያቸው ስም ሆኖ ቀርቷል።

አቡነ አረጋዊ ገና በህፃንነታቸው ከሮም ወደ ግብፅ መጥተው ሥርዓተ ምንኩስናን ፈፅመዋል። ከእናት ከአባታቸው ተለይተው ወደ ግብፅ ሔደው ጳኩሚስ ገዳም ገቡ። አባ ጳኩሚስ አቡነ አረጋዊን ሲያዩአቸው በታላቅ ደስታ ተቀበሏቸው ለምን እንደመጡ ከገለፁላቸው በኋላ የንጉሡ የይስሐቅ ልጅ መሆናቸውን ያውቁ ስለነበር አንተ የንጉሥ ልጅ ስትሆን እንዴት እመነኩሳለሁ ትላለህ የምንኩስና ሥራ እኮ በቀላሉ የሚቻል አይደለም ጽኑ ነው። ከአንተ በፊትም ብዙ ሰዎች እንመነኩሳለን እያሉ መጥተው ነበር። ግን አልተቻላቸውም፤ በየመጡበት ተመለሱ አሏቸው። አቡነ አረጋዊ ግን ቆርጠው ስለመጡ እኔ አንድ ጊዜ ዓለምን ትቻለሁ ከእንግዲህ ወዲህ ወደ ዓለም የምመለስበት ምክንያት የለም፤ ይልቁንስ ሥርዓተ ምንኩስናን እንድትፈፅምልኝ ነው ሲሉ ሃሳባቸውን ገለፁላቸው።

አባ ጳኩሚስ ይህን ከሰማ በኋላ «እግዚአብሔርን ለማገልገል ወደ ገዳም በምትሔድበት ወቅት አስቀድመህ ሰውነትህን ለመከራ አዘጋጅ» ይላልና ከሆነልህ ለጥቂት ጊዜ አረጋውያኑን እየረዳህ ቆይ አላቸው። አቡነ አረጋዊ ከአባ




www.ethiopianorthodox.org

ጳኩሚስ የተሰጣቸውን መመሪያና ቃል ተቀብለው መነኮሳት ሊሠሩ የሚገባቸውን ነገሮች እየፈፀሙና ልዩ ልዩ ትሩፋት እየሠሩ ከቆዩ በኋላ መንፈሳዊ ተልኮአቸውን በመመልከት አባ ጳኩሚስ አልባሰ ምንኩስናን አለበሷቸው አስኬማ መላእክትንም አስታጠቋቸው:: ስማቸውንም ዘሚካኤል ብለው ሰየሟቸው:: አቡነ አረጋዊ የምንኩስና ሥርዓት ጀማሪ ከሆኑት ከአባ እንጦንስ አራተኛ ትውልድ መሆናቸውን የተሰአቱ ቅዱሳን ሐዋርያዊ ተግባራቸውን ለ5 መድበን በተመለከትነው ክፍል ውስጥ ሥርዓተ ምንኩስናን አደራጅተዋል በሚለው አንቀፅ ላይ ተመልክተነዋል::

ዘሚካኤል የሚለው መጠሪያ ስማቸው እዚህ ከመጡ በኋላ ተቀይሮ አቡነ አረጋዊ ተብለዋል:: በኀብረት እንደመጡ ቤተ ቀጢን በነበሩበት ጊዜ ፍፁም በሆነ ትኅትና ፍቅር በተላበሰ ሁኔታ ወንድሞቻቸውን ስላገለገሉ ይህ ስም ሊሰጣቸው ችሏል:: በመንፈሳዊ ሕይወት ከሌሎች በልጦ የተገኘ ማለት ነው:: የአቡነ አረጋዊ እናት ልጃቸውን በመከተል በአባ መቃርስ ሥር ይተዳደር በነበረው በሴቶች ገዳም ገብታ እንደ ልጇ ሥርዓተ ገዳምን እንድትማር አድርገዋል::

ከአባ እንጦንስ ጀምሮ እስከ አቡነ ተክለሃይማኖት ድረስ ያለውን የምንኩስና አወራረድ ቅደም ተከተል «ማኅደረ መዝገብ ዘኢትዮጵያ» በተሰኘው ጽሑፋቸው ላይ ዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ እንደሚከተለው አስቀምጠውታል::[8]




[8] ቁጥር 1፣ ገጽ 77፣ 1986





## የደብረ ዳሞ ገዳም መመስረት

ተሰአቱ ቅዱሳን መንፈስ ቅዱስ በመደበላቸው ቦታ ለማስተማር ሲበተኑ አቡነ አረጋዊ ከአክሱም በስተ ምስራቅ 70 ኪ.ሜ. ያህል ርቆ ወደሚገኘው ወደ ደብረ ዳሞ ሔዱ:: ደብረ ዳሞ ዙሪያው ገደል የሆነ መውጫ የሌለው ተራራ ነው:: አቡነ አረጋዊ በዚህ መኖር ተመኝተው ነበርና እግዚአብሔር ወደዚህ ተራራ ላይ የሚያወጣቸው ዘንዶ አዘላቸው ወደ አንባው ለመውጣት ችለዋል:: አቡነ አረጋዊ ይህን ቦታ ሦስት ነገሮች ለማከናወን ተጠቅመውበታል:-

1. በየቦታው እየተሰማሩ ውለው ሲመሽ በመመለስ የፀሎት በአታቸው መሆኑን አስመስክረውበታል::
2. ስብከተ ወንጌል ለማስፋፋት በየቦታው ሲዘዋወሩ የሚያገኟቸውን ለመማር ፍላጐት ያላቸውን እየሰበሰቡ ብዙ መምህራነ ወንጌልን አፍርተውበታል::
3. ሥርዓተ ገዳምን አስተምረውበታል:: በአገራችንም የመጀመሪያው ገዳም ይሔ ሲሆን በዚህ ገዳም ውስጥ ታላላቅ አበው መነከሳት ምንኩሰናን ተቀብለውበታል:: ለምሳሌ በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሱት የሐይቅ እስጢፋኖስ መሥራች አቡነ ኢየሱስ ሞዐ የመነኮሱት በዚህ ነው::

ቅዱስ ያሬድ ወደ ደብረ ዳሞ አምባ በመውጣት ከአቡነ አረጋዊ በረከትን ተቀብሏል:: ይህ ገዳም ሊሠራ የቻለው ከዕለታት አንድ ቀን ፀዬ ገብረ መስቀል አቡነ አረጋዊን ለመጐብኘት ወደ ደብረ ዳሞ በሔዱ ጊዜ አቡነ አረጋዊ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠሩላቸው አጥብቀው ጠየቋቸው:: ከዚህ በኋላ ሀፄ ገ/መስቀል ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት ወደ ተራራው የሚያወጣ ደረጃ ሠርተው በሁለት ዓመት ውስጥ በጥሩ ሁኔታና ተመልካችን በሚያስደንቅ መንገድ አሠሩላቸው:: ይኸውም ቤተ ክርስቲያን በትንንሽ ጥርብ ድንጋይ፣ በጥርብ እንጨት አጊጦ የተሠራ ነው::

የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ እንደተጠናቀቀ ሀፄ ገ/መስቀል «ደረጃውን ላፍርሰው ወይስ ይሁን» ብሎ አቡነ አረጋዊን ሲጠይቃቸው «ዳህምሞ» አሏቸው:: ማለትም አፍርሰው



www.ethiopianorthodox.org

ማለት ነው:: ከዚህ በኋላ ደብረ ዳህምሞ ተብሎ ተጠራ:: ከጊዜ ብዛት ግን ደብረ ዳሞ እየተባለ መጠራት ጀመረ:: የደብረ ዳሞ ገዳም በኢትዮጵያ ከሚገኙ እጅግ የተከበሩ ቦታዎች አንዱና ዋነኛው ነው:: ገዳሙ ሦስት ቤተ መቅደስ የያዘ በብዙ ሐረግ ቅርፅ ያጌጠ ነው:: ቅዱስ ያሬድም የተሠራውን ቤተ ክርስቲያን ተመልክቶ በጣም አድንቋል:: ሕሊናንም የሚመስጥ ጣዕመ ዜማ አሰምቷል:: ዙሪያው ገደል ሆኖ የጠረጴዛ ቅርፅ ያለው አምባ ሲሆን ስፋቱ 1.827x255 ሜትር ነው::

የደብረ ዳሞ ገዳም ከፍ ያለና በገደላ ገደል የተከበበ ይሁን እንጂ በዘንዶ አምሳያ በተገመደው ጠፈር ከእግር እስከ ወገብ ታስረው ከወጡ በኋላ በጣም ሠፊና ለጥ ያለ ቦታ ላይ በመስራቱ ከሌሎች ገዳማት ልዩና አስደናቂ ከሚ ያደርገው ሁኔታ አንዱ ነው:: ወደ ላይ መውጣትና መውረድ የሚቻለው በገመዱ ጫፍ ላይ በተንጠለጠለ 16 ሜትር ርዝመት ባለውና በዘንዶ አመሳያ በወፍራሙ በተጐነጐነው ጠፈር ወገብ ላይ ይታሠርና የተንጠለጠለውን የጠፈር ጉንጉን በእጅም ጭምር አጥብቆና አቅፎ በመያዝ ስለሆነ በጣም አስፈሪና አስቸጋሪ ነው:: የመወጣጫው ገመድ የሚጐነጐነው ለአቡነ አረጋዊ በዓል ከሚታረደው የበሬ ቆዳ ላይ ነው::[9]

ከገዳሙ ግርጌ የሴቶች ገዳም ይገኛል:: ይህ ገዳም በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በሴቶች ገዳምነቱ የመጀመሪያ ነው:: ገዳሙን የመሠረተችው የአቡነ አረጋዊ እናት ቅድስት እድና ናት:: እናታቸው ከአቡነ አረጋዊ ጋር ግብፅ ወርዳ ሥርዓተ ገዳምን እንደተማረች ባለፈው አውስተናል:: ገዳሙ የሚጠራው በኪዳነ ምሕረት ስም ነው:: የደብረ ዳሞ ገዳም ታሪካዊነቱ ሰፊ ሲሆን በኋለኛው ዘመን ሃይማኖትን ለማጥፋት በተደረጉት አያሌ ጦርነቶች ገዳሙ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል::[10]

[9] የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ገፅ 100::

[10] በዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን 40 ዓመት ሙሉ ቤተ ክርስቲያን ስታቃጥል የነበረችው ዮዲት ከእርሷ ጥፋት ለመሸሽ ዋና ዋናዎቹ የአክሱም መጻሕፍትና ንዋየ ቅድሳት የተቀመጡት በዚሁ ገዳም ነው:: 15 ዓመታት ያህል የቱርክን ጥይት በቤተ





የደብረ ዳሞ ገዳም በሥነ ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ የማያሻማ ሚና ተጫውቷል:: ከገድለ ኢየሱስ ሞዐ መረዳት እንደሚቻለው የደብረ ዳሞ መነኮሳት በ13ኛው ክፍለ ዘመን ለሥነ ጽሑፍ ሥራ ትኩረት ሰጥተው ነበር:: አቡነ ኢየሱስ ሞዐ የቁም ጽሕፈት በሚገባ ተምረው አንድ አርባዕት ወንጌል ጽፈው ለገዳሙ ሰጥተዋል:: ወደ ሐይቅም እንደተመለሱ ጽሕፈቱንም ከአስተዳደር ጋር ደርበው ይሠሩ ነበር:: እሳቸው የጻፉት አርባዕት ወንጌል ዛሬም በሐይቅ እስጢፋኖስ በገዳሙ ይገኛል:: ይህ ወንጌል በውስጡ ስዕል ስላለው ለዘመኑ ኪነ ጥበብ አንድ መለኪያ ነው:: ጽሕፈቱንም ሆነ የስዕል አጣጣሉን አቡነ ኢየሱስ ሞዐ የተማሩት ከደብረ ዳሞ መሆን አለበት:: እንደሚታወቀው ኢየሱስ ሞዐ የመነኮሱት በዚህ ገዳም መሆኑን አውስተናል:: ማቲው የተባለ እንግሊዛዊ ቤተ ክርስቲያኑን ሲያድስ አያሌ የብራና መጻሕፍትን ተመልክቷል::[11]

ይህ ገዳም በጠላቶቹ ባይቃጠልም የእድሜ ሸክም እየጎዳው መንገዳገዱ አልቀረም:: ስለዚህ ጥገና እድሳት ያስፈልገው ነበርና በ1940-41 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መንግሥትና የብሪትሽ ካውንስል ገንዘብ አዋጥተው ከላይ የተጠቀሰው ማቲው የሚባል እንግሊዛዊ አድሶታል:: የዚህ ገዳም መሥራች አቡነ አረጋዊ በሐዋርያዊ ተግባራቸው እስከ ጎንደር ድረስ ወርደው አስተምረዋል:: አቡነ አረጋዊ ሳይሞቱ በሕይወት የተሠወሩ ናቸው:: በዓላቸውም ጥቅምት 14 ቀን በታላቅ ድምቀት ይከበራል:: በዓሉ የሚከበረው ወደ አቡነ አረጋዊ ገዳም ሴቶች መግባት ስለማይፈቀድ የበዓሉ ዕለት ሴቶች በሴቶች ገዳም፣ ወንዶች በወንዶች ገዳም ሆነው በዓሉን ያከብራሉ::

ክርስቲያናችን ላይ ሲያነድ የነበረው ግራኝ በዘመኑ የነበሩትን ንጉሥ አፄ ልብነ ድንግልን ሲያሳድድ ንጉሠ ነገሥቱ ከእነቤተሰቦቻቸው የሸሹት ወደ ደብረ ዳሞ ነበር:: ግራኝ ወደዚህ ከፍተኛ አምባ መውጣት ስላልቻለ አብዛኛዎች ገዳማት ሲቃጠሉ ይህ ሊተርፍ ችሏል:: ንጉሡም በዚህ ሲኖሩ ሞተው በገዳሙ ተቀብረዋል፤ ልጃቸው ገላውዴዎስ ደግሞ ነግሠውበታል:: [የግራኝ መሐመድ ወረራ ገፅ 576-579::]

[11] አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቀጥር 10 ገፅ 191-95::



www.ethiopianorthodox.org

# አቡነ ጰንጠሌዎን ገዳም

የአቡነ ጰንጠልዮን የሕይወት ታሪካቸውን የሚናገረው ገድላቸው ነው:: አባታቸው የሮም ሦስተኛ ሹም የነበረ ታላቅ ሰው ነው ካለ በኋላ እናታቸውን አይናገርም:: ቢሆንም የጰንጠልዮን አስተዳደግ እንደነብዩ ሳሙኤል በቤተ መቅደስ ነበር:: አቡነ ጰንጠልዮን፣ከሕፃንነታቸው ጀምሮ በጸሎት፣ በምፅዋት ነዳያንን በመርዳት ጸሎት በማዘውተር በቤተ እግዚአብሔር አደጉ:: አቡነ ጰንጠልዮን ከአገራቸው ወጥተው ከአባ እንጦንስ ገዳም ገብተው ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጽመዋል:: በዚሁ ገዳም ብዙ አበው ቅዱሳንን በመርዳት አገልግለዋል:: ከዚህ በኋላ እጣቸው ኢትዮጵያ መሆኗን መልአከ እግዚአብሔር ገለጠላቸው:: በእግዚአብሔር ኃይል ተረድተው ኢትዮጵያ ገብተዋል::

ለመጀመሪያ ጊዜ አክሱም ጽዮን ደርሰው ዳግማዊ አልአሜዳ በክብር ተቀበላቸው:: ለጥቂት ጊዜ በቤተ መንግሥት አካባቢ ቤተ ቀጢን በተባለው የእንግዶች ማረፊያ ቦታ እረፍት አድርገዋል:: ዛሬ ቤተ ጰንጠሌዎን ተብሎ ወደሚጠራው ከአክሱም አጠገብ 3 ኪ.ሜ. ርቀት ባለው ቦታ ገብተው በገድል በትሩፋት በጸሎት በስግደት እግዚአብሔርን አገልግለዋል:: የመንፈስ ቅዱስ ጓደኛቸው:: አባ ሊቃኖስ ይጸልዩበት የነበረው ቦታ 1 ኪ.ሜ. ርቀት ስለ ነበረው አቡነ ሊቃኖስ ከአቡነ ጰንጠልዮን ቀድመው ቆናፅል በተባለው በአታቸው ላይ አርፈዋል:: አቡነ ጰንጠልዮንም ከመንፈስ ቅዱስ ወንድማቸው በመለየት ቢያዝኑም በዚያው በሚጸልዩበት ቦታ ቀብረዋቸዋል:: የእረፍታቸው ዕለት ኅዳር 28 ነው ሲል ገድላቸው ይናገራል:: ያ ገዳም እስከ ዛሬ ድረስ ቤተ ክርስቲያኑ ይፍረስ እንጂ ደብረ ቆናፅል ተብሎ ይጠራል::

ከዚህ በኋላ አቡነ ጰንጠልዮን አቡነ ሊቃኖስን ከቀበሩ በኋላ ዛሬ ቤተ ጰንጠልዮን ከተባለው ተራራ ወጥተው ገብተዋል:: ተራራዋ ምድረ በዳ ነበረች:: ከዚህች ተራራ ላይ በራስጌዋ አንዲት ደንጊያ አስፈልፍለው በዚህች ገብተው ብዙ ዘመናትን አሳልፈዋል:: የአቡነ ጰንጠልዮን የድንጋይ ዋሻ ወርዱና ቁመቱ እንደሚከተለው ነው:: ወርዷ 5 ክንድ፣ ግድሟ 2 ክንድ፣ ስፋቷ 3 ክንድ ዋሻ ስትሆን ይቺ ዋሻ ደጃፍ መስኮት የሌላት ድፍን ናት:: ለመግቢያ ያህል ነው በር ያላት:: በዚህች ዋሻ ያለእረፍት በጸሎትና በስግደት 45 ዓመት ቆይተዋል:: ይህች ቦታ ደብረ ፆማዕት በመባል ትታወቃለች:: ፆማዕት ማለት እጅግ በጣም አስጨናቂ፣ አስቸጋሪ የጸሎት ጉድጓድ ዋሻ ማለት ነው::





## ዐፄ ካሌብ ወደ የመን ለመዝመት አቡነ ጰንጠሌዎንን የጸሎት እርዳታ መጠየቁ

የናግራን ክርስቲያኖችን ለመታደግ ጢሞቴዎስ 3ኛ የተባለ በ519 ዓ.ም የነበረ የእስክንድርያ ፓትርያርክ አብያተ ክርስቲያናት ሲቃጠሉ ክርስቲያኖች ሲሰደዱ ለምን ዝም ትላለህ በማለት ለሀፄ ካሌብ መልእክት ላከ:: ጨካኙ ዱኖባስ በዚህ በየመን ናግራን ጉድጓድ አስቆፍሮ እሳት እያስነደደ ክርስትናን አንክድም ያሉትን ክርስቲያኖች ሁሉ ወደዚህ እየጨመረ አቃጠላቸው፣ አስፈጃቸው:: በዚህ ቀን 20 ሺ ክርስቲያኖች ተፈጁ:: በዚህን ጊዜ በቁስጥንጥንያ ዙፋን ዮስጢኖስ ነግሦ ነበርና የዚህን ወሬ ሲሰማ በጣም አዘነ:: ስለዚህ ጉዳይ ለእስክንድርያው ፓትርያርክ ለጢሞቴዎስ መልእክት ጻፈ:: ሊቀ ጳጳሱም ወደ አክሱም ንጉሥ ደብዳቤ ጻፍለት ብሎ መከረው:: ከዚህ በኋላ ኖኖስ የተባለውን ዋና መልእክተኛ አድርጐ ደብዳቤ አስይዞ ወደ አክሱም ላከው::

የአክሱም ንጉሥ ካሌብ በወርቅ ሠረገላው ላይ የመዓረግ ልብሱን ለብሶ በጦር አለቆችና መኳንንት ታጅቦ እንደተቀመጠ መልእክተኞችን ተቀብሎ አነጋገራቸው:: ደብዳቤው ከተነበበ በኋላ መልእክተኞችን በፍቅርና በሽልማት አስናበተ:: ንጉሡም ይህን ከሰማ በኋላ በቀጥታ አቡነ ጰንጠልዮን ወዳሉበት ዋሻ በመሄድ ነገሩን ገልጸ ነገራቸው:: አቡነ ጰንጠልዮንም የአገረ ናግራን ክርስቲያኖች እልቂት ስላሳዘናቸው ወደ እግዚአብሔር አመልክተው አይዞህ አትፍራ ድል ታደርጋለህ በማለት ነገሩት:: እርሱም ጉዞውን ወደ የመን



www.ethiopianorthodox.org

አደረገ፤ ሀፄ ካሌብ ወደ የመን ሲዘምት ቁጥሩ 70 ሺ የሚደርስ ጦሩን በደንብ አደራጅቶ በ524 ዓ.ም. ወደ የመን ተጓዘ፤ እዚያ እንደደረሰ 3 ሺ ጦር ይዞ የአይሁድ ጦር ከመርከብ ሲወርድ ተዋጋው:: የካሌብ ጦር ወዲያው አሸንፎ በታተናቸው:: ወደ የመን ተጠግቶ ከተማዋን ያዘ፤ የንጉሡም ባለቤት በዚህን ጊዜ ተማረከች:: ከራሱ ከፊንሐስ ጋር ተዋግቶ ከፈረሱ ላይ ገለበጠውና ሞተ:: በከተማው ያሉትን ለክርስቲያኖች አልቂት ደም መፍሰስ ተባባሪ የነበሩትን አስይዞ ጨረሳቸው::

በአገረ ናግራን የተፈጁትን ምዕመናን (ክርስቲያኖች) ደም በሚገባ ተበቀለ:: ክርስቲያኖችም በየስፍራው ተመለሱ:: ካሌብ ወደ እስክንድርያው ጳጳስ የድል አድራጊነቱን ደብዳቤ ገለፁ:: ሊቀ ጳጳሱም ወደ ቁስጥንጥንያው ንጉሥ መልዕክቱን ልኮ በሁሉም ዘንድ ታላቅ ደስታ ሆነ:: ካሌብም ሹም ሾሞ ወደ አክሱም ተመለሰ::[12] ጸሎቱን የሰማውና ይህን ድል አድራጊነት የሰጠውን አምላኩን ለማስደሰት [አስቀድሞ የተሳለውን በሥራ ለመግለፅ] የነገሠበትን ዘውዱን ጌታችን መቃብር በራፍ ላይ እንዲሰቀልለት ለኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ ልኮ፣ የተደላደለ መንግሥቱን ትቶ፣ ይህን ዓለም ንቆ አባ ጳንጠልዮን ገዳም አጠገብ በአንዲት ዋሻ አንዲት ሰሌን ለመኝታው፤ አንዲት ውሀ መጠጫ ቅል ብቻ ይዞ ገብቶ ተቀመጠ:: በዚያም በጸሎት በስግደት ኖሮ በግንቦት 20 ቀን አረፈ:: ሀፄ ካሌብ በሕይወት ዘመኑ ያሠራው መካነ መቃብር ከአክሱም ሐውልት በስተምሥራቅ 2 ኪ.ሜ. ያህል ተጉዞ በሚገኝ አፋፍ ላይ የሚገኝ ሲሆን ይህ መካነ መቃብር ተቆፍሮ የወጣው በ1898 ዓ.ም. ኢኖ ሊትማን በተባለ ጀርመናዊ አርኪዎሎጂስት አማካኝነት ነው::

ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ 44 አብያተ ክርስቲያናትን አሠርቶ ልጁን ገብረ መስቀልን አንግሦ በአቡነ ጳንጠልዮን እጅ መንኩሷል:: መቃብሩም በአቡነ ጳንጠልዮን ቤተ ክርስቲያን ይገኛል:: ሀፄ ካሌብ ከዚህ ዓለም እስከተለየበት ድረስ

[12] የኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም እስከ ዛጉዬ ገፅ 275::





ለዚህ ዓለምና መንግሥት ጓጉቶ አንድም ቀን አለመመለሱን ስናስብ ቆራጥ ንጉሠ ነገሥት መናኒ መሆኑን ያስገነዝበናል:: ከአረብ አገር (ከየመን) ተመልሶ በምናኔ የኖረበት ዘመን 12 ዓመት ሲሆን፤ እድሜው 70 ዓመት ነበር:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እንደ ፃድቅ ቆጥራ ታከብረዋለች:: ከእኛ ሌላ ምዕራባውያን (የካቶሊክ ቤተክርስቲያን) በጥቅምት (October) 27 አከብራለሁ ትላለች::

ይህ አስተሳሰብ ከሌላ የመነጨ ከሆነ ዐፄ ካሌብን የሚያከብሩት ስህተት ነው:: ምክንያቱም ንጉሥ ካሌብ አክሊሉን የላከው የሁሉ የበላይ ነን ወደሚሉ ሮማውያን ሳይሆን «ወደ ቅድስት አገር ኢየሩሳሌም ነው» ካሌብ በየመን ያሉ ክርስቲያኖችን መታደግ ብቻ ሳይሆን በአረብ አገር ሊጠፋ የነበረውን የክርስትና እምነት መልሶ አቃናው:: በቃል ኪዳን ጓደኝነት ተባብረው በነበሩት በአይሁድና በፋርስ ሕዝብ መካከል አደጋ ጥሎ ግዛታቸውን ክብራቸውን አስወግዶ የራሱንና የኢትዮጵያን ክብርና ግዛት ተካበት:: የመን በአረቦች በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ ተወረረችበት ጊዜ የኢትዮጵያ ነበረች:: ከዚህ በኋላ ግን በፋርሶች ተወርራ የመሀመድን እምነት የተከተሉ አረቦች ምን የመሳሰለውን የሰንአ አብያተ ክርስቲያናትን አፈራረሱት::

## የአቡነ ጳንጠልዮን ገዳም ይዞታና ገድላቸው

አቡነ ጳንጠልዮን ከንጉሥ ካሌብ ጋር 1 ሺ 500 ሰዎችን አመንኩሰዋል:: የአቡነ ጳንጠልዮን ገድል ስለ ነገሥታቱ ይናገራል:: ኢትዮጵያ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ሲናገር ይመጣና በመካከል የዲዮቅልጢያኖስና የቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት፣ ዘመነ ሰማዕታት ከቆጠረ በኋላ የኢትዮጵያ እምነትን በሰፊው ያስረዳል:: የተሰአቱ ቅዱሳንን ከንዋየ ቅድሳት ጋር ወደዚህ መግባታቸውን ይገልጻል:: በሕይወት ሳሉ ብዙዎችን በሽተኞች ፈውሰዋል:: መስቀላቸውና መቋሚያቸው በዚሁ መቃብር ቦታቸው ቤተ ጳንጠልዮን ይገኛል:: የአቡነ ጳንጠልዮን ገድል ዋናው የሚገኘው በጣሊያን አገር ሲሆን



www.ethiopianorthodox.org

አሁን እዚህ ያለው ከድጓና ከስንክሳር ተወጣጥቶ የተዘጋጀ እንደሆነ ይነገራል።

## የቤተክርስቲያኑ አመሠራረት

ቦታው ላይ ማይጨው ይባላል። በአክሱም ጽዮን ወረዳ ነው። ምልክት ግዛቱጂ ያው ገዳሙ ሲሆን የገዳሙ ስም ቤተ ጰንጠልዮን ይባላል። በአጠገቡ ደብረ ቆናፅል የአቡነ ሊቃኖስ መቃብርና መካየዳ እግዚእ ይገኛል። የሚያስተዳድረውም የገዳሙ መምህር ነው። ገዳሙ የአንድነት ገዳም ሳይሆን የቁሪት ገዳም ነው። መነኮሳትም በብዛት አይገኙበትም። የነገሥታቱና የጳጳሳቱ እረፍት ይታሰብበታል። ዝርዝራቸው:-

| | |
|---|---|
| ♦ የአቡነ ጰንጠልዮን | ጥቅምት 6 |
| ♦ ዐፄ ካሌብ | ግንቦት 20 |
| ♦ ዐፄ ገብረ መስቀል | ኅዳር 30 |
| ♦ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ | ጳጉሜ 3 |
| ♦ ዐፄ ናዖድ | ነሐሴ 7 |
| ♦ ዐፄ በእደ ማርያም | ኅዳር 11 |
| ♦ ከጳጳሳት አቡነ ዮሳብና አቡነ ዮሴፍ ናቸው። | |

የቤተ ክርስቲያኑ አቀማመጥ ከአክሱም ጽዮን በስተ ምሥራቅ ሲሆን፣ ከታቹ የቅዱሳኑና የነገሥታቱ (የዐፄ ካሌብ፣ ዐፄ ገ/መስቀል) መቃብር ሆኖ በላዩ ላይ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶበታል። የቅዱሳኑ መግቢያ በር ላይ በመቅደሱ እንደ እርከን የተሠራውን እየረገጡ ወርዶ በመቃብር ደጃፍ ስማቸው ይገኛል። ቄሱ ሁል ጊዜ ያጥነዋል። የሚገባውም በመብራት እንጂ ያለ መብራት መግባት አይቻልም። ቤተ ክርስቲያኑ የተመሠረተው በዐፄ ገ/መስቀል ዘመነ መንግሥት ሲሆን እርሱ ራሱ ከዚሁ መቅደስ ተቀብሯል። አቀማመጡ የአቡነ ጰንጠልዮን ከታች ሆኖ ሁለቱ እንደ የዘመናቸው ተቀብረዋል። መቃብራቸው ይህ በመሆኑ ለመረዳት ሙት ዓመታቸው በዓመት በዓመት የሚፈፀመው በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ስለሆነ የመሬቱ ሥሪት ከዚሁ ገዳም አካባቢ ስለሚገኝ ይህ ገዳም ከሁሉ ቅድሚያ አለው።





## በገዳሙ ውስጥ ያሉ ጥንታውያን መጻሕፍት

- 🕮 ቅዱስ ወንጌል ዐፄ ገ/መስቀል የሰጡት፤
- 🕮 መጽሐፈ ነገሥት ጥንታዊ፤
- 🕮 ምሳሌያተ ሰሎሞን የጥንት ብራና፤
- 🕮 ሁለት ወንጌል ጥንታውያን፤
- 🕮 4 ቅዳሴ ጥንታውያን፤
- 🕮 አምስት ዳዊቶች ጥንታውያን፤
- 🕮 መጽሐፈ ሐዲሳት፤
- 🕮 የዓመት ስንክሳር ጥንታዊ፤
- 🕮 8 ተአምረ ማርያም፤
- 🕮 ሁለት ተአምረ ኢየሱስ ጥንታዊ፤
- 🕮 አራት ግንዘቶች ጥንታዊ፤
- 🕮 አራት ድርሳነ ሚካኤል ጥንታዊ፤
- 🕮 ገድለ አቡነ ጰንጠልዮን፣ የአቡነ አረጋዊ ገድል በአንድ ላይ፤
- 🕮 ሁለት ሃይማኖተ አበው ጥንታዊ፤
- 🕮 መጽሐፈ ቄርሎስ፤
- 🕮 ገድለ አቡነ ኪሮስ፤
- 🕮 ገድለ አቡነ ገሪማ ጥንታዊ፤
- 🕮 ገድለ መድኃኒነ እግዚእ፤
- 🕮 ድጓና ዝማሬ መዋስዕት ጥንታዊ፤
- 🕮 ግብረ ሕማማት ጥንታዊ፤
- 🕮 አርኬ ጥንታዊ፤

በተጨማሪ ቀዋሚ መስቀል ዐፄ ገ/መስቀል የሰጡት እና በዐፄ ገ/መስቀል ዘመነ መንግሥት የተቀረፀ መስቀል የሠጪው ስም አባ ፀንሎ ይባላል። ስሙ በመስቀሉ ላይ ይገኛል። ሌሎች በርካታ ነዋየ ቅድሳት በአቡነ ጰንጠልዮን ገዳም ይገኛል።[13] የጻድቁም ገድል በፓሪስ ታትሟል።[14]

---

[13] ኮንቲ ሮሲኒ (CONTI ROSSINI) ያሳተመውን ገድለ ጰንጠልዮንን (ACTAS PANTALEON) መረጃ በማቅረብ ዶ/ር ሥርግው ጠቅሰዋል። አማርኛ የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት ገፅ 21-29፤ ትንሣኤ 1972 ቁጥር 74።

[14] መርሐ ልቡና ገፅ 77።



www.ethiopianorthodox.org

## አባ ይምአታ ገዳም

አቡነ ይምአታ በተለይ ብዙ የቆዩበት በትግራይ ውስጥ ገርአልታ በሚገኘው ልዩ ስሙ ጐሕ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው። የአካባቢው አሰያየም ከእኝህ ጻድቅ አባት ታሪክ ጋር የተገናኘ በመሆኑ ይነገራል። አቡነ ይምአታ ከአክሱም ተነስተው «አብ ጎሕ፤ ወልድ ጎሕ፤ መንፈስ ቅዱስ ጎሕ»፤ ብለው ቅኝሴ ማርያምን እየዜሙ ከዛሬው የጎሕ መንደር ነጋባቸው። ብዚህ የተነሳ የመንደራቸውን ስም «ይኩን ስምኪ መካነ ጎሕ» ብለው ሰየሚት።

የአቡነ ይምአታ ቤተ ክርስቲያን ከሐውዜን 13 ኪ.ሜ. በመኪና ከተጓዙ በኋላ የግማሽ ሰዓት መንገድ ተጉዞ የሚገኝ ነው። ቤተ ክርስቲያኑ ሰማይን እንደ ምሰሶ ደግፈው የቆሙ ከሚመስሉት ረጃጅም የገርአልታ ተራራዎች ውስጥ የሚገኝ ሲሆን አጠገቡ ካልደረሱ የማይታይ የቀደሙት አበው ድንቅ የመንፈሳዊነትንና የብርቱነት ውጤት ነው። ይህ ከባሕር ወለል በላይ 2 ሺ ሁለት መቶ ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኘውን የአለት ተራራ መውጣት አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ለመወጣጫ የእጅ መያጠጫ፣ ለእግር መቆንጠጫ የሚያገለግሉ ጉድጓዶች ብቻ ያሉት ከ240ጠ 300 ሜትር ርዝመት ያለው ገደል ቁልቁል ሲመለከቱት እጅግ የሚያስደነግጥና የሚያስፈራ ነው። ይህ ቤተ ክርስቲያን በተራራዎች ጉያ የተሸጐጠ በመሆኑ በፊት በዮዲት በኋላ ከግራኝ ጥፋት ሊያመልጥ ችሏል። ይህን ቤተ ክርስቲያን ልዩ ከሚያደርጉት አንዱ የሆነው ደግሞ የበርካታ ሰዎች አፅም የተቀበረበት ከአለት ተፈልፍሎ የተሠራ የመቃብር ሥፍራ መኖሩ ነው።

ቤተ ክርስቲያኑ ከአለት ተፈልፍሎ የተሠራ ሲሆን ከውስጥ ራሳቸውን ችለው የቆሙ አራት አምዶች አሉት። ጠቅላላ ሥፋቱ ስድስት በ9 ሜትር ከወለል ወደ ጣሪያ ያለው ከፍታ ደግሞ 3 ሜትር ነው። ቤተ ክርስቲያኑ ድንቅና ልዩ እንዲሆን ያደረገው ከድንጋይ ተፈልፍሎ መሠራቱ ብቻ ሳይሆን በውስጡ ያሉት ቅዱሳት ሥዕሎች ናቸው።





በቅኔ ማህሌቱ ጣሪያና ግድግዳ የሚታዩት ደማቅ ሥዕሎች ተከታታይ ታሪክ የያዙ ናቸው። የአቤል፣ የኖህ፣ የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ ሥዕሎች ደምቀው ይታያሉ። በተጨማሪ የ9ኙ ቅዱሳን ሥዕል ይታያል። ሦስቱ መስቀል፣ 5ቱ መጻሕፍት እንደያዙ ሲሆን አንደኛው ግን ባዶ እጃቸውን ናቸው። አቡነ ይምአታ በፈረሳቸው ላይ ተቀምጠው እና አቡነ አሮን፣ አቡነ ማትያስ፣ የአቡነ ብንያም የ12ቱ ሐዋርያት ሥዕሎች የቤተ ክርስቲያኑ የዘመናት ጌጦች ናቸው። ሥዕሎቹ በጣም ደማቅ በመሆናቸው ብዙ ክፍለ ዘመናትን አልፈው የመጡ ድንቅ ቅርሶች አይመስሉም። የአቡነ ይምአታ ቤተ ክርስቲያን በአገራችንና በዓለም ደረጃ ካሳወቁት የውቅር ዓለት አብያተ ክርስቲያናት እንደ አንዱ መሆኑ የክልል 1 ቱሪዝም ቢሮ ይገልፃል።

## አባ ገሪማ ገዳም

የቀድሞ ስማቸው ይስሐቅ ሲባል ገሪማ የሚለው ኢትዮጵያ ከመጡ በኋላ የወጣላቸው ስም ነው። ይህ ስም የቀድሞውን ሸፍኖት ይገኛል። ስሙ የወጣላቸው ምክንያት «እግዚአብሔር በእሳቸው አማካኝነት ገቢረ ተአምራት ስለገለፀ ነው» አስደነቀኝ ገረመኝ ለማለት ነው። አቡነ ገሪማ ትውልዳቸው ከቤተ መንግሥት ወገን ነበሩ። ይህን ዓለም ንቀው ገዳም ገቡ። ከዚያም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከ8ቱ ቅዱሳን ጋር ተቀላቀሉ። እንደሌሎቹ ሁሉ እርሳቸውም ቅድመ ዝግጅት አድርገዋል። አክሱም ተቀምጠው የአገሩን ቋንቋና ባሕል አጥንተዋል። ከዚያ በኋላ ለስብከተ ወንጌል ከአክሱም በስተምሥራቅ ተሰማርተዋል። ለእርሳቸው የደረሳቸው ሥፍራ መደራ የሚባል ከአድዋ በስተምሥራቅ በግምት 10 ኪ.ሜ የሚርቅ ነው።

በማሠረቱ ተሰአቱ ቅዱሳን የተሰማሩት የጣኦት አምልኮ ከተንሰራፋባቸው ቦታዎች ነበር። በዚህም ላይ ስሙ ራሱ «መደራ» የሚባለው የደቡብ አረብ የቦታ ስም ነው። አንድ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ከደቡብ አረብ ፈልሰው የመጡ ሰዎች የቦታቸውን ስም አምጥተው ስፍራውን ሰይመውታል ማለት



www.ethiopianorthodox.org

ነው:: ከዚሁ ጋር የምንረዳው ነገር ቢኖር እነዚህ ሰዎች ያመጡት የአገራቸውን ስም ብቻ ሳይሆን አምልኮታቸውንም ጭምር ነበር:: በዚህ ዓይነት እዚህኛው መደራ የደቡብ አረብ አማልእክት የሚመለክበት ቤተ መቅደስ ተቋቁሞ አምልኮቱ እየተስፋፋ እስከ 6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደርሷል:: አቡነ ገሪማ ከሥፍራው ከደረሱ በኋላ ነገሮችን ለውጠዋል:: ቦታውንም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሰዎችንም ክርስትና እንዲቀበሉ አድርገዋል:: መደራ አባ ገሪማ ገዳም እስከ አሁን በኢትዮጵያ ከታወቁት አርባዕቱ ወንጌላት ይገኛል:: የገዳሙ መነኮሳት እንደሚሉት አቡነ ገሪማ በእጃቸው የጻፉት ነው ይላሉ:: የዚህ ጥንታዊ መጽሐፍ እዚያ መገኘት ትልቅ ክብር ነው::[15]

## አባ ጽሕማ ገዳም

አገራቸው አንጾኪያ ሲሆን ወደ እንጦንስ ገዳም ሔደው ሥርዓተ ምንኩስናን ፈፅመዋል:: ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር እጣቸውን ገልጾ በራዕይ አሳያቸው ወዲያው በመልአከ እግዚአብሔር ተመርተው አክሱም ቤተ ክርስቲያን ደርሰዋል:: ዳግማዊ አልአሜዳ ተቀብሎ በቤተ መንግሥቱ አጠገብ ቤተ ቀጢን በተባለው ቦታ አስቀመጣቸው፤ ከሁሉ ሽማግሌ አባ ፅህማ ስለነበሩ አቡነ ዘበስማያት የሚሰጡት የሚያሳርጉ እርሳቸው ናቸው:: 9ኙ ቅዱሳን ወደ እጣ ክፍላቸው ለወንጌል ሲሄዱ አባ ፅህማ የደረሳቸው ፅንብል ነበር:: ይህ ገዳም አውራጃው አድዋ ወረዳው ድንበላ አባ ጽህማ ሲሆን ግዛቱ የገዳሙ ነው:: አባ ፅህማ ይህቺን ገዳም ደብረ ሐተታ ብለው ጠርተዋታል:: አባ ፅህማ ብዙ ዘመን ተጋድሎ ካደጉ በኋላ በዚች በደብረ ሐተታ ገዳማቸው ልዩ ልዩ ተአምራትን አድርገዋል::

እረፍታቸው ጥር 16 ቀን ነው:: በሰአት በሰአት በጸሎት በስግደት ሲኖሩ ዕለተ ሞታቸውን ከእግዚአብሔር የተላከ መልአክ ይነግራቸው ነበር:: መቃብራቸው በዚህ በደብረ ሐተታ ነው:: ቤተ ክርስቲያኑ ከመቃብራቸው በላይ ተመስ

[15] አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁጥር 11 ገፅ 140::





ርቶ ተሠርቷል:: አባ ፅህማ ይጸልዩበት የነበረው ወይራቸው ዛሬም እንዳሉ ይገኛሉ:: ወደ ቤተ ክርስቲያኑ መድረሻ ላይ የፃድቁ የአባ ፅህማ የእግር ጫማቸው ልክ የረገጡት የደንጊያ ላይ ቅርፅ ትገኛለች:: ከተራራ ላይ ሆነው ሲመለከቱት መላው ትግራይ ይታያል:: አባ ጽህማ የባረኩት ፀበል «ማይ ጻሎት» ተብሎ ይጠራል::

የቦታው አቀማመጥ ክብ ተራራና ሜዳ የከበበው ነው:: ርዝመቱ በጣም ትልቅ ነው:: ከባህታውያን በቀር ሌላ ሰው አይቀመጥበትም ከዚህ አካባቢ የወይራ ዛፎች በብዛት ይገኛሉ:: እነዚህ ወይራ ጥንታውያን ናቸው:: ፍሬያቸውን ለቅመው ለመቁጠሪያ ይሰሩታል:: የአገሬው ህዝብና መነኮሳቱ እነዚህን ወይራዎች በክብር ይጠብቋቸዋል:: ጻድቁ አላንድያ የሚባል እንጨት በጸሎታቸው አብቅለዋል:: ቁመቱ 6 ሜትር ነው:: በዚሁ ተራራ በጥግ በጥጉ ብዙ መነኮሳት የሚኖሩበት ዋሻ አሉ:: ከዋሻው ውስጥ አንዳንድ መነኮሳት አሉበት:: ፃድቁ ይፀልዩበት የነበረው ዋሻ በምሥራቅ በኩል ይገኛል:: በአካባቢው የሚገኙ ሕዝቡና መነኮሳቱ ይህን ዋሻ በክብር ይጠብቁታል:: ቤተ ክርስቲያኑ የተተከለው በዐፄ ገ/መስቀል ዘመን ሲሆን፤ የተገደመውም በዚሁ ዘመን ነው:: ገዳሙ የአንድነት ገዳም ነው:: በዚሁ ገዳም ብዙ የዘጉ መነኮሳት ይገኛሉ:: አሁንም ይህ ገዳም በዚሁ ፀንቶ ይገኛል::

በገዳሙ ውስጥ አያሌ ነዋየ ቅድሳት ይገኛሉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ራስ ወልደ ሥላሴ የሰጡት፤ መጽሐፍ አሪት ጥንታዊ፣ መጽሐፈ ኢዮብ፣ መጽሐፈ ሰሎሞን፣ መጽሐፈ ቄርሎስ፣ መጽሐፈ ማር ይስሐቅ፣ አረጋዊ መንፈሳዊ መጽሐፈ ስንክሳር ራስ ወ/ሚካኤል የሰጡት እና አባ ፅህማ ከአገራቸው ያመጡት ጽንሐሕ፣ መስቀላቸው፣ መቋሚያቸው ዛሬም ይገኛሉ::[16]

[16] ዝኒ ከማሁ ገፅ 99::



www.ethiopianorthodox.org

# አቡነ አፍጼ ገዳም

በገድላቸው መሠረት የትውልድ አገራቸው እስያ ሲሆን አባታቸው አቡድራስ እናታቸው አቅሌስያ ይባላሉ:: ወላጆቻቸው ክርስቲያን በመሆናቸው ክርስትና ተነስተዋል:: በ15 ዓመታቸው ዲቁና ተቀበሉ:: ወዲያውኑ ወደ ግብፅ ሔደው ገዳመ አስቄጥስ ገብተው ሥርዓተ ምንኩስና ተደርሶላቸው መንኩሰዋል:: ከዚያም ከ7 ሌሎች መነኮሳት ጋር ሆነው መጻሕፍትንና ንዋየ ቅድሳትን ይዘው ከብዙ ደቀ መዛሙርቶቻቸው ጋር ሆነው ወደ ኢትዮጵያ መጡ::

አክሱም በነበሩበት ጊዜ የኢትዮጵያን ቋንቋን ባሕል አጠኑ:: የሚያስፈልገውን ዝግጅት ካደረጉ በኋላ ስብከተ አገራቸውን ተከፋፍለው ተሰማሩ:: ለአቡነ አፍጼ የደረሰው የታወቀው ጥንታዊው ከተማ የሓ ነበር:: እዚህ ከተማ ጵልሙካ በሚመለክበት የቆየ ምን አልባት በ6ኛው ዓመተ ዓለም ከክርስቶስ ልደት በፊት የታነፀ ቤተ ጣኦት ይገኝበታል:: ይህ ሕንፃ አሠራሩ አራት ማዕዘን ሆኖ አቅጣጫው ወደ ምሥራቅ ስለሆነ መግቢያው አንድ በር በምዕራብ በኩል አለው:: ምንም እንኳ ሕንፃው ከዕድሜ ብዛት በአንዳንድ ሥፍራ ፈርሶ ቢታይም በጠቅላላው በደህና ሁኔታ ላይ ነው ያለው ለማለት ይቻላል:: ስለ ዘመኑ ሕንፃ ሥራ አንድ ዓይነት ሃሳብ ይሰጠናል:: ከበሩ በስተቀር መስኮቶች የሉትም:: ይህም የጥንት ቤተ ጣኦት ጨለምለም ማለቱን ይመርጣሉ:: ምክንያቱም ፍርሃትና አክብሮትን በአማንያኑ ላይ ለማሳደር ሳይሆን አይቀርም::

የዚህ ከተማ ነዋሪዎች አቡነ አፍጼ እስከሄዱበት ጊዜ ድረስ በአምልኮ ጣኦት የተጠመዱ ነበሩ:: እሳቸው እዚያ ከደረሱ በኋላ ግን ሁኔታው ተለውጧል:: ነዋሪውን አሳምነው አስተምረው አጥምቀዋል:: የጣኦት መመለኪያ የነበረውንም ቤተ ጣኦት ወደ ቤተ ክርስቲያን ለውጠው የእመቤታችንን ጽላት አስገብተው ደብረ ሐመልማል ተባለ::[17]

[17] በዚህ ቦታ አስቀድሞ የጣኦት ማምለኪያ የነበረ መሆኑንና ወደ ቤተ ክርስቲያን መለወጡን የሚያመለክቱ ብዙ ማስረጃዎች ተገኝተዋል:: ቤተ ጣኦት ለመሆኑ ጌጣጌጦች፣ አልማዝ ከእንቁእ የተሠሩ በአንድ ሳጥን ተከማችተው ሲገኙ፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመለወጣቸው ደግሞ መስቀል ጽንሐሕ፣ ቃጭል ተገኝተዋል:: የፃድቁ ገድል እነዚህን ሁሉ የሚደግፍ ነው::





ይህ ሥያሜ እንዴት እንደተሰጠ ገድሉ ሲያብራራ በአካባቢው ውሃ አልነበረምና አቡነ አፍጼ በእጅ መስቀላቸው ባርከው ውሃ አፈለቁ:: ሥፍራውም በልምላሜ ተዋጠ ከዚያም በኋላ ደብረ ሐመልማል ተባለ ይላል:: አቡነ አፍጼ ያፈለቁት ውሃ ከገዳማቸው አጠገብ ነው:: ከእርሳቸው በፊት የተመሠረተ ጥንታዊ ከተማ ያለ ውሃ ኖረ ለማለት አይደለም:: የዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ከተሞች ሲመሠረቱ ሦስት አስፈላጊ መስፈርቶች መሟላት ነበረባቸው::

1. በአንድ በኩል ተራራ ወይም ከፍተኛ ቦታ ከተማውን ለመጠበቅ፤
2. በሌላ በኩል የተንጣለለ ሜዳ ለእርሻ ለገበያ የሚያገለግል፤
3. ውሃ ያለበት ሥፍራ ለሕይወታቸው ስለሚያስፈልግ::

እነዚህን መስፈርቶች የሓ አሟልቶ ነው ከተማ የሆነው፤ ተራራ በስተሰሜን በኩል አለው፤ ሜዳም በስተ ምሥራቅ በኩል ተንጣሏል፤ የውሃ ምንጭም አሉት:: እዚህ ቦታ አቡነ አፍጼ ገዳም መሥርተው የአንድነት ማኅበር እንዳቋቋሙ ገድላቸው ይናገራል:: ይህንን ገዳም ንጉሡ ዐፄ ገብረ መስቀል መጥቶ ጐብኝቶ መተዳደሪያ ርስት ጉልት ሰጥቷል:: ከዚህ የሚገኘውን አበል ሲሰው የመነኮሳት ምግብ ይሁን ብለው ንጉሡና ጳጳሱ ስለፈቀዱ ይህም በግዝት ፀንቷል:: አቡነ አፍጼ ሕዝቡን እያስተማሩ ሥርዓተ ምንኩስናን እያጠናከሩ ለብዙ ዓመታት ከኖሩ በኋላ በእርጅና እድሜአቸው በዐፄ ገ/መስቀል ዘመነ መንግሥት አርፈው እዚያው የሓ ተቀብረዋል:: ከሞታቸው በኋላም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ አድርጋቸዋለች፤ ለክብረ በዓላቸው ተስማሚ የሆነ ቀለም ቅዱስ ያሬድ ሠርቶላቸዋል፤ እስመለዓለም አንገርጋሪ፣ ዚቅ ደርሶላቸዋል፤ የእኚህ ጻድቅ ገድል በብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት የሚገኝ የኢትዮጵያ ቅርስ ነው::[18]

[18] አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁጥር 6 ገፅ 170::



www.ethiopianorthodox.org

## አባ ሊቃኖስ ገዳም

አባ ሊቃኖስ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ አክሱም ከቆዩ በኋላ ለስብከት በየእጣ ክፍላቸው ሲሰማሩ አቡነ ጰንጠልዮንና አቡነ ሊቃኖስ ርቀው እንዳይሄዱ ሕዝቡ ስለተማፀናቸው ከከተማው ሳይርቁ 5 ምዕራፍ እርቀው ገዳማቸውን መሠቱ አቡነ ሊቃኖስ ከአክሱም በስተሰሜን ከሚገኘው ደብረ ቆናፅል ከሚባለው ኮረብታ መቀመጫቸውን አድርገው የከተማውን ሕዝብ እያስተማሩ ለ21 ዓመታት ቆይተዋል::[19]

የአባ ሊቃኖስ ገዳም ደብረ ቆናፅል በመባል ይታወቃል:: ደብረ ቆናፅል ማለት «የቀበሮ ተራራ» ማለት ነው:: ከአባ ጰንጠልዮን ባዕት ያማዕት ከሚባለው የ1 ኪ.ሜ. ርቀት አለው:: ደብረ ቆናፅል ከላይ እስከ ታች ድረስ በተ ፈጥሮ ልምላሜ የማይለየው ቦታ ሲሆን፣ ከፍታማ ተራራማ ሆኖ ዙሪያው ጥቅጥቅ ባለ ደን የተሸፈነ ነበር:: ለመጀመሪያ ጊዜ አስቄጥሳዊ ሥርዓት ያለው ገዳም በኢትዮጵያ የተመሠረተው በዚሁ በደብረ ቆናፅል ነው:: ይህ ገዳም ጉራንጉሮች ስለሚገኙበት ባሕታውያን በደን ውስጥ ይኖሩበት ነበር:: ይህ ገዳም ለአባ ጰንጠልዮን ገዳምና ለአክሱም ከተማ በጣም ቅርብ ስለነበር ከመላው ኢትዮጵያ ወደ ጽዮን ማርያም ለመሳለም የሚመጡ መናንያን ሁሉ በዚሁ ገዳም ዙሪያ ሱባኤ እየገቡ ወራትና ዓመታትን ያሳልፍ ነበር:: የአክሱምና የአካባቢው ክርስቲያኖች ንዋየ ቅድሳቱን የሚጠብቅላቸውና ፅላተ ሙሴን የሚያጥንላቸው መነኩሴ የሚመርጡት ከዚሁ ከአባ ሊቃኖስ ደብረ ቆናፅል ገዳም ነበር:: አመራረጡም በምንኩስና በሚያሳየው ቅድስና ነው::

የአክሱም ሕዝብ ይህን የተመረጠውን መነኩሴ ንዋየ ቅድሳት ጠባቂ፣ አጣኝ ብቻ ሳይሆን ከጳጳስ በበለጠ መንፈሳዊ አባትነቱን ይቀበሉታል:: ደብረ ቆናፅል በአካባቢው ነዋሪዎች ቅዱስ ቦታ መሆኑ ስለሚታወቅ እጅግ ስፋት ካለው ተራራ ዙሪያ አንዲት ቅጠል እንኳ አይበጥሱም፣ ከብቶቻቸ

[19] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 1 ገፅ 33::





ውንም ወደዚያ አያሰማሩም:: በዚህ አኳኋን እስከ 1928 ዓ.ም. ድረስ ተጠብቆ የኖረውን ገዳም ፋሽስት ኢጣልያ አገራችንን በግፍ ሲወር ይህን ገዳም እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ አጉሳቆሉት፣ ቤተ ክርስቲያኑን ማደሪያቸውንና የጦር መሣሪያ ተሸካሚዎች የአጋሰሶች ማጐሪያ አደረጉት:: ገዳሙ ከፋሽስት ኢጣልያ ወረራ ጀምሮ ጠፍ ሆኖ ሲኖር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ጥቂት መነኩሳት በቦታው መቀመጥ ጀምረዋል::[20] ይህን ገዳም የመሠረቱት ከተስአቱ ቅዱሳን አንዱ የሆኑት አባ ሊቃኖስ ለአክሱም ከተማ ቅርብ በሆነ ቦታ ስለተቀመጡ ከዐፄ ካሌብና ከዐፄ ገ/መስቀል ጋር ለመገናኘት እድል ስለነበራቸው ለሐዋርያዊ ተግባራቸው እገዛ አድርጎላቸዋል:: በዚህ መሠረት ደግሞ ከዕርዕ፣ ከሱረስት ቋንቋዎች መጽሐፈ ሐዲሳትን በከፊል ወደ ግዕዝ እንደ ተረጐሙ ይነገራል:: እረፍታቸው ህዳር 28 ቀን ነው::

## አባ አሌፍ ገዳም

ከስማቸው ስያሜ አንፃር ስንመለከተው ከተሰዓቱ ቅዱሳን መካከል ቀድመው የመጡት አባ አሌፍ ናቸው:: አሌፍ የእብራይስጥ የመጀመሪያ ፊደል ስያሜ ነው:: አቡነ አሌፍ አገራቸው ቂሳርያ ሲሆን አባታቸው አውሎግሶን እና ታቸው አትናስያ ይባላሉ:: የአቡነ አሌፍ ወላጆች ደግ ልጅ ከአብራካቸው የሚከፈል መሆኑን መልአክ እግዚአብሔር በራእይ ተገልፆ እንደነገራቸው ገድሉ ይናገራል:: አቡነ አሌፍ ከሕፃንነታቸው አንስቶ የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ገዳም እንዲሔዱ ስለአነሳሳቸው ወደ አባ እንጦንስ ገዳም ሔደው የገዳሙን ማኅበር እየረዱ በዚያው ገዳም መንኩሰዋል::

ከዚህ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በአክሱም ቤተ ቀጢን በሚባለው ቦታ በመቀመጥ የኢትዮጵያን ባሕል ቋንቋ አጥንተዋል ንጉሥ አልአሜዳ በክብር ተቀብሏቸዋል:: አቡነ አሌፍ ገዳም መሥርተዋል ይህ ገዳም የተመሠረተው በዐፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት ነው:: አቡነ አሌፍ

[20] ክርስትና በኢትዮጵያ ቁጥር 1 ገፅ 137::



www.ethiopianorthodox.org

ወደ ክፍለ እጣቸው «ብንዘ» ወደ ተባለው ቦታ ከአክሱም ተነሥተው በሚሔዱበት ጊዜ ከዚያ እስኪደርሱ ድረስ ስድ ስት ቦታ በጸሎት ውሃዎች አፍልቀዋል።

ይህ ብንዝት ተብሎ የሚጠራው ተራራ በጣም ትልቅ ስለሆነ ዘንዶ ነበረበት ይህን ዘንዶ ባርከው አጥፍተውታል። እርሳቸውም በዚሁ ቦታ ፝ገብተው ተቀመጡ አቡነ አሌፍ ከዚህ ተራራ ያሉትን እፅዋት ሁሉ አይተውና ተመልክተው ስላስደሰታቸው ወደ እግዚአብሔር አመልክተው ይህቺን ተራራ ደብረ ማነው ብለው ጠርተዋታል ገድላቸውም፦ «ወለይእቲ ደብረ ሰመያ ደብረ ማነው...» ይላታል። በዚህ ቦታ ፃድቁ አምስት መቶ መነኮሳትና አራት መምህራን እንደነበሯቸው ይነገራል። ገድሉ እንደሚናገረው አቡነ አሌፍ በዚሁ ገዳም ታላላቅ ተአምራትን ሰርተዋል እዚህ ቦታ በገቡ በሰባ ዓመታቸው መጋቢት 11 ቀን ቃልኪዳን ተቀብለው አርፈዋል።[21]

## አባ ጉባ ገዳም

አባ ጉባ ሐዋርያዊ ተግባራቸው ምን ያህል እንደሆነ አይታወቅም፤ ሆኖም ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር (ከ8ቱ ቅዱሳን) ጋር ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል። እኝህ ጻድቅ ስማ ቸው እንደሚያመለክተው ግርማቸው የሚያስፈራ ግዙፍ መሆ ናቸውን ይገልጻል። አባ ጉባ የመሠረቱት ገዳም ከተሰአቱ ቅዱሳን መካከል የእሳቸው ጠፍ ሆኖ ቀርቷል። ቦታው ከአ ድዋ ከተማ ጥቂት ወጣ ብሎ ወደ አባ ገሪማ ገዳም በሚ ወስደው መንገድ ላይ ይገኛል። ቤተ ክርስቲያኑ በጣም ትንሽ ጐጆ መሰል ቤት ሆኖ በአካባቢው የሚገኙ ክርስቲ ያኖች በጣም ትንሽ ናቸው። ይህ ቤተ ክርስቲያን በዓመት 1 ጊዜ ብቻ እንደሚከፈት ይናገራሉ። ለቦታው መጐሳቆል ምክንያት የአድዋ ከተማ መስፋፋት እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል። ከተማው እየተስፋፋ ሲሔድ አዳዲስ አብያተ

[21] አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁጥር 5።





ክርስቲያናት በከተማው መሐል መሠራት ጀመሩ። የአባ ጉባ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ነዋሪዎችም ከነበሩበት እየለቀቁ ወደ መሐል ከተማ ስለገቡ ቦታው ከዚህ ወዲህ አስታዋሽ አጥቶ እንደቀረ ተገልጿል።[22]

እንግዲህ የተሰአቱ ቅዱሳን ታሪካቸውንና ገዳማቸውን አሁን ባለው መልኩ ምን እንደሚመስል ተመልክተናል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለእነዚህ ቅዱሳን አበው የቅድስና ማዕረግ ሰጥታቸዋለች። በአጠቃላይ እነዚህ ቅዱሳን 4 መን ግሥታትን በዘመናቸው አሳልፈዋል። ከዳግማዊ አልአሜዳ ዘመነ መንግሥት 8 ዓመታት፤ ታዜና ዘመነ መንግሥት 12 ዓመት፤ በካሌብ ዘመነ መንግሥት 30 ዓመት፤ በገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት 7 ዓመት የኖሩ ሲሆን በአጠ ቃላይ 57 ዓመት ይሆናል። ጠቅለል ባለ መልኩ የመጡበት አገር የክብረ በዓላቸውን ቀን እንደ ሚከተለው ተቀምጧል።

| ስማቸው | የመጡበት አገር | የተቀመጡበት ቦታ | የክብረ በዓላቸው ቀን |
|---|---|---|---|
| አቡነ አረጋዊ | ሮም | ደብረ ዳሞ | ጥቅምት 14 |
| አቡነ ጳንጠልዮን | ሮም | ከአክሱም ሰሜን ምሥራቅ | ጥቅምት 6 |
| አቡነ ይምአታ | ቆስያ | ገርአልታ | ጥቅምት 28 |
| አቡነ ገሪማ | ሮም | መደራ አድዋ ሰሜን ምሥራቅ | ሰኔ 17 |
| አቡነ ጽሕማ | አንጾኪያ | እንዳ አባ ጽሕማ ፀዲያ | ጥር 16 |
| አቡነ አፍጼ | እስያ | የሐ | ግንቦት 29 |
| አቡነ ሊቃኖስ | ቁስጥንጥንያ | ደብረ ቆናፅል ከአክሱም በስተ ሰሜን የሚገኝ ኮረብታ | ህዳር 28 |
| አቡነ አሌፍ | ቂሳርያ | ደብረ ሃሌ ሉያ እሕሳእ አክሱም ሰሜን ምሥራቅ | መጋቢት 11 |
| አቡነ አባ ጉባ | ኪልቅያ | እንዳ አባ ገሪማ አጠገብ | ግንቦት 29 |

[22] ክርስትና በኢትዮጵያ ቁጥር 1 ገጽ 149።



www.ethiopianorthodox.org

## የተስዐቱ ቅዱሳን አስተዋፅኦ

1. ሕይወታቸው በአጠቃላይ አሁንም ሆነ ወደፊት ለሚነሳው ትውልድ አስተማሪ ሆኗል:: ይህም፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመጻፍ፣ ስብከተ ወንጌልን በየቦታው ለማዳረስ፣ የአምልኮ ጣኦት ቦታን አፍርሶ በምትኩ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ የሚፈተትበት ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት፤ ክህነትን ከምንኩስና ጋር በጥሩ ሕይወት ለመያዝ ለሚፈልግ የእነዚህ አበው መነኮሳት ሕይወት ይመራዋል::

2. አገራቸውን ትተው ቢመጡም እግዚአብሔር ያልተለያት አገር በመሆኗ እንደራሳቸው ወይም እንደተወለዱባት አገር ቆጥረው ክርስትናን በማስፋፋታቸው የዘረኝነት መንፈስ የሌላቸው መሆኑን ያመለክታል:: ተስአቱ ቅዱሳን እነዚህንና ሌሎችን በአገልግሎታቸው ስላንፀባረቁ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አበርክተዋል::

3. ለትምህርት፣ ለማኅበራዊ ኑሮ፤ ለሥነ ጽሑፍ መስፋፋት፤ ለኪነ ጥበብ መዳበር አመቺ የሆኑ ገዳማት በቅድሚያ የመሠረቱት እነርሱ ሲሆኑ፤ ለአገራችን የመጀመሪያዎቹ የገዳማት ሕልውና ከመንፈሳዊ እውቀት ጋር ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አቅርበዋል::

4. እውነተኛውን መንገድ ይዘው፣ ንጽህናቸውን ጠብቀው ምድራውያን መላእክት የሆኑ የመነኮሳት አገር ለመሆን የበቁ አባቶች ለዚህ ሕይወታቸው አስተዋፅኦና በር የከፈቱ ተስአቱ ቅዱሳን ስለሆኑ የመነኮሳት /የምንኩስና/ አብነት ሆነዋል::

5. ከተለያዩ አህት አብያተ ክርስቲያናት በመምጣታቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በትምህርት ሁሉም የደረሱበትን በአንድ ጊዜ እንድትደርስበት አድርገዋታል::

6. መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ከግሪክኛ ወደ ግዕዝ የተተረጎመው በእነሱ ስለሆነ አገራችን በገዛ ቋንቋቸው መጽሐፍ ቅዱስን ካገኙ አገሮች እንድትመደብ አድርገዋል::

7. ለሥነ ጽሑፍ እድገት ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ለኢትዮጵያ ጭምር አበርክተዋል::





## የቅዱስ ያሬድ መነሳት
### [ከ505 - 570 ዓ.ም]

በ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኖረ የአክሱም ንጉሥ የዐፄ ካሌብ ልጅ ምን አልባት ሁለተኛ ልጁ ሳይሆን አይቀርም:: የመጀመሪያ ልጁ ቤተ እሥራኤል ይሆናል:: ይህ ከገብረ መስቀል በፊት ነግሦ ነበር፤ ገንዘብም አስቀርጿል:: በቅርቡ በተገኘው የድንጋይ ጽሑፍ መሠረት ዐፄ ካሌብ 3ኛ ልጅ ገብረ ክርስቶስ የሚባል ነበረው:: ይህ ነግሦ እንደነበር በትክክል አይታወቅም:: ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ «ዋዜማ» በተባለው መጽሐፋቸው ባሰፈሩት የነገሥታት ስም ዝርዝር ውስጥ ገብረ ክርስቶስን አልገለጹትም::[23] ሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ በጻፉት «መጽሔተ አሚን» በተባለው መጽሐፋቸው በዘረዘሩት የነገሥታት ስም ዝርዝር ውስጥ ደግሞ ሁለቱንም ማለት ቤተ እሥራኤልና ገብረ ክርስቶስን ጠቅሰዋል::[24] ገብረ መስቀል ከወንድሙ ከቤተ እሥራኤል ቀጥሎ በዙፋኑ ላይ ወጥቷል:: የገብረ መስቀል ስም በአጭርም ሆነ በረጅም ታሪክ ሲነሳ ሳያወሱት የማያልፉት በእርሱ ዘመን ቅዱስ ያሬድ መነሳቱንና ዜማ መድረሱን ነው::

ቅዱስ ያሬድ የተወለደው ሚያዝያ 5 ቀን በ505 ዓ.ም. ነው:: አባቱ አዳም እናቱ ታውክልያ ትባላለች:: የተወለደው በአክሱም ከተማ ነው:: የ6 ዓመት ሕፃን እያለ ወሳጆቹ ይስሐቅ ለሚባል አክሱማዊ መምህር ሰጡት:: በትምህርቱም ላይ ሳለ አባቱ አረፈ:: እናቱም ያሬድን ለወንድሟ ለአክሱም ቄሰ ገበዝ ለአባ ጌዴዎን ሰጠችው:: ነገር ግን ቅዱስ ያሬድ ትምህርቱ ፈጽሞ ሊገባው ስላልቻለ አንድ ቀን መምህሩ ስለተበሳጨበት ገረፈው:: በዚህም ተማርሮ ወደ አባቱ አገር ወደ «ባይወለል» ጉዞ ጀመረ::

መንገድ ላይ ሲሄድ ኃይለኛ ዝናብ ስለዘነበበት ከአክሱም ከተማ 4 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ «ማይ ከረም»

[23] ዋዜማ ገፅ 26::

[24] መጽሔተ አሚን ገፅ 84::



www.ethiopianorthodox.org

ዛፍ ስር እንዳለ አንድ ትል ስድስት ጊዜ ወድቆ ተነስቶ በሰባተኛው ዛፉን ሲወጣና ፍሬዋን ሲበላ አየ፤ ከዚህም ትዕግሥት ካለ ካሰቡበት እንደሚደረስ ተረዳ። ቅዱስ ያሬድ እግዚአብሔር በትል አስተማረው። ተስፋ መቁረጥ እንደማይገባ በምሳሌ ነገረው። ቅዱስ ያሬድ በዲቁና ማዕርግ በአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን እያገለገለ ይኖር ጀመር። በዚያን ዘመን ቀስ ብሎ በጉሮሮ እንደ ውርድ ንባብ እያዜሙ ያገለግሉ ነበር እንጂ ድምፅን ከፍ አድርጐ ማገልገል የለም ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን ከገነት በምሳሌ ሆነው ሦስት አእዋፍ ወደ ቅዱስ ያሬድ መጡ። እነዚህ ወፎች [የግእዝ፣ የዕዝል፣ የአራራይ ዜማ እንዲሁም የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ናቸው]። ከሦስቱ አንዷ «ያሬድ ሆይ አንተ ብፁዕ ነህ የተሸከመችህ ማህፀን ብፅዕት ናት» አለችውና ከዐይኑ ተሰወረች። ከዚያ በተመስጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ተነጠቀ። ያሬድ ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ተነጥቆ ልዑል እግዚአብሔርን በመንበሩ ዙሪያ ቆመው በታላቅ ዜማና እንደበገናም እንደመሰንቆም ባማረ ልዩ ቃና ባለው ድምፅ ሲያመሰግኑት አየ። ቅዱስ ጳውሎስ ሦስተኛ ሰማይ ወጥቶ እንዳየው 2ቆሮ.12÷2-5፤ የምስጋናውም ጣዕም ምንም ቢያስደስተውም ወደቆመበት ለመጠጋት አልቻለምና እዚያ ቀድሞ ያያቸው ወፎች ወደ እርሱ መጡ። ከዚያም አንዲቱ እንደቀድሞዋ «ይህንን የሰማኸውን ማሕሌተ መላእክት አልተገነዘብከውምን» አለችው። እሱም አልተገነዘብኩትም አለ። የምትገነዘበውን እኔ እነግርሃለሁ። ለእግዚአብሔር አዲስ ምስጋና ጀምር አለችው።

ወዲያው ከካህናተ ሰማይ የሰማው ማሕሌተ መላእክት ሁሉ በመንፈሰ እግዚአብሔር ተገለጠለትና በልቦናው የተሳለበትን ምሥጢር ሁሉ በዜማ ይናገር ጀመር። ከዚያም ወደ ቀደመ ቦታው አክሱም ቤተ ክርስቲያን በሦስት ሰዓት ገባና በታቦተ ጽዮን አንፃር ቆሞ በከፍተኛ ድምጽ «ሃሌ ሉያ ለአብ፤ ሃሌ ሉያ ለወልድ፤ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ፤ ቀዳሚሃ ለጽዮን ሰማየ ሳረረ ወበዳግም አርአዮ ለሙሴ ዘከመ ይገብር ግብራ ለደብተራ» ብሎ አዜመ። የዚህ ውስጠ ምሥ





ጢሩ ለሙሴ በደብረ ሲና የተገለፀለትን ምሥጢር ያስረዳል። ዜማ የደረሰበት ወሩ ታህሳስ ዕለቱ ሰኞ ነው። ዜማው ሦስት ሲሆን ግዕዝ፣ እዝል፣ አራራይ ይባላል። ይህንንም ማሕሌተ አርያም ሲደርስ የቆመበት ሥፍራ እስከ አሁን ምልክት ይዛ ትታያለች።

የጻድቁ የዐፄ ካሌብ ልጅ ዐፄ ገ/መስቀል ቃለ ዜማውን ለማዳመጥ በአንድነት ወደ አክሱም ቤተ ክርስቲያን ሮጠው ገቡ። ወዲያው ጳጳሱና ሊቃውንቱ፣ ካህናቱ የመንግሥቱም ታላላቅ ሰዎች ወደዚሁ ቀርበው ያዳምጡት ጀመር። በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘው ድምፁም ከጣዕሙ የተነሳ እጅግ ልቡናን የሚመስጥ የሚያስደስት በመሆኑ ሰው ሁሉ እንግዳ ነገር ተገኘቷልና እንሂድና እናዳምጥ እየተባባሉ ይሰበሰቡና ያዳምጡ ጀመር። እንስሳት አራዊት ሳይቀር ፈዘው ይቆሙ ነበር። ምሥጋናውም ለ4ቱ ክፍላተ ዘመን ለክረምት፣ ለበጋ፣ ለመፀው (ለጥቢ)፣ ለፀደይ (በልግ) እንደሚበቃ አድርጐ አዘጋጅቶታል።

በየጊዜው ሁሉ እግዚአብሔርን ሰውና መላእክት ስሙን እንዲቀድሱ ክብሩን እንዲወርሱ መፍጠሩን አምልቶ አስፋቶ ተናግሯል። ነቢያት ክርስቶስ ይወርዳል ይወለዳል እያሉ ትንቢት መናገራቸውን፣ ጌታም የተቆጠረው ሱባኤ ሲፈፀም ወደዚህ ዓለም መምጣቱን ሰው መሆኑን፣ ሥጋ መልበሱን ተናግሯል። ሐዋርያትም ወረደ ተወለደ በማለት የሰበኩትን ስብከት ከእነ ምስጢሩ እየገለፀ፤ ጥምቀቱን፣ ህማሙን፣ ሞቱን፣ ትንሣኤውን፣ እርገቱን በየማነ አብ በዘባነ ኪሩብ መኖሩን (መቀመጡን) ዳግመኛ ለጻድቃን ሊፈርድላቸው ለኃጥአን ሊፈርድባቸው መምጣቱን በየዘመናቱና በየወራቱ በየዕለቱ እየለየ በተከናወነ ዜማ ለሰው በሚረዳ ትርጓሜ እየተረጐመ ከማዜሙ በላይ የተዋህዶን ምስጢር በብዙ አይነት አጉልቶ አሳይቷል።

ከፈጣሪው ምስጋና በኋላ ነቢያትና ሐዋርያትን፣ ፃድቃን፣ ሰማዕታትን፣ መላእክተን ሥራቸውንና ክብራቸውን እየተናገረ አወድሷቸዋል። ይልቁንም በንፅህ ሥጋ በንፅህ ነፍስ በንፅህ ልቡና ፍፅምት ሆና አምላክን የወለደች ድንግል



www.ethiopianorthodox.org

ማርያምን አመስግኗል:: የዜማው ጣዕም እንኳን ሌላውን እራሱን እጅግ የሚመስጠው ከመሆኑ የተነሳ አንድ ቀን ንጉሡ ዐፄ ገብረ መስቀል ከተቀመጠበት ስፍራ ዝቅ ብሎ ቃለ እግዚአብሔርን ሲናገር ንጉሡ ሹል ብረት ያለበት ዘንግ ይዞ ነበርና ሳያስበው እግሩን ወጋው ደሙ በቤተ ክርስቲያኑ አውደ ምህረት ላይ ፈሰሰ:: ቅዱስ ያሬድ ግን የማህሌቱ ጣዕም ህሊናውን ስለመሰጠው አገልግሎቱ እንዳይስናከልበት ሃሳቡን ስላበረታታው ህማሙን ታግሶ ቆየ:: ማሕሌቱ ከተፈፀመ በኋላ ንጉሡ ደንግጦ ዘንጉን ቢነቅልለት ደሙ መፍሰሱ ቆሟል::

ንጉሥ ገብረ መስቀልም በዘንጉ መውጋቱን ዓይቶ ትዕግሥቱን አደነቀ:: ምድራዊ ዋጋን የሚፈልግ መስሎት ስለ ደምህ ዋጋ የፈለከውን ንገረኝ አደርግልሃለሁ አለው:: ቅዱስ ያሬድም የምፈልገውን እንዳትከለክለኝ እንጂ እኔ የምፈልገው ሌላ ነው ብሎ መለሰለት:: እሱም የፈቀደውን ሁሉ እንደማይከለክለው በጽኑ ቃል ኪዳን ገባለት:: በዚህን ጊዜ ከዚህ ዓለም ተለይቼ እንድመነኩስ አሰናብተኝ ብሎ ሃሳቡን አሳወቀ:: ንጉሡም ይህን ቁርጥ ሃሳቡን በሰማ ጊዜ እጅግ ደነገጠና ከቀድሞ ጀምሮ እስከ ዛሬ እንደ ያሬድ ያለ ካህን አልተነሳም:: የአክሱም ቤተ ክርስቲያን ሽልማቷና ጌጧ እርሱ ነበር:: በዜማው ጣዕም የተደሰትኩትን ያህል በመሄዱም ብዙ ጉዳት ሊያገኘኝ ነው እያለ እጅግ ያዝን ጀመር:: ወዲያው በቤተ መንግሥቱ በአክሱም በካህናቱና በሕዝቡም ሁሉ ዘንድ ታላቅ ህዘን ተደረገ::

ከዚያ በኋላ ንጉሡ ከቃሉ ያወጣውን መሐላ አስቦ እንዲመነኩስ አሰናበተው:: ቅዱስ ያሬድም ወደ ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ገባና ሁለት እጆቹን በታቦቱ አምሳል ላይ ዘርግቶ «ቅድስት ወብፅዕት ስብሕት ወቡርክት ክብርት ወልዕልት አንቀፀ ብርሃን ማዕረገ ሕይወት» ብሎ ንባቡን ከዜማው በማስማማት አዲስ ድርሰት ደረሰ:: ይህም «አንቀፀ ብርሃን» የተባለው የእመቤታችንን የምስጋና ድርሰት ነው:: አንቀፀ ብርሃን ማለት የብርሃን በር ማለት ነው:: የእርሱም ቁጥር 12 የሆነ፣ ቅዱስ ያሬድ ስለእመቤታችን ምስጋና የደረሰው ይህ ድርሰት 12 የሆነበት ምክንያት ቅዱስ ያሬድ በጥንት





ዘመን በአክሱም ቤተ ክርስቲያን አምድ ልክ ስለደረሰው ነው:: በበሩም ልክ ስለደረሰው «አንቀፀ ብርሃን» ተብሏል::[25]

አንቀፀ ብርሃንን ሲደርስ በዕዝል ዜማ ሲናገር በተአምራት እግሩ ከምድር አንድ ክንድ ያህል ለቆ ይታይ ነበር:: በዚህን ግዜ በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች እመቤታችን ብፁዕ ነህ በማለት አመሰገነችው:: መሄዱ እንደማይቀር በፈቃደ እግዚአብሔር የተወሰነ ስለሆነ የመሰናበቱ ጉዳይ ቀጠለ:: የአክሱም ካህናትም ሲሸኙት ጽኑ ልቅሶ አለቀሱ:: እርሱም ከእነሱ ጋር አለቀሰ:: እስከ ተከዜ ድረስ ሸኝተውት የመመለሻቸው ጊዜ ሲቃረብ «ሰላምን ገንዘብ አደረግን ለእናንተም ሰላምን ገንዘብ አደረግንላችሁ:: ሰላመ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይኑር» ብሎ በአባትነት መረቃቸው:: ዳግመኛም «ሁሉ የሚገኝበት ሰላመ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይኑር» በማለት የመጨረሻውን ቡራኬ ሰጣቸውና ተሰናበታቸው:: ከእሱ በመለየታቸው እያዘኑ ወደ አገራቸው ገቡ::

ንጉሡ ዐፄ ገ/መስቀል ለቤተ ክርስቲያን መገልገያ እንዲሆን ድርሰቱን ተቀብሎ ለሊቃውንቱ ቢያሳውቅ ፈቃደኛ አልሆኑም:: ስለዚህ ምሕላ ይዘው ፈቃደ እግዚአብሔርን እንዲጠይቁ አዘዘ:: ከልደታ እስከ ሥላሴ ምሕላ ይዘው ፈቃደ እግዚአብሔርን አግኝተው ድርሰቱን እንዲቀበሉም ምልክት አገኙ:: ስለዚህ ነው ዛሬ ከ1 እስከ 7 ምሕላ የሚያዘው:: እሱም ፀለምት ወደምትባለው ወደ ሰሜን በረሀ ገባና በጾም በጸሎትና በብዙ ትጋት የትሩፋቱን ሥራ ቀጠለ:: የእግዚአብሔርንም ምስጋና ከቀድሞ አብልጦ ለፀለምትና ለሰሜን ሰዎች፣ ከሌሎችም አገሮች ለመጡ ሁሉ እያስተማራቸው ኖረ:: ከብዙ ዘመን በኋላ የጽዮን ካህናት ሊያዩት መጥተው ቀርበው እጅ በነሱት ጊዜ «ቸር አላችሁን? በፍቅርም እጅ አነሳችኋለሁ፤ አብያተ ክርስቲያናት ደህና ናቸውን? ይልቁንስ ቅድስት ጽዮን ደህና ነችን? እናንተም በፍቅር እጅ እንደነሳችሁኝ እኔም በፍቅር እጅ እነሳችኋለሁ» እያለ በዜማ አሰምቶ ተናገረ:: በእንዲህ ዓይነት በሥነ ትሩፋት ፈጣሪውን

[25] ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት ገፅ 53::



www.ethiopianorthodox.org

ሲያገለግል ኖሮ በግንቦት 11 ቀን አረፈና በዚህችው ስሜን በምትባለዋ አገር በስተምሥራቅ በኩል ተቀበረ:: አጽሙ ያረፈበትንም ልዩ ቦታ እግዚአብሔር ከፈቀደላቸው አንዳንድ ባሕታውያን በቀር የፈለገ ሁሉ ሊያየው አልቻለም:: የበቁ አባቶች ግን በረድኤተ እግዚአብሔር እየተገለፀላቸው ብዙ መንፈሳዊ ሥራ ሠርተውበታል:: ገድለ ያሬድ ማሕሌታይ በፓሪስ ታትሟል::[26] የቅዱሱ ያሬድ ታሪክ የሚገኝባቸው የአገራችን ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል ገድለ ያሬድ ከ1 እስከ 3፣ ድርሳነ ዑራኤል፣ ገድለ አረጋዊ፣ ገድለ ተክለሃይማኖት፣ ገድለ አባ ሊባኖስ፣ መቅድመ ድጓ፣ ታሪክ ነገሥት፣ ድርሳነ ፍልሰታ ዋናዎቹ ናቸው::

## የቅዱስ ያሬድ ትውፊት

የዐፄ ገብረ መስቀል ዘመን የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያናችን የሥነ ጽሑፍ ዘመን ነው ማለት ይቻላል:: በዚህ ዘመን ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ጸዋተወ ዜማዎችን የደረሰበት እና ተስአቱ ቅዱሳን የነበሩበት ጊዜ ነበር:: እነዚህ አበው ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ባለፈው እንዳየነው ዝም ብለው አልተቀመጡም:: በአባ ሰላማ ተጀምሮ የነበረውን ሥነ ጽሑፍ እነሱ ቀጥለውበት መጻሕፍትም ለየአድባራቱ በስፊው እንዲዳረስ አድርገዋል:: እስከ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ድረስ (1268-1283) ዓ.ም. መሆኑ ነው:: በእነዚህ ዘመናት እነዚህ ቅዱሳን የጻፉት መጽሐፍና የተጻፈላቸው ገድል ከኢትዮጵያ አልፈው በውጭ አገር በፓሪስ፣ በለንደን፣ በሮም ቤተ መጻሕፍት እንደሚገኙ ሊቃውንት በመጽሐፋቸው ጠቅሰዋል::[27] በዚህ መሠረት ቅዱስ ያሬድ አሁን ድረስ የምንጠቀምባቸውን ትውፊት /Tradition/ አውርሶናል:: ከእነዚህም መካከል የደረሳቸው የዜማ መጻሕፍት አሉ:: ከዜማ መጻሕፍቱ ሌላ «አንቀጸ ብርሃን» «ይዌድስዋ መላእክት» የተባሉት የእመቤታችን የምስጋና ድርሰቶቹ ይጠቀሳሉ:: የዜማ መጻሕፍቱ አገልግሎታቸው እንደሚከተለው ነው::

[26] መርሐ ልቡና ገፅ 79::

[27] ዝኒ ከማሁ::





| የመጻሕፍቶቹ ስም | ትርጉማቸው | አገልግሎታቸው |
|---|---|---|
| ዝማሬ | መዘመር፣ አዘማመር፣ ዝመራ፣ ጅመራ፣ቅንቀና፣ ዜማ፣ ማኅበራዊ ምስጋና ማለት ነው:: | ከድርገት በኋላና በቅዳሴ መካከል የሚቃኝ የሚዜም የሚዘመር የጸሎተ ቅዳሴውን ዓላማ ተከትሎ የሚሔድ ነው:: |
| መዋስዕት | ለዋሰወ ነፍስ /የነፍስ መሸጋገሪያ/ መርህ ለመንግሥተ ሰማያት ወይም መንግሥተ ሰማያት መርቶ የሚያገባ ማለት ነው:: | ለዕለት ፍትሀት ለሙት ዓመታትና፣ የሙት ዓመታቱ በሚደረግበት ቀን የዳዊት መዝሙርን መነሻ እያደረገ በዕለቱ የዋለውን በዓል፣ ምዕመኑ በሕይወተ ስጋ በነበረበት ጊዜ የሠራውን መልካም ሥራ ከበዓሉ ጋር በማነፃፀር የሚደረስ ነው:: |
| ምዕራፍ | ማረፊያ፣ ማሳረፊያ፣ መኖሪያ፣ መቀመጫ ቦታ ሠፈር ማለት ነው:: | የዘወትርና የጾም ምዕራፍ ተብሎ በሁለት ታላላቅ ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን፤ የዘወትር ምዕራፍ የሚባለው ዓመቱንሳ ይጠብቅ በዓመቱ ውስጥ ባሉት ሳምንታትና በዓላት ወቅቱን እየ ጠበቀ በአገልግሎት ላይ የሚውል ሲሆን፤ የጾም ምዕራፍ የሚባለው ደግሞ በጾመ አርባዕና በአንዳንድ የምሕላ ቀኖች የሚውል ወይም የሚያገለግል ነው:: |
| ድጓ | በሐማሴን አነጋገር ዳጉዓ ማለት አልቃሽ፣ አሚሽ፣ ገጣሚ፣ ቆዛሚ፣ የልቅሶ ዜማ፣ ምሾ፣ ግጥም፣ መዝሙረ ሐዘን ዝማሬ ምስጋና ማለት ነው | በታላላቅ በዓላትና በዓብይ ጾም የሚደርስ ዝማሬ ነው:: |
| ጾመ ድጓ | የጾም ድጓ | ይህ ሦስተኛው የድጓ ክፍል ከዮሐንስና ከአስተምህሮ ቀጥሎ ያለ ሲሆን ይህ ጾመ ድጓ በወርሃ ዓብይ ጾም፣ በነግህ፣ በሠለስት፣ በቀትርና በሠርክ እንዲሁም በሌሊት የሚዘመር መዝሙር ነው:: የጾምን የጸሎትንና የምጽዋትን ጠቃሚነት የሚያስተምር ታላቅ ምስጢር ያለው ነው:: |



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ያሬድ ካስተማረባቸው የዜማውን ቅርስ ከተወባቸው ጣና ቂርቆስ ገዳም አንዱ ነው:: በዚህ ቦታ 29 ዓመት አስተምሯል:: ጣና ቂርቆስ ከቅዱስ ያሬድ ጋር የተቆራኘ ግንኙነት አለው:: ቅዱስ ያሬድ ለመጀመሪያ ጊዜ የዜማ መጻሕፍቱን የጻፈው እዚሁ ገዳም ውስጥ ነበር በማለት መጽሐፉ በአስረጅነት ይቀርባል:: ቅዱስ ያሬድ ድጓውን ሲጽፍ ለጥቁርና ቀይ ቀለማት መ(ቀ)ጥበጫነት ይጠቀምበት የነበረው ከድንጋይ ተቦርቡረው የተሠሩ ጉድጓዶች እዚያው ይገኛሉ:: የቅዱስ የያሬድ ምልክት የሌለው ድጓ፣ ካባውም አሉ::[28] የ14ቱን የቅዳሴ ዜማ ያዘጋጀበት ቦታ መደባይ ታብር ይባላል:: ይህ ቦታ አቀማመጡ ለአክሱም ሰሜን ሆኖ ከአክሱም የግማሽ ቀን ያህል በእግር ያስኬዳል::[29] ስለዚህ ቅዱስ ያሬድ:-

ብሉይና ሐዲስን በማስማማት ቅኔን አበርክቷል፣ በብሉይ የነበረውን ምሳሌ በአንድምታ ትርጓሜ በመጠቀም ወደ ሐዲሳት ለውጧል፤ ዜማ በመድረሱ የቤተ ክርስቲያናችን መቅረዝ ነው:: ቅዱስ ያሬድ ከመላእክት የሰማው ዜማ [ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ የጌትነትህ ቅድስና በሰማይና በምድር መላ ከቅዱሳን መላእክት የሰማሁት ዜማዋ ምንኛ ይደንቅ] በማለት የዜማ አባትነቱን ገልጿል:: የቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት (አምስቱ ጸዋተወ ዜማ ይባላሉ) እነዚህ የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች ምንጫቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው:: ይኸውም:-

- ብሉይ ኪዳን፤
- አዲስ ኪዳን፤
- መጻሕፍተ ሊቃውንት፤
- መጽሐፈ መነኮሳት፤
- መጻሕፍተ አዋልድ፤

ማለት ድርሳናትና ሌሎችም ናቸው::[30]

[28] የአማራ ክልል የቱሪስት መስህብ ሀብቶች አጭር ቅኝት 1991 ዓ.ም::

[29] ያሬድና ዜማው ገፅ 33::

[30] ዝኒ ከማሁ ገፅ 63::





በሀፄ ገብረ መስቀል ጊዜ የተነሳው ቅዱስ ያሬድ ለአሁኑ ዘመን ካቆየልን ትውፊት አንዱ የሆሣዕና በዓል አከባበር ነው:: ይህ በዓል የአክሱም ጽዮን መምህር በአህያ ውርንጭላ ተቀምጦ «ይባእ ንጉሠ ስብሐት» እየተባለ ይዘመር ነበር:: ቅዱስ ያሬድ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፤ ንጉሥ ገ/መስቀል በቤተ መንግሥት ሥርዓት እየተመሩ ለመጀመሪያ ጊዜ በአክሱም ከተማ ያከናወኑትና ያከበሩት ሥርዓተ ሆሣዕና እስከ ዛሬ በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ሥርዓት ሲካሔድ ይገኛል:: ዘመኑ ከ530-544 ዓ.ም. እንደሆነ ይታወቃል::[31]

## የዜማ ምልክቶች* ትርጉም

አንድ የዜማ ዓይነት ትውልድ የሚከተለው ትምህርት ከሆነ መመሪያ ሕግ ወይም ምልክት (ኖታ) እንዲኖረው ግዴታ ነው:: የአገር ውስጡንም ሆነ የውጭው ዓለም የዜማ ይዞታ ቢዳሰስ ያለ ሕግና መመሪያ (ያለ ምልክት) የሚመራ ዜማ እንደሌለ እንረዳለን:: ሊቁ ቅዱስ ያሬድም ለዜማው መመሪያ የሚሆኑ የፊደል ቅርፅ የሌላቸው 8 ዓይነት ሲሆን [አንብርና ድርስ] ሲጨመሩ 10 ይሆናሉ:: ይህም፣ «አሥር አውታር ባለው በበገና አመሰግንሃለሁ» መዝ.143÷9፤ ተብሎ በተነገረው መሠረት በምሳሌ የተዘጋጁ ናቸው:: ስለዚህ ስማቸውን፣ ምልክታቸውን፣ አገልግሎታቸውን እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ለማስቀመጥ ተሞክሯል::

[31] አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁጥር 1 ገፅ 21::

* እነዚህ የዜማ ምልክቶች በአራት ይከፈላሉ:: ይኸውም:-

1. ራሱ ቅዱስ ያሬድ ያስገኛቸውና የፊደል ቅርጽ የሌላቸው፤
2. የኋላ ሊቃውንት ከዜማው ዘር ለምልክትነት በመምረጥ አገልግሎት እንዲሰጡ ያደረጓቸው፤
3. በተለያዩ ጊዜያት አንዳንድ ታላላቅ ሥራዎችን የሠሩ ሰዎች ሥራቸው እንዲታወስ ተብሎ በስማቸው የተዘጋጁ፤
4. መምህሩ ደቀመዝሙሩን በሚያስተምርበት ጊዜ በአካባቢው ባለው ሁኔታ እንዲሁም ራሱ ተማሪው ዜማው አልያዝለት ሲል በቀላሉ ትዝ እንዲለው የተፈጠሩ የምልክት ዓይነቶች አሉ:: /የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ በ2000 ገጽ 112/



www.ethiopianorthodox.org

| ስሙ | ምልክቱ | አገልግሎቱ |
|---|---|---|
| ድፋት |  | ድምፅህን አንገትህን ወደ ታች አርግጥ አድርገህ ትንፋሽህን ወደ ሆድህ ውስጥ መልሰህ አዚም ማለት ነው:: |
| ሂደት |  | መንገድ እንደ በይ ውሃ ስተት ብሎ እንደሚሔድ አትቁም አታቋርጥ ምንም ሳትይዝ ስተት ብለህ ሂድ ማለት ነው:: |
| ቅናት |  | በዜማው መጨረሻ ያለውን አንዱን የፊደል ቃል ይዘህ አንገትህን ወደ ላይ አቅንተህ በማጋነን ድምፅ አዚመህ አቁም ማለት ነው:: |
| ይዘት | ● | ዜማው እንደ ንባብ በፍጥነት ሲነገር ከመካከሉ አንዱን የፊደል ቃል ያዝ አድርገህ አዚም ማለት ነው:: |
| ቁርጥ |  | ስታዜም ድምፅህን በኃይል ቁርጥ አድርገህ ወደ ታች ትንፋሽህን አምቀህ ዜማህን አቁም ማለት ነው:: |
| ጭረት |  | በዜማው መካከል ያለው ንባብ አንዱን የፊደል ቃል ጐተት ወይም ሳብ አድርገህ አንገትህን እንደሚዋጋ በሬ ወደ ላይ አቅንተህ አዚም ማለት ነው:: |
| ርክርክ | ⋮ | ዜማው እንዲረዝም በላይ በላዩ እየረከረከ መጨመርና ማስረዘም ማለት ነው:: |
| ደረት |  | ፊት ለፊት ደረት ለደረት ቀጥ ብሎ በጉልህ ድምፅ በጉሮሮ የሚነገር ማለት ነው:: |
| አንብር | ር | በመዝሙሩ መካከልና መጨረሻ እየገባ የመዝሙሮቹና የዜማዎቹ መክፈያ ወሰን አጥር ሆኖ የሚገኝ ምልክት ነው:: አንብር ማለት ቃልህን አስቀምጥ ወይም አሳርፍ ማለት ነው:: |
| ድርስ | ርስ | በመዝሙሮቹ መካከልና መጨረሻ እንደ መክፈያ ወይም እንደ መጋረጃ ሆኖ እየገባ በናላ የሚዜም ነው:: |

ምንጭ:- የቅዱስ ያሬድ ታሪክና የዜማው ምልክቶች ገፅ 56::





ይህን በዚህ መልክ ከተመለከትን አሁን ደግሞ እነዚህን ምልክቶች ትርጉማቸውን እናያለን:: ፍፁም መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ እነዚህ ምልክቶች በሙሉ የክርስቶስን የማዳን ሥራን የሚያስገነዝቡን ወይም የሚተረጉሙሉን ናቸው:: ይህንንም እንደ ላይኛው በዚህ ሠንጠረዥ መልክ ተቀምጧል::

| የዜማው ምልክት | ትርጉማቸው |
|---|---|
| ድፋት | ርደትን ከወዲያ ወዲህ መምጣትን ያመለክታል:: ይህ ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወረዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ወደዚህ ዓለም መምጣቱንና ሰው መሆኑን የሚያስረዳ ነው:: |
| ሂደት | መሔድ መጓዝ መራመድን የሚያሳይ ሲሆን፤ መድኃኒታችን በኢየሩሳሌም ከተሞች እየተዘዋወረ ማስተማሩን፣ በኋላ በስቅለቱ ጊዜ ተከሶ እንዴ ወደ ሐና፣ ወደ ሄሮድስና ወደ ጲላጦስ መመላለሱን ይገልፃል:: |
| ቅናት | መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድንቅ ተአምራት በመስራቱ አይሁዶች አይተው በመቅናት ለሞት አሳልፈው እንደሰጡት ያስረዳል:: |
| ይዘት | በትምህርቱና በተአምራቱ ቀንተው ከሳሽ መስካሪ ሆነው በሀሰት ማስያዛቸውን፤ በተጨማሪ ዓለሙ በእጁ (በመዳፍ) የያዘ አምላክ መሆኑን ያስተምራል:: |
| ቁርጥ | አይሁዶች ጌታችንን በሐሰት መስክረው ቢያሲዙትም ለሚደርሰው መከራ ሁሉ በሲኦል ተግዞ የነበረውን የአዳምን ዘር ለማዳን ቆርጦ መነሳቱን ያመለክታል:: |
| ጭረት | መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግርፋቱን የሚያስረዳ ምልክት ነው:: |
| ርክርክ | መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገረፍ የተንጠባጠበው ደሙን ይገልጣል:: |
| ደረት | መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ከፈፀመ በኋላ በክብር በብርሃን በውዳሴ በቅዳሴ በቅዱሳን መላእክት ታጅቦ ወደ ሰማይ ማረጉን ያስተምራል:: |
| አንብር | ሁሉን ከፈፀመ በኋላ በአባቱ ቀኝ መቀመጡን የሚያስረዳ ነው:: |
| ድርስ | ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል ይሞታል ይነሣል ወደ ሰማይ ያርጋል ሲሉ የተነበዩት ሁሉ አንድም ሳይቀር በሙሉ ደርሶ መፈፀሙን ያረጋግጣል:: |

ምንጭ:- ያሬድና ዜማው ገጽ 187-188::



www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

ጠቅለል ባለ መልኩ ቅዱስ ያሬድ ይህን የመሰለ ትውፊት አውርሶናል፡፡ ይህን ቅዱስ አባት አጠቃለን ስንመለከተው:-

- ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመንፈሳዊ ሀብት መገኛ የሆነ፤
- ከእነ ሞዛርት በፊት የዜማ ምልክትን በዓለም ላይ የሠራ፤
- የዜማ መጻሕፍት በመድረስ ለኢትዮጵያ ቤ/ክ ያስረከበ፤
- የቅኔን መንገድ በኋላ ለተነሱ ሊቃውንት ያስተማረ፤
- ከመላእክት የሰማውን ዜማ ለወገኖቹ ያበረከተ፤
- ሊጠፋ የማይችል የኢትዮጵያ ቤ/ክ መቅረዝ፤
- ብሉይና ሐዲስን አስማምቶ የተረጐመ፤
- ኢትዮጵያዊ ርዕሰ ሊቃውንት፤

ቅዱስ ያሬድ ነው፡፡

## የተቀጸለ ጽጌ በዓል አከባበር መጀመር

ከቀድሞ አባቶች ጀምሮ የተወረሡና ለትውልድ እየ ተላለፉ ሲሰራባቸው እስከ አለንበት ክፍለ ዘመን ከደረሱ የበዓላት ቅርሶች አንዱ «ተቀጸል ጽጌ/ዐዌ መስቀል» በዓል አከባበር አንዱ ነው፡፡ ይህ በዓል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ከሚከበሩት ዐበይት በዓላት እጅግ የላቀና ከፍተኛ ደረጃ የያዘ ነው፡፡ ይህ በዓል መከበር የተጀመረው በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዐፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት እንደሆነ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና የባሕል ተመራማሪ ዎች ያስረዱናል፡፡ የዚህ በዓል አከባበር መነሻው ወደ ኋላ መለስ ብለን መጻሕፍትን ስንመለከት በአሪት ከነበሩት ደጋግ ሰዎች ሲያያዝ የመጣ መሆኑን እናገኘዋለን፡፡

መሠረቱም «የአበባ በዓል» ነው፡፡ ይህ የአበባ በዓል የክረምቱ ወራት አልፎ የበጋው ወራት ሊጀምር ሲል ይከ በራል፡፡ ኢትዮጵያ በመሠረቱ በሃይማኖት ረገድ ያላት መነ ሻና በእምነት የታወቀላት ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደ ዕብራውያን በአንድ አምላክ ማመን፣ የኦሪት የነቢያት መጻ ሕፍትን መቀበል ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ተወዳጅ የሆኑ የባ ሕል ቅርሶች የተወረሱት ከብሉይ ኪዳን ከመጣው ሥርዓት የተገኙ የሃይማኖት ዘርፎች ናቸው፡፡ ይህን በመሳሰለው





መንገድ የተቀጸል ጽጌ በዓል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምታከብረው ከንጉሥ ሰሎሞን ተያይዞ የመጣውን ሥርዓት በመከተል ነው፡፡ ይህ የአበባ በዓል ንጉሥ ሰሎሞን በእንዴት ያለ አኳኋን ያከብረው እንደነበር በትውፊት የደረሰንን በአ ጭሩ እንመልከት፡፡

በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ /1ነገ 1፥1 ም.2/ እንደ ምናነበው ሰሎሞን ንግሥናውን ከአባቱ ከዳዊት ከተቀበለና በኢየሩሳሌም ከነገሠ በኋላ በዘመነ መንግሥቱ አምስት መቅ ረዝ በቀኙ አምስት መቅረዝ በግራው የሚገኙበትን ተቋመ ማኀቶት አሠርቶ እርሱ በመካከል ተቀምጦ ባማረ ልብሰ መንግሥት አጊጦ ለመኳንንቱና ለሕዝቡ ተገልጦ ይታያል፡፡ ጊዜውም የክረምት ወራት አልፎ በጋው ሲተካ ምድር ልብሰ ልምላሜን ተጎናፅፋ እፅዋት በቅጠል አጊጠው በአበባ ደመ ቀው በሚታዩበት፤ ሰማዩ በከዋክብት ሲያሸበርቅ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ራሱ ሰሎሞን በመኃልዩ «እነሆ ክረምት አለፈ ዝናም ተመለሰ አበቦች በምድር ላይ ተገለጡ /ፈኩ/ የመከር መቁረጫ ጊዜ ደረሰ የቁርየ /ሽመላ/ ድምፅ በምድራችን ተሰማ በለሱ ጎመራ ወይኖች አበቡ መአዛቸውን ሰጡ» መኃልየ መኃልይ 2፥11-13፤ ብሎ እንደ ተናገረው የአበባ በዓል የሚከበረው ክረምቱ አልፎ በጋው ሲተካ መሆኑን ገልጿል፡፡

በዚሁ መሠረት ሥርወ መንግሥታቸው ከዳዊት ዘር ሲያያዝ የመጣው የኢትዮጵያ ነገሥታትም ይህን በመከተል በዚህ በዓል ላይ በመስከረም 25 በቤተ መንግሥት ይከበ ራል፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ በዙፋኑ ሲቀመጥ ጳጳሱ በቀኝ፤ እጨ ጌው በግራ ተሰይመው ሊቃውንትና መምህራን በየማዕርጋ ቸው በቀኝና በግራቸው ይቀመጣሉ፡፡ መዘምራን በልብሰ ስርጋዌ (ባማረ ልብስ) በካባ አጊጠው በቤተ መንግሥቱ አደባባይ ቀኝና ግራ ይሰለፋሉ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ለበዓሉ የመረ ጠው ምስባክ ይሰበካል፡፡ ወንጌል ይነበባል ከምልጣን በኋላ ተቀጸል ጽጌ የተባለው ዝማሬ በካህናቱ ባማረ ጥንግ ድርብ ተሸልመው በንጉሠ ነገሥቱ እንዲሁም በሕዝቡ መካከል በማሸብሸብ ይዘምራሉ፡፡ በዚህን ጊዜ መአዛው ደስ የሚያሰኝ



www.ethiopianorthodox.org

አበባ ተመርጦ መጀመሪያ ለንጉሡ ይበረከታል፡፡ በመቀጠል ለመኳንንት ለመሣፍንት፣ ለሠራዊቱ፣ በየማዕርጋቸው ለተቀመጡ ሁሉ አበቦች ይታደላሉ፡፡

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ከንጉሥ ሰሎሞን ጀምሮ ተያይዞ የመጣው ይህ ተወዳጅ ባሕል እንደ አገራችን የዘመን አቆጣጠር ክረምቱ ከሰኔ 26 ገብቶ በመስከረም 25 ቀን ስለሚወጣ በዚሁ በመስከረም 25 ቀን እየተከበረ ለረጅም ጊዜ ቆይቷል፡፡ ከ515-529 ዓ.ም. የነበረው የአገራችን ንጉሥ ፀዬ ገብረ መስቀል በዘመኑ ይህን የአበባ በዓል እጅግ ከፍ ባለ አኳኋን ያከብረው ነበር፡፡ ይልቁንም ደስ ከመሰኘቱ የተነሳ ነቢዩ ዳዊት ከተልባ እግር የተሠራና ሐር ቀሚሱን ለብሶ በፍፁም ደስታ በታቦተ ጽዮን ፊት «ከበግ እረኝነቴ መርጠህ በዚህ ታላቅ ክብር ላይ ባስቀመጥከኝ በእስራኤል አምላክ በኪዳኑ ታቦት ፊት እዘምርልሀለሁ» 2ሳሙ. 6÷14-23፡፡ እያለ በሕዝቡ መካከል ይዘምር እንደ ነበር ሁሉ፤ ፀዬ ገብረ መስቀልም በዚህ በአበባ በዓል ቀን በሕዝቡና በካህናቱ መካከል ያሸበሽብ ነበር፡፡ በበዓሉ አከባበር ላይም ዘጠኙ ቅዱሳን እየተገኙ ይዘምሩ ነበር፡፡ በዚህ ዘመን የነበረው ሊቁ ቅዱስ ያሬድም ተቀጸል ጽጌ ገብረ መስቀል ፀዬጌ ብሎ ጣዕም ባለው ዜማ የፀዬ ገብረ መስቀልን ልብ ደስ አሰኝቶታል፡፡

አንድ የታሪክ ማስታወሻ በፀዬ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት የተደረገውን ይህን ሥርዓት ሲናገር እንዲህ ይላል:- ንጉሡ የነጭ የጥቁር የቀይ እበባ የእንቁ ፈርጥ ያለበት ዘውድ ደፋ ተቀዳጀ ያን ጊዜ ካህናቱ ተቀጸል ጽጌ እያሉ አሸበሸቡ፣ ሴቶችም ሕፃናቶች አበባ ይዘው ዘመሩ ተቀጸል ጽጌ ማለት የተለመደው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው ይላል፡፡ ተቀጸል ማለት ተቀዳጀ ማለት ሲሆን፤ ጽጌ ማለት አበባ ማለት ነው፡፡ አበባ የምድር ጌጥ ነው፡፡ ዘውድም የአገር ጌጥና ክብር ስለሆነ፤ አበባ በእግዚአብሔር ስጭነት ከእፅዋት ከአዝርእት ራስ ላይ እንዲገኝ ዘውድም ከነገሥታት ራስ ላይ የሚገኘው በእግዚአብሔር ስጭነት በመሆኑ ዘውድን አበባ ብለውታል፤ በአበባ መስለውታል፡፡ የተቀጸል ጽጌ በዓል





በዚህ ዓይነት እስከ ዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ደርሶ በዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት መስከረም 25 ቀን መከበሩ ቀርቶ በመስከረም 10 ቀን እንዲከበር ተወሰነ፡፡ ይህም ከዚህ ቀጥሎ እንደምናየው በበዓላት መደራረብ ምክንያት እንደሆነ በቂ መረጃ እናገኛለን፡፡

የመስከረም ወር ከዚህ በፊት 4 በዓላትን ያስተናግድ ነበር፡፡ ይህም መስከረም 1 ቀን ዘመን መለወጫ፤ መስከረም 10 ቀን ግማደ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ የገባበት፤ መስከረም 17 ቀን እፀ መስቀሉ እሌኒ ንግሥት ያስወጣችበት፤ መስከረም 25 ቀን ክረምት መውጫ የእበባ ጉንጉን በማቅረብ በአክሱም ዘመነ መንግሥት ከዐፄ ገብረ መስቀል ጀምሮ የሚከበርበት (ይህ ከላይ ያየነው በዓል ሲሆን) በአንድ ወር ውስጥ አራት በዓላትን ማክበር አመቺ ባለ መሆኑ የክረምቱ መውጫ በዓል ከግማደ መስቀል በዓል ጋር ተጣጥቶ ለብዙ ጊዜ ሦስቱ ብቻ ሲከበር ቆየ፡፡ ስለዚህ ነው መስከረም 10 ተቀጸል ጽጌ የሚባለው፡፡ ይህ በዓል እስከ 1966 ዓ.ም. ሲከበር ቆይቶ ከዚያ ፍፁም ሃይማኖታዊ ጠባይ ወስዶ (ይዞ) በአፀደ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ይከበራል፡፡

መስከረም 10 ቀን በዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ከብዙ ንዋየ ቅድሳት ጋር ግማደ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ ገባ በዚህም ምክንያት «ፀዬ መስቀል» የሚል ተደራቢ ስምን አገኘ፡፡ ይህ ዕለት በዓል እንዲሆን ሌላ ተጨማሪ ምክንያት ነበር፡፡ ይህም ፀዬ ዳዊት ወደ ተለያየ ማንኛውም ቦታ ጉዞ ለማድረግ ሲያስቡ የሚነሱት ወር በገባ በ10ኛው ቀን ነበር፡፡ ይህ ቀን ፀዬ ዳዊት የተወለዱበት በኋላም የነገሡበት ቀን ነው፡፡ ስለሆነም የፀዬ መስቀልን በዓል አክብረው መስከረም 25 እንደገና የተቀጸል ጽጌ «የአበባ በዓል» ለማክበር አስቸጋሪ ስለሚሆን በመስከረም 25 ይከበር የነበረውን የአበባ በዓል በመስከረም 10 እንዲከበር ተደረገ፡፡ ስለዚህ በዓሉ «ተቀጸል ጽጌ/ፀዬ መስቀል» እየተባለ ይጠራል፡፡[32]

[32] ሕይወት በቤተ ክርስቲያን ገፅ 376፤ ዜና ቤተ ክርስቲያን ልዩ እትም መስከረም 10 ገፅ 17፤ መስቀል ገብረ ሕይወት ገፅ 13-14፡፡



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አምስት

## አምስተኛው ወርቃማ ዘመን

[ከ912 - 1500 ዓ.ም.]

በዚህ ዘመን የምናተኩርባቸው አበይት ነገሮች:-

- ❖ የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት፤
- ❖ ስብከተ ወንጌል መስፋፋትና ሥነ ጽሑፍ መዳበር፤
- ❖ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም፤
- ❖ ገዳማት መተከል በጣና ሐይቅ ዙሪያ፤
- ❖ አባ ጊዮርጊስና ሥነ ጽሑፍ፤
- ❖ የግማደ መስቀል መግባት፤
- ❖ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብና መንፈሳዊ ሥራዎቹ፤
- ❖ በዚህ ወርቃማ ዘመን የተነሡ ቅዱሳን አባቶች፤

## ክፍል አንድ

### የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት

*ስለነዚህ (ስለ ላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት) ሥራዎች ብዙ ብጽፍ የሚያምነኝ ሰው መኖሩ በጣም ያሳስበኛል፣ ያስጨንቀኛል:: እስከ አሁን ያልኩትንም እንኳ ቢሆን «ውሸት ነው» የሚሉኝ:: ነገር ግን የጻፍኩት በሙሉ እውነት ለመሆኑ በኃያሉ እግዚአብሔር ስም እምላለሁ:: እንደውም ከዚህ በላይ ማለት ይቻላል:: ሆኖም በቀጣፊነት ስሜ እንደማይነሳ ተስፋ አደርጋለሁ::*

[ከ1512-1518 ዓ.ም. ጀምሮ ለ6 ዓመታት በስሜኑ የአገራችን ክፍል ሲዘዋወር የነበረው ፖርቱጋላዊው ካህንና ታሪክ ዘጋቢ





ፍራንሲስኮ አልቫሬዝ «የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት» ለመጀመሪያ ጊዜ ተመልክቶ ካሰፈረው ጽሑፍ የተወሰደ::]

የአክሱም መንግሥት ወደ ላስታ ሲዘዋወር በዛጉዬ (በላስታ) ከነገሡት ነገሥታት ብዛታቸው 11 ናቸው:: እነ ሱም መራ ተክለሃይማኖት፣ ጠጠውድም፣ ጃን ስዩም፣ ግርማ ስዩም፣ መይራሪ፣ ሀርቤይ፣ ይምርሐነ ክርስቶስ፣ ቅዱስ ሐርቤ (ገ/ማርያም)፣ ላሊበላ፣ ነአኩቶ ለአብ፣ ይትባረክ ይባላሉ:: የእነዚህ 11 ነገሥታት የግዛት ዘመናቸው በአጠቃላይ 333 ዓመት ይሆናል:: ከ922-1268::[1] ከእነዚህ ነገሥታት መካከል ስመ ጥሩ የሆነውና በመላው ዓለም የታወቀው ቅዱስ ላሊበላ ነው:: ላሊበላ ላስታ ውስጥ ከነገሡት ከ11ዱ ነገሥታት መካከል 9ኛው ሲሆን፣ ዣን ስዩም ከተባለው አባቱና ኪረወይና ከተባለችው እናቱ በ1120 ዓ.ም. ታህሳስ 29 ቀን ተወለደ:: ላሊበላ ማለት በላስታዎች ትርጉም «ንብ የተነበየለት» ማለት ነው:: ይኸውም ሲወለድ ንቦች ከበውት ስለነበር ይህን ስም አወጡለት::[2] ላሊበላ ከአባቱ መንግሥትን ወርሶ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ መሆኑን አወጀና መስቀል ክብራ የተባለችውን ከላስታ ባላባት የተወለደችውን አግብቶ፤ «ገብረ መስቀል» መባልን ስመ መንግሥቱ አድርጐ በ1160 ዓ.ም. ሥርዓተ ንግሡን ፈፀመ::

ቤተ መንግሥቱን መካነ ልዕልት ብሎ ሰይሞ ቦታው ላይ ቤተ መንግሥት ሠራ:: በዚያው አቅራቢያ ታላላቅ ቋጥኝ ድንጋዮች መኖራቸውን ስላረጋገጠ በግዛቱ የሚገኙትን ዜጐቹን አዟቸው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ማነፅ ጀመረ:: የሥራው መሪ ምንም ራሱ ቢሆንም በዘመኑ የነበሩት ዜጐቹ ሁሉ ጥበብ ተገልጾላቸው በፈቃደ እግዚአብሔር እየተረዱ ሥራውን እያፋጠኑ ይሠሩ ነበር:: ላሊበላም የሥራው መሪ ብቻ ሳይሆን እንደ ሕዝቡ በጉልበቱ ይሠራ ነበር:: የሥራው ዘመን በ23 ዓመት እንዳጠናቀቀው ይነገራል:: የቦታውንም ስም ለተወለደበት ሥፍራ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ «ሮሐ» አለው::

---

[1] ዋዜማ ገፅ 26::

[2] ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ትንሣኤ ታሪክ ገፅ 180::



www.ethiopianorthodox.org

ላሊበላ በአጠቃላይ ከአለት ተፈልፍለው ያሠራቸው አብያተ ክርስቲያናት በመላው ኢትዮጵያ 23 ይደርሳሉ። ንጉሥ ላሊበላ በተወለደ በ80 ዓመቱ በነገሠ በ40 ዓመቱ በ1197 ዓ.ም. አረፈ። የተቀበረውም ራሱ ባሠራው በቤተ ጐልጎታ ነው።

ላሊበላ በነገሠበት ዘመን በመካከለኛው ምሥራቅ ሦስተኛው የመስቀል ጦርነትይካሔድ ነበር። ይህ ጦርነት ዓላማው ኢየሩሳሌምን ከእስላሞች እጅ ለማላቀቅ ስለነበር ወደ መካከለኛው ምሥራቅ የሚደረገው ጉዞ ስለተቋረጠ፤ ሁለተኛዋን ኢየሩሳሌምን ኢትዮጵያ ውስጥ ለመፍጠርና ክርስቲያኖች ምእመናን ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ያደርጉት የነበረውን ረጅም፣ አስቸጋሪና አድካሚ የእግር ጉዞ ለማስቀረት ነበር። የሕንፃዎቹ ስምና አሠራራቸው የራሳቸው የሆነ ውበት አላቸው። ቤተ መድኃኔዓለም፣ ቤተ ማርያም፣ ቤተ ሚካኤል፣ ቤተ ደናግል፣ ቤተ ጎልጎታ፣ ቤተ መስቀል፣ ቤተ አማኑኤል፣ ቤተ መርቆሬዎስ፣ ቤተ ገብርኤል፣ ቤተ ሊባኖስ፣ ቤተ ጊዮርጊስ በመባል ይታወቃሉ። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በሦስት ምድብ የተከፈሉ ናቸው።

1. ቤተ መድኃኔዓለም
2. ቤተ ማርያም
3. ቤተ ሚካኤል
4. ቤተ መስቀል
5. ቤተ ጎልጎታ
6. ቤተ ደናግል [ምድብ 1 ናቸው]
7. ቤተ አማኑኤል
8. ቤተ መርቆሬዎስ
9. ቤተ ገብርኤል
10. ቤተ አባ ሊባኖስ [ምድብ 2 ናቸው]
11. ከሁለቱ ምድቦች ፈንጠር ብሎ የሚገኘው ደግሞ ቤተ ጊዮርጊስ ምድብ 3 በመባል ይከፈላሉ።

ከእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ቤተ መድኃኔዓለም በግዙፍነቱ፤ ቤተ አማኑኤልና ቤተ ማርያም በፎቅነታቸው፤ ቤተ አባ ሊባኖስ ከዋናው አለት ጋር የተያያዘ በመሆኑ፤ ቤተ ጊዮርጊስ በመስቀል ቅርፅ በመሠራቱና ረቂቅ የኪነ ሕንፃ ጥበብ የተከናወነበት በመሆኑ የየራሳቸው ልዩ





ባሕርይ አላቸው። ይሁን እንጂ 11ዱ አብያተ ክርስቲያናት በመጠንና በጥበባዊ አሠራራቸው የየራሳቸው ውበት ልዩ መለያ አላቸው። የሕንፃዎቹ አሠራር እንደሚከተለው እናያቸዋለን።

## ቤተ ማርያም

ከአሥራ አንዱ አብያተ ክርስቲያናት በአሠራር የመጀመሪያዋ ናት። ሦስት ድርብ የሆነ ፎቅ ነው። ቤተ መቅደሱ በጥንታዊ ሥዕሎች የሸበረቀ ከመሆኑም በላይ ልዩ ልዩ ዓይነት የሆኑ ምልክቶች በስዕልም በቅርፅም የተሠሩ ይታዩባታል። ይህች በቀዳሚነት የተሠራች ከመሆኗም በላይ ዙሪያዋ (በማሜጋሪ) የተከበበች መግቢያዋ በቤተ መድኃኔዓለምና በምዕራብ በኩል ሲሆን ከመግቢያዋ ውስጥ በሰሜን በኩል አንድ ጥልቅ የሆነ ባሕርና አንድ በሰው ቁመት ልክ የሚሆን ባሕር አላት። እንዲሁም ቤተ መቅደሷ ሦስት በር ሲኖራት በውስጧ 12 አምዶች ይገኙባታል። ከቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት /ዓምደ ብርሃን/ የተሠኘች ከምድር እስከ ጣሪያው በሥዕልና በጽሑፍ ያጌጠች በመጋረጃ የተለበጠች ረዘም ያለ ዓመት ያላት ካህናቱ ከፍተኛ ክብርና እንክብካቤ የሚያደርጉላት ታሪካዊት አምድ ይገኝባታል። ይህ አምድ በዘመኑ ስለ ቤተክርስቲያኖቹ አሠራር የተነገረውን ጽሑፍ የያዘ ነው በማለት ይጠረጠራል።

ቤተ ማርያም በውስጥ በኩል ጣሪያዋና ግድግዳዋ በተለያዩ ብሩህ የሆነ ቀለማት ያጌጡ ስዕሎች ለምሳሌ የጻድቃን፣ የሰማዕታት፣ የሐዋርያት በተጨማሪ የአእዋፍ የእንስሳትን በሰው መልክ በጣም በሚያስደንቅ የድንጋይ ላይ ሥዕል አሸብርቃለች። መስኮቶቿ እንደሌላው በቅርፅ አይመስለውም። ለሁሉም ታሪክ አላቸው ከቤተ መቅደሱ (መንበሩ) ግራና ቀኝ ሁለት ክፍሎች አሏት። እነዚህም ብዙ ተንቀሳቃሽ ነዋየ ቅድሳትና አልባሳት፣ መጻሕፍትን ይዘዋል። እንዲሁም ላሊበላ ሕንፃውን ያነፀበት መጥረቢያና ይጸልይበት የበረው ክብ የሆነ እርሳስ ይገኝበታል። በውጭ በኩል ጋራው



www.ethiopianorthodox.org

ጥግ ቤተ መስቀልና ቤተ ደናግል ሕንፃዎች ዙሪያውን አጅበው ይገኙባታል።

## ቤተ መድኃኔዓለም

ይህ ሕንፃ ከሥፋቱ የተነሳ «ቤተ አባይ» ተብሎ ነው የሚጠራው። ከአስሩ ጽርሐ ቤተ ክርስቲያናት በስፋቱ ልቆ የሚገኝ እርሱ ነው። እጅግ ጥበብን የሚጠይቅና በአስደናቂ ሁኔታ ከተሠሩት ሕንፃዎች መካከል ረጅሙና ሰፊው ግርማ ሞገስ ያለው የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ርዝመቱ 33.7 ሜትር፤ ስፋቱ 23 ሜትር፤ ከፍታው 11.50 ሜትር ያህል ነው። በውስጡም የአለቱን ጣራ የሚደግፍ 28 አምዶች ይገኛሉ። ሕንፃው በአጠቃላይ 72 ዓምዶች አሉት። እንዲሁም ሦስት በሮች በሰሜን፣ በምዕራብ፣ በደቡብ በኩል ይገኛሉ። ይህ አንጋፋ ሕንፃ ውስጡ ፍፁም ጠንካራ አለት ነው። መስኮቶቹ የከዋክብትና የጨረቃ ምስሎችን አቅፎ ይዟል። በመንበሩ ግራና ቀኝ ሁለት የእቃ ክፍሎች አሉት። በውስጡ በጥንቱ ጊዜ የኃያላን ጋሻዎች የነበሩ በጣሪያው ተንጠልጥለው ይታያሉ። እንዲሁም በላሊበላ ዘመን የነበረ አንድ መስቀል የሐዋርያትን ቁጥርና የክርስቶስን አቀማመጥ የያዘ ከአምዶቹ በአንደኛው ፍልፍል ውስጥ ተቀምጦ በመገኘቱ በዚሁ ቤተ መቅደስ አለ። የወጣበትም ሥፍራ በግልፅ ይታያል። እንዲሁም ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የኖረ በመሀከሉም በጥንታዊው ግሪክኛና፣ በአረብኛ በግዕዝ ቋንቋ የተጻፈበት አንድ የአዲስ ኪዳን ወንጌል አለ።

## ቤተ ጎልጎታ (ሚካኤል)

በመሠረቱ የላሊበላ ሕንፃዎች በኢየሩሳሌም ሀምሳል የተሠሩ ናቸው። ይሁን እንጂ ይህ ሕንፃ በውጭ በኩል ምንም ቅርፅ የያዘ ሳይመስል ውስጡ ግን ዋና የታሪክ መደብር ነው። በአጠገቡ ብዙ ዋሻዎች አሉት። እነሱም «ቀራንዮ» የተባለ ራሱን የቻለ እንድ ቤተ መቅደስ የሚቆጠር ግንብ የማይገለገሉበት፤ ሁለተኛ «የአዳም መቃብር» የተባለች





አነስተኛ ፎቅና ምድር ቤት ሕንፃ ይገኛል። ከቤተ ማርያም ወደ ጎልጎታ የሚወስድ አንድ ትንሽ ባሕር ያለባት ጨለማ መንገድ አለ። ይህ ቤተ ክርስቲያን ሁለት በሮች ብቻ አሉት። መጀመሪያ ገባ እንዳሉ «ደብረ ሲና» የኪዳነ ምሕረት መንበር ያለበት ይገኛል። ከዚያም ውስጥ ውስጡን ፊትን ወደ ሰሜን መልሶ በቀጥታ ቅኔ ማህሌቱን አቋርጠው እንዳለፉ አንድ በር አለ። እንደገቡ ስፊ የሆነ ቤተ መቅደስ ይገኛል።

ከዚያም በስሩ የላሊበላ መቃብር ሆኖ ላዩን ከራሱ ላይ ከሕንፃው ተያይዞ የተፈለፈለ የክርስቶስ መግነዝ ይገኛል። ከፍ ብሎ ወደ ላይ ቀና ሲሉ በዋሻ መልክ የተሠራች «ደጋ» የሆነች ናዝሬት የምትባል ትታያለች። በቀጥታ ያንን ሁሉ አይተው ወደ ቀኝ ሲመለከቱ ትንሽ ክፍል ውስጥ በጣም ጠባብ የሆነች «ጎል» የተሠኘች በሀረግ የተንቆጠቆጠች ስትሆን አይተው እንደወጡ እንደገና ሌላ ክፍል ይገኛል፤ እዚህ ክፍል ውስጥ እንደተገባ በጣም ስፋት ያለው መቅደስ አለ። ከዚህም ውስጥ ከሕንፃው ጋር ተያይዘው ወጥ ሆነው የተቀረፁ ሦስት የሥላሴ መንበር ታሪክን ያቀፈ የአንድነትና የሦስትነት አምሳል [ገጸ ላህም፣ ገጸ ሰብዕ፣ ገጸ አንበሳ፣ ገጸ ንስር] መልክ ያለበትን አይቶ ወደ ላይ ቀና ሲሉ ክርስቶስ ሲያርግ ያለበት ቅርስ ይገኛል።

ቤተ ጎልጎታ በቅርሳ ቅርስነቱ ሀብታም ነው። ግድግዳው በየመአዘኑ የጻድቃንና የሐዋርያትን ሐውልት መስል ቅርፅ ከሕንፃው በልዩ መልክ በገሀድ የሚናገር የሚመስል መስቀል የያዘ የሰው ቅርፅ ይታያል። እንዲሁም ቅዱስ ላሊበላ በዘመነ መንግሥቱ የነበረ መስቀልና የራሱ መቋሚያ ይገኛል። በእውነቱ ይህ የጎልጎታ /የሚካኤል/ ቤተ ክርስቲያን በውስጡ ይህ ነው የማይባል ቅርስ አለበት። ጎልጎታ የተባለው የሥፍራ ስም ሲሆን በውስጡ የቅዱስ ሚካኤል መቅደስ ይገኝበታል። የቅዱስ ላሊበላ ሕንፃ ውስጥ የሚገኙ መቅደሶች 10 ናቸው።



www.ethiopianorthodox.org

## ቤተ አማኑኤል

ከቤተ መድኃኔዓለም ቀጥሎ በስፋት የሁለተኛነትን ደረጃ የያዘ ነው:: እንደዚህ ቤተ ክርስቲያን ደስ የሚል የውጭ ቅርፅ የያዘ የለም:: በውጭ በኩል ያሉት የህረጐች እረቂቅነት ምን ያህል መጠበብን ስናይ እራሳችንን ወደ መጠየቅ እንደርሳለን! እንዴት ሲቀረፅ አይበላሽም? እንዴትስ አይፈርስም? መሳሳትስ እንዴት አይኖርም? ለዚህ ሁሉ ግሩም! ማለት ብቻ ነው:: የቤተ ክርስቲያኑ አሠራር በሁለት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን ምድር ቤትና ፎቅ ነው:: የምድር ቤቱና የፎቁ ሁኔታ ከቤተ ማርያም ጋር ይመሳሰላል:: ቤተ አማኑኤል ብዙ ተጠላላፊ የዋሻ መንገድ አለበት:: በመሬቱ ውስጥ ለውስጥ የሚያስኬድ በጥሩ ቅርፅ እየተዘዋወረ የታነፀ 100 ሜትር ርዝመት ያለው አንድ የምድር ውስጥ መንገድ አለበት:: ይህ ከቤተ አማኑኤል ቅኔ ማሕሌት እስከ ቤተ መርቆሬዎስ ቤተ ክርስቲያን ድረስ የሚያስኬድ ነው:: ቦታውም በመጨለሙ ምክንያት የአገሩ ሰው በሲኦል አምሳል የተሠራ ነው ሲል ይተረጉመዋል::

ቤተ ክርስቲያኑ እንደሌሎች በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምዕራብ መግቢያ የሚሆኑ ሦስት በሮች አሉት:: በስሩ ማለትም በከርሰ ምድር ጥልቅ የሆነ የጨለማ መንገድ ወደ ቤተ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የሚወስድ መንገድ አለው:: ቤተ አማኑኤል በውጭ በኩል በስተ ምሥራቅ አንድ የመነኮሳት ገዳም የሆኑ 12 ዋሻዎች ይገኙበታል:: እነዚህም ለምነና የሚሔዱ ማረፊያ ናቸው:: ዋሻዎቹ እንዲሁ ካላጋጠማቸው በስተቀር ቱሪስቶች ሆን ብለው አይጎበኟቸውም::

## ቤተ መርቆሬዎስ

ቤተ መርቆሬዎስ ምንም እንኳ ግማሽ አካሉ ፈርሶ ፅላቱ፣ ንዋየ ቅድሳቱ ከቤተ አማኑኤል ቢዳበልም ቤተ ክርስቲያኑ ጥንት ትልቅ የነበረ ይመስላል:: አሁን አልፎ አልፎ አምዶች ብቻ ይታያሉ እንጂ ሙሉ ሆኖ እንደነበረው አልተገኘም:: ቤተ መቅደሱ ከመፍረስ የተረፈ ሆኖ በአንድ





አነስተኛ ሥፍራ ላይ በግንብ ተከልሎ ይቀደስበታል:: ለታሪክም ያህል ጥንታዊነቱን ሳይለቅና ሳይጠፋ በቅርንጫፍ ይሠራበታል:: ይህ ቤተ መቅደስ አካባቢው በብዙ ዋሻዎች የተከበበና ፍፁም ፀጥታ የሰፈነበት ነው:: የሰው ድምፅ በሩቅ የማይሰማበት በመሆኑ አምስት ደቂቃ ለመቆም ሆድ ያባባል:: ካህናቱ ግን ስለለመዱት ምንም አይመስላቸውም:: እንዲያውም ለጸሎት ሲሉ እዚያው የሚያድሩ አሉ::

በቤተ መርቆሬዎስ ቤተ ክርስቲያን ግድግዳ ላይ ለበረከት ያህል ከጥንታዊዎቹ ሰአሊዎች የተላለፈ ስዕል አሉበት ከእነዚህ አንዱ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ንጉሠ ነገሥቱ ካዩት በኋላ በጥንት ሁኔታው እንዲጠገን ለአዋቂዎች ተሰጥቶ በጀርመን አገር ተሠርቶና ተመልሶ አዲስ አበባ ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር ሕንፃ ውስጥ ተቀምጧል:: ስዕሉ የ800 ዓመት እድሜ እንዳለው በተመራማሪዎች ተመስክሮለታል::

## ቤተ አባ ሊባኖስ

ይህ ቤተ ክርስቲያን ከጣሪያው በኩል ከተራራው ጋር የተያያዘ ነው:: ደግሞ የዚህ ሕንፃ አሠራር ልዩ ስለሆነ ለአይነት የተሠራ ነው ይባላል:: በንድ በኩልም ደግሞ ሕንፃዎቹን የፈለፈላቸው ይህን ከሚያህል ተራራ (ደንጊያ) መሆኑን ለማመልከት ሲል የተወው ይመስላል:: ሕንፃው እንደ አምድ ሆኖ ዋሻውን ተሸክሞታል:: ቤተ መቅደሱ መጠነኛ ከመሆኑም በላይ ድንጊያው እንደሌላው ጠንካራ ባለመሆኑ የጨው ባሩድ አመንምኖት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ (1904-1922 ዓ.ም.) አስጠግነውታል:: ከመንበሩ ውስጥ ከመንበሩ በላይ ወደ ጣሪያው ጠጋ ብሎ በጠባብ ቀዳዳ የሾለከ ብርሃን የሚመስል እንደ ብልጭታ ሌትና ቀን ሳያቋርጥ ይበራል:: በአጠገቡ ሲደረስበት በሕንፃው በኩል ምንም የሚታይ ነገር የለም:: የውጭ አገር ቱሪስቶች ይህን ቀዳዳ እየመሰላቸው ዘንግ ለማሾለክ ይሞክሩና ተጠግተው ሲዳስሱት ከሕንፃው በቀር ምንም ነገር አይገኝም::



www.ethiopianorthodox.org

ነገር ግን ይህ ነገር ብርሃን የሚሰጡ ድንጋዮች ስላሉ ከእነዚያ አንዱ ይሆናል በማለት ያስባሉ። ቤተ ክርስቲያኑም የአገሩ ሰው በልማድ የላሊበላ ሚስት በነበረችው በመስል ክብራ ስም ይጠሩታል። በእውነቱ ይህ ቤተ ክርስቲያን የመስኮቶቹ፣ የበሩ፣ የህረጉ አቀራረፅ በጣም የሚያሳሳ ከራሱ በላይ የተሸከመው ገደል ማለትም ተያይዞ በመሠራቱ ቤተ መቅደሱን የሚጫነውና የሚሰብረው ስለ ሚመስል ያስጋል። ግን ከጨው ባሩድ በስተቀር ከድሮው ምንም ለውጥ አላሳየም፤ አልቀነሰም። ቤተ ክርስቲያኑ እንደሌሎች ሕንፃዎች ሦስት በሮች አሉት። ራሱን የቻለ ክፍል እንደመሆኑ ዋሻ ነው ሊባል አይገባም ምክንያቱም ጣሪያው ከገደሉ የተገኘ እንጂ ዙሪያውን መዞር ይቻላልና።

## ቤተ መስቀል

ራሱን ሳይችል ማለትም እንደ ዋሻ መልክ ቢሆንም በውጭ በኩል ገፅታው በሐረግ ያሸበረቀ ነው። ከበሩ መግቢያ ግራና ቀኝ ሁለት አምዶች ቆመዋል። እንዲሁም ለመግቢያ ሁለት በሮች ይገኛል። አንዱ ለቅኔ ማህሌት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ወደ መቅደሱ መግቢያ ያገለግላል። ከውስጥ ሲገቡ ወደ መቅደሱ ሲመለከቱ የየመስኮቶቹ አቀማመጥ፣ የአምዶቹ አሰላለፍ ልዩ ነው። ከውስጥ በግራ በኩል ያለው ትልቅ መስኮት አዘቅዝቀው ሲመለከቱት ወደ ቀራንዮ (በቤተ ጎልጎታ) በቀጥታ የሚወስድ መንገድ ይታያል።

## ቤተ ደናግል

ከቤተ ማርያም በስተግራ በኩል የሚገኝ ሕንፃ ሲሆን በምዕራብና በሰሜን በኩል ሁለት መግቢያ በሮች አሉት። በተለይ የምዕራቡ በር ቅርፅ ግሩም ከመሆኑም በላይ ወደ ጎልጎታ ከሚወስደው ትንሽ የጨለማ መንገድ ፊት ለፊት ትይዩ ሲሆን፤ ውስጡ ፍፁም ጠንካራና ጥቁር አለት ነው። እንኳን ቅርፅ ሊሠራበት ይቅርና መጥረቢያ ሲያርፍበት





ብልጭ የሚል ነው የሚመስለው። እንደማንኛውም ቤተ ክርስቲያን አምዶች አሉት። በመንበሩ አናት ፊት ለፊት ከጣሪያው እንደ ገበታ መሠል ሆኖ በህረግ ያሸበረቀ ነገር አለው።

## ቤተ ገብርኤል

የዚህ ቤተ ክርስቲያን ርዝማኔ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የበለጠ ነው። የመጀመሪያው አሠራር ፎቅና ምድር ቤት ሲሆን፤ ምድር ቤቱ በውሀ ስጥሞ መቅደሱ ፎቅ ላይ ሆኗል። የጥንቱ መግቢያ በመዳፈኑና በመጥፋቱ ከአንዱ አፋፍ ወደ አንዱ አፋፍ በእንጨት ድልድይ ተሸጋግሯል። በቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ ከመሬት 12 ሜትር ያህል ቁመት፣ 15 ሜትር ርዝማኔ፣ 70 ሴንቲ ሜትር ስፋት ያለው የመንግሥተ ሰማያት መንገድ የሚባል አንድ መንገድ አይነት ሆኖ የተዘረጋ ድንጋይ አለ። በአገሩ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች «መፈራረጃ» ይሉታል። «ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚያስኬደው መንገድ ጠባብ ነው። በዚያም የሚያልፉ ጥቂቶች ናቸው» ማቴ. 7÷13፤ ተብሎ በቅዱስ ወንጌል በተነገረው አምሳል የተሠራ ነው።

## ቤተ ጊዮርጊስ

ይህ ቤተ ክርስቲያን ከ10ሩ ሕንፃዎች በመልክ፣ በመጠን፣ በቅርፅ፣ በይዘትም አንዱንም አይመስልም። ቤተ ጊዮርጊስ ሦስት በሮች፣ ሰባት ደረጃዎች፣ 12 መስኮቶች አሉት። ከእነኚህ ከአለት ተፈልፍለው ከተሠሩት አብያተ ክርስቲያናት ልዩ ሆኖ በልጦ የሚታየው ምሳሌም የሌለው የቤተ ጊዮርጊስ ሕንፃ በሁለት ወንዞች መገናኛ አቀበትና ቁልቁለት በሆነ ንጣፍ ድንጋይና ደልዳላ ቦታ ላይ ከሌሎች ፈንጠር ብሎ የተሠራ ነው። ከወለሉ እስከ ጣሪያው እንደ መስቀል ሆኖ ተቀርጿል። በጣሪያው ላይ ውሀ እንዳይቋጥር ሆኖ ማፍሰሻ አሸንዳ የድንጋይ ቧንቧ ተቀርጾለታል። በእውነት ያስደንቃል ይህ ሁሉ ተጠንቶ መሠራቱ በመስኮቱም



www.ethiopianorthodox.org

ላይ ልዩ ልዩ ቅርጾች አሉበት:: ከውስጥ በኩል በመንበሩ አቅጣጫ የሚውለው የጣሪያ ሥራ እንደ እንቁላል ግማሽ የተከበበ ሆኖ የመስቀል ቅርፅ አለበት::

ከሌሎች ድንጋዮች ሁሉ በጥንካሬና በውበትም ይበልጣል:: በሕንፃው ላይ በማርጀትና በመኖር የደረሰበት ጉዳት የለም:: ቤተ ጊዮርጊስ ቁአብዛኛው በአገራችን በሚወጡ ፖስተሮች የታወቀ ነው:: በውጭውም ዓለም አስደናቂ ነገሮች ከሚባሉት አንዱ ስለሆነ ቅርስነቱ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የዓለም ሀብት መሆኑን ዩኔስኮ አረጋግጦለታል:: በጠቅላላው የቤተ ጊዮርጊስ ሕንፃ የሚማርክ ውበት ያለውና ፍፁም የተቀናጀ የጠቢባን ሀሳብ የሚታይበት ረቀቅ ጠለቅ ያለ የሕንፃ ጥበብ የሚታይበት ሥራ ነው::[3]

የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ለ333 ዓመት ድረስ እንደ ቆየ በዚህ ወርቃማ ዘመን በመግቢያ ላይ ተመልክተናል:: በእነዚህ ዓመታት ውስጥ የነገሡት 11 ነገሥታት የውጭ አመራራቸው በጣም ሰላማዊ ነበር:: በዙሪያው ከመሸጉት እስላሞች ጋር በሰላም ለመኖር አስችሏቸዋል:: ለምሳሌ ቅዱስ ላሊበላ በነበረበት ዘመን ሦስተኛው የመስቀል ጦርነት በናዝሬት፣ በጥብርያዶስ መካከል የተፋፋመ ጦርነት ተደርጐ ነበር:: በዚህ ጦርነት ሳላዲን የተባለው በእስላሞች የሚመራው ጦር በካቶሊኮች የሚመሩትን የእንግሊዝ፣ የጀርመንን፣ የፈረንሳይን ነገስታቶችን የእነዚህን ሁሉ ጦር አሸንፎ ኢየሩሳሌምን መልሶ በቁጥጥሩ ስር አደረገ:: ሳላዲን በዚህ በሦስተኛው የመስቀል ጦርነት ድል አድርጐ ኢየሩሳሌምን ሲይዝ በጎልጎታ በሚገኘው በቅዱስ መቃብር አጠገብ ያለውን፣ እሌኒ ንግሥት ቅዱስ መስቀሉን ያስወጣችበትን ዋሻና በቤተልሔም ጌታ የተወለደበትን ጎል ለቅዱስ ላሊበላ በስጦታ ያበረከተ መሆኑን «ኤዎፌቶስ» የተባለ ቆጶሮሳዊ የቤተ ክርስቲያን ጸሐፊን በመጥቀስ አባ ጎርጎሪዎስ በጻፉት መጽሐፍ

[3] ዜና ላል ይበላል፣ ትንሣኤ ቁጥር 124-125::





ገልጸውታል::[4] ይህ የሚያመለክተን ቢኖር በዲኘሎማሲያዊ አመራራቸው በሳል መሆናቸውን ነው::

ከ11ዱ ነገሥታት ውስጥ ለ4ቱ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቅድስና ማዕርግ ሰጥታቸዋለች:: እነዚህም ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ፣ ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ፣ ቅዱስ ሐርቤ፣ ቅዱስ ላሊበላ ናቸው:: ከእነዚህ ውስጥ በተደጋጋሚ እንደ ገለፅነው ዘመኑን በፍፁም መንፈሳዊ ተግባር ያሳለፈው ቅዱስ ላሊበላ በዘመኑ ያሠራቸው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን መላውን ዓለም ሲያስደንቅ ይኖራል:: ስለነዚህ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ብዙ የውጭ አገር ሰዎች በሥነ ጽሑፎቻቸው አስፍረዋል:: ከእነዚህም ውስጥ 3ቱን እንደሚከተለው ቀርበዋል:-

1. ፍራንቺስኮ አልቫሬጽ (Francisco Alvares):- በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ይህን ሰው የምናስታውሰው ከግራኝ አህመድ ወረራ ቀደም ብሎ ማቴዎስ የሚባል የአርመን ተወላጅ ከዐፄ ልብነ ድንግል ባለቤት ከንግሥት እሌኒ ወደ ፖርቹጋል መንግሥት ከተላከ በኋላ ለተላከው ደብዳቤ መልስ የፖርቹጋል ንጉሥ አማኑኤልና የሮማ ሊቀ ጳጳስ ልዮን 15ኛ ወደ ሀፄ ልብነ ድንግል በ1520 ዓ.ም. ከላኳቸው መልእክተኞች አንዱ ፍራንችስኮ አልቫሬጽ ነው:: ይህ ሰው ኢትዮጵያ በነበረበት ዓመታት ራሱ ላስታን አንድ በአንድ የተመለከተ ሲሆን ወደ አገሩ ሲመለስም በዚህ ወርቃማ ዘመን የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት በሚለው ርእሳችን ለመግቢያ የተጠቀምኩበትን የተናገረው እርሱ ነው::

2. ጀራልድ ሮልፍ (Gerhard Rohlfs):- ይህ የጀርመን ተወላጅ ሲሆን በኢትዮጵያና በአፍሪካ ከ1865-1870 ዓ.ም. ቆይቶ ነበር:: ቅዱስ ላሊበላ የተቀበረው በጎልጎታ መሆኑን ከሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ሥራ በተለይ የቤተ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ሥራ ይበልጥ ማማሩን ገልጧል:: ከቅድስት አገር ከኢየሩሳሌም አስመጥቶ ቅዱስ

[4] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገፅ 39::



www.ethiopianorthodox.org

ላሊበላ ያስተከላቸውን ሰባት ያህል የወይራ ዛፍ ማየቱን ይገልጥና፤ በመጨረሻ የእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ሥራ የመሰለ በዓለም አለመኖሩን ያረጋግጣል::

3. አሺል ራፍሬይ (Achille Rafray):- ይህ ሰው በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ቆንስል የነበረ ሰው ነው:: እ.ኤ.አ በ1882 የቅዱስ ላሊበላ ሕንፃዎቹ የተመለከተ ሲሆን፤ የሕንፃዎቹ ማማር፣ በዚሁ አካባቢ ብአረቢኛና በግዕዝ የተጻፈ መጽ ሐፍ ማግኘቱን (መመልከቱን) መስክሯል:: የሕንጻዎቹ አቀማመጥ 5ቱ በአንድ ቦታ፤ 4ቱ በአንድ ቦታ፤ 1ዱ በሌላ ቦታ በአጠቃላይ በ3 ቦታዎች ተለያይተው መሠረ ታቸውን ገልጿል::[5] በአጠቃላይ እነዚህ የቅዱስ ላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት:-

- የኢትዮጵያ የሥልጣኔ ምንጭ እንደሆኑ ያስገነዝባሉ፤
- የባዕድ እጅ የሌለባቸው መሆኑን ይገልፃሉ::
- በሌላው ዓለም ይህን የመሰለ የኪነ ሕንፃ ጥበብ አለመ ኖሩን ይጠቁማሉ፤
- በውስጣቸው በርካታ ትውፊትን ይዘዋል፤
- በቱሪዝሙ በኩል በደንብ ቢተዋወቁ የኢኮኖሚ ገቢን ያዳብራሉ፤
- በዚያ ዘመን የነበረው ታላቅ ሥልጣኔና የቅዱሳን አባቶች ትጋት ለዛሬው ትውልድ በአድናቆት እንዲመለከተው ይጠቁማሉ፤ መጻሕፍት ሆነው ይነበባሉ::
- ከዛጉዬ ሥርወ መንግሥት በፊት የነበረው የኪነ ሕንፃ ጥበብ በእነሡ መቀጠሉን ይገልጻሉ::

[5] ከኑብያ-አክሱም እስከ ዛጉዬ ገፅ 397-399::



የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት

- ለታሪክ ተመራማሪዎች እንዴት ሠሩት? የተጠቀሙበት መሣሪያ ምን ይሆን? ምን ያህል ዘመን ፈጀ. . . ለምር ምር ይጋብዛል::
- ታሪካዊነታቸው ከሰው ልጅ ሥልጣኔያዊ ጥበቦች እንደ አንዱ ተወስደው ቅርስነታቸው የዓለም እንዲሆኑ በዩኔስኮ የተረጋገጠላቸው::

# ክፍል ሁለት

## የሥነ ጽሑፍ መዳበርና፤ ሐዋርያዊ ተልዕኮ፤ እንቅስቃሴ መስፋፋት [ከ1268-1327 ዓ.ም.]

በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ አዲስ ዓይነት የፖለቲካ ለውጥ የተካሔደበት ዘመን ነው:: የኢትዮ ጵያ ቤተ መንግሥት ሮሐ መሆኑ ቀርቶ ወደ አክሱም ተዘ ዋወረ ሰሎሞናውያኑ ሥልጣን ሲይዙ አገሪቱ ያልነበራትን ጥንካሬ ለማግኘት በቃች:: የክርስትና እምነትም በአዲስ መልክ እየተጠናከረ ሄደ:: ከግብፅ ጋር የነበራትም ግንኙነት እየታደሰ በመሔዱ የሥነ ጽሑፍ የብህትውና የምንኩስና ሕይወትም አድጓል:: በዚህን ጊዜ በዐፄ ይኩኖ አምላክ (1268-1283) ዓ.ም. ብዙ ነገሮች ተሠርተዋል:: በጣና ሐይቅ ዙሪያ የተተከሉ ገዳማት የተመሠረቱት ጥቂቶች በህፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ሲሆን፤ ይልቁንም ከይኩኖ አምላክ በኋላ የተነሳው አምደ ጽዮን ንግሥናውን ሲይዝ ብዙ ነገሮ ችን አስፋፍቷል:: ይህ የአምደጽዮን ዘመነ መንግሥት ሥነ ጽሑፍ የዳበረበት ዘመን ስለነበር «ሁለተኛው የሥነ ጽሑፍ ዘመን» ይባላል::

በዚህ ዘመን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እድገት ከፍ ተኛ ትኩረት የተሰጠበት ትልቅ ዘመን ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ይህ የሆነበት ራሱን የቻለ ምክንያት አለው::



www.ethiopianorthodox.org

ከ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ 11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ «የጨለማው ዘመን» በመባል ይታወቃል፤ ይህም የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ የተዳከመበት፣ ዮዲትን የመሰሉ የአይሁድ እምነት ተከታዮች ባደረጉት ወረራ ሥነ ጽሑፍ የጠፋበት የሚተረጐሙ ሥራዎች እንዲቆሙ የተደረገበት ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪ በሰሎሞናውያኑና በዛጉዌ መካከል የነበረው አንዳንድ አለመግባባት ለሥነ ጽሑፍ እድገት መቀዝቀዝ አይነተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል:: ይህ በአገር ውስጥ የተፈጠረው ችግር ነው::

በውጭው ስንዳሰስ ደግሞ በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሩብ ዓመት ውስጥ በመካከለኛው ምሥራቅ የመሀመድ መነሳትና የእስልምና እምነት መስፋፋት ነው:: በአካባቢው ያሉትን አገሮች ግብፅን ጨምሮ ተቆጣጥረዋል:: በዚህ ግዜ ግብፃውያኑ ክርስቲያኖች ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን ግንኙነት አቋርጠው ስለነበር ወደ ኢትዮጵያ የመጣ አንድም ጳጳስ አልነበረም:: ይህም ይተረጐሙ የነበሩ መጻሕፍት ለመቆም ተገደዋል:: ክርስትና ቀዝቀዝ ብሷል፣ ካህን ጠፍቷል፣ ዘመኑ ጨለማ ነበር:: በዚህ ባልነው ዘመን ውስጥ ተተረጐመ ወይም ተጻፈ የምንለው ነገር የለም የሚሉ አሉ:: ነገር ግን በዚህ የጨለማ ዘመን የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ ጨርሶ አልነበረም ማለት አይደለም:: በጨለማው ዘመን የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ መኖሩን አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ዘመኑ ሲያልቅ የምናገኘው የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ «ዜና መዋዕል» ተገኝቷል:: ይህም የሥነ ጽሑፍ እንቅስቃሴ ጨርሶ አልሞተም ነበር::

ከላይ በተገለጠው መሠረት ከላስታ ዘመነ መንግሥት ወዲህ በዐፄ አምደ ጽዮን ዘመን የሥነ ጽሑፍ ይዞታ ለየት ባለ መንገድ መስፋፋቱን ቀጥሏል:: ሥነ ጽሑፎቹ በጠቅላላው በሃይማኖት ላይ የተመሠረቱ ናቸው:: ምክንያቱም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ዘመን ከእህት አብያተ ክርስቲያናት ጋር መገናኘት ስላልቻለችና በመሐመዳውያኑ ስለተከበበች በሥነ ጽሑፍ ላይ እንድታተኩር አድርጓታል:: ዐፄ አምደጽዮን በነገሰበት ዘመን የአክሱም መንግሥት ተጠናክሮ አገሪቷ አንፃራዊ የሆነ ሰላምና መረጋጋት አግኝታ እንደነበር ነው የምንረዳው:: በእነዚህ ምክንያት ለክርስትና እምነት መስፋፋት አመቺ የሆነ ሁኔታ በመፈጠሩ በጨለማው ዘመን ተገትቶ የነበረው የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ ማንሠራራት ጀምሯል:: የሥነ ጽሑፎቹ ዓይነት በሁለት ለመመደብ ይቻላል [ትርጓሜና አዲስ ወጥ] ናቸው:: ትርጉሙ በጠቅላላው ሳይሆን በይበልጡ ከአረቢኛ ነው:: በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል የነበረው ግንኙነት በ1270 ዓ.ም. እንደገና ተጠናክሮ ሲቀጥል፤ በግብፅም የመግባቢያ ቋንቋ በአረቢኛ ተተክቶ ስለነበር «አረባዊ ክርስቲያናዊ ሥነ ጽሑፍ» ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው ወደ ግዕዝ ተተርጉመው የተገኙት::





በዐፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ለብዙ ዘመናት በኖረው በግዕዝ ቋንቋ ብዙ መጻሕፍት ተጽፈዋል:: ሀፄ አምደጽዮን የታሪክና የሥነ ጽሑፍን ጥቅም በማወቁ ወደ መረሳቱ ተቃርቦ የነበረውን የአክሱምን ታሪከ ነገሥት በማጻፍ መንገድ የከፈተ እርሱ ነው:: እንዲሁም ቤት እየመቱ ግጥም እያሰናዱ ስንኝ መጻፍ የተጀመረው በዐፄ አምደጽዮን ዘመነ መንግሥት እንደሆነ ይነገራል::[1] በዚሁ ወርቃማ ዘመን አንዱ የሆነውን ሁለተኛው የሥነ ጽሑፍ ዘመን ከተጻፉትና ከተተረጐሙት መጻሕፍት መካከል የሚከተሉትን እንመለከታለን::

[1] የሥነ ጽሐፍ ቅኝት ገፅ 71::



www.ethiopianorthodox.org

## በዐፄ አምደጽዮን ዘመነ መንግሥት የተተረጐሙና የተጻፉ መጻሕፍት

| የመጻሕፍቶቹ ስም | የተጻፈባቸው ወይም የተተረጐመባቸው ቋንቋዎች | መጻሕፍቶቹ የሚያተኩሩባቸው መልዕክቶች |
|---|---|---|
| መጽሐፈ ግንዘት | ከአረብኛ የተተረጐመ | ሰው ሲሞት ከእልፈተ ሕይወቱ በኋላ ከግብአተ መሬቱ አስቀድሞ በእስክሬኑ ላይ የሚጸለይ ጸሎትን የያዘ ነው:: |
| ውዳሴ ማርያም | ከአረብኛ የተተረጐመ | ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም የሚቀርብ ምስጋና ሲሆን የደረሰው ሶሪያዊው ቅዱስ ኤፍሬም ነው:: |
| ክብረ ነገሥት | በግዕዝ የተጻፈ | በዚህ ዘመን ተደረሱ ከሚባሉት መጻሕፍት አንዱ ሲሆን በኢትዮጵያ ታሪክ ከፍተኛ ቦታ ተሰጥቶትና በመንግሥትም ከፍተኛ ቦታ ተችሮት የኖረ መጽሐፍ ነው:: ንግሥት ሳባ ወደ ሰሎሞን የሔደችበትን ዝርዝር ታሪክ ይገልፃል:: ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ንቡረ እድ ይስሐቅ በሚባል ሰው ነው:: በ1994 ዓ.ም. ወደ አማርኛ ተተርጉሟል:: |
| ሥርዓተ መንግሥት | በግዕዝ የተጻፈ | እስከ አምደ ጽዮን ዘመን ድረስ የመንግሥትን የአስተዳደር ሥርዓት የሚያመለክት መጽሐፍ ወጥቶ አያውቅም ነበር አስተዳደሩ በዘልማድ ነበር የሚከናወነው:: በአምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት መንግሥቱ ቋሚ ሥርዓትና ደንብ እንዲኖረው ሕዝቡም ይህን አውቆ እንዲተዳደር ስለፈለገ ይህን መጽሐፍ እንዲዘጋጅ አደረገ:: ይህ መጽሐፍ ለሃሳቡ መነሻ የሚሆኑ ከሌሎች ቋንቋዎች የተወሰዱ ይኑሩ እንጂ ትርጉም አይደለም:: |
| የታሪክ መጽሐፍ | በግዕዝ የተጻፈ | በአምደ ጽዮን ዘመን ግዕዝ ለ መጀመሪያ ጊዜ የታሪክ መጽሐፍ የተጻፈበት ቋንቋ ሆኖ እናገኘዋ |





| | | |
|---|---|---|
| | | ለን:: ንጉሥ አምደ ጽዮን ያደረጋቸውን ጦርነቶችና ድሎች ይጻፍ እንጂ አልፎ አልፎ ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አለበት:: ንፁህ ዓለማዊ ጽሑፍ እስከዚያ ድረስ ያለመኖሩን እንረዳለን:: |
| መጽሐፈ ባሕል /መጽሐፈ ፋሐሬስት/ | ከሮማይስጥ የተተረጐመ | ከልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የተሰበሰቡ አባባሎችን የያዘ መጽሐፍ ሲሆን ቁመቱ 36ሴ.ሜ ተኩል ወርዱ 32 ሴንቲ ሜትር ተኩል የገፁ ብዛት 602 ነው:: |
| መጽሐፈ ኪዳን | ከአረብኛ የተተረጐመ | ይህ መጽሐፍ /ቅዳሴ እግዚእ/ በመባል ይታወቃል:: እንደ ቤተ ክርስቲያናችን እምነት ይህ ኪዳን የተባለው መጽሐፍ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤ በኋላና ከእርገቱ በፊት ለሐዋርያቱ ያስተማራቸው ክፍል ነው:: |
| ዜና አይሁድ | በግዕዝ የተጻፈ | ኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳንን የተቀበለች አገር እንደመሆኗ ብሉይ ኪዳን የበለጠ ለመረዳት የአይሁድን እውነተኛ ታሪክ ለማወቅ ዜና አይሁድ ወደ ግዕዝ ተተረጐመ:: ይህን መጽሐፍ የደረሰው ዮሴፍ ወልደኮርዮን የተባለ ሰው ነው:: |
| ሥርዓተ ቅዳሴ | እነዚህ ቅዳሴያት በአብዛኛው ከግሪክና ከአረብኛ ቋንቋዎች ከዚያም ወደ ግዕዝ የተተረጐሙ ናቸው:: | የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የቅዳሴን ደንብ የሚያሳይ መጻሕፍት ናቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምባቸው 14 በህትመት ላይ የዋሉ ቅዳሴዎች አሏት 6 ደግሞ በህትመት ላይ ያልዋሉ እንዳሉ ታውቋል:: 14ቱ ቅዳሴያት እጅግ ደስ በሚል ቃላት የተዋቡ ሲሆኑ ሁሉም ማለት ይቻላል በክርስቶስ የማዳን ሥራ ላይ ያተኮሩ ናቸው:: «እኮቴተ ቁርባን» የቁርባን ምስጋና በመባል ይታወቃሉ:: |
| ግብረ ሕማማት | ከአረብኛ የተተረጐመ | ከትንሣኤ በዓል በፊት ከሆሳዕና በዓል በኋላ በሰሙነ ህማማት የምንገለገልበት መጽሐፍ ነው:: |



www.ethiopianorthodox.org

ከእነዚህ መጻሕፍት በተጨማሪ በEMML (Ethiopia Manuscript Microfilming Library) ተመዝግበው የሚገኙና በዚህ ክፍለ ዘመን ማለትም ከ13-14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተጻፉና ከተተረጐሙ መጻሕፍት መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ::

- 🕮 ድርሳነ ሐዋርያት፣
- 🕮 መጽሐፈ አስቴር፣
- 🕮 ደቂቀ ነቢያት፣
- 🕮 መጽሐፈ ኢሳይያስ፣
- 🕮 መጽሐፈ ኤርሚያስ፣
- 🕮 መጽሐፈ ሔኖክ፣
- 🕮 መጽሐፈ ሕዝቅኤል፣
- 🕮 መጽሐፈ ሰሎሞን፣
- 🕮 መጽሐፈ ዮዲት፤ [EMML Pag. 12 - 13]

## የገድላት መጻሕፍት

በዚህ ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ አገልግሎት ላይ የዋለ የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ ቅርስ ነው:: በትርጉም መልክ ነው ወደ ኢትዮጵያ የገቡት «ገድል» ማለት እንደ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገላለጽ:-

1. በቁሙ ትግል፣ ፈተና፣ ውጊያ፣ ሰልፍ ድልና አክሊል እስከሚገኝ ድረስ የሚደክሙት ድካም የሚሠሩት ሥራ የሚቀበሉት መከራ ማለት ነው::
2. መንፈሳዊ ዜና ወግ ታሪክ የቅዱሳንን መከራና ጸጋ ተጋድሏቸውን የሚናገር መጽሐፍ ገድለ አዳም፣ ገድለ አብርሃም፣ ገድለ ሐዋርያት የመሳሰለው ሁሉ (መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ገፅ 301)

### በዚህ ክፍለ ዘመን ከተተረጐሙት ገድላት መካከል

1. ገድለ ሰማዕታት ይህ መጽሐፍ ቀደም ሲል የነበሩትን የሰማዕታት ታሪክና አዲስ ተጨምረው ወደ ግዕዝ የተ ተረጐመ መጽሐፍ ነው::





2. ገድለ ሐዋርያት ሐዋርያት የክርስቶስን መንገድ ተከት ለው ያደረጉትን ተጋድሎ የሚያትት መጽሐፍ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ የሚከተሉት ገድላት ተተርጉመዋል ገድለ እስጢፋኖስ፤ ገድለ መቃቢስ፤ ገድለ ሚናስ፤ ገድለ ዮሐንስ መጥምቅ፤ ገድለ መርቆሬዎስ፤ ገድለ ኤዎስጣጤዎስ የተተረጎሙት በዚሁ ወርቃማ ዘመን ነው:: [EMML Pag. 12 -13]

በአምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ተተርጉመው የምና ገኛቸው የገድል ትርጉሞች ለመጀመሪያ ጊዜ የተተረጐሙ ገድሎች በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ክብር የሚሰ ጣቸው ሲሆኑ ኢትዮጵያ ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምራ የጸናው ቤተ ክርስቲያን ስለተመሠረተባት ለሃይማ ኖቱ የታገሉ ሰዎች ለክርስትናቸው እንዴት እስከ ደም ጠ ብታ ድረስ ይመስክሩ እንደነበር ለትውልዱ ለማስተላለፍ በዚህ መልክ ወደ ግዕዝ ተተርጉመዋል::

## የገድላት መጻሕፍት ዓበይት ዓላማ

የቅዱሳን ሐዋርያት፣ የሰማዕታት፣ የጻድቃን የመከራ ሕይወት ከሰቆቃውም በኋላ የሚገኘው አኩሪ መንፈሳዊ ድል መዝግቦ ለመጭው ትውልድ ለማቆየት፤ የክርስትና እምነት ጥንካሬና የተከታዮቹም በሚደርስባቸው መከራ አይፈተሸ ነት (አለመናወፅ) ማስተማሪያ ነው:: መምሕረ አሕዛብ ወሕ ዝብ ቅዱስ ጳውሎስ «የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሯችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ:: የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሏቸው» ዕብ. 13÷7፤ ያለው ይህን አይነቱን ሕይወት ወይም ዜና ገድላቸውን ትውልዱ ተመልክቶ እምነ ቱን እንዲያፀናበት ነው:: በመሆኑም:-

- ✤ እስከ ደም ጠብታ ድረስ በመስቀል ላይ ለተገለጠው ሕይወት የመሰከሩ አባቶች መኖራቸው፤
- ✤ የክርስትና እምነት ጥልቅ ምስጢር ያለው ሕይወት መሆኑን፤
- ✤ በመከራ መጽናት ከበስተኋላ አክሊል እንደሚገኝ፤



www.ethiopianorthodox.org

- የሚያዩትን ዓለም በማያዩት ዓለም ስለ እምነታቸው መለወጣቸውን፤
- የቀደምት አባቶች የሐዋርያትን ሕይወት በኋላ የነሱ አባቶች መላበሳቸው፤
- እግዚአብሔር በእነሱ ላይ አድሮ የሠራው ድንቅ ሥራ መኖሩ፤
- የቤተ ክርስቲያን መዉረቷ ጥልቅ አጥሯ ጥብቅ መሆኑ፤ የገድላት መጻሕፍት ለአሁኑ ትውልድ የሚያስተላልፉት ዋና ዓላማቸው ነው።

## ታሪካዊና ሥነ ጽሑፋዊ ጠቀሜታቸው

ከላይ ካየነው በተጨማሪ የገድላት መጻሕፍት ከፍ ተኛ የሆነ ታሪካዊና ሥነ ጽሑፋዊ ጠቀሜታ አላቸው::

1. በታሪካዊ ጠቀሜታቸው ስናይ በአንድ ጻድቅ ገድል ውስጥ ከሥጋ ለባሹ የሃይማኖት ሰው የመከራ ኑሮ ጋር በተያያዘ የዘመኑን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ አቋምን የሚገልጹ በርካታ ጉዳዮችን እናገኛለን:: ለም ሳሌ፣ «ገድለ ፊሊጶስ» ውስጥ በአባ ፊሊጶስና በንጉሥ አምደጽዮን መካከል ቅራኔ እንደተፈጠረ እናያለን:: ቅራ ኔው የተፈጠረው ንጉሥ አምደጽዮን የአባቱን ሚስት በማግባቱ ምክንያት አባ ፊሊጶስ ክርስትና የተቀበለች አገር ንጉሥ ነህ እንዴት ይህን ታደርጋለህ ብለው ስለገ ሰፁት ግርፋት ደርሰባቸዋል:: ቤተ ክርስቲያን በዚህን ጊዜ እንዲህ ዓይነት ሕገ ወጥ ድርጊት ሲፈጸም ተቃ ውሞ ታደርግ እንደነበር በገድለ ፊሊጶስ ውስጥ እናገኛለን::

ምንም እንኳ ንጉሥ አምደጽዮን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መስፋፋት በተለይ በሥነ ጽሑፍ ረገድ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደረገ ንጉሠ ነገሥት ቢሆንም እንዲህ ዓይነት ደካማ ጐኑ በገድላት መጽሐፍ ተመዝግቦ ስላለ በዚህም ከቤተ ክርስቲያን አባቶች ተግሳፅ ደርሶበታል:: ስለዚህ ለታሪክ ምርምር ጠቃሚነት አላቸው::





2. በሥነ ጽሑፋዊ ጠቀሜታቸው የገድላት መጻሕፍት የሚ ያሳዩን ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርይ ላቅ ያለ ሆኖ እናገኛቸዋ ለን:: የአንድ ሰማዕት ገድል ሲጻፍ የመከራውንና የፈተ ናውን ጽናት እንድናየው ስዕላዊ በሆነ ስሜትን በሚነካ መልኩ ይገልፁልናል:: በፈጠራ ሥራ (በልብ ወለድ) መጽሐፍ ውስጥ የምናየው ወረቀትና ጽሑፍ ነው:: በገድ ላት ግን ስሜት አለ:: ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቸው በዚህ ይገለጻል:: የገድለኛውን የምንጻቤውን ብርታት ከዚ ያም የድሉን ግርማ ለማብራራት በዘይቤአዊ አነጋገር ይገልፃል::

ጸሐፊው የሚያቀርበው የቅዱሱን ታሪክ በሕይወት ዘመኑ ያሳለፈውን መከራ ያደረገውን ገድል ብቻ ሳይሆን እንዲያደርገው የሚመኘውንም ጭምር ነው:: እንግዲህ ሥነ ጽሑፋዊ ጠቀሜታቸው በዚህ ሊገለፅ ይችላል::

## መልክእ

በብዙ ገድላት መጨረሻ ላይ ሥነ ጽሑፋዊ ደረጃው ላቅ ያለ አንድ ነገር አለ:: እሱም በርዕሱ የጠቀስነው «መል ክእ» የሚባል የጽሑፍ ቅርስ ነው:: ይህ ጽሑፍ የሚቀርበው በግጥም ነው:: ገድሉ ስለተጻፈለት ቅዱስ ስለ እያንዳንዱ የአካል ክፍል የሚገልፅ ሙገሳ ነው:: መልክእ አንድ መሠረ ታዊ የሆነ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እምነትን የሚገልፅ ድርሰት ነው:: ይህን የመሰለ ድርሰት ያለው ቤተ ክርስቲያን በዓለም ውስጥ ሌላ የለም::

መልክእ ማለት ገፅታ እንደማለት ነው:: አደራረሱም የቅኔን መልክ የተከተለ ሆኖ የሰውነት ክፍሎችን የሚዳስስ ነው:: በዚህ ምክንያት ነው የመልክእ ሁሉ ቤት ተመሳሳይ የሚሆነው:: ስለዚህ መልክአ ኢየሱስ 52፤ መልክአ ማርያም 57፤ መልክአ ጊዮርጊስ 50 የመልክእ ሰላምታዎች አሏቸው:: መልክእ የባለ መልኩን ቅድስና የሚገልፅ ከራስ ጸጉር እስከ እግር ጥፍር ድረስ ባሉት አካላቶች በመመሰል ይገለፃሉ:: በእያንዳንዱ አካልም የእግዚአብሔርን የበረከት ሥራ ይነገራል::



www.ethiopianorthodox.org

ነገር ግን የሥላሴ መለኮታዊ አካል የሚዳሰስና የሚጨበጥ ስላልሆነ የመልክአ ሥላሴ ደራሲ «አባ ስብሐት ለአብ» በአካላትና በባሕርይ እያደረገ የሥላሴን ክብር ይገልፃል:: መልክአ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባሕል መሠረት በተደረሰበት በግዕዝ ቋንቋ መጸለይ አለበት:: የሚጸለየውም በበአላት ቀን በመታደልና በመቀባበል ይጸለያል:: መልክአ ኢየሱስ እንደ ቅኔ የመጨረሻዎቹ ቤቶች በሆሄያት ይገጣጠማሉ ለምሳሌ:-

ሰላም ለዝክረ ስምከ ስመ መሐላ ዘኢይሄሱ፤
ዘአንበረ ቅድመ እግዚአብሔር በአትሮኖሱ፤
ኢየሱስ ክርስቶስ ለዳዊት ባሕርየ ክርሡ፤
አክሊለ ሦምከ እንዘ ይትቄጸል በርዕሱ፤
አህጉረ ፀር ወረሠ ኢያሱ፤... እያለ ይቀጥላል::

አንድ መልክአ በመሠረቱ 5 ቤቶች አሉት:: መልክአ በታላላቅ በአላት ጊዜ በንዑስና በአብይ የሚፀነፀል ሲሆን በአሉ ድርብ ሲሆን ሁለቱንም በአላት የሚያስተባብር ኃይለ ቃል ያለው መልክአ ተመርጦ ይህም ይፀነፀላል:: ከመልክአ በኋላም በዓሉን የሚመለከት ዚቅ የሚባል ሌላ ተጨማሪ ቃለ እግዚአብሔር አለ:: በመልክአ ውስጥ ብዙውን ጊዜ ቅድስና ንፅህናና የጻድቁ (የሰማዕቱ) ድል ይነገርበታል:: በአጠቃላይ ግን ገድላት በውስጣቸው ለምርምር የሚጋብዙ እነዚህን መሰል ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርይ አላቸው:: ለዛሬ የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች መበርከት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገችው ወይም በር የከፈተችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሆኗን አንባቢ ልብ ሊል ይገባዋል::

## ሐዋርያዊ ተልዕኮ መስፋፋት

ከተሰአቱ ቅዱሳን በኋላ መልክ ያለው የተደራጀ የወንጌል እንቅስቃሴ የተደረገው በዐፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ነው:: የተሰአቱ ቅዱሳን ሐዋርያዊ ተልዕኮ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ የታከለበት ነበር:: ይህም በአምልኮ ጣዖት የተያዙ ቦታዎች ላይ አብያተ ክርስቲያናትን በመትከል፣





በአምልኮ ጣኦት የተያዙ ሰዎችን ወደ አሚነ ክርስቶስ መለወጥ፤ ሥነ ጽሑፍ ማስፋፋት፤ ገዳማዊ ሕይወት እንዲበለፅግ ለዚህ የሚያገለግሉ የሕግ መጽሐፍትን በመተርጎም ሐዋርያዊ ተልዕኮአቸውን በእነዚህ ነገሮች በማጀብ አከናውነዋል:: ከዚህ በኋላ ጎላ ያለ ሐዋርያዊ ተልእኮ የተካሔደው በዐፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ነው::

ንጉሥ አምደጽዮን ለቤተ ክርስቲያን መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አድርጓል::[2] ይኸውም በአባቱ የንግሥና ዘመን የመጣው ግብፃዊ ጳጳስ አቡነ ዮሐንስ በሞቱ ጊዜ መልእክተኞቹን ወደ ግብፅ ልኮ አዲስ ጳጳስ አቡነ ያዕቆብን አስመጥቷል:: ይህ ጳጳስ የደብረ ሊባኖሱን እጨጌ አቡነ ፊሊጶስን አስጠርቶ፣ «ኢትዮጵያ ሰፊ አገር እንደመሆኗ መጠን በአንድ ጳጳስ መወሰን የለባትም:: አሥራ ሁለት አባቶችን ምረጥና አንተም ጭምር ኤጲስ ቆጶሳት ይሹሙና ክርስትናን እናስፋፋ» ብሎ ሃሳብ አቀረበ::

ከላይ የገለጥነው ግብፃዊ ጳጳስ ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶስ መሾም የለባቸውም የሚለውን አጉል ልማድ ወደ ጎን በመተው አባ ፊሊጶስን ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ በመሾም ከሱ ጋር ያሉትን 11ዱን ንቡራነ እድ ክርስትናን በእያሉበት እንዲያዳረሱ አደረገ:: እነዚህ ንቡራነ እድ ሹመታቸው በቃል ብቻ ሳይሆን እጅ በራሳቸው ላይ በማኖር ሳይሆን አልቀረም ይህ ስም የተሰጣቸው:: 11ዱ ንቡራነ እድ ስማቸውና ስብከተ ህገራቸው የሚከተለው ነው:-

[2] የአምደ ጽዮን ታሪክ በሊዝበን ታትሟል፤ መርሐ ልቡና ገፅ 91::



www.ethiopianorthodox.org

| የንቡራነ እዱ ስም | ሐዋርያዊ ተልዕኮ ያካሄዱበት ቦታ |
|---|---|
| ፊሊጶስ ዘደብረ ሊባኖስ | — |
| አድኃኒ ዘዳሞት | — |
| ሳሙኤል ዘወገግ | ከአመልል እስከ ንብ ገደል ከምድረ አኑሲ እስከ አዳል |
| ገብረ ክርስቶስ ዘድም | ከዳባት እስከ ኝል ወንዝ ይህም አምሐራንና ታቦርን ይይዛል |
| ኢዮስያስ ዘወጅ | ከሙቁር እስከ ጉራጌ |
| አኖሪዎስ ዘሞረት | ከእንሳሮ ወንዝ እስከ አነዳባይዛሮ ከዝማ እስከ ሸምብራ ኮሬ |
| አኖሪዎስ ዘወረብ | ከእምባሰል ገንታ እስከ ሸረታ ወንዝ |
| መርቆሬዎስ ዘመርሐቤቴ | ደራ ከዋዲያት እስከ ከሳያት ወንዝ |
| ቀውስጦስ ዘመህግል | ከእማን እስከ ሸምብራ ካሬ |
| ማትያስ ዘፈጠጋር | ከጎሬ እስከ ዳዋሮ፣ ከባካን ሳላሽ እስከ አዋሽ ጅረት ይህም፡ በር ቅቀን ምንጃርኛ ምጀን ይይዛል |
| ታዴዎስ ዘፅላልሽ | ከጥጎር እስከ ፈጠጋርና ዳዋሮን በመላ ያጠቃልላል |
| ዮሴፍ ዘአናርያ | ከቀጨ እስከ ሜጫ |

እነዚህ አሥራ ሁለቱ ንቡራነ እድ እንደ 12ቱ ቅዱሳን ሐዋርያት በመሆን እጨጌ ፊሊጶስ እንደ አለቃቸው እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ሆነው ዞረው ወንጌልን አስፋፍተዋል። የእነዚህ ሀገረ ስብከት ወሰን ተደርጎለት ሐዋርያዊ መልእክታቸውን ፈፅመዋል። ዐፄ አምደጽዮን ያስመጣው ጳጳስ አቡነ ያዕቆብ እስከዛሬ ወደ ኢትዮጵየ ከመጡት ግብፃውያን ጳጳሳት የተለየ መሆኑን ታሪኩ ያስገነዝበናል።

ምክንያቱም ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ጳጳሳት ሁሉም ባይሆኑም አብዛኛዎች የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ጎድተዋታል። ከግል ጥቅማቸው ባሻገር የቋንቋ ብቃት የላቸውም፤ የሚቀመጡት በቤተ መንግሥት ክልል ስለሆነ ተዟዙሮ ወንጌልን መስበክ (ማስፋፋት) ተስኗቸው ነበር፤ ከእነዚህ የባሰበት ደግሞ በግብፅ የሚኖሩ ክርስቲያኖች የመሀመዳውያኑ አገዛዝ እንዲቀንስላቸው በማለት ግብፅን ከሚያስተዳድሩ ሡልጣኖች ጋር እየተስማሙ መስኪድ እስከ ማሠራት የደረሱ ግብፃውያን ጳጳሳት ነበሩ። (የቤተ ክርስቲያን ታሪክ





በኢትዮጵያ ገጽ 34፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም እስከ ዛጉዌ ተ.ፃ.መ) ጠላት ኢትዮጵያን ሲወር በጎችን ለአውሬ ጥለው ሹመታቸውን ለማፅደቅ የኮበለሉም አልጠፉም፤ /ዝርዝር ታሪኩን የፓትርያርክነቱ መንበር እንዴት ተገኘ የሚለውን በዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ የቀረበውን መጽሐፍ ተመልከት።/ እነዚህን የመሳሰሉትን ስንመለከት እላይ የጠቀስነው ግብፃዊ ጳጳስ አቡነ ያዕቆብ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መስፋፋት በጥሩ እቅድ ተነስቶ የራሱን ሹመት ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያውያንም በማጋራት የኢትዮጵያን መምህራነ ቤተ ክርስቲያንን አስመርጦ ለሐዋርያዊ አገልግሎት በየቦታው እንዲሰማሩ ባርኳቸው መላኩ በትክክለኛው መንፈስ ወንጌል በኢትዮጵያ እንዲሰበክ ከፍ ያለ ፍላጐት የነበረው አባት በመሆኑ ሥራውን ልናደንቅለትና ልናመሰግነው ይገባል፤ ይህ ዓይነቱ ድርጊት ከእርሱ በፊትና በኋላ በመጡ ግብፃውያን ጳጳሳት ሕይወት ላይ አልታየም።

እላይ ያየነውን የተጠናከረ የስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ ሲካሔድ ከዘጠኙ ቅዱሳን በኋላ የመጀመሪያው ነው። ሆኖም ግን እንዲህ ዓይነት ተመሳሳይ የስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ በሰሜን ኢትዮጵያም ተከናውኗል። ይህም በደብረ በንኮል አበምኔት በአቡነ መድኃኒነ እግዚእ አማካኝነት ነው።

የደብረ በንኮል ገዳም ከአክሱም በስተምዕራብ 30 ኪ.ሜ. ያህል ርቆ የሚገኝ በተፈጥሮ ደን የተሸፈነና ዙሪያው ገደላማ የሆነ አንባ ምድር ገዳም ነው። የዚህ ገዳም መሥራች አቡነ መድኃኒነ እግዚእ በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፀፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ወደዚህ መጥተው ከመስፈራቸው በፊት ይህ አምባ ምድር ደን የሌለውና እርቃኑ የወጣ አለታማ ሥፍራ እንደነበር ገድለ መድኃኒነ እግዚእ የሚገልፅ ሲሆን፤ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ በገዳሙ ውስጥ መኖር ከጀመሩ በኋላ ግን እሳቸውና ተማሪዎቻቸው የሦስት ሰዓት መንገድ እየተጓዙ በትከሻቸው እንስራ እየተሸከሙ የደብረ በንኮል ድንጋያማ አምባና ገደላማው ተራራ የጥድና የወይራ ዛፍ እየተከሉ ጥቅጥቅ ወዳለ ደን ለውጠውታል።



www.ethiopianorthodox.org

የደብረ በንኮል ገዳም በአሁኑ ወቅትም ቢሆን 123 መነኰሳት 82 አርድእት 200 ተማሪዎች ሩባ ሸዊት ከተባለ ወንዝ ዙሪያ ሙዝና ሸንኮራ፣ ሎሚና ብርቱኳን እየተከሉ እርሻ እያረሱ በሕብረትና በአንድነት የሚኖሩ ሲሆን ገዳማዊ ስነ ሥርዓታቸውና ማኅበራዊ አኗኗራቸው የጥንታዊት ኢትዮጵያ ገዳማዊ ስርዓትና ረድኤት ያልተለየው ገዳም ነው:: አቡነ መድኃኒነ እግዚእ በዚህ ገዳም ሲኖሩ ከጸምና ከጸሎት ሌላ ሰባቱ ከዋክብት፤ አምስቱ ቅዱሳን የተባሉ መነኮሳትን አስተምረው በመላዋ ትግራይና በጐንደር ተሠራጭተው አዳዲስ ገዳማት እንዲመሠርቱ ወንጌል እንዲያስፋፉ አድርገዋል:: 7ቱ ከዋክብት የተባሉትም:-

1. ሳሙኤል ዘቆየፃ፤
2. ሳሙኤል ዘጠሬዛ፤
3. ሳሙኤል ዘዋልድባ፤
4. ያሳይ ዘምንድባ፤
5. ዮሐንስ ዘጉርናቄ፤
6. ታዴዎስ ዘባልተዋር
7. ያፍቅረነ እግዚእ ዘጉብጉቤ ሲሆኑ፤

አምስቱ ቅዱሳን ተብለው የሚጠሩትም የሚከተሉት ናቸው:-

1. አሮን ዘከቱር፤
2. መርቆሬዎስ ዘዳባ፤
3. ዘካርያስ ዘከፋ፤
4. ገ/ክርስቶስ ዘቢታንያ፤
5. ዳንኤል ዘፀአዳ ናቸው::

የሦስቱም አገረ ስብከት እላይ አሥራ ሁለቱን ንቡራነ እድ ጨምሮ በዛሬው አከፋፈል የመደብናቸው እንደሆነ ይነስም ይብዛም አንጂ፣ ኤርትራን፣ ትግራይን፣ ወሎን፣ ጎንደርን፣ ጎጃምን፣ ሸዋን፣ አርሲን፣ ሲዳሞን፣ ከፋን ያጠቃልላል:: እነዚህ አበው መነኮሳት እውቀትን ከንፅህና ጋር አስተባብረው የያዙ ሲሆኑ ብዙውን ሕዝብ ባስተማሩበት አገረ ስብከታቸው የክርስቶስ አድርገዋል:: በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እነዚህ በሦስት መድበን እያየናቸው የቅድስና ማዕርግ ተሰጥቷቸዋል::





# ክፍል ሦስት

## ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም

ገድለ ኢየሱስ ሞዐ እንደሚነግረን ክርስትና ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ የደረሰው (የገባው) በ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዐፄ ድልነዓድ ከ902-912 ዓ.ም. በጳጳሱ በአቡነ ሰላማ ሁለተኛ እንደሆነ ይነገራል:: ይህ ገዳም ከመቆርቆሩ በፊት የቅዱስ ጴጥሮስና ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን እንደ ነበርና አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ከደብረ ዳሞ በመንፈስ እግዚአ ብሔር ተመርተው ወደዚህ መጥተው እያገለገሉ ለብዙ ዓመታት ኖረዋል:: ይህ ሥፍራ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የምንኩስና፣ የትምህርት፣ የአስተዳደር መገኛና አብነት ሆኗል::

ሐይቅ ለምንኩስና ሥርዓት ቀደምት እንደመሆኑ በአካባቢው የነበሩ አበው ወደዚህ እየሔዱ የምንኩስና መዓረግ ተቀብለዋል:: ከእነዚህም መካከል ሊጠቀሱ የሚገባቸው አቡነ ተክለሃይማኖትና አቡነ ኂሩተ አምላክ ናቸው:: አቡነ ተክለሃይማኖት 7 ዓመት ከመመንኮሳቸው በፊት፤ 3 ዓመት ከመነኮሱ በኋላ ሐይቅ ተቀምጠዋል:: ከዚህም በኋላ ወደ ሸዋ ተመልሰው ደብረ አስቦ ገብተዋል:: አቡነ ኂሩተ አምላክ እዚህ ተምረውና መንኩሰው ወደ ጣና በመሔድ ዳጋ እስጢፋኖስን መስርተዋል:: አቡነ ኢየሱስ ሞዐ የዘመኑን ትምህርት የሚያጠናቅቅ ትምህርት ቤት አቋቁመው ነበር::[1] ይህ ትምህርት ቤት የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም (University) ነው:: የመጀመሪያው የትምህርት ተቋም ብቻ ሳይሆን የመጀመሪያውም ቤተ መጻሕፍት (Library) ጭምር ነው::

[1] ገዳሙን ያቋቋሙት አባ ኢየሱስ ሞዐ የሴት መናኝ ወደ ደሴቱ እንዳይገባ የወንድ መናኝ መነኮሳት ብቻ እንዲሆን ወስነው በመቶ የሚቆጠሩ መናንያን አቋቁመው በዚሁ ገዳም ህዳር 26 ቀን አርፈው ተቀብረዋል:: በዚህ ገዳም በጠቅላላው የ24 ቅዱሳን አፅም አርፎበታል ከእነዚህም ውስጥ ነገሥታት አሉ:: ዐፄ ደናግዣን ከ882-902 ዓ.ም፤ ዐፄ ድል ነአድ ከ902 912 ዓ.ም፤ ዐፄ ያግባ ፅዮን ከ1268-1277 ዓ.ም፤ የነገሡ ነገሥታት ተቀብረውበታል:: [ትንሣኤ ቁጥር 124 ገፅ 22::]



www.ethiopianorthodox.org

አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ወደ ሐይቅ ከገቡ በኋላ እዚያ ሆነው ያስተማሩትና በጸሎታቸው ታምኖ መንግሥትን በእጁ ያደረገው ዐፄ ይኩኖ አምላክ መንግሥቱን ከዐፄ ይትባረክ ተረክቦ ሲመለስ ቃል በገባው መሠረት ወደ አቡነ ኢየሱስ ሞሀ መጣ፤ ከዚያም ከደሴቱ ውጭ ካለው የብስ ላይ ቆሞ አቡነ ኢየሱስ ሞዐ የምንኩስና ሥርዓት ይበልጥ ጠባዩን እንዲይዝ ሴቶች ከገዳሙ ቆንዲወጡ የፈለጉት ከዚህ የተነሳ ነበር። ይህን ጉዳይ ለመፈፀም አስቸጋሪ ስለነበር የንጉሡ እርዳታ አስፈልጓል። በዐፄ ይኩኖ አምላክ የእናቶች ከገዳሙ መውጣትን እንዳሉት ተፈፅሞላቸዋል። ከዚህ በኋላ በየቦታው ያሰባሰቧቸውን ራሳቸውም የጻፏቸውን መጻሕፍትና የተማሩትን ትምህርት በመጠቀም በዚህ ቦታ ላይ በአይነቱ ለየት ያለ የትምህርት ማዕከል ከፈቱ። ማዕከሉ ሦስት አጠቃላይ ነገሮችን ይዟል።

**1** በርካታ ትምህርቶችን በአንድ ላይ በማካተቱ፤
- ሥርዓተ ምንኩስና፤
- የአስተዳደር፤
- የመጻሕፍት፤
- የጽሕፈት፤
- የቅኔ፤
- የዜማ፤
- ማኅበራዊ ሕይወት ይሰጥበታል።

**2** ትምህርቱ ከተግባራዊ የቅድስና ሕይወት ጋር መስጠቱ፤
- ፍኖተ ሐዋርያትን እንዲከተሉ የሕይወት ትምህርት፤
- ምንኩስና ከመንፈሳዊ እውቀት ጋር ማስተባበርን፤
- ለአገልግሎት መሳካት ንፅህናን፣ ቅድስናን ገንዘብ ማድረግን፤
- በጾም በጸሎት በስግደት የሚገኘውን መንፈሳዊ እድገት መጠቀም ይሰጥበታል።

**3** በርካታ መጻሕፍትን ያሰባሰበ በመሆኑ፤
- የተማሪን የእውቀት ጥማት የሚያረኩ፤
- መንፈሳዊ ሕይወትን የሚያበለፅጉ፤
- አርቶዶክሳዊነትን የሚያንፀባርቁ፤
- ለመናፍቃን መልስ የሚሆኑ፤
- ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የሚያፀኑ፤ መጻሕፍትን ያሰባሰበ ማዕከል ነው።





ሐይቅ እስጢፋኖስ የትምህርትና የቅድስና ማዕከል በመሆን በቅድስናቸው እንደ ኮከብ የሚያበሩ፣ በትምህርታቸው ወደ ሕይወት መንገድ የሚወስዱ፣ የተጠማን ነፍስ የሚያረኩ በሁለት ወገን እንደተሳለ ሰይፍ (ሰይፍ ዘክልኤ አፉሁ) ቅድስናን ከሊቅነት የተላበሱ የእልፍ አዕላፋት ቅዱሳን መወለጃ ማህፀን ሆነ። ስለዚህ ነው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተባለበት ምክንያት፤ ይኸውም የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በአብዛኛው አጠቃሎ ከቅድስና ሕይወት ጋር የሚሰጥበት ማዕከል በመሆኑ ነው።

ከዚህ ባሻገር ከዚህ ተቋም ተመርቀው የሚወጡ ቅዱሳን መምህራን በልዩ ልዩ ቦታዎች እንደ አባታቸው አባት የመሆን፤ እና እንደተማሩበት ገዳም ደግሞ ገዳም የመመሥረት ግዴታ ነበረባቸው «አባት አባትን ሲወልድ ገዳም ገዳምን ይወልዳል» ማለት እንዲህ ነው። በዚህ መሠረት አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ላቋቋሙት ቋሚ ትምህርት ቤት 800 መነኮሳት፣ ቅዱሳን መምህራን በትምህርት በሃይማኖት አሠልጥነው በንቡረ እድነት ማዕርግ በመላ አገሪቱ አሰማርተዋቸዋል። ከእነዚህ አባቶች መካከል በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል:-

- ☩ አባ እስትንፋሰ ክርስቶስ
- ☩ አባ ገብረእንድርያስ
- ☩ አባ ተክለሃይማኖት
- ☩ አባ በጸሎተ ሚካኤል
- ☩ አባ ኂሩተ አምላክ
- ☩ አባ ገብረ ናዝራዊ
- ☩ አባ ሕዝቅኤል
- ☩ አባ ዮሴፍ
- ☩ አባ አሮን
- ☩ አባ ሠረቀ ብርሃን*
- ☩ አባ ጊዮርጊስ** ወዘተ ...የሚጠቀሱ ናቸው።

* አባ ጊዮርጊስን በሃይማኖት በምግባር የወለደ

** በጸሎቱ መላእክትን ያስደነቀ፣ በድርሰቱ ቤተ ክርስቲያንን ያሸበረቀ፣ ከሀድያንን ያሳፈረ መናፍቃንን በሰይፈ ግዝቱ መትሮ የቤተ ክርስቲያንን ክብር ያስጠበቀ።



www.ethiopianorthodox.org

እነዚህን የመሳሰሉ ቁጥራቸው የበዛ አባቶችን ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሲያበረክት የኖረ ቦታ ቢኖር ሐይቅ ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከጉዳትና አረመኔያዊ ጥፋት በኋላ ምንም እንኳ ከዛግዌ የመጨረሻዎች አራት ነገሥታት [ይምርሃነ ክርስቶስ፣ ነአኩቶ ለአብ፣ ገብረ ማርያምና ላሊበላ] መጠነኛ ማንሠራራት ብታደርግም ከዛጉዌ ዘመን በኋላ ከ13-16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሱ የቤተ ክርስቲያን የውስጥም የውጭም ችግሮችን ይፈቱ የነበሩት የዚህ የሐይቅ ትምህርት ቤት ተማሪዎችና መምህራን ነበሩ። በጣና ሐይቅ ዙሪያ ያሉ ገዳማት የመመስረታቸውና የመስፋፋታቸው ምክንያት የሐይቅ እስጢፋኖስ ትምህርት ቤት መከፈት ነበር። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ በጣና ሐይቅ ዙሪያ ባሉት ገዳማት ውስጥ በርካታ ቅዱሳት መጻሕፍት፤ ቁጥራቸው የበዛ መነኮሳት፤ ገዳማት ስለሚንፀባረቁበት ለዚህም ምክንያቱ የሐይቅ እስጢፋኖስ ትምህርት ቤት መመሥረት መሆኑን ምንጭ ይሰጡናል። ምክንያቱም በጣና ሐይቅ ዙሪያ ያሉት ገዳማት ከመመስረታቸው በፊት በሐይቅ ገዳም እነዚህ ነገሮች ታይተዋልና በተጨማሪ በሐይቅ ተምረውና መንኩሰው ወደ ጣና በመሔድ ዳጋ እስጢፋኖስን የመሠረቱ አቡነ ኂሩተ አምላክን መመልከቱ በቂ መረጃ ሊሆነን ይችላል።

በሐይቅ እስጢፋኖስ መንፈሳዊ ትምህርት ብቻ ሳይሆን አስተዳደራዊ ትምህርትም ይሰጥበት እንደነበር አላይ ጠቁመናል። ሀፄ ይኩኖ አምላክ ከመንገሡ በፊት የልጅነቱን ወራት የኖረውም የተማረውም እዚህ ነው። እዚህ ቦታ ባገኘው እውቀት ትምህርትና ምክር መንግሥቱን ለመምራት አስችሎታል። ሐይቅ እስጢፋኖስ ለትምህርት አመቺ ሁኔታ ያመቻቸች ስለነበረና ቦታዋ ዙሪያዋን በባሕር የታጠረች ጭምር ስለሆነች የተማሪ አዕምሮ በትምህርት ላይ ብቻ እንዲያርፍ ታደርጋለች። በውስጧ የታወቁ መምህራን በየመስኩ ይገኙ ነበር። ቤተ መጻሕፍቱ በብዙ መጻሕፍት የተሞላ በመሆኑ የተማሪን የእውቀት ጥማት የሚያረካ ነበር።[2]

[2] አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁጥር 12 ገፅ 52።





የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም በግራኝ ዘመን የገዳሙ ንብረት የተበረበረ ቢሆንም ቤተ ክርስቲያኑ ግን አልተቃጠለም፣ መጻሕፍቱም አልተቆነፃፀለም። ከዚያም በኋላ ገዳሙ እንደተከበረ ለብዙ ዘመናት ቆይቷል። ነገሥታቱም ብዙ ርስት ጉልት ሰጥተዋል። በርከት ያሉ የብራና መጻሕፍት የቆዩና ታሪካዊ ዋጋ ያላቸው አሁን ድረስ አሉበት። ከእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ በማይክሮ ፊልም የተነሱትን ብቻ ከእነ ስማቸውና የገፃቸውን ብዛት እንደሚከተለው ቀርቧል። ይህ የመጻሕፍት ዝርዝር በመነኮሳቱ እጅ በግል የተያዙትን መጻሕፍትን አያጠቃልልም።

| የመጽሐፉ ርዕስ | የብራናው ገጽ ብዛት |
|---|---|
| ዳዊት | 210 |
| መጽሐፈ ርቱዐ ሃይማኖት | 280 |
| ዮሐንስ አፈወርቅ | 257 |
| ግብረ ሕማማት | 234 |
| ገድለ ሰማዕታት | 117 |
| ገድለ ሐዋርያት | 232 |
| ደቂቀ ነቢያት | 282 |
| ግብረ ሕማማት | 199 |
| ግንዘት | 91 |
| ሃይማኖተ አበው | 180 |
| ገድለ ቅዱሳን | 216 |
| ገድለ ሐዋርያት | 152 |
| ገድለ ቅዱሳን | 225 |
| ገድለ ሰማዕታት | 207 |
| 4ቱ ወንጌል | 251 |
| መጽሐፈ ምስጢር | 210 |
| 4ቱ ወንጌል | 346 |
| ገድለ ቅዱሳን | 170 |
| ገድለ ቅዱሳን | 131 |
| ድርሳነ ሚካኤል | 247 |
| መጽሐፈ መነኮሳት | 203 |



www.ethiopianorthodox.org

| | |
|---|---|
| ጠቢበ ጠቢባን | 172 |
| ገድለ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ | 50 |
| ሐተታ ኦሪት ዘዮሐንስ አፈወርቅ | 410 |
| ገድለ ቅዱሳን | 296 |
| ድርሳነ ሚካኤል | 206 |
| ኦሪት | 164 |
| መጽሐፈ ሲኖዶስ | 131 |
| ገድለ ቅዱሳን | 220 |
| ኦሪት | 171 |
| 4ቱ ወንጌል /በ13ኛ ክ.ዘ/ የተጻፈ | 198 |
| ተአምረ ማርያም | 182 |
| ሲኖዶስ | 185 |
| ገድለ እስጢፋኖስ | 47 |
| ፍትሐ ነገሥት | 221 |
| አርጋኖን | 105 |
| አረጋዊ መንፈሳዊ | 175 |
| ግጻዌ | 131 |
| ገድለ ሰማዕታት | 174 |
| ገድለ ኢየሱስ ሞዐ | 107 |
| አቡሻክር | 84 |
| ድርሳነ ዑራኤል | 107 |
| አርጋኖን | 150 |
| የጳውሎስና የሌሎች መልእክቶች | 186 |
| ሕገ ወሥርዓተ ዘቤተ ክርስቲያን | 156 |
| ገድለ ስብስትያኖስ | 167 |
| ምሳሌያተ ሰሎሞን | 61 |
| የጳውሎስ መልእክቶችና ሌሎች | 193 |
| አረጋዊ መንፈሳዊ | 186 |
| ሄኖክ | 124 |
| ሥርዓተ መነኮሳት | 74 |
| ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን | 94 |
| ገድለ አረጋዊ | 45 |
| ነግሥ | 179 |
| የጳውሎስ መልእክትና ሌሎች | 215 |





| | |
|---|---|
| ለሃ ማርያም | 105 |
| ጸሎተ ባስልዮስ | 199 |
| ግንዘት | 153 |
| መልክዓ ጉባኤ | 89 |
| ገድለ አባ አቢብ | 102 |
| ገድለ ሐዋርያት | - |
| ነገረ ማርያም | 162 |
| ድጓ | 187 |
| ዳዊት | 196 |
| ዳዊት | 164 |
| ግብረ ሕማማት | 179 |
| ተአምረ ኢየሱስ | 123 |
| ሃይማኖተ አበው | 236 |
| ተአምረ ኢየሱስ | 96 |
| ድጓ | 180 |
| ስንክሳር | 248 |
| 4ቱ ወንጌል | 168 |
| ተአምረ ማርያም | 181 |
| ተአምረ ማርያም | 150 |
| ተአምረ ማርያም | 218 |
| ድጓ | 166 |
| 4ቱ ወንጌል | 183 |
| መርሐ እውር | 139 |
| ጾመ ድጓ | 66 |
| ተአምረ ማርያም | 163 |
| ግብረ ሐዋርያትና መልእክታት | 175 |
| የማቴዎስ ወንጌል ትርጓሜ | 152 |
| ግንዘት | 166 |
| ዜና አበው | 145 |
| ዳዊት | 139 |
| ግንዘት | 145 |
| ጾመ ድጓ | 71 |
| አረጋዊ መንፈሳዊ | 167 |



www.ethiopianorthodox.org

| | |
|---|---|
| ምዕራፍ | 158 |
| መጽሐፈ ጥምቀት | 28 |
| አርኬ | 192 |
| ኤርምያስ | 121 |
| ዳዊት | 164 |
| ጉባኤ መልክ /አርኬ/ | 150 |
| ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ | 184 |
| የማቴዎስ ወንጌል ትርጓሜ | 140 |
| መጽሐፈ ክርስትና | 58 |
| መጽሐፈ አርኬ | 160 |

እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት በአማካኝ በማይክሮ ፊልም ላይ የመታወቂያ ቁጥር ተሰጥቷቸው በአብዛኛው ደግሞ ዓመተ ምሕረታቸው ታውቆ ተመዝግበዋል። ይኸውም ጥንታዊ መጽሐፍ የተባለው በገዳሙ መሥራች በአቡነ ኢየሱስ ሞዐ በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጻፈው 4ቱ ወንጌላት ሲሆን፤ የመጨረሻው ደግሞ በ1961 ዓ.ም. የተጻፈው እንደ ዚሁ 4ቱ ወንጌላት ናቸው። እንግዲህ እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ የተጻፉ መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል። የእነዚህ መጻሕፍት እዚያ መገኘት ራሱን የቻለ ፍንጭ የምናገኘው ሐይቅ እስጢፋኖስ የተማሪን የእውቀት ጥማት የሚያረኩ መጻሕፍት እንደተከማቹበትና በእነዚህ መጻሕፍት ተጠቅመው ሕይወታቸውን ያፀኑ የቤተ ክርስቲያንን በመንፈሳዊ ሀብት ያስጌጡ ቅዱሳን አባቶች እንዳደጉበት ያስረዳናል። ስለዚህ ነው የመጀመሪያው የአገራችን ቤተ መጻሕፍት ነው በማለት በዚህ ታሪክ መግቢያችን ላይ ያሰፈርነው። ሌላው እነዚህ ቅዱሳን መጻሕፍት የሚያስገነዝቡን ነገር ቢኖር በብራና የተጻፉ እንደመሆናቸው መጠን የጉልበት፣ የጊዜ፣ የእውቀት መስዋዕትነት ተከፍሎባቸዋል፤ እንደዛሬው የህትመት ማሽን የለም ሆኖም ጊዜ ባፈራው ነገር ተጠቅመው ከፍተኛ የታሪክ ዋጋ ያላቸው መጻሕፍት ተረክበናል።





# ክፍል አራት

## የገዳማት መስፋፋት በጣና ሐይቅ ዙሪያ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ገዳማት ከ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ የሥነ ጽሑፍ፣ የታሪክ፣ የማኅበራዊ ሕይወት፣ የትምህርት በጠቅላላውም የኪነ ጥበብ መገኛዎች ሆነው መገኘታቸው በታሪክ የታወቀ ነው። በዚህ መሠረት በውስጣቸው በያዙት የቅርስ ክምችት፣ በዘመን ብዛታቸው፣ በአካባቢ ውበትነታቸው ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን የውጭ አገር ቱሪስቶችን ህሊና መስጠው «ምነው ኢትዮጵያዊ ሆኜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ በሆንኩኝ» የሚያሰኙ ገዳማት አሉን። ከእነዚህም ውስጥ በጣና ሐይቅ ዙሪያ የሚገኙ ገዳማት ዋንኞች ናቸው፤ የተመሠረቱት ጥቂቶች በህዴ ይኩኖ አምላክ ሲሆኑ፤ አብዛኞዎቹ ግን በዐፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ነው። በዚህ አካባቢ የተመሠረቱት ገዳማት ከግራኝ መሐመድ ወረራ በፊት የተተከሉና የገዳም ማኅበራዊ ኑሮ የተመሠረተባቸው፣ ብዙ መምህራነ ቤተክርስቲያን የወጡባቸ፣ ልዩ ልዩ ቅዱሳን አፅም ያረፈባቸው ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ያበረከቱ የበረከት ቦታ ናቸው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት ሐይቆች ትልቁ ጣና ሐይቅ ነው። ስፋቱ 3600 ካሬ ኪሎ ሜትር ሲሆን፤ በውስጡ የሚገኙ ደሴቶችና በዙሪያው በርካታ ገዳማት አሉ። አንዳንዶች ገዳማት ከ7 መቶ ዓመት እድሜ በላይ ያላቸውና፤ ከተለያዩ የአገራችን ክፍሎች የተሰበሰቡ ውድ የታሪክ ቅርሶችና የመካከለኛው ክፍለ ዘመን የአገራችን ነገሥታትን አፅም የያዙና «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሙዚየም» ናቸው ማለት ይቻላል። በዚህ አካባቢ የሚገኙ ገዳማትና አድባራት አብዛኛዎች በፀዔ አምደጽዮን ዘመነ መንግሥት የተቋቋሙ ከመሆናቸውም ሌላ ያቀኑትም ከሸዋ ጠቅላይ ግዛት በተለይ



www.ethiopianorthodox.org

ከመርሐ ቤቴና፣ ከመንዝ የዚህን ዓለም ሀብትና ንብረታቸውን ትተው እየመነኑ የሔዱ ሰዎች እንደሆኑ እያንዳንዳቸው የቤተ ክርስቲያን ታሪክና መጽሐፈ ገድላቸው ይመሰክርላቸዋል:: እነሱም የሚከተሉት ናቸው፤

| ገዳማቱን ያቀኑት | የገዳሙ መጠሪያ |
|---|---|
| 1. ታዴዎስ | ደቅረ ማርያምን ያቀኑ፤ |
| 2. በትረ ማርያም | ገዳም ዘጌን ያቀኑ፤ |
| 3. ኂሩተ አምላክ | ዳጋ እስጢፋኖስን፤ |
| 4. አቡነ ዮሐንስ | ክብራን ገብርኤልን፤ |
| 5. አሣይ /ሐሳይ/ | ገዳመ ምንድባን /ጕርጕራን/፤ |
| 6. ዘካርያስ | ገዳመ ገሊላን፤ |
| 7. ያፈቅረነ እግዚእ | ጕብጕቤን ገዳም ጐንደር፤ |
| 8. ቶማስ | ብርጊዳ ማርያምን፤ |
| 9. እንድርያስ | አንጋረ ተ/ሃይማኖትን አቅንተዋል:: |

ከእነዚህ ውስጥ ያፈቅረነ እግዚእ የትግራይ ተወላጅ ናቸው:: እነዚህ እያንዳንዳቸው ጽላትን እየያዙ ወደ ጣና ደሴቶች ገብተዋል::[1] በዚህ ወርቃማ ክፍለ ዘመን የተመሠረቱትን ገዳማት ጥቂቶችን እንደሚከተለው እናያቸዋለን::

## ዳጋ እስጢፋኖስ

ከጣና ሐይቅ ደሴቶች ለደቅ ደሴት የሚቀርበው የዳጋ ደሴት ነው:: ደሴቱ ከሐይቁ ከፍ ብሎ የሚገኝ በመሆኑ ከማንኛውም የሐይቁ ዳርቻ ሊታይ ይችላል:: ዳጋ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ የተሸፈነና በውስጡ የእስጢፋኖስን ገዳም የያዘ ነው:: ይህ ገዳም በሀፄ ይኩኖ አምላክ በ1268 ዓ.ም. እንደ ተመሠረተ ይነገራል:: ገዳሙን ያቀኑት አቡነ ኂሩተ አምላክ ናቸው:: በዚህ ገዳም በአብርሃ ዘመነ መንግሥት በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ቤተ ክርስቲያን ታንጾበት ስለነበር እኝህ ጻድቅ ታቦተ ማርያምን እያጠኑ የተባሕትዎ ሥራ

[1] ዜና ቤተ ክርስቲያን 24ኛ ዓመት ቁጥር 38 ገፅ 4::





እየሠሩ እስከ ዐፄ አምደጽዮን ዘመነ መንግሥት ቆይተው በዐፄ አምደጽዮን ፈቃድ ታቦተ ማርያምን በደቅ ውስጥ ኮታ በተባለው ቦታ ተክለዋል:: ታቦተ ማርያም ወደ ኮታ ከሔደች በኋላ ግን ታቦተ እስጢፋኖስ ተብሎ ሲጠራ ኖሯል:: ቤተ ክርስቲያኑ የተሠራው በይኩኖ አምላክ ቢሆንም የኋላ ዘመን ነገሥታት ዘርዓ ያዕቆብ፣ ሱስንዮስ፣ ዐፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት የተለያየ የመሠራትና የእድሳት እድሎችን አግኝቷል::

በጐንደር የነገሡ ነገሥታት ሁሉ ይህን ገዳም ጐብኝተው ከሰው ተለይተው ሦስት ሱባኤ፣ አራት ሱባኤ ያህል ይቆዩ ነበር:: ገዳሙን አምሳለ ገነት ብለው ይገምቱት ስለነበር እሑድ እሑድ የገነት ነፋስ ይነፍስበት ነበር ይላሉ:: ነገሥታቱ በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ብቻ ሳይሆን ከሞቱም በኋላ የዳጋ አየር አይልቀቀን ብለው አዕማቸው ያረፈው በዚሁ ነው:: ገዳሙን ልዩ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ የእነዚህ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት አፅም ሳይፈርስ የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት ባሠራላቸው የመስታወት ሳጥን ውስጥ ተቀምጠው መገኘታቸው ነው::[2] እነዚህ ነገሥታት:-

| ነገሥታቱ | የነገሡበት ዘመን |
|---|---|
| ዐፄ ዳዊት | ከ1382 - 1430 |
| ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ | ከ1434 - 1468 |
| ዐፄ ሱስንዮስ | ከ1607 - 1632 |
| ዐፄ ፋሲል | ከ1632 - 1667 |

የቤተ ክርስቲያኑ አሠራር በሐይቁ ውስጥ ካሉት ገዳማት የተለየ ነው:: በመርከብ ቅርፅ የተሠራ ሲሆን ምሳሌውም በጥፋት ውሀ ዘመን የሰው ዘር በኖህ መርከብ አማካኝነት መዳኑን ለማመልከት ነው:: ዳጋ እስጢፋኖስ በርካታ መናንያን መነኮሳት የሚገኙበትና ትክክለኛ የገዳም ሕይወት ሥርዓት የሚታይበት ሥፍራ ነው:: ደሴቱ የተፈጥሮ ፀጋና

[2] የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት 10 ዓመት የሥራ እርምጃ ገፅ 155 160::



www.ethiopianorthodox.org

መስህብ ብቻ ሳይሆን ያለው፤ በውስጡ ያሉት የመነኮሳት መንፈሳዊ ሕይወትም በጣም የጠለቀ ነው:: የቤተ ክርስቲያኑ የሣንቃ መዝጊያዎች ፍፁም ግዙፍና ወፍራም ናቸው:: አንዱ ሳንቃ የአምስት ሜትር ቁመትና የ3 ሜትር የወርድ ስፋት አለው:: በእቃ ቤቱ በርካታ ንዋየ ቅድሳት ይገኛሉ:: መጠናቸው ግዙፍ የሆኑ በጥንት ጊዜ የነበሩ የቅዱሳን አበው ቀለም በጥብጠው ብራና ቆምጠው የጻፏቸው መጻሕፍት በርካታ ናቸው:: እንዲሁም ልዩ ልዩ ረጅም ዘመን ያስቆጠሩ ነዋየ ቅድሳት፤ የነገሥታቶ ቅርሶች፤ የታላላቅ ሰዎች የወግ እቃዎች፤ ይገኛሉ:: ከዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የተበረከቱ የብራና መጻሕፍቶች የወርቅ የነሐስ መስቀሎች፣ ከዐፄ ዳዊት የተበረከቱ የሚከፈትና የሚዘጋ የነሐስ መስቀል የገዳሙ ልዩ ቅርሶች ናቸው::

## ዘጌ ደሴት

የጣናን ሐይቅ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ በመግፋት ተንሰራፍቶ የሚታየው ባሕረ ገብ መሬት (ፔኒንሲዮላ) ዘጌ ይባላል:: በቅርብ ርቀት ሆነው ሲመለከቱት ክንፍን ዘርግቶ የተቀመጠ አሞራ ይመስላል:: ዘጌ ከባሕር ዳር ከተማ 15 ኪ.ሜ. ያህል የሚርቅ ሲሆን በጀልባ 1 ሰዓት ከ30 ደቂቃ ያህል ያስኬዳል:: በመኪና ደግሞ 2 ሰዓት ይፈጃል:: ርቀቱ 23 ኪ.ሜ. እንደሆነ ይገመታል:: በዘጌ ባሕረ ገብ መሬት ላይ 7 የሚሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ:: እነኚህም:- መሐል ዘጌ ጊዮርጊስ፣ አቡነ በትረ ማርያም፣ አዝዋ ማርያም፣ ኡራ ኪዳነ ምሕረት፣ ደብረ ሥላሴ፣ ይጋንዳ አቡነ ተ/ሃይማኖት፣ ፍሬ ማርያም ይባላሉ::

ከመጨረሻዎቹ ሁለቱ በስተቀር ሌሎች ገዳማት አነስተኛ ጀልባዎችን ሊያስጠጉ የሚችሉ ወደቦች አሏቸው:: በጣና ሐይቅና በዙሪያዋ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ገዳማት 9ኙ ከዋክብት በሚል መጠሪያ ከሚታወቁት የሃይማኖት አባቶች ጋር የተሳሰረ ታሪክ አላቸው:: መነሻቸው ከተለያዩ የአገራችን ክፍሎች እንደሆነ የሚነገርላቸው እነዚህ አበው ጻድቃን:- አቡነ ታዴዎስ ደብረ ማርያምን፣ አቡነ ዘዮሐንስ ክብራን ገብርኤልን፤ አቡነ በትረ ማርያም ዘጌን፣ አቡነ ኂሩተ አም





ላክ ዳጋ እስጢፋኖስን፤ አቡነ ሐሳይ ምድባን፤ አቡነ ዘካርያስ ደብረ ገሊላን፣ አቡነ ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ ጣና ቂርቆስን እንደገዳሙ እንዳቀኑ ይነገራል::[3] እነዚህ ገዳማት በዘጌ ደሴት ውስጥ የሚገኙ እና በዚህ በ5ኛው ወርቃማ ዘመን የተመሠረቱ ናቸው:: በደሴቱ ውስጥ የሚገኙትን ገዳማት እንደሚከተለው እናያቸዋለን::

## መሐል ዘጌ ጊዮርጊስ

ከዘጌ ገዳማት በእድሜ አንጋፋ እንደሆነ የሚነገርለት የመሐል ዘጌ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ነው:: ቤተ ክርስቲያኑ በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዐፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት የተመሠረተ ሲሆን የመሥራቹን የአቡነ በትረ ማርያም ገድል በመጥቀስ ካህናቱ ይገልፃሉ:: አቡነ በትረ ማርያም ከሸዋ ልዩ ስሙ ሙገር ከተባለ አካባቢ እንደ መጡ ይታመናል:: በመሐል ዘጌ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በርካታ ጥንታዊ ቅርሶች ይገኛሉ:: ከብረት የተሠራ የአቡነ በትረ ማርያም የጸሎት ልብስ፣ የጥንት ነገሥታት መኳንንት ስጦታዎች፣ የብራና መጻሕፍት ከቅርሶቹ ጥቂቶች ናቸው:: ቤተ ክርስቲያኑ በተለያየ ጊዜ የመፍረስና እንደገና የመሠራት እድል ቢገጥመውም፤ የጥንቱን እደ ጥበብ የሚመሰክሩ የእንጨት ቅርሳ ቅርሶች በበሮቹና በመስኮቶቹ ላይ ይገኛሉ::

ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ጥንታዊ ገፅታቸውን ጠብቀው ከቆዩት ቤተ ክርስቲያናት መካከል አንዱ የሆነው የበትረ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይገኛል:: ይህ ቤተ ክርስቲያን አቡነ በትረ ማርያም ካረፉ በኋላ ረዳታቸው የነበሩት በአቡነ በርተሎሜዎስ አማካኝነት በመቃብራቸው ላይ ለመታሰቢያነት የተተከለ ነው:: በውስጡ ባማሩ ጥንታዊ ቅዱሳት ሥዕሎች ያሸበረቀውና በክብ ቅርፅ ተሠርቶ በባህላዊ የሣር ክፍክፍ የተከደነው የአቡነ በትረማርያም ቤተ ክርስቲያን የጥንቱ ዘመን የቅርፃ ቅርፅ ጥበብ የሚዘክሩ በሮችና መስኮቶች አሉት::

[3] የዓማራ ክልል የቱሪስ መስህብ ሐብቶች አጭር ቅኝት ገፅ 65::



www.ethiopianorthodox.org

## ኡራ ኪዳነ ምሕረት

ይህቺ ቤተ ክርስቲያን በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዐፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት በአቡነ ዘዮሐንስ ተመሠረተች:: መስራቹ አቡነ ዘዮሐንስ ከሸዋ መርሐ ቤቴ የመጡ ሲሆን በቀድሞ ደብረ አስቦ ገዳም በአቡነ ሕዝቅያስ እጅ ቅስና እንደተቀበሉ፤ በጣና ሐይቅ ደቡባዊ ምሥራቅ ዳርቻ በደራ ወረዳ ከሚኖሩ ጥቂት ክርስቲያኖች ጋር ቆይታ አድርገው ወደ ክብራን ገብርኤል ደሴት እንደሔዱ ገድላቸው ይናገራል:: ኡራ ኪዳነ ምሕረት በክብ ቅርፅ የተሠራች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ናት:: የቅኔ ማህሌቱ ከሸንበቆ፣ ቅድስቱና መቅደሱ ከጭቃና ከድንጋይ የተሠሩ ሲሆኑ እስከ ቅርብ ጊዜ ጣሪያው በሳር ክፍክፍ የተሸፈነ ነበር:: የመቅደሱ ዙሪያ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደተሠሩ የሚነገርላቸው ውብ ቅዱሳት ሥዕሎች ያጌጠ ነው:: ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት፣ የነገሥታት ዘውዶች፣ ካባዎችና መስቀሎች ከታሪካዊ ቅርሶች ጥቂቶች ናቸው:: ኡራ ኪዳነ ምሕረት ወንዶችም ሴቶችም ሊጐበኟት ይችላሉ::

## ደብረ ማርያም ገዳም

ከባሕር ዳር ከተማ የሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫን በመያዝ በጀልባ ለ20 ደቂቃ አልያም በእግር ለ30 ደቂቃ በመጓዝ የአባይ ወንዝ በታንኳ በማቋረጥ የደብረ ማርያም ገዳም ወደ ምትገኝበት ደሴት መግባት ይቻላል:: አካባቢው በሁለት ተጨማሪ ስሞች ይታወቃል:: እነኝህም ጉማሬ ባሕር እና «አባይ ራስ» ይባላሉ:: ጉማሬ ባሕር የተባለው በአካባቢው ጉማሬዎች ስለሚገኙ ሲሆን፤ አባይ ራስ የተባለው ደግሞ የአባይ ወንዝ የሐይቁን ውሀ ሰንጥቆ የሚወጣበት ሥፍራ በመሆኑ ነው::

የተለያዩ የታሪክ ቅርሶችን የያዘችው የደብረ ማርያም ገዳም የተመሠረተችው በዐፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት 1307-1327 ዓ.ም. ሲሆን፤ ደብሩ እንዳሁኑ ሳይሆን ስመ ጥር





ገዳም እንደነበር ይነገርለታል:: የገዳሙ ታላቅነት የሚታወቀው በድሮ ዘመን የደብረ ሊባኖስና የሌሎች ገዳማት ካህናት ስለ ገዳማትና ካህናት የአስተዳደር ሥርዓትና ስለ ሃይማኖት ጉዳይ እንዲመካከሩ ወደዚህ ገዳም ተልከው እንደነበር ይታወቃል:: ይህን ገዳም ያቋቋሙት አቡነ ታዴዎስ ናቸው:: የመጡት ከሸዋ ሲሆን፤ የአባታቸው ስም ሩማንዮስ የእናታቸው ማርታ ይባላል:: አስተዳደጋቸው እንደ ሌሎች ሕፃናት ሳይሆን የሚሠሩት ሁሉ እንደ አዋቂ ነበር:: ታዝለው ቤተ ክርስቲያን ሲሔዱ ካህናቱ ስብሐተ እግዚአብሔር በሚናገሩበት ወቅት እጃቸውን እየዘረጉ አብረው ይዘምሩ ነበር:: የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ በየቦታው እየዞሩ መንፈሳዊ ሥራዎችን ፈፅመው በ60 ዓመታቸው ከሌሎች ብዙዎች የሥጋ ዘመዶቻቸው ጋር ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ሥርዓተ ምንኩስናን ተቀበሉ:: የአቡነ ተክለሃይማኖት ረድእ ሆነው ብዙ ጊዜ በደብረ ሊባኖስ ተቀምጠዋል:: ከዚያ ወደ ጣና በመሔድ ይህቺን ገዳም መሠረቱ::[4]

## ክብራን ገብርኤልና እንጦንስ ገዳም

ከባሕር ዳር ከተማ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ የ45 ደቂቃ የጀልባ ጉዞ በኋላ ብዙም ያልተራራቁ ደሴቶች ይገኛሉ:: ደሴቶቹ የሚገኙት ማራኪ በሆነ ተፈጥሮአዊ የመሬት አቀማመጥ ባለው ደን በተሸፈነ ኮረብታማ ሥፍራ ነው:: ደሴቶቹ ክብራን ገብርኤልና እንጦንስ በመባል ይታወቃሉ:: ክብራን ገብርኤል የወንድ እንጦንስ ደግሞ የሴት መናንያን መኖሪያ በመሆን ለብዙ ዓመታት ቆይቷል:: ይህን ገዳም ያቀኑት አቡነ ዘዮሐንስ የተባሉ ናቸው::

አቡነ ዘዮሐንስ በመርሐ ቤቴ በሸዋ ተወለዱ፤ በደብረ ሊባኖስ የተማሩና የመነኮሱ ሲሆን ወንጌልን ለማስተማር ወደ ጣና ባሕር አካባቢ አጠገብ ደረሱ:: በዚህ ዘመን የነበሩት የደብረ ሊባኖስ 4ኛው እጨጌ ሕዝቅያስ ከእርሳቸው በፊት እንደነበሩት እጨጌ አቡነ ፊሊጶስ የወንጌልን ማስፋ

[4] ዜና ቤተ ክርስቲያን 24ኛ ዓመት ቁጥር 43 ገፅ 4::



www.ethiopianorthodox.org

ፋት ከፍተኛ ስሜት ያላቸው መሆኑ ይታወቃል። ይህም አቡነ ዘዮሐንስ ወደ ጣና የተላኩት በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም።

በገድለ ዮሐንስ እንደተመዘገበው ጻድቁ በመጀመሪያ እምብራ ደርሰው ከአንድ ቤተሰብ ቤት አረፉ። የእነዚህ ቤተሰብ ባልየው ገብርኤል ሚስትየዋ መስቀል ክብራ ይባላሉ። እዚህ ሆነው የአካባቢውን ሁናቴ ካጠኑ በኋላ እርሳቸው ክብራን ብለው ወደሰየሙት ደሴት ገብተው ገዳም አቋቋሙ። የገዳሙን ቤተክርስቲያን ታቦተ ገብርኤልን አደረጉ። የመልአኩም ስም ሆነ ደሴቱ እላይ ጻድቁን ካስተናገዱ ሰዎች ጋር ግንኙነት አለው። ገድሉም ይህን ይደግፋል ይህም:- «ገብርኤል የመስቀል ክብራ ባለቤት ሥራው አሣ ማጥመድ ነበር። አቡነ ዘዮሐንስ በገብርኤል ቤት ከተስተናገዱ በኋላ ዓሣ አጥማጁን ከደሴቱ እንዲያደርሳቸው ጠየቁትና አደረሳቸው ደሴቲቱን በሚስቱ ስም ክብራን አሉዋት በደሴቲቱ ታቦተ ገብርኤልን ስለ ወዳጃቸው ፍቅር ብለው ተከሉት» ይላል።

አቡነ ዘዮሐንስ በመሠረቱት ገዳም ማኅበር ሠሩላቸው። መነኮሳትና መነኮሳይያት ከያሉበት ተሰበሰቡላቸው። ግን ወንድና ሴት መነኮሳት በአንድነት መኖር ደግ መስሎ ስላልታያቸው በአጠገቡ የሚገኘውን ደሴት ዛሬ እንጦንስ ተብሎ የሚታወቀውን የሴት ገዳም አድርገው ሴት መነኮሳቱን በሙሉ ወደዚያው አዛወሩአቸው። ከዚህ በኋላ ሴቶች በዚህ ገዳም እንዳይገቡ ከለከሉ። ይህ ደንብ እስከዛሬ እንደፀና ይገኛል። የ9ኙ ከዋክብት ሐዋርያዊ ተልእኮ ንጉሥ አምደጽዮን የሚደግፈው ስለነበር የመልእክታቸውን ውጤት በቅርብ ይከታተል ነበር። እንዲያውም አንድ ጊዜ ራሱ ወደ ቦታው በመሔድ የሚደርስባቸውን ችግር ለማቃለል ሞክሯል። ዋናው ችግራቸው መገልገያ ቤተ ክርስቲያን ስለነበር እንዲሠሩላቸው አድርጓል። አቡነ ዘዮሐንስም የንጉሥ አምደ ጽዮን እርዳታ በዚህ መልክ አልተለያቸውም።

የአቡነ ዘዮሐንስ ገዳም በቅንጅት ረገድ የተዋጣለት ሆኗል። የመነኮሳቱ ቁጥር ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ





ሔዷል፤ በዚያው ልክ የሥራ ክፍፍሉ አምሯል፤ በቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት የተሠማሩ የነበሩ ደግሞ በተግባረ እድ ያገለግሉ ነበር፤ የተግባረ እዱ ሲነሣ ጐላ ብሎ የሚታየው የጽሕፈቱ ሥራ ነበር። በጽሕፈት ሥራ የሚያገለግል አንድ የመነኮሳት ቡድን ነበር። የእነርሱ አገልግሎት መጻሕፍትን መገልበጥ ነበርና በዚህ ረገድ ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አድርጓል። ክብራን ለየብስ የቀረበ በመሆኑ ለአደጋ የተጋለጠ ነው። ይህም ሆኖ ዛሬ ወደ ሁለት መቶ የሚጠጉ የብራና መጻሕፍት ግማሹ አልጋ ላይ ተጋድመው፣ ሌሎች ደግሞ በማህደር ገብተው ይገኛሉ። ከእነዚህ በአብዛሃዎቹ ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት የተጻፉ ናቸው። በመሐመዳውያኑ አረመኔያዊ ድርጊት (በግራኝ ወረራ) ጊዜ ከጥፋት ድነዋል። ክብራን የትምህርት ማዕከል ስለሆነች አያሌ ምሁራንን አስመርቃለች።

የክብራን ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ የተሠራው በሀፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ሲሆን በዳግማዊ ዳዊትና በኋላም በአድያም ሰገድ ኢያሱ በድጋሚ እንደተሠራ ይነገራል። ቤተ ክርስቲያኑ በወጉ በተጠረቡ ቀያይ ድንጋዮች የታነፀ ነው። በቤተ መቅደሱ ዙሪያ ከድንጋይ የተጠረቡ 12 ዓምዶች ይገኛሉ። ከመቅደሱ ግድግዳ ጋር ተያይዞ የተሠራ ክፍል ውስጥ የገዳሙ መሥራች የአቡነ ዘዮሐንስ መቃብር ይገኛል። በደሴቱ አናት ላይ በታነፀው የክብራን ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንና እንዲሁም በዐፄ ፋሲል እንደተሠራ የሚነገርለት እቃ ቤት ውስጥ በርካታ ታሪካዊ ቅርሶች ይገኛሉ። ከእነዚህም ውስጥ በሉቃስ እንደተሠራች የሚነገርላት ስዕለ ማርያም፣ ከብረት የተሠራ የአቡነ ዘዮሐንስ የጸሎት ልብስ፣ የዐፄ ኢያሱ አልጋና ሰይፍ፣ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ተደራራቢ አልጋ፣ ከእንጨት የተሠሩ መቅረዝና አገልግል፣ መስቀሎች፣ የገበታ ላይ ሥዕሎች፣ እላይ ያየናቸው በርካታ የብራና መጻሕፍት የገዳሙ ንዋያተ ቅድሳት የኢትዮጵያ ቅርስ ናቸው።[5]

[5] መለከት መጽሔት 6ኛ ዓመት ቁ. 1 ገጽ 29፤ የቤ/ክ መዝገበ ቃላት ቁ.8ገፅ 56-59።



www.ethiopianorthodox.org

## ደብረ ሲና ማርያም ገዳም

ከጎረጎራ ወደብ ክበብ በአጥር ብቻ የተለየችውና በጣና ሐይቅ ዳርቻ የምትገኘው ደብረ ሲና ማርያም ቤተ ክርስቲያን በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዐፄ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግስት አባ ኤስድሮስ በሚባሉ ባህታዊ እንደ ተሰራች የቤተክርስቲያኑ ካህናት ያስረዳሉ። አባ ኤስድሮስ አመጣጣቸው ከሸዋ ደብረ ሲና ስለነበር ቤተ ክርስቲያኗም ደብረ ሲና ማርያም ተብላ ተጠራች። በክብ ቅርፅ ከጭቃና ከእንጨት የተሰራችውና ባማረ የሣር ክፍክፍ የተሸፈነችው የደብረ ሲና ማርያም በደህና ሁኔታ ከሚገኙት ጥንታዊ አብያተ ክርስቲያናት አንዷ ናት።

የቤተ ክርስቲያኗ መቅደስ ዙሪያ እጅግ በሚያስደንቅ መንፈሳዊ ስዕል የተሞላ ነው። ስዕሉ የተሰራው በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሲሆን ያሰሩትም የፀዬ ፋሲል እህት ወ/ሮ መለኮታዊት ናቸው ይባላል። በ1970ዎቹ በባሕል ሚኒስቴር ባለሙያዎች አማካኝነት ሳይንሳዊ የቅርስ ጥገና እደሳ መርህን በተከተለ መንገድ በተደረጉት የእድሳት እርምጃዎች የቤተክርስቲያኑ ስዕሎች ጥንቲዊ ገፅታቸውን እንደጠበቁ ይገኛል። ስንክሳርና ሃይማኖተ አበው፣ ድጓ ሌሎች የብራና መጻሕፍት የቤተክርስቲያኗ ጥንቲዊ ቅርሶቿ ናቸው።[6]

## ኮታ ማርያም ገዳም

ደቅ በተባለው ደሴት ውስጥ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች የሚነገርላት ኮታ ማርያም ናት። ቤተ ክርስቲያኗ ዳጋ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ባቀኗት በአቡነ ኂሩተ አምላክ እንደተመሰረተች የገዳሟ ካህናት ያስረዳሉ። ኮታ ማርያም በክብ ቅርፅ የታነፀች ዙሪያዋ ከእንጨት፣ ከጭቃና ከኖራ የተሰራች ጣሪያዋ በሣር ክፍክፍ የተከደነ ነው። ወለሉ ደግሞ በጥንቃቄ ተስንጥቀው በጠፈር በተያያዙ ሸንበቆዎች ተሸፍኗል። ጣሪያውን ደግፈው የያዙት 12





ረዥምና ወፋፍራም አምዶች ናቸው። በመቅደሱ ዙሪያ የተገጠሙት መስኮቶች ልዩ የቅርፃ ቅርፅ ጥበብ ይታይባቸዋል። በ1978 በ1983 እና በ1984 ዓ.ም አንዳንድ የቤተ ክርስቲያኗ አካሎች በባሕል ሚኒስቴር የቅርስ ጥገና ባለሙያዎች የተወሰነ እድሳት ተደርጎላቸዋል። በመቅደሱ ግድግዳ ላይ የነበሩ ጥንታዊ የቅዱሳን ስዕሎች ግን ከእድሜ ብዛትና ከእንክብካቤ ጉድለት ከፉኛ ተጎድቷል። ኮታ ማርያም ገዳም የተመሠረተችው ከ1268-1337 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።[7]

## አዝዋ ማርያም

በጥንታዊ ቅብ ስዕሎች ከሚታወቁት የዘጌ ገዳማት አዝዋ ማርያም አንዷ ናት በዐፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት እንደተመሰረተች የሚነገርላት አዝዋ ማርያም በመቅደሷ ዙሪያ ያማሩ የግድግዳ ቅብ ስዕሎች የያዘች ናት። በዘጌ የሚገኙ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ስዕሎች የተሠሩት በአዝዋ ማርያም ስለነበር አንዳንድ ጊዜ «ስዕል ቤት» ተብላ ትጠራለች። ይህቺ ቤተ ክርስቲያን ረጅም ዘመን እንዳሳለፈች ዙሪያውን በቅፅረ ቤተ ክርስቲያኑ የተተከሉና ረጅም እድሜን ያሳለፉ አፀዶች ምስክሮች ናቸው። የቤተ ክርስቲያኗ አሰራር ዙሪያ ክብ ሆኖ በሦስት ክፍሎች የተከፈለ ነው። የአዝዋ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የግድግዳው እና የጣሪያው ማገር ለማስተሳሰር ይረዳ ዘንድ እንደ ገመድ የተጠቀሙበት የ400 ከብቶችን ቆዳ በመተልተል ነው። የአዝዋ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በር የመዝጊያ ቁልፍም ከታቦተ ሕጓ ጋር ከቅድስት አገር ኢየሩሳሌም በአቡነ ዮሐንስ እጅ እንደመጣ ይነገራል።[8]

---

[6] የአማራ ክልል የቱሪስት መስህብ ሐብቶች አጭር ቅኝት ገፅ 69።

[7] ዝኒ ከማሁ ገፅ 69።

[8] ቅዱሳን ማካናት በኢትዮጵያ ክፍል 1 ገፅ 102።



www.ethiopianorthodox.org

## ምንዳባ መድኃኔዓለም

ይህ ገዳም የሚገኘው በጎረጎራ ወደብ አካባቢ በሚገኝ ቦታ ላይ ሲሆን ግማሽ ጎኑ በውሀ የተከበበና ቀሪው የገዳሙ ክፍል ደግሞ ከየብስ ጋር ተያይዞ የሚገኝ ገዳም ነው:: ገዳሙ የተመሰረተው በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሲሆን የገዳሙ አቅኚ አባ አሳይ የተባሉ አባት ናቸው:: እንዲያ ውም እኝህ ጻድቅ አባት የጣና ሐይቅ ገዳማትን ካቀኑ ከ9ኙ ከዋክብት ተብለው ከሚጠሩት አንዱ ናቸው:: አቡነ አሳይ ወደ ገዳሙ የመጡት በድንጋይ ላይ ቆመው ከእምነታቸው ፅናት የተነሳ ድንጋዩን እንደ ጀልባ ተጠቅመውበት እንደ ነበር መነኮሳቱ የጻድቁን ገድል በመጥቀስ ያስረዳሉ::

ይህ የድንጋይ ጀልባ አሁን ድረስ ከገዳሙ ግቢ በስተ ምዕራብ በኩል በክብር ምእመናን እንዲያዩት ተደርጎ ተቀ ምጦ ይገኛል:: የገዳሙ መጠሪያ ስም የተገኘው ከእኝሁ ጻድቅ ግሩም ሥራ የተነሳ ነው:: አባ አሳይ በድንጋይ ጀልባ ተቀምጠው በውሀ ላይ በሚያስደንቅ ሁኔታ በመመላለሳቸው ምክንያት የተነሳ «ማን እንደ አባ አሳይ» እንደርሳቸው ያለ የለም ተባለ:: ከዚህም ጋር የገዳሙ ስም «ማንዳባ መድኃኔ ዓለም ገዳም» ተብሎ ተሰየመ::[9] እነዚህ እንግዲህ በአብዛኛው በመግቢያው እንዳነሳነው በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተመ ሠረቱ ቅዱሳን መካናት ናቸው:: ለእነዚህ ገዳማት በበለጠ ለመስፋፋትና ለመደርጀት ምክንያቱ የሐይቅ ትምህርት ቤት መመስረት መሆኑን ባለፈው ተመልክተነዋል:: እውነ ተኛ የምንኩስና ሕይወት በተግባር ከሚፈፀም ባቸው የአገራ ችን ገዳማት ዋነኞቹ የሆኑት እነዚህ በጣና ሐይቅ ዙሪያ ያሉት ገዳማት:-

- ቅድስናን ገንዘብ ያደረጉ መምህራነ ቤተ ክርስቲያን የወጡባቸው
- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሙዚየም በመሆን እያገለገሉ ያሉ፤
- የምንኩስና ሕይወት በእጅጉ እንዲበለፅግ አስተዋፅኦ ያደረጉ፤
- የቅ/ያሬድንና የሌሎች አባቶች ቅርስ የተከማቹባቸው፤
- የኪነ ጥበባት መገኛ ሆነው የሚታዩ ገዳማት፤
- በውጭ አገር ቱሪስቶች ምድራውያን ገነት የተባሉ፤
- ገዳማቱ ለብዙ መነኮሳት መውጣት አብነት የሆኑ ናቸው::

---

[9] ዝኒ ከማሁ ገፅ 118።





# ክፍል አምስት

## አባ ጊዮርጊስ

አቡነ ኢየሱስ ሞዐ ከመሠረቱት ከሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ከተገኙት አባቶች አንዱ አባ ጊዮርጊስ ነው:: አባ ጊዮርጊስ የተወለደው በአሁኑ ጊዜ የአካባቢው ስም ጋስጫ ያለበት ቦረና በሚባለው ወረዳ ውስጥ በ1357 ዓ.ም ነው:: ለወላጆቹ አንድ ብቻ ሲሆን፤ አባቱ ከቤተክርስቲያን ሊቃው ንት አንዱ የነበረና በቤተ መንግሥትም መምህር ሲሆን ሕዝበ ጽዮን ይባላል:: እናቱም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እና መኳንንት ከሆኑት ከዚያው አገር ሰዎች የተወለደች እምነ ጽዮን ትባላለች:: አባቱ በተለይ የድጓ መምህር እንደነበር የሚያገለግለውም የቤተ መንግሥት ባለሟሎችና ነገሥታት በሚገለገሉባቸው ቦታዎች እንደሆነ ገድለ አባ ጊዮርጊስ ያስረዳል:: እናቱ ሃይማኖተኛ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላት መፍቀሪተ እግዚአብሔር ስለነበረች ልጅ በወለደች ጊዜ ስሙን በስማዕቱ በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም ሰየመችው:: ይህም የሆነው አንደኛ በሰማዕቱ ፍጡነ ረድኤት ሰማዕተ ልዳ በጊዮርጊስ ምልጃ ልጅ ስለአገኘች ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በእርሱ ስም የሰየመችው እንደሰማዕቱ የእውነት ምስ ክር መፍቀሬ እግዚአብሔር የተዋህዶ አርበኛ እንዲሆን ስለ ፈለገች በጊዮርጊስ ዘልዳ ታሪክ ትመስጥ ስለነበር ነው::

በዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት /ከ1365-1395/ ዓ.ም የገዳሙ አበምኔት አባ ሠረቀ ብርሃን ገዳሙን በሚያስተ ዳድርበት ዘመን አባ ጊዮርጊስ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገባ:: አባ ሠረቀ ብርሃን የተማረ ብቻ ሳይሆን ለቀናች ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪ ጭምር ነው:: በእርሱ ዘመን በዚያ መማር መታደል ነበር:: አባ ጊዮርጊስን በትምህርት ብቻ ሳይሆን በቀናች ሃይማኖትም ለመቅረፅ መልካም አጋጣሚ ሆኖለታል:: ከቅዱስ ያሬድ ቀጥሎ ሁለተኛውን ቦታ የያዘው ታላቅ የቤተ ክርስቲያናችን አባት ለመሆን የበቃው አባ ጊዮርጊስ በሥነ ጽሑፍ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን አገልግሏል::



www.ethiopianorthodox.org

ቀደም ብለን በሐይቅ ገዳም ታሪክ እንደተመለከት ነው አባ ጊዮርጊስ የተማረበት ሥፍራ ሐይቅ በመጽሐፍ የበለፀገ ስለነበር ልዩ ልዩ መጻሕፍትን በማንበብ እውቀትን አዳብሯል። በዘመኑ ከነበሩት ታላላቅ ሊቃውንት ስለ እምነት ተጠያቂ ከነበሩት አንዱ አባ ጊዮርጊስ ነበር። የትምህርቱን ጥልቀት የተረዳው ሀፄ ዳዊት 8 ወንድ ልጆቹንና 1 ሴት ልጁን እንዲያስተምርጸት ወደ ቤተ መንግሥት ወሰደው የልጆቹ ስም:- ቴዎድሮስ፣ ይስሐቅ፣ ቴዎፍሎስ፣ እንድርያስ፣ ህብተ ኢየሱስ፣ ሕዝቅያስ፣ ኢዮስያስ፣ እሌኒ፣ ዘርዐያዕቆብ ናቸው። ሁሉንም የንጉሡን ልጆች በእውቀትና በምግባረ ሠናይ ቀርጿቸዋል። ሁለቱን ብንመለከት የመጀመሪያው ቴዎድሮስና የመጨረሻው ዘርዓያዕቆብ ቅድሚያ አላቸው። ቴዎድሮስ ሕይወቱን በንፁህ ክርስቲያናዊ ሕይወት ከመምራቱም በላይ ቅዱስ ተብሏል፤ መታሰቢያውም ሰኔ 29 ቀን ይከበራል።[1] ዘርዓ ያዕቆብ በይበልጥ በሥነ ጽሑፍ የመምህሩን ፈለግ ተከትሏል። እንደ መምህሩ መጻሕፍትን ደርሷል ይህን እቦታው ላይ ስንደርስ እንመለከተዋለን።

አባ ጊዮርጊስ የዐፄ ዳዊትን ልጆች በቤተመንግሥት በሚያስተምርበት ጊዜ አልመነኮሰም ነበርና ንጉሡ ሴት ልጁን አጋብቶ በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ሊያስቀምጠው ፈለገ። አባ ጊዮርጊስ በምንኩስና መኖርን ስለመረጠ ጋብቻውን አልፈፀመም። ከዚህ በኋላ በዘመኑ ከነበሩት ጳጳስ አቡነ በርተሎሜዎስ ዘንድ ሔዶ ቅስናን ከዚያም አከታትሎ ምንኩስናን

[1] ቴዎድሮስ ቀዳማዊ ከዓፄ ዳዊት ቀጥሎ በኢትዮጵያ የነገሠ ሲሆን፤ ስሙ ግን በክብረ ነገሥት አልተመዘገበም። በዘመነ መንግሥቱ ገዳማትና አድባራት በርስት ጉልትነት የያዙትን መሬት ቀምቶ በዚህ ትልቅ ሀብት ሕዝብ /ምስኪኑ/ ይጠቀምበት ብሎ አከፋፍሏል። ለሥልጣንና ለውዳሴ ከንቱ ሳይጓጓ የቤተክነቱን ሔሜትና ወቀሣ ሳይፈራ ደፋር ንጉሥ እንደነበር ያመለክታል አባ ጊዮርጊስ ትምህርትን የመቀበል ችሎታውን ከሌሎች ወንድሞች የላቀ ሆኖ ስላገኘው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ልትከተለው የሚገባትን ዓላማ ያስረ ጻው ይመስላል። ቴዎድሮስ ቀዳማዊ በሁለት ነገሮች በክብረ ነገሥት ስሙ ሳይመዘገብ ቀርቷል አንደኛው ውዳቤ ከንቱ የማይፈልግ በመሆኑና ጸሐፊ ትዕዛዞችን ባለመመደብ ሲሆን፤ ሌላው ምክንያትን ነገሥታትን ተገን አድርገው ደሀውን የሚበድሉ በጊዜው የነበሩ የቤተክህነት ሰዎች ሕዝቡን የሚበዘብዙበትን መሬብ ለስበጠሠባቸው እንደከሃዲ ቆጥረው ስሙን በክብረ ነገሥት እንዳይመዘገብ ስለአደረጉ ነው። ግን በቤተ ክህነቱ ፈጽሞ የተጣላ ሰው አልነበረም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት፣ ተደራቢ ሚስት ያላገባ አብያተ ክርስቱያናትን የተከለ በመሆኑ የአረፍት ቀኑን በቅዱሳን ደረጃ መጽሐፍ ሥንክሳር ተመዝግቦለታል /ሰኔ 29 ተመልከት/ የተቀበረውም በአማራ ሳይንት ተድባበ ማርያም ነው [የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ልብነ ድንግል እስከ ይኩኑ አምላክ ተ.የ.መ ገጽ 124]





ተቀበለ። ምንኩስናን የተቀበለው በደብረ ጎል በአቡነ በጸሎተ ሚካአል ገዳም ነው። አባ ጊዮርጊስ እመቤታችንን በጣም ከመውደዱ የተነሳ ስሟን ከአፉ ለይቶ አያውቅም። ይህም በድርሰቶቹ ውስጥ በብዛት ይንፀባረቃል። በገድሉ እንደሚነበበው ድርሰት የምታስደርሰውም እርሷ እንደሆነች እንገነዘባለን። አባ ጊዮርጊስ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሕይወቱም ሆነ በሠራቸው ሥራዎች የሚከተሉትን ሦስት ነገሮች አበርክቷል።

## ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንዳይፋለስ ጠብቋል

አባ ጊዮርጊስ በሐዋርያዊ አገልግሎቱ ለእውነት የቆመ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንዳይፋለስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል። በዘመኑ በቅዳሴ ሥርዓት ንጉሡና ንግሥቲቱ የሚኖሩ ከሆነ ሥጋ ወደሙ ከቆሙበት ቦታ ይሄድላቸው ነበር። አንድ ቀን አባ ጊዮርጊስ ቅዳሴ ገብቶ ሳለ ንጉሥ ዳዊትና ሚስቱ ሊቆርቡ ቆመው ስጋ ወደሙ እስኪመጣላቸው ይጠብቁ ጀመር። እርሱ ግን በድርገት ጊዜ ይዞ መቆም ካለበት በር ላይ ቆመ፤ ንፍቁ ካህንም ወደ ንጉሡና ንግሥቲቱ እንሂድ ሊቀበሉ ይፈልጋሉና አለው። እርሱ ግን አይሆንም አለ። ንፍቁም ንጉሥ እኮ ነው ቢለው ወደ ሥጋ ወደሙ እያመለከተ «ንጉሠ ነገሥት ውእቱ ሥጋ ወደሙ ለክርስቶስ» የንጉሥ ክርስቶስ እውነተኛ ስጋ ወደሙ ነው አለው። ይህም መምህረ ሥርዓት እውነተኛ ሐዋርያ ምድራውያን ነገሥታትን በመፍራት ሕገ እግዚአብሔርን በመጣስ ንጉሠ ሰማይ ወምድር ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያሳዝን አለመሆኑን ያመለክታል።

## ብቃት ያለው ሥነ ጽሑፍ አቅርቧል

አንድ አባት ሊቅ የሚያሰኘው በትምህርት ደረጃው፤ በምርምር ሥራው፤ በሥነ ጽሑፍ አቀራረቡ እንዲሁም በብቃትና በመንፈስ ቅዱስ ሀብት በተቃኘው ሕይወቱ ነው። «ብዕር የአዕምሮ ምላስ ነው» እንደሚባለው በምሥጢር



www.ethiopianorthodox.org

ባሕር ይዋኝ የነበረው አባ ጊዮርጊስ ብዙ መጻሕፍትን በመድረስና በማስተላለፍ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ሁሉ ቅድሚያ አለው:: በሕይወቱ ከጻፋቸው መጻሕፍት በአሁኑ ጊዜ እስከ 26 የሚሆኑ ታውቀው፤ በግራኝ መሐመድ ከጠፉት ከተረፉት ውስጥ አሉ:: እነዚህንም ለማየት እንኳ ባይቻልም በስም መዘርዘር ይቻላል::[2] እነዚህም:-

፨

- 🕮 መጽሐፈ ምስጢር፤
- 🕮 መጽሐፈ ሰአታት /የቀን የሌሊት/፤
- 🕮 መሰንቆ መዝሙር፤
- 🕮 መጽሐፈ ብርሃን /የቀን የሌሊት/፤
- 🕮 እንዚራ ስብሐት፤
- 🕮 መጽሐፈ ድንግል ወይም ሕይወተ ማርያም፤
- 🕮 ኖህተ ብርሃን፤
- 🕮 ውዳሴ ስብሐት ወሰላምታ፤
- 🕮 ውዳሴ መስቀል፤
- 🕮 ውዳሴ ማርያም ዘአባ ጊዮርጊስ፤
- 🕮 መዝሙረ ማርያም፤
- 🕮 መልክአ ሕማማት፤
- 🕮 እሴብሀ ጸጋኪ፤
- 🕮 ቅዳሴ ማርያም መአዛ ቅዳሴ፤
- 🕮 ዜና ማርያም፤
- 🕮 ቅዳሴ እግዚእ ዘአባ ጊዮርጊስ፤
- 🕮 ርቱዕ ሃይማኖት፤
- 🕮 አርጋኖን፤
- 🕮 መልክዓ ስዕል፤
- 🕮 ጸሎተ ፈትቶ፤
- 🕮 መልክዓ ኤዶም፤
- 🕮 ውዳሴ ሐዋርያት፤
- 🕮 ጸሎተ ማዕድ፤
- 🕮 ተአምኖ ቅዱሳን፤
- 🕮 መልክአ ውዳሴ ናቸው::

[2] የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ታሪክ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ያልታተመ አነስተኛ ጥንታዊ ጽሑፍ 1993 ዓ.ም::





ከእነዚህ ሌላ ብዙ የማይታወቁ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን በማሕሌት አገልግሎት የሚውሉ አሉ:: ለምሳሌ በአባ ሳሙኤል ዘዋልድባ በመቃብሩ ላይ ሔዶ «በሰቀ ጽጉር ገዚፍ ይሰክብ ሥጋሁ፤ አባ ሳሙኤል ዘምዕዛ ምንኩስናሁ፤ አራዊተ ገዳም ሥዕናሁ፤ ይትጋነዩ ቅዳሜሁ፤ አካለ አንበሳ ግሩም ይመጥን በእዴሁ፤» ትርጉም:- «ምንኩስናው የእጣን መህዛ የሆነ አባ ሳሙኤል ሥጋው በወፍራም ፀጉር ማቅ ይተኛል፤ የበረሀ አራዊት በፊቱ ምስጋና ያቀርባሉ የሚያስፈራ አንበሳ አካልን በእጁ ይለካል» እያለ እንደደረደረው፤ በትርጓሜ በጸሎት የምንጠቀምባቸው ድርሰቶች ሲኖሩ የቤተክርስቲያንንም ሥርዓተ ጸሎት (Order of Prayer) የነደፈው እርሱ ነው:: የነግህ የሰርክ የመአልት የሌሊት እያለ ማለት ነው:: ለምሳሌ የጸሎት ቅደም ተከተልን ብናይ ከበስመ አብ ከሚለው ጀምሮ እስከ ይዌድስዋ መላእክት ድረስ ቅደመ ተከተላቸውን አስቀምጧል:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስና የሊቃውንት ጉባኤ በሌለበት በዚያን ዘመን ብቻውን የጸሎት ቅደም ተከተሎችን ሠርቷል::

## በሐይቅ ምን ዓይነት ትምህርት ይሰጥ እንደነበር ድርሰቶቹ ምንጭ ሆነዋል

በሐይቅ እስጢፋኖስ ምን ዓይነት ትምህርት እንደነበር ምንጭ የሚሰጡን ከላይ የገለጥነው የአባ ጊዮርጊስ ድርሰቶች ናቸው:: እነዚህም የዜማ፣ የቅኔ፣ የትምህርት ተብለው በሦስት ሊከፈሉ ይችላሉ:: እነዚህ ሦስት የትምህርት ዓይነቶች በድርሰቶቹ ውስጥ በጉልህ ሠፍረው ስለሚታዩ እንደ ምንጭነት ያገለግላሉ:: ስለዚህ በሐይቅ እስጢፋኖስ የዜማ፣ የቅኔ፣ የትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርት እንደነበር ለመረዳት እንችላለን::

አባ ጊዮርጊስ የቅዱስ ያሬድን ትምህርት በጥልቀት ከሚያውቁት አንዱ ነው:: በዜማ በኩል በያሬድ መስመር ከያሬድ ቀጥሎ ከተነሡት የዜማ መምህር 8ኛው ለመሆን ችሏል:: ከሌሎች በተለይ ግን በጉዲት የጠፋውን የቅዱስ



www.ethiopianorthodox.org

ያሬድን ድጓ እንደገና ሲጻፍ ከያሬድ በኋላ ለተነሱ ቅዱሳን እስከ እርሱ ድረስ ላሉት ማሕሌት የደረሰ የቅዱስ ያሬድን ዜማ በሁሉ መልኩ ያስፋፋ የድጓ መምህር ነበር። ይህ ሊቅ በዜማ ረገድ ከያሬድ የወረደውን ዜማ በማስተላለፍ ብቻ አስተዋፅኦው አልተገታም። አዲስ አስተዋፅኦ በማድረግ ለቤተ ክርስቲያን መገልገያ አዲስ ድርሰትና ዜማ በማዕከል አቅርቧል። ይህንኑ የኢትዮጵያዊቤተ ክርስቲያን እስከ ዛሬ ትገለገልበታለች። ይኸውም የማዕልትና የሌሊት ሰአታት ነው።

የቅኔ ትምህርቱ የሚለካው ደግሞ ውዳሴ መስቀል፣ ውዳሴ ሐዋርያት፣ መጽሐፈ ስብሐት የሚባሉት በግጥም የተጻፉት ድርሰቶቹ ናቸው። የመጽሐፍ ትመህርቱ የሚለካው እንደዚሁ ድርሰቶቹ ሲሆኑ፤ በተለይ መጽሐፈ ምሥጢር የሚባለው መጽሐፍ የእውቀቱን ስፋት፣ ጥልቀት አጉልቶ ያሳያል እነዚህ መጻሕፍቶቹ ግማሹን ሐይቅ ሌላውን በጋስጫ በሚገኘው ገዳሙ እንደጻፈው ይታማናል።

## የአባ ጊዮርጊስ እረፍት

አባ ጊዮርጊስ በተወለደ በ60 ዓመቱ ሐምሌ 7 ቀን 1417 ዓ.ም አርፏል። በስሙ የሚጠራው ገዳም በወሎ ክፍለ አገር በቦረና አውራጃ ይገኛል። እዚህ አባ ጊዮርጊስ ከጳጥኝ አንድ ቤተ ክርስቲያን ሠርቷል። የተቀበረውም በዚሁ ገዳም ሲሆን ቤተ ክርስቲያኑ የተሰራው በህፄ ይስሐቅ ዘመን ከ1399-1414 ዓ.ም ሲሆን፤ ይህን ገዳመ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ግራኝ አቃጥሎት ነበር።[3] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በሞት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ መሪር ኀዘን አዝነዋል። የተወሰኑትን ኀዘናቸው የሚከተለው ነበር።

[3] አማርኛ የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁጥር 7 ገጽ 83።





- ⇨ አ መዝገበ የውኃት ወትራህርሆት አይቴኑ ኀድገነ፤
  *የየወህት መዝገብ ሆይ ለማን ተውከን፤/*
- ⇨ አ ቀላየ መጽሕፍት ወምንሐረ ድርሳናት አይቴኑ ኀለፍከ፤
  *የመጻሕፍት ወንዝና የድርሳናት ምንጭ ሆይ ወደየት አለፍክ፤*
- ⇨ አ ፍካሬ ህቡአት ወፀባቴ ሐቲ መለኮት አይቴኑ ፈለስከ እማዕከሌነ፤
  *የተሰወሩትን የምትተረጉምና አንዲት መለኮትን የምትመረምር ሆይ! ከመካከላችን ወደየት አለፍክ፤*
- ⇨ አባ አባ አፍሆሙ ለነቢያት ወልሳኖሙ ለሐዋርያት፤
  *ብርቱ አባት ሆይ! የነቢያት አፋቸው የሐዋርያት አንደበታቸው ነበርክ፤*
- ⇨ አባ አባ እፎ ያንቀለቅል ልበ ወየሃውከ አመፀቱ ወዝክረ ሞትከ፤
  *ብርቱ አባት ሆይ የሞትህ መታሰቢያ በገባ ጊዜ ምንኛ ልብን ያንዋውፃል ያውካል፤*
- ⇨ አባ አባ አፈወርቅ ሐዲስ እፎ ተገደፍቀ ውስተ ገጸ ምድር፤
  *ብርቱ አባት ሐዲስ አፈወርቅ ሆይ በምድር መቃብር ውስጥ እንዴት ተጣልህ፤*
- ⇨ አባ አባ ብዕሲ ሰማያዊ ወመልአከ ምድራዊ
  *ብርቱ አባት ሆይ! ሰማያዊ ሰውና ምድራዊ መልአክ ነበርህ፤*
- ⇨ አባ አባ ፀሀይ ብሩህ ዘበሔረ አግአዚ ወገህህ ወርህ ምሉዕ ዘዕልመተ ሌሊት፤
  *ብርቱ አባት ሆይ! ብሔረ አግአዚት የተባለች ኢትዮጵያ በሩህ ፀሀይና የሌሊት ጨለማ የምሉዕ ጨረቃ ብርሃን ነበርህ፤*
- ⇨ አባ አባ ተቅዋመ ማህቶት ለቤተ ክርስቲያን ዘያበርህ ዕልመተ ህሊናሆሙ ለውሉዳ፤
  *ብርቱ አባት ሆይ ለቤተ ክርስቲያንና ለልጆቿ ሀሳብ ጨለማን የምታበራ የመብራት መቅረዝ ነህ፤*

ይህን የመሳሰለውን ለቀሶ እያለቀሱ እንዳዘኑ ገድሉ ይጽፋል። ከዚህና እዚህ ላይ ካልተጻፉት የደቀመዛሙርቱ ኀዘን የምንረዳው ነገር ቢኖር አባ ጊዮርጊስ የሁሉም ነገር መምህር መሆኑን ነው።



www.ethiopianorthodox.org

# ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የአባ ጊዮርጊስ አስተዋፅኦ

## 1 ኢትዮጵያዊ ትምህርተ ሃይማኖት አስተላልፏል::

አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን በቅዱስ ማርቆስ የተሰበከውን የተዋህዶን እምነቷ ከእስክንድርያ በማምጣት በመላ ኢትዮጵያ እየዞረ ሰብኳል:: በ5ኛው መቶ ክፍለ ዘን የመጡትም ተሰዓቱ ቅድሳን በልኦን ሊዮን በኬልቄዶን ያፀደቁትን የአንድ አካል ሁለት ባህርይ ትምህርት እነቅዱስ ዲዮስቆሮስ አውግዘው ጥርሳቸውን ያረገፉበትን የተዋህዶን እምነት ወደ ኢትዮጵያ በማምጣት ሲመሰረት የፀናችውን ቤተክርስቲያን የበለጠ አጠናክረዋታል:: አቡነ ሰላማም ሆነ ተሰዓቱ ቅዱሳን ያስተማሯቸው ትምህርቶች በበለጠ ምስጢር ተበራርቶ አልተገለጸም እንጻለ ነበር የተቀመጠው:: ስለዚህ ኢትዮጵያዊ ይዘት እንዲኖረው ቋንቋን ባሕልን በጠበቀ መልኩ እንዲተላለፍ ማድረጉ «መጽሐፈ ምስጢር» እና «መጽሐፈ ሰዓታት» መመልከቱ የበለጠ ያስረዳል:: ለምሳሌ በመጽሐፈ ሰአታት ስለ ነገረ ክርስቶስ የገለፀውን አንዱን ክፍል እንመልከት:

«ሞገሳችን ክብራችን የመድኃኒታችን ቀንድ ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እሱን የምናምንበት የፍቅር አንድነታችን ምልክት የምንጠጋበት የደኅነታችን ግድግዳ የማዕዘን ማቆሚያ የሕይወት ደንጊያ ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የተሰበሰበ ወርቅ የተሸሸገ እንቁ የበዛ ወርቅ ዐሥር እልፍ ነጥር ወርቅ ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ያልተሠራ ልብስ ያልተፈተለ መጎናፀፊያ ዱቄቱን ወደ መጣጣ የሳበ እርሾ ያለውን ያጣፈጠ ጨው ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ማዕበል የማይቀርበው መርከባችን ሌባ የማያገኘው ብል ነቀዝ የማያበላሸው ሣጥናችን ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እግዚአብሔር በተከላት በምስክር ድንኳን ለንጹሐን ቀሞ የሚያገለግላቸው የካህናት አለቃ ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ከምሥራቅ የወጣ ኮከብ በሰማይ የሚታይ እውነተኛ ፀሐይ ንጹሕ የሆነ ሙሽራ ይህ ኢየሰሱ ክርስቶስ ነው:: በአብ ዘንድ ልጅ በመንፈስ ቅዱስም ዘንድ መንፈስ /ሕይወት/ በድንግል ዘንድ ሕፃን በነቢያት ዘንድ ነቢይ በሐዋርያትም ዘንድ ሐዋርያ በሰማዕታት ዘንድ አክሊል /ዘውድ/ የሚሆን የማኅበር አለቃ እውነተኛ መምህር ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: [መጽሐፈ ሰዓታት ገጽ 68-69]





☞ ኢየሱስ ክርስቶስ ጥዑመ ስም ለዘይጼውዖ
ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚጠሩት ስሙ ጣፋጭ ነው::

☞ ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብስተ ሕይወት ለዘይበልዖ
ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚበሉት የሕይወት እንጀራ ነው::

☞ ኢየሱስ ክርስቶስ ጽዋዐ መድኃኒት ለዘይጸምዖ
ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚጠጡት የሕይወት ውሀ ነው::
/መጽሐፈ ሰዓታት/

እነዚህን አትኩረን ስንመለከት ፍፁም ኢትዮጵያዊ ባሕልና ጠብቀው ምስጢረ ሥጋዌን ያብራራሉ:: ይሁን እንጂ አባ ጊዮርጊስ አዲስ ትምህርተ ሃይማኖት /ዶግማ/ አመጣ ለማለት እንዳልሆነ አንባቢ ልብ ሊል ይገባል::

## 2 ኢትዮጵያዊ የመጻሕፍትን እይታ አንፀባርቋል::

በቋንቋ ይዘቱ፤ በህሳብ ጥልቀቱና ስፋቱ፤ ቅኔያዊነትን የተላበሰ የሥነ ጽሑፍ ሙያው፤ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ ነው:: የአባ ጊዮርጊስ ሥነ ጽሑፍ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሥነ ጽሑፍ የበላይነትን እንድትይዝ ካደረጉ ቅዱሳን አባቶች አንዱ ነው:: አርጌንስ፣ አርዮስ፣ ሰባልዮስ... በሥነ ጽሑፍ እየተጠቀሙ ቤተ ክርስቲያንን ባወኩ ጊዜ የእነቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፤ ቄርሎስ፤ አትናቴዎስ፤ ኤጲፋንዮስ፤ ባስልዮስ... በበለጠ ሥነ ጽሑፍ እየጻፉ የእነሱን የኑፋቄ ስርጭት አዝቅጠውታል:: በዚህም የክርስትና እምነት ባለበት እንዲሔድ አድርገውታል:: እንደዚሁም ሁሉ አባ ጊዮርጊስ በዘመኑ ተነስቶ ከፍተኛ ጥቅም ያለው ኢትዮጵያዊ ሥነ ጽሑፍ አቅርቧል::

## 3 ኢትዮጵያዊ የትርጓሜ ዘይቤ አበርክቷል::

ምንም እንኳ በእነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የተተረጎሙ ቅዱሳት መጻሕፍት ቢኖሩም አባ ጊዮርጊስ ኢትዮጵያዊነት ይዘታ ያላቸው ቦታና ቋንቋን፣ ባሕልን... በመጠቀም



www.ethiopianorthodox.org

በሥነ ጽሑፍ ውስጥ አስፍሯል፤ በደረሳቸው ድርሰቶች ውስጥ በበለጠ ተጠቅሞበታል:: ይህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሟላ /ያልጎደለ/ ቀጥተኛ እምነት እንዳላት ለትውልዱ በሚገባ ቋንቋ ኢትዮጵያዊ የሆነ የትርጓሜ ዘይቤ አበርክቷል:: ይህን የተረከበ ሰውም «የቀረበለትን መብላት እንጂ ሌላ እንዳይቀላውጥ» ያስገነዝበናል:: እነዚህ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያበረከታቸው ጹስተዋፅኦ ሲሆኑ እርሱ ደግሞ:-

- ❖ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቅ፤
- ❖ ቤተ ክርስቲያንን ከመናፍቅ የጠበቀ ሐዋርያ፤
- ❖ አሠረ ሊቃውንትን የተከተለ ሕይወት ያለው አባት፤
- ❖ ከታላላቅ በተለይ በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከነበሩ የነገረ መለኮት መምህራን /Teologians/ አንዱ ሊባል የሚችል አባት ነው::

# ክፍል ስድስት

## በዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት የገባው ግማደ መስቀል

የታላቁ ቆስጠንጢኖስ እናት እሌኒ ንግሥት የተባለች ደግ ሴት የክርስቶስን መስቀል መስከረም 17 ቀን በ320 ዓ.ም በእጣን ጢስ ምልክት ቁፋሮ አስጀምራ መጋቢት 10 ቀን አግኝታ በማስወጣት ታላቅ ቤተ መቅደስ ጎልጎታ ላይ ሠርታ በክብር አስቀመጠችው ይህ መስቀልም ከዚያ ዕለት ጀምሮ እንደ ፀሐይ እያበራ፣ ድውይ እየፈወሰ፣ አጋንንትን እያባረረ ልዩ ልዩ ተአምራትን እየሠራ ሙት እያስነሳ፣ እውራንን እያበራ ተአምራቱን ቀጠለ:: ይህንንም የፋርስ መንግሥት መስቀሉን ማርኮ ፋርስ ወስዶ አስቀመጠው:: በዚህን ጊዜ የኢየሩሳሌም ምእመናን የሮማውን ንጉሥ ሕርቃልን እርዳታ በመጠየቅ እንዲመለስ አድርገው በኢየሩሳሌም ብዙ ዘመን ሲኖር እንደገና ኃያላን ነገሥታት ይህን መስቀል እኔ እወስድ እኔ እወስድ እያሉ ጦርነት ፈጠሩ በዚህን ጊዜ የኢየሩሳሌም፣ የቁስጥንጥንያ፣ የአንጾኪያ፣ የኤ



የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት

ፌሶን፣ የአርመኒያ፣ የግሪክ፣ የእስክንድርያ የሃይማኖት መሪዎች በሽምግልና ጠቡን አበረዱት ከዚህም አያይዘው ኢየሩሳሌም የሚገኘውን የክርስቶስን መስቀል ለ4 ከፍለው በእጣ አድርገው በስምምነት ተካፈሉ:: ከሌሎች ነዋየ ቅድሳት ጋር በየአገራቸው ወስደው በክብር አስቀመጡት:: የቀኝ እጁ የተቸነከረበት የደረሰው ለአፍሪካ ሲሆን፤ ከታሪካዊ ነዋየ ቅድሳት ጋር በግብፅ የሚገኘው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ተረክቦ ወስዶ በክብር አስቀመጠው:: ይህ ግማደ መስቀል ለብዙ ዘመን በእስክንድርያ ሲኖር በዐፄ ዳዊት ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ገብቷል:: ስለዚህ ግማደ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ መግባት ሁለት ዓይነት የተለያዩ የታሪክ ምንጮች አሉን::

① ይህ ግማደ መስቀል ለብዙ ዘመን በእስክንድርያ ሲኖር በግብፅ እስላሞች እየበዙ ኃይላቸው እየጠነከረ ሔደ:: ከእስክንድርያም የሚኖሩ ክርስቲያኖች ለመስቀሉ ክብር አትስገዱ፣ የክርስትናን እምነት አጥፉ፣ ግብር ክፈሉ እያሉ እስላሞች አገዛዝ አፀኑባቸው:: በግብፅ የሚኖሩ ክርስቲያኖችም ስለሚደርስባቸው ግፍ አንድ ሆነው መክረው ለኢትዮጵያ ንጉሥ ለዳግማዊ ዐፄ ዳዊት እንዲህ የሚል መልእክት ላኩበት:- «ንጉሥ ሆይ በዚህ በግብፅ ያሉ እስላሞች ለክርስቶስ መስቀል ክብር አትስጡ፤ ክርስትናን አጥፉ ግብር ክፈሉ እያሉ መከራ እያፀኑብን ስለሆነ 10ሺ ወቄት ወርቅ እንስጥህለን አስታግስልን» ብለው ጠየቁት:: በዚህ መሠረት ዳግማዊ ዐፄ ዳዊት ለሃይማኖቱ ቀንቶ 20ሺ ሠራዊት አስከትሎ ወደ ግብፅ ለመዝመት ሲዘጋጅ በሌላ በኩል ደግሞ የአባይን ውሀ ለመገደብ ሙከራ ያደርግ ጀመር:: በዚህ ጊዜ በግብፅ ያሉ እስላሞች ፈሩ:: ከዚህ የተነሳ በግብፅ ያሉ እስላሞች በግብፃውያን ክርስቲያኖች ላይ ያደርሱት የነበረውን ግፍና መከራ ወዲያው አቆሙት::

የግብፅ ክርስቲያኖችም በዚህ ተደስተው 12ሺ ወቄት ወርቅ ለዳግማዊ ዐፄ ዳዊት ላኩላቸው ንጉሡም መልሰው «እንኳን ደስ ያላችሁ የላካችሁትን ወርቅ ልኬአለሁ የእኔ ዓላማ ወርቅ ፍለጋ አይደለም የክርስቶስ ፍቅር አስገድዶኝ



www.ethiopianorthodox.org

በተቻለኝ መጠን ችግራችሁን አስወግጃለሁ አሁን የምለምናችሁ በአገሬ ኢትዮጵያ ረሀብና ቸነፈር ድርቅ ስለ ወረደብኝ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሎበት የነበረውን መስቀልና የቅዱሳንን አፅም ከሌሎች ንዋየ ቅድሳት ጋር ለበረከት እንድትልኩልኝ» ብለው ላኩባቸው:: በእስክንድርያ ያሉ ምእመናን ይህ መልእክት እንደደረሳቸው ከሊቃነ ጳጳሳቱና ከኤጲስ ቆጶሳቱ ጋር ውይይት በማድረግ ይህ ንጉሥ ታላቅ ክርስቲያን ነው:: ስለዚህ ልቡ ደስ እንዲለው የፈለገውን የጌታችን ግማድ መስቀል ከቅዱሳን አፅምና ከንዋየ ቅድሳቱ ጋር አሁን በመለሰው 12 ወቄት ወርቅ የብርና የነሀስ የወርቅ ሳጥን አዘጋጅተን እንላክለት ብለው ተስማምተው በክብር በሥነ ሥርዓት በስረገላ በግመል አስጭነው ስናር ድረስ አምጥተው በአስረከቧቸው ጊዜ እያሸበሸቡ በግንባራቸው እየሰገዱ በክብር በደስታ ተቀበሏቸው:: ይህ የሆነው መስከረም 21 ቀን ነው::[1]

② ሌላው ስለ ግማደ መስቀሉ አገባብ ታሪክ ደግሞ በሀፄ ዳዊት ዘመን በአገራችን ረሀብ፣ በሽታ፣ ቸነፈር፣ ዛር፣ ጋኔን ሰዎችን እያጠቁ ነበር:: እነዚህ የተፈጥሮ መቅሰፍቶች ለማስወገድ መምህራነ ቤተ ክርስቲያን ለምሳሌ የደብረ ቢዘኑ አቡነ ፊሊጶስ፤ የዳጋው አቡነ ኂሩተ አምላክና፤ የዘጌው አቡነ በትረ ማርያምን፤ አስጠርቶ ምን ማድረግ እንደሚገባው ይጠይቃቸዋል:: እነሱም የክርስቶስን ግማደ መስቀል ከኢየሩሳሌም ቢያመጣ በሽታውም ረሀቡም እንደሚጠፋ ይነግሩታል:: ወዲያው ለእስክንድርያው፣ ለቁስጥንጥንያው፣ ለኢየሩሳሌሙ ፓትርያርኮች ግማደ መስቀሉን ከእነ ሥርዓቱ እንዲልኩለት በደብዳቤ ይጠይቃቸዋል:: እነሱም ለመላክ ፈቃደኛ ሆነው ተቀባይ ሰዎችን እንዲሰድ ይጽፉለታል:: ይህ ደብዳቤ የደረሰው መስከረም 10 ቀን ስለሆነ በዚሁ ቀን ሊቃውንቱንና ካህናቱን ሰብስቦ መስቀሉን የሚያመጡ 10 መነኮሳትን አስመርጧል:: እነሱም:-

[1] ትንሣኤ ቀጥር 72 ገጽ 6::





1. አባ ያፈቅረነ እግዚእ ዘጉብጉቤ፤
2. አቡነ ኂሩተ አምላክ ዘዳጋ፤
3. አባ ፊሊጶስ ዘደብረ ቢዘን፤
4. አባ በትረ ማርያም ዘዘጌ፤
5. አቡነ እንድርያስ ዘጣና፤
6. አቡነ ዮሐንስ ዘክብራን፤
7. አባ ያስያ /ሐሳይ/፤
8. አባ ታዴዎስ፤
9. አባ ዘካርያስ፤
10. አባ ቶማስ ሲሆኑ፤

እነዚህ መነኮሳት የጌታን ግማደ መስቀል ከኢየሩሳሌም ለማምጣት ከኢትዮጵያ ተነስተው ረጅሙን ጉዞአቸውን ተያያዙት:: በደህና ካሰቡበት ደርሰው ለሚመለከታቸው የሀፄ ዳዊትን ደብዳቤ አቅርበው ግማደ መስቀሉን መስከረም 10 ቀን ተረከቡ:: ከዚያም የመልስ ጉዞአቸውን ጀምረው በደህና ከአገራቸው ደረሱ:: ግማደ መስቀሉ ኢትዮጵያ የደረሰው በ1393 ዓ.ም. ነው:: የመስቀሉ መምጣት ዜና ቀደም ብሎ ከንጉሡ ዘንድ ደርሶ ነበርና ዐፄ ዳዊት ሠራዊቱን አሰልፎ ወደ ስናር ተጉዞ ግማደ መስቀሉን ተቀበለ:: ከመስቀሉ ጋር ተጨማሪ 27 ንዋየ ቅድሳት መጥተዋል:: ከእነዚህ መካከል አፅመ ቅዱሳን፣ ሉቃስ የሳላቸው ስዕሎች፣ ሐሞት የጠጣበት ሰፈነግ፤ አፅመ ገላውዴዎስ፤ ልብሱን ገፈው ያስታጠቁት ከለሜዳ፤ አፅመ ሐና፤ አፅመ በርተሎሜዎስ፤ አፅመ ጊዮርጊስ፤ አፅመ ሳዊሮስ፤ አፅመ ሕፃናት /በዘመነ ሰማዕታት የሞቱ/፤ እነዚህ የመሳሰሉት ንዋየ ቅድሳት መግባታቸውን በጣና ደሴት ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ የሚገኝ «መስቀል ዘዮም» የተባለ መጽሐፍ ይገልፃል::[2] እንግዲህ ግማደ መስቀሉ በዚህ መልክ በሀፄ ዳዊት ጊዜ ወደ አገራችን ኢትዮጵያ ገብቷል:: ዐፄ ዳዊት ስናር ላይ ሲደርሱ ተቀም ጠውባት የነበረችው ባዝራ ጥላቸው አርፈዋል::

[2] ማዕዶት ቀጥር 18 ገጽ 13::



www.ethiopianorthodox.org

ዐፄ ዳዊት ካረፉ በኋላ የመጨረሻ ልጃቸው ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሲነግሥ ወደ ስናር ሔዶ መስቀሉን ካስመጣ በኋላ በመናገሻ ከተማው ደብረ ብርሃን ላይ ቤተመቅደስ ሠርቶ ለማስቀመጥ ሲደክም በሕልሙ «መስቀሌን በመስቀልኛ ቦታ ላይ አስቀምጥ» የሚል ሕልም አየ። ንጉሡም መስቀለኛ ቦታ እየፈለገ በኢትዮጵያ አውራጃዎች ሁሉ እንዲህ አይነት ቦታ ለመፈለግ ዞረ። በመጨረሻ በወሎ ክፍለ አገር አምባስል አውራጃ ውስጥ ግሸን ከምትባል ቦታ ደረሰ። በእርግጥም ይህች ቦታ ጥበበኛ ሰው እንደቀረፃት የተዋበች መስቀለኛ ቦታ ሆና ስለተገኘች የልቡ ስለደረሰለት በዚህች አምባ ታላቅ ቤተ መንግሥት አሠርቶ መስቀሉንና ሌሎች ንዋየ ቅድሳት በየማዕርጋቸው በክብር ቦታ መድቦ አስቀመጧቸው። ዘመኑም በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው። የተቀመጠው በግልጥ ቦታ ሳይሆን በስውር ቦታ ነው። እግዚአብሔር አብ በሚባል ቤተክርስቲያን በአንድ ዋሻ ውስጥ በድንጋይ ተለስኗል።[3]

ከመስቀሉ ጋር የመጡትን ንዋየ ቅድሳት ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለግሸን ካህናት በጽሑፍ መስከረም 21 ቀን በ1440 ዓ.ም. ላይ ተናገሩ። እንደገና ቤተ መቅደስ ተሰርቶ ቅዳሴ ቤቱ የተከበረው መስከረም 21 ቀን ነው። ስለዚህ በዚህች ደብር አሁን ድረስ መስከረም 21 ቀን ሕዝብ በብዛት እየተሰበሰበ ያከብራል። የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ እህት እሌኒ መስቀሉ ከሚገኝበት ከእግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በእመቤታችን ስም ቤተ ክርስቲያን አሠርታለች። ጥር 21 ቀን ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ። ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብም ይህችን ደብር «ደብረ ከርቤ ዳግማዊ ጎልጎታ» ብለው ሰየሟት።

[3] በዓፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ዋሻውን ለመክፈት ሙከራ ተደርጐ ነበር ዐፄ ቴዎድሮስ ከልብ የሚወዷቸው እና የሚያከብሯቸው ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች በሞቱ ጊዜ ሬሳቸውን አሸክመው በክረምት ወራት ወደ ጊሸን አመሩ። በስንት ጭንቅ በስፍራው ከደረሡ በኋላ የዘመን ታሪካቸው እቴጌ ተዋበች ግሸን መቀበራቸውን ገልጦ ያበቃል። ወደዚህ የመጡበት ምክንያት እቴጌ ተዋበች ግማደ መስቀሉን አስወጥተው የሚወዷቸውን ባለቤታቸውን ከሞት ለማስነሳት ነበር ሲከፈትም ከዚያ የሚወጣው ጋዝ የያዘ አየር ሰዎችን ገደለ። ከዚህ በኋላ የተከፈተው ዋሻ ተመልሶ እንዲዘጋ ተደረገ [አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁጥር 9 ገጽ 114]





ግሸን ማርያም ከላይ እንደገለፅነው በወሎ ክፍለ አገር በአምባሰል አውራጃ ውስጥ የምትገኝ ሲሆን በሐይቅና በመቅደላ፣ በዳለንታ፣ በየጁ መካከል በበሽሎ ወንዝ አዋሳኝ የምትገኝ ዙሪያዋን በገደል የተከበበች አምባ ናት። በበርዋ ከተገባ በኋላ ግቢዋ ከላይ ሜዳና መስቀለኛ ነው። ወደዚህች ደብር ለመሄድ በረህ አቋርጦ በሽሎን በመሻገር የ3 ሰዓት መንገድ አቀበት በመውጣት አንድ ቀን ሙሉ ተጉዞ ማታ 12 ሰዓት ይገባል። ግሸን በፊት ደብረ እግዚአብሔር ትባል ነበር። ይህ ደብረ እግዚአብሔር የሚባለው ስያሜ በንጉሥ ላሊበላ እጅ ከቋጥኝ ድንጋይ ተፈልፍሎ የተሠራ ቤተ መቅደስ በእግዚአብሔር አብ ስም ስለነበር ደብረ እግዚአብሔር ተብሎ ይጠራል። ከዚያ ዐፄ ደናግዣን /ከ822-841/ ዓ.ም. ዘመነ መንግሥት ሐይቅ እስጢፋኖስን ሲመሰርት፣ በአጠገቡ ደብረ ነጎድጓድ የሚባል ታላቅ ደብር ነበር፤ ግሸን የሐይቅ ግዛት ስለሆነች ከደብረ እግዚአብሔር ደብረ ነጎድጓድ ተብላለች። ከዚያም በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የክርስቶስ ግማደ መስቀል ግሸን ገብቶ ሲቀመጥ ከደብረ ነጎድጓድ ደብረ ከርቤ ተብላለች። የደብሩ አስተዳዳሪ መምህር እሥራኤል ዘደብረ ከርቤ ይባል ነበር።

# ክፍል ሰባት

## ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ ለቤተ ክርስቲያን ያደረገው አስተዋፅኦ

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የተወለደው በ1399 ዓ.ም. ከንጉሥ ዳዊትና ከእግዚእ ክብራ ነው። በልጅነቱ በአክሱም ከነበሩ ከአንድ መነኩሴ መምዐር ሲማር ከቆየ በኋላ መምህሩ ሲያርፍ ወደ ደብረ አባይ ሸዋ ሽሬ ተመለሰ። ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከጉርምስና እድሜው ጥቂቱን ያሳለፈው በግሸን አምባ ነበር። ከወንድሙ ከዐፄ ሕዝበናኝ ሞት በኋላ በተከታታይ በሥልጣን ላይ ወጥተው የነበሩት የዐፄ ዳዊት ሁለት ልጆች አጭር የንግሥና ዘመን ሲያበቃ የዘመዶቹ ሠራዊት አምባው ድረስ መጥተው ለሥልጣን እንዳበቁት በደብረ ጽጌ በሚገኝ «ገድለ



www.ethiopianorthodox.org

ዜና ማርቆስ» በተሰኘ ገድል እና እራሱ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በጻፈው «መጽሐፈ ብርሃን» በተሰኘ ድርሰቱ ላይ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በሥልጣን ላይ የቆየው ከ1426 እስከ 1460 ዓ.ም. ድረስ ለ34 ዓመታት ነው፡፡ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የታላቁ ሊቅ የአባ ጊዮርጊስ ደቀ መዝሙር ስለነበር የመምህሩን ፈለግ በመከተል በርካታ መጽሐፍትን በመድረስ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን አገልግሏል፡፡ ሀፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሳያቋርጥ ለ12 ዓመታት በደብረ ብርሃን ሥርዓትን እየደነገገ መጽሐፍትን እየጻፈና እያጻፈ ተቀምጧል፡፡ በዚህ በደብረ ብርሃን ከደነገጋቸው ነገሮች፤ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. በዓላትን አስወስኗል፤ የበዓላት በየወሩ መከበር የጀመረው የዚህን ጊዜ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን የተፈለገበት ምክንያት የዚያን ጊዜ አምልኮተ ጣኦት፣ ጥንቆላ ተስፋፍቶ ስለነበር እነዚህን ነገሮች ለማጥፋት ክርስቲያኖች እየተሰበሰቡ ትምህርት መውሰድ ነበረባቸው፡፡ አንድ እሑድንና በዓመት በዓላት ብቻ መገኘት በቂ አልነበረም፡፡ በዓሉን ብሎ የመጣውን ሰው ሰብኮ ለማስቀረት ያመቻልና፡፡ በዚህ መሠረት ቅዱሳን በዓመት አንድ ጊዜ ገድላቸው ተጽፎላቸው መታሰቢያቸው እየተከበረ ከ1ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደርሶ ነበር፡፡ ዘርዓ ያዕቆብ ግን በነገሠበት ዘመን መንፈሳዊ ስሜት ስለነበረው የቅዱሳንን ሕይወት፣ ታሪክ በሰፊው እየተነገረ፣ በዓላቸው እየተከበረ እንዲኖር ሕዝቡ ይህን ወደ መስማትና ወደ መከተል ያዘነብላል፡፡ የዚህን ጊዜ የጣኦት አምልኮት ከንቱ ሆኖ ይቀራል፡፡ የእግዚአብሔር ስም በየቦታው ይቀደሳል /ይጠራል/ የሚል ሃሳብ አመጣ፡፡ ይህን ሃሳብ ለመወሰን የተገደደበት ምክንያት ከዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ቀደም ባሉት ነገሥታት አምልኮተ እግዚአብሔር ቀዝቅዞ በማየቱ የተነሳ በየቦታው ባዕድ አምልኮ ተስፋፍቶ እንደነበር ይገመታል፡፡ ዘርዓ ያዕቆብ እንደነገሠ ይህ በመቀጠሉ፡-





ሀ. ባዕድ አምልኮ እንዲጠፋ አምልኮተ እግዚአብሔር እንዲስፋፋ፤

ለ. ባዕድ አምልኮ ወደሚፈፀምበት ቦታ ሰው እንዳ ይሄድ ወደ ቤተ ክርስቲያን የመሄጃ ምክንያት ለመፍጠር ሲሉ፤

ቅዱሳን በየወሩ በተለያዩ ዕለታት እንዲከበሩ፣ እንዲታሰቡ፤ በዚህን ጊዜ ዜና ገድላቸው እንዲነበብ እንዲተረጐም አደረገ፡፡ ከዚህ የተነሣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እያንዳንዱ ቅዱስ በየወሩ በተወሰነለት ዕለት ሲታሰብ ይገኛል፡፡ የዓመት በዓልም ተብሎ በስንክሳሩ እየተጻፈ ሁሉም በተለያየ ጊዜ ይከበራል፣ በጸሎት ይታሰባል፡፡ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ይህን በመወሰኑና በማስወሰኑ እስከ አሁን ድረስ ይህም ውሳኔ በቤተ ክርስቲያናችን ተጠብቆና ተከብሮ ይገኛል፡፡ ምክንያቱም ሕዝበ ክርስቲያኑን በአንድ ጊዜ ለማግኘትና ለማስተማር ቤተ ክርስቲያናችን አመቺ ጊዜን ፈጥሮላታልና፡፡[1]

በዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ይመለክ የነበረው ትልቁ «ዳስክ» የተባለው ዛር እጅግ ኃይለኛና ብዙ ተከታይ ያላት ሴት እንደሆነች ይነገራል፡፡ ፀፄ ዘርዓ ያዕቆብ ይህን ለማጥፋት የተጠናከረ እርምጃ አካሂዷል፡፡ ነገር ግን ዘመቻው በተጠናከረ መጠን የ«ዳስክ» እምነትም ስር እየሰደደ ይሄድ ነበር፡፡ ይህ እምነት መስፋፋት የወንጌል መልዕክተኛ እጦት እንደሆነ ስለደረሰበት የደብረ ሊባኖሱን እጨጌ /በዘመኑ የነበረውን ማለት ነው/ መርሐ ክርስቶስን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ሙገር ሔዶ እንዲያስተምሩ ታዝዘው እዚያ ብዙ ወራት አሳልፏል፡፡ እጨጌ መርሐ ክርስቶስም መልእክቱ ተሳክቶላቸዋል፡፡ ይህን የመሳሰለው ነገር እንዲጠፋ በዐላት መሠራታቸው ወሣኝ ነበር፡፡

2. ክርስቲያኑ ሕዝበ በአንገቱ ላይ ማተብ እንዲያስር የተወሰነውም በዚሁ በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ነው፡፡ የነገሩ አመጣጥ በደላይ የሚባል የአዳል መስፍን በጦርነት ተነስቶበት ነበር፡፡ በዚህን ጊዜ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጦርነት ከመግጠሙ በፊት አትርሡኝ እያለ በየገዳማቱና

[1] ትንሣኤ ቁጥር 140 ገጽ 7-8



www.ethiopianorthodox.org

አድባራቱ ይልካሉ:: ይህ መልዕክት የደረሳቸው አንዱ አባ ተከስተ ብርሃን የደብረ ወርቅ ጐጃም መምህር ናቸው:: እርሳቸውም ፈትል በእመቤታችን ሥዕል ላይ አኑረው ከጸለዩበት በኋላ ወታደሮችህ ይህን ክር አድርገው ወደ ጦር ሜዳ ይሰማሩ ብለው ፈትሉን ለዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ይልኩታል:: እርሱም እንደ ተባለው አድርጎ ከባለጋራው ጋር ጦርነት ገጥመው አሸንፈዋል:: ትምህርተ መዊዕ፣ ትምህርተ ኃይል ነው ሲል ክርስተያኖች ሁሉ ማተብ እንዲያደርጉ አዘዋል:: ከዚያ ተያይዞ እስከ አሁን ደርሷል በማለት ዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ በደብረ ወርቅ ጎጃም የሚገኘውን ገድለ ተከስተ ብርሃንን ጠቅሰው ገልፀዋል::[2]

3 ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት እንዲያመቸው ሁለት ጳጳሳትን እንዲሁም 1 ኤጲስ ቆጶስ ከግብፅ በ1438 ዓ.ም አስመጥቷል:: እነዚህ ጳጳሳት አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል ሲባሉ ኤጲስ ቆጶሱ ደግሞ አባ ዮሐንስ ይባላሉ:: ንጉሡ እነዚህን ሁለት ጳጳሳት በሁለት መንበር አድርገው:- አባ ሚካኤልን ባላስታ መንበራቸውን ዘርግተው በወሎ፣ በትግራይ፣ በኤርትራ እንዲሰብኩ ሲያደርግ፤ አባ ገብርኤልን ደግሞ በሸዋና በደቡብ ኢትዮጵያ እንዲሰብኩ አድርጓል::

4 እያንዳንዱ ካህን ማስተማር አለበት የማያስተምር ካህን ካለ ገዳም ገብቶ ይማር ያለዚያ ግን ንብረቱ፣ ርስቱም ይወረስ፤ ክህነቱም ይነጠቅ ብሎ አውጇል::

5 ለ100 ዓመታት ሲያከራክር የነበረውን የቀዳሚት ሰንበት መከበር አለመከበር እልባት ያገኘው በዚህ ዘመን ነው:: ሁለቱም ሰንበታት /ቅዳሜና እሁድ/ እንዲከበሩ ውሳኔ ላይ ተደርሷል::

[2] አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁጥር 2 ገጽ 223::





6 ቅዳሜና እሁድ እያንዳንዱ ምዕመን ወደ ቤተክርስቲያን ሔዶ ማስቀደስ አለበት:: በአጠገቡ ቤተ ክርስቲያን ከሌለ ካህናት ወደ መንደሩ እየሔዱ እንዲያስተምሩ አዟቸዋል።

7 እያንዳንዱ ክርስቲያን የንስሀ አባት ሊኖረው ያስፈልጋል:: ያለ ንስሀ አባት ፈቃድ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ሊቀበል አይችልም::

8 በእያንዳንዱ ቤተክርስቲያን ቤተ መጻሕፍት መቋቋም አለበት:: ልክ እንደ ኃይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ማለት ነው::

9 አረማዊ ምግባራት በማንኛውም ክርስቲያን ላይ እንዳ ይደረጉ፤ ድግምት፣ አስማት፣ የመሳሰሉት የምትሀት ሥራዎች እንዳይስፋፉ፤

10 ክርስቲያኖች በቤታቸው ላይ፣ በልብሳቸው፣ በማረሻቸው የመስቀል ምልክት እንዲያደርጉ በተጨማሪ እያንዳንዱ ቤተክርስተያን የእመቤታችን ታቦት በድርብ እንዲኖር፤

ይህን የመሳሰሉትን ሥርዓቶች በዘመኑ አስወስኗል:: ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጣኦታትን ለማጥፋት፣ ሥነ ጽሑፍ ለማስፋፋት የነበረው ፍላጐት ከፍ ያለ ሥለነበር ከክርስትና እምነት ውጭ የዛር፣ የቆሌ፣ የመናፍስት እንዲሁም የልዩ ልዩ ባዕድ አምልኮ ይዞ ይጓዝ የነበረውን ሕዝብ ለማስቀረት በሥነ ጽሑፍም በአዋጅ የፈፀመው መንፈሳዊ አገልግሎት በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በዓላትን፣ ስርዓትን መወሰን ማስወሰን ብቻ ሳይሆን ሊቅም ነበረ:: ሥነ ጽሑፍ እንዲስፋፋና በዘመኗ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሥነ ጽሑፍ የበላይነት እንዲኖራት አድርጓል:: የቤተ ክርስቲያን አባቶችን መጻሕፍትን እንዲጽፍ የሚያበረታታ ንጉሥ ነበረ::



www.ethiopianorthodox.org

## በዘመነ መንግሥቱ የተስፋፋው ሥነ ጽሑፍ

ይህ የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን «ሦስተኛው የሥነ ጽሑፍ ዘመን» በመባል ይታወቃል:: በዚህ ክፍለ ዘመን አዳዲስ ድርሰቶችና የትርጉም ስራዎች የተካሔዱበት ዘመን ነውና:: ገድል መጻፍ የተጀመረው በሀፄ አምደ ጽዮን ሲሆን አብዛኛዎቹ የተተረጎሙ ቃበር:: በዘመነ ዘርዓ ያዕቆብ ግን አዳዲስ ወጥ ገድሎች እናገኛለን ይህም በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የተጻፉ ናቸው:: በወጥነት የተደረሱት ገድሎች የመጀመሪያዎቹ በሃይማኖት በስደት ምክንያት የመጡት የዘጠኙ ቅዱሳን ነው:: ከእነዚህ በኋላ የተጻፉት የአብርሃ ወአፅብሐ እንደገና የቅዱስ የሬድ ገድል ከእነዚህ በኋላ ተጽፏል:: ከዘጠኙ ቅዱሳን መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ ገድላቸው የተጻፈላቸው አባ አረጋዊ፣ አባ ገሪማና አባ ጰንጠልዮን ናቸው::

ከዚህም ሌላ የደብረ ሊባኖሱ አበምኔት የነበሩት የአቡነ ፊሊጶስ ገድልም የተጻፈው በዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ነው:: አባ ፊሊጶስ የነበሩት በሀፄ አምደ ጽዮን ዘመን ነው:: እንደ አባ ፊሊጶስ ሁሉ የአንዳንድ ቅዱሳን ገድሎችም ተጽፈዋል የአባ ብጸሎተ ሚካኤልና የአባ አኖሪዎስ ዜና ገድላቸው ተጽፈዋል:: ገድለ ተክለ ሃይማኖትም የተጻፈው በዚሁ ዘመን ነው:: የጻፉት በደብረ ሊባኖስ የነበሩ መነኮሳት ናቸው:: በሀፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ግዕዝ ለታሪክ መጻፊያነት ውሏል:: በዚህ ዘመን ከተጻፉ አንዱ የንጉሥ ላሊበላ ታሪክ ነው ከንጉሥ ላሊበላ ሌላ ነአኩቶ ለአብ፣ ይምርሐነ ክርስቶስ የቅዱስ ላሊበላ ሚስት መስቀል ክብራ ታሪኮች በተጨማሪ የሀፄ ናዓድ ታሪክ የተጻፈበት ዘመን ነው::

እስከ አሁን ያየነው በአገር ውስጥ ሊቃውንት የተጻፉ ድርቶችን ነው፤ በዚሁ በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ብዙ መጻሕፍትም ተተርጉመዋል:: ከእነዚህም ውስጥ የእመቤታችንን ተአምር የሚገልፀው «ተአምረ ማርያም» ንጉሡ ከግብፅና ከኢየሩሳሌም አስመጥቶ ከአረቢኛ ቋንቋ ወደ ግዕዝ አስተርጉሞታል፤ ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ መጽሐፍም ተጣርቶ





የተጻፈውም በዚሁ ዘመን ነው:: በዚህ ወርቃማ ዘመን ከአረቢኛ ቋንቋ ከተተረጎሙት መጻሕፍት አንዱና ዋነኛው «ስንክሳር» ነው:: እንደ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገላለፅ በአረቢኛ ስንክሳር በግሪክ /ዕርዕ/ ሲናክሳሪያ ይባላል የመጽሐፍ ስም ነው:: ከዓመት እስከ ዓመት የሚነበብ የቅዱሳን ዜና ከገድላቸው ባጭር በአጭር ቃል የተሰበሰበ እሉድ ምእላድ እስትጉቡእ /ስብስብ/ ነው [መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ገፅ 876]

ይህ መጻሕፍ ይዘቱ የልዩ ልዩ ቅዱሳንን ተጋድሎ የሚያትት ነው:: ከዜና እረፍታቸው ጀምሮ በግጥም መልክ የተጻፈ አለው «አርኬ» ይባላል:: አርኬን የደረሰው አርከ ሥሉስ የተባለ የጎጃም ሊቅ ነው ስንክሳርን የተለየ የሚያደርገው በዓመቱ ቀኖች ልክ አንድ አንድ ምዕራፍ አለው:: አንድ ምዕራፍ በተሰጠው በአንዱ ቀን ውስጥ ለየቅዱሳኑ፣ ለየመላእክቱ የሚነበብ አለው:: ይህ መጽሐፍ ወደ ግዕዝ ከተተረጎመ በኋላ በአገር ውስጥ በየጊዜው የተነሱ የጻድቃን ታሪክ እየተጨመረበት በበለጠ ተቀነባብሮና ተጨምሮ ተዘጋጅቷል:: ስንክሳር ትውልዱ የቅዱሳንን በረከት እንዲሳተፍና ድንቅ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን እንዲያውቅ ከግዕዝ ወደ አማርኛ መተርጎሙ የሚያስደስት በጎ ጅምር ነው:: ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍትን በዚህ መልክ ወደ አማርኛ ቢመለሱ የሃይማኖት ማዕኛ ይሆናሉ የሚል የአዘጋጁ በጎ ህሳብ ነው::

ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ የቤተክርስቲያን አባቶች ጳጳሳትና ካህናት ሊያስቡትና ሊሰሩት የሚገባቸውን የቤተክርስቲያን ደንብና ሥርዓት እንዲሁም የቅዱስ ቁርባንን፣ የጾምን፣ የበዓላትን አከባበር ሌሎችም ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከቱ ሕጎችና ደንቦችን ከምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ሊቃነ ጳጳሳት እየተዘጋጀ የሚወጣውን ሕግ በሲኖዶስ ያገኘውን ሁሉ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በትክክል ለማስፈፀም እንዲቻል እያባዛ ለካህናቱ በነፍስ ወከፍ እንዲዳረስ አድርጓል:: እራሱ በደረሷቸው ድርሰቶች ውስጥ አትኩሮ በመመልከት የሚቃ



www.ethiopianorthodox.org

ወማቸው አምልኮ ጣአትን ነው::[3] ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የደረሳ ቸው መጻሐፍትም የሚከተሉት ናቸው:-

- ጦማረ ትስብዕት፣
- መጽሐፈ ብርሃን፣
- መጽሐፈ ምዕላድ፣
- መጽሐፈ ክህደተ ሰይጣን፣
- መጽሐፈ ባሕርይ፣
- መጽሐፈ ተአቅቦ፣
- መልክአ ማርያም፣
- መንገደ ሰማይ፣
- መልክአ ጉባኤ፣
- እግዚአብሔር ነግሠ ናቸው::

በዚህ ዘመን ሥነ ጽሑፍ የተስፋፋበት ምክንያት ከዚህ በታች በተገለፁት ነገሮች አይዘልም:: ይህም:-

- ዘመኑ ሰላምና መረጋጋት የሰፈነበት ዘመን ስለነበር፣
- ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ ለኦርቶዶክሳዊት እምነቱ ካለው ቅናት የተነሳ፣
- ስልጥነው የነበሩትን ባዕድ አምልኮት በሥነ ጽሑፍ ትምህ ርት ለመቋቋም፣
- በዘመኑ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የአባቶች ድርሰት አስፈላጊ መሆኑን ስለታመነበት እነዚህን በመሳ ሰሉት ምክንያቶች ለሥነ ጽሑፍ መስፋፋት አስተዋፅኦ አድርገዋል::

ከእነዚህ የዘርዓ ያዕቆብ ድርሰቶች መካከል «መንገደ ሰማይ» የተባለው መጽሐፍ በፓሪስ የታተመ ሲሆን፣[4] «መልክአ ጉባኤ» ደግሞ በሮም መታተሙን አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ ገልፀዋል::[5] የራሱም ታሪክ በፓሪስ ታት ሟል::[6] ከእነዚህ ከላይ ከተዘረዘሩት መጻሕፍት በተጨማሪ «መልክአ ጊዮርጊስን» የደረሰው እርሱ መሆኑ ይነገራል::[7] በዚህ ታላቅ ንጉሥ ዘመን ያልተጻፈ መጽሐፍ፣ ያልተተረ ጐመ የአባቶች ድርሰት የለም:: እንዲያው በአጠቃላይ በዚህ በመካከለኛው ዘመን ታሪክ ወንጌል በኢትዮጵያ የበራበት ዘመን ነው ማለት ይቻላል:: የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ እረፍታቸው ጳጉሜ 3 ቀን ሲሆን አፅማቸው ያረፈው በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም መሆኑን ተመልክተናል::

---

[3] ትንሣኤ ቁጥር 28 ገጽ 21-22፣
[4] መርሐ ልቡና ገጽ 85፣
[5] ዝኒ ከማሁ ገጽ 86፣
[6] ዝኒ ዘማሁ ገጽ 91፣
[7] አማርኛ የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁጥር 10 ገጽ 74፣





# ክፍል ስምንት

## በመካከለኛው ዘመን
## [912-15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን]

## የተነሱ ቅዱሳን አባቶች

ቅዱሳንን ማክበር ቅድስናቸውንም መቀበል ለቤተክ ርስቲያን ጥንታዊ ሥርዓት ነው:: የቤተክርስቲያን አባቶች ቅዱሳን የሆኑ ክርስቶስ የመረጣቸው ቃሉን የስተላልፉ ዘንድ ብቻ ሳይሆን፣ የቤተክርስቲያን ጠበቆች ይሆኑ አንድ ጭምር ነው:: ስለዚህ ቅድስናቸውን አርጋግጠን አባትነታቸ ውን ተመልክተን ቃላቸውን እንደንሰማ፣ እርምጃቸውን /አካ ሔዳቸውን/ እንድንከተል ነው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልዕክቱ 13፥7 ላይ «የእግዚአብሔርን ቃል የነገሯችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ የኑሮአቸውን ፍሬ የተመለከታችሁ በእ ምነት ምስሉአቸው» የሚለን ይህኑን ነው::

### መሟላት ያለባቸው መመዘኛዎች

1. ለቅዱስነት ሥያሜ የሚቀርበው ሰው በሕይወት የሌለ መሆን አለበት፣
2. በሕይወት ዘመኑ ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል፣ በሙያው በመምራት፣ በማስተዳደር የክርስትናን ውለታ የከፈለ፣
3. ለቤተክርስቲያን የልማት ተቋማትን የመሠረት፣ ረዳት የሌላቸውን የሙታን ልጆች ትምህርት ቤት፣ ጧሪ የሌላቸውን አረጋውያን መረጃ ተቋም ያደራጀ፣ አብያተ ክርስቲያናትን ያነፀ፣
4. ስለአውነተኛ ኦርቶዶክሳዊት እምነት እራሱን መስ ዋዕት አድርጐ ያቀረበ፣



www.ethiopianorthodox.org

5 የኦርቶዶክሳዊት እምነቱን ከመናፍቃን ትምህርት የተከላከለ የጠበቀ መሠረታዊውን እምነት «በሩቅ ላሉ በጽሑፍ በቅርብ ላሉ በአፍ» የተናገረ ያስተማረ፤

6 በምግባሩ በትሩፋት፤ በጾም በጸሎቱ ስለ ሰው ልጆች ይህንነት፤ ስለ ሀገር ሰላም፤ በገዳም በዋሻ፣ በበረሀ ድምፀ አራዊትን ግርማ ሌሊትን ርሀብና ጥምን ታግሶ፤ ጤዛ ልሶ ድንጋይ ተንተርሶ ሲጸልይ የኖረ፤

7 በጾም በጸሎቱ ድውይ ሲፈውስ ኃይለ አጋንንትን ከሰዎች ቁራኝነት ሲያላቅቅ፤ በልብሱ[1] በመስቀሉ ገቢረ ተአምራት ወመንክራት ሲያደርግ የኖረ፤

እነዚህን የመሳሰሉትን እንደፈፀመ ለሚረጋገጥለት ሰው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ሲኖዶስ አማካኝነት «ቅዱስ» ተብሎ እንዲጠራ ታፀድቅለታለች::[2] እነዚህ ቅዱሳን አለማቀፍ የሆኑ፤ በወገን በሀገር የማይወሠኑ ሲሆን በቤተሰብ የሚኖረው ሁሉ ወደ ቅድስና ሕይወት የሚመራ ሆኗል ከላይ በዘረዘርናቸው መንገዶች የኖሩ ኖረውም ያለፉ ቤተ ክርስቲያን የቅድስና መአርግ ሰጥታቸዋለች::

## ቤተ ክርስቲያን ለቅዱሳን የምትሰጠው ከበሬታ

1 ስሙ ከቅዱሳን ስም ተርታ ይመዘገባል ሥንክሳር ይጻፍለታል፤

2 አምላክ እገሌ ተብሎ በጸሎት ጊዜ ስሙ ይነሳል እንዲህ በመባል «ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሎ ምስሌነ»፤[3]

[1] «እግዚአብሔር በቅዱስ ጳውሎስ እጅ የሚያስደንቅ ሥራ ያደርግ ነበር:: ስለዚህም ከአካሉ ጨርቅ ወይም ልብስ ወደ ድውዮች ይወስድ ነበር:: ደዌአቸውም ይለቃቸው ነበር ክፉዎች መናፍስትም ይወጡ ነበር» ዮሐ ሥራ 19፥11-12 ይላል ቅዱስ መጽሐፍ፤

[2] ፍንጭ ፍተሻ ገጽ 27፤

[3] በሕዝበ ክርስቲያን ላይ ይደር ይባላል እንጂ /አዕርፍ ነፍስ/ ወይም ነፍሱን ይማር ተብሎ አይጸለይም፤





3 ለመታሰቢያው የዓመት ክብር በዓል ቀን ይወሰንለታል በስሙ ቤተክርስቲያን ይታነፅለታል ፅላት ይቀረጽለታል፤ ገድል ይጻፍለታል፤

4 ለማንነቱ መገለጫ ሥዕል እንደሌሎች ቅዱሳን ሁሉ በራሱ ዙሪያ ብርሃን የከበበው ሆኖ ይሳልለታል::

5 አፅሙ በክበረ ሳጥን ታሽጐ በክብር ይቀመጣል፤ ይህ ብቻ ሳይሆን ከቅዱሱ አካል ጋር ንክኪ ያላቸው ነገሮች እንደልብስ፣ መቋሚያ፣ የእጅ መስቀል... የተለየ የቅድስና ክብር ይሠጣቸዋል::[4]

ይህን ሁሉ በቅዱስ ሲኖዶስ አማካኝነት ውሳኔ አግኝቶ የሚከናወን ነው:: ከዚህ በኋላ ነው ይሁንታን የሚያገኘው:: በእርግጥ ባህሉ ሰፊና የበለፀገ ነው ይላሉ ይህን የቅዱስ ሲኖዶስ ኃላፊነትና ሥልጣን የገለፁ ሊቃውንት[5] የአንዲት ነፃ ቤተክርስቲያን አንዱ መገለጫ /የሉአላዊነተ ምልክት/ እነዚህንና ተዛማጅነት ያላውቸውን ውሳኔ መወሠን መቻል ነው::

ከዚህ በተጨማሪ አነዚህ ቅዱሳን ለዚህ ማዕርግ የበቃቸውን ሦስት ነገሮችን ገንዘብ አድርገው ሲሆን እነዚህም:- ፈቃደኝነትን፤ ተአማኒነትን፤ ታዛዥነትን በመያዛቸው ነው:: «ቀድመው የኖሩ አባቶቻችን የሚሆኑ ቅዱሳንን በሃይማኖታቸውና በሥራቸው ልንመሥላቸውና ልንከተላቸው ይገባናል:: እነሱን መከተላችን መምሰላችን ለእነሱ የተሰጣቸው ጸጋና ክብር አይተን መርምረን ነው ስትል ቤተ ክርስቲያን ወስናለች::[6]

ከላይ ለመግለፅ የሞከርነው የቅድስና ክብር እንዴት አንደሆነ ለሠጠነው ርዕስ መግቢያ ይሆናል በማለት የሠፈረ ነው:: በዚህ መሠረት በስጠነው ርዕስ ላይ ቅድስት አገር ኢትዮጵያ ብዙ ቅዱሳን የተስተናገዱባትና ያረፉባትም ናት

[4] ፍንጭ ፍተሻ ገጽ 28፤ ትንሣኤ ቁጥር 139

[5] ዝኒ ከማሁ::

[6] አራተኛ ክፍል የቤተክርስቲያን ጸሎት::



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ወርቃማ ዘመን /ከ912-1500 ዓ.ም የተነሡ አባቶቻችን ስማቸውና ክብረ በዓላቸውን እንመለከታለን:: የክብረ በዓላ ቸው ቀን ሥንክሳር ያልተሠራላቸው ደግሞ እንዲሁ የተነ ሱበትን ዘመን ብቻ ለማስቀመጥ ተሞክሯል::

| የቅዱሳኑ ስም | የክብረ በዓላቸው ቀን |
|---|---|
| አባ ኢየሱስ ሞዓ | ህዳር 26 |
| አቡነ ተክለሃይማኖት | ታህሳስ 24፣ ግንቦት 12፣ ነሐሴ 24 |
| አባ ሳሙኤል ዘወገግ | ጥቅምት 29 |
| አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ | ታህሳስ 12 መስከረም 6 |
| አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ | ጥቅምት 5፣ መጋቢት 5፣ ሐምሌ 5 |
| አቡነ በትረ ማርያም | ጥር 27 |
| አባ ኤዎስጣጤዎስ ከፋሌ ባሕር | መስከረም 18 |
| አባ ተክለ አልፋ ዘዲማ | ታህሳስ 8 |
| አቡነ ሐራ ድንግል | ጥር 11 |
| አባ ቀውስጠስ | ግንባት 1፣ ጥር 21 |
| አባ ጽጌ ድንግል | ጥቅምት 27 |
| አባ መለከ ፄዴቅ | ህዳር 4 |
| አቡነ ሀብተ ማርያም | ህዳር 26 |
| አቡነ ፊሊጶስ ዘ.ሊባኖስ | ሐምሌ 28 |
| አባ በግዑ | ታህሳስ 27 |
| አቡነ ዳንኤል ዘወቄን | ታህሳስ 7 |
| አቡነ ድምያኖስ | ሰኔ 18 |
| አቡነ ፊቅጦር | ሚያዝያ 27 |
| አቡነ ገብረ መስቀል ዘ.ገታማሳ | የካቲት 6 |
| አቡነ ገብረ ናዝራዊ | ጥር 29 |
| አቡነ ሀፃን ሙአ | ጥቅምት 25 |
| አቡነ ኢያሱ | ህዳር 7 |
| አቡነ ተከስተ ብርሃን | መጋቢት 10 |
| አቡነ ዮስጢኖስ | ነሐሴ 18 |
| አቡነ ዘካርያስ ዘገሊላ | ጥቅምት 13 |
| አቡነ ዘርዓ ብሩክ | ሚያዝያ 24 |
| አቡነ ዘካርያስ ዘዐርበር | ታህሳስ 9 |
| አቡነ ዘኢየሱስ | ሐምሌ 16 |
| አቡነ ዮሐንስ ዘክብራን | |
| አቡነ መድኃኒነ እግዚእ | ህዳር 3 |
| አቡነ ሠይፈ ሚካኤል | |
| አቡነ መርሐ ክርስቶስ | ጥር 24 |





| | |
|---|---|
| አቡነ መልከጼዲቅ ዘዳግና | ግንቦት 4 |
| አቡነ አብሳዲ | መስከረም 5 |
| አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ | ሐምሌ 7 |
| አቡነ አቢየ እግዚእ | ግንቦት 19 |
| አባ ፊሊጶስ ዘደብረ ቢዘን | ነሐሰ 5 |
| ፃድቁ አቡነ ዮሴፍ ዘላስታ | ግንቦት 19 |
| አቡነ ዜና ማርቆስ | ታህሳስ 3 |
| አቡነ በፀሎተ ሚካኤል | ሐምሌ 21 |
| አባ ሊባኖስ | ጥር 3 |
| አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስ | ሚያዝያ 9 |
| አቡ ያፌቅረነ እግዚእ | ጥር 19 |
| አባ ዳንኤል | ህዳር 16 |
| አቡነ ዮሐኒ ዘደብረ አሳ | ህዳር 5 |
| አቡነ መብአ ጽዮን | ጥቅምት 27 |
| አቡነ ኂሩተ አምላክ ዘዳጋ እስጢፋኖስ | የካቲት 14 |
| አቡነ በርተሎሚዎስ | ጥቅምት 4 |
| አቡነ ያዕቆብ ግብፃዊ | መስከረም 18 |
| አቡነ ተክለ ሐዋርያት | ህዳር 27 |
| አቡነ መልከፄዴቅ ዘመርሐቤቴ | ግንቦት 4 |
| አቡነ እነሆረት ዘደብረ ለሞ | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ብሩክ አምላክ | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ኤልያስ | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ አድንድርየስ ዘስራኢ | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ፍሬ ሚካኤል | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ገብረ ማርያም | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ማትያስ ሻሞ | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ መዝሙረ ድንግል | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ተክለ ጽዮን | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ተወልደ መድህን | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ዮሐንስ ዘቢዘን | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ዮናስ | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ዮሐንስ ዘይፋት | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ዮስጦስ | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ዘርዓ አብርሃም | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ገ/ክርስቶስ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ገብረ መራዊ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ገብረ ኢየሱስ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ግርማነ እግዚእ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ሕንፃ ሃይማኖት | በ14ኛው ክ.ዘ |



www.ethiopianorthodox.org

| | |
|---|---|
| አቡነ መርሐ ኢየሱስ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ መርቆሬዎስ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ መዝርአተ ክርስቶስ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ኖላዊነ ሔር | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ስምረ ክርስቶስ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ሳሙኤል ዘሃሌሉያ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ አኖሬዎስ ዘሞረት | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ሳሙኤል ዘቆየፃ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ኢዮስያስ ዘወጅ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ሲኖዳ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ አኖሬዎስ ዘወረብ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ታዴዎስ ዘባርተበ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ማትያስ ዘፌጠጋር | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ታዴዎስ ዘፅላልሽ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ተክለሃዋርያት | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ሳሙኤል ዘቆየፃ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ተሳዌ ክርስቶስ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ቀወስጦስ ዘመህግል | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቱነ ቶማስ ዘቆሬሳ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ዮሴፍ ዘአናርያ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ያሳይ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ዮሐንስ ዘጉርናቄ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ይርድአነ ክርስቶስ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ዳንኤል ዘፀአዳ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ዮሐንስ ዘበንከል | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ገ/ክርስቶስ ዘቢታንያ | በ19ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ዮሐንስ ከማዘአግድ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ዘካርያስ ዘጊፋ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ዘዮሐንስ | በ14ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ ሰርፀ ጴጥሮስ | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አቡነ በናድልዮስ | በ15ኛው ክ.ዘ |
| አፄ ቴዎድሮስ ወልደ ዳዊት | ሰኔ 29 ቀን |
| ቅድስት ሠብለ ወንጌል | ህዳር 25 |
| ቅድስት መስቀል ክብራ | ሐምሌ 28 |
| ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ | ግንቦት 12 |

ከእነዚህ ቅዱሳን መካከል አንዳንዶች ምናኔ ከሐዋርያነት፣ ከስማዕትነት እንዲሁም ከማኅበራዊ አገልግሎት ጋር በማጣመር፣ ሌሎች ደግሞ በገዳማዊ ኑሮ ብቻ ራሳቸውን ከዓለም ፈፅሞ በማግለል በፈፀሙት ገድልና ትሩፋት የቃል





ኪዳን ቅዱሳን ለመሆን የበቁ ቅዱሳን ናቸው:: በመሆኑም አብዛኛዎች በስማቸው ቤተ ክርስቲያን የታነፀላቸውና ገድል የተጻፈላቸው ሲሆን፤ የቀሩት ደግሞ ስማቸውና ገድላቸው በስንክሳር ብቻ የሚዘከሩ ቅዱሳን ናቸው:: በዚህ ወርቃማ ዘመን የተነሱ ቅዱሳንን በዚህ መልክ ከተመለከትን አሁን ደግሞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቅድስና ማዕርግ ከስጠቻቸው እና በዚህ ወርቃማ ዘመን ከነገሡ ነገሥታት 4ቱ የሚከተሉት ናቸው::

| የነገሥታቱ ስም | የነገሡበት ዘመን | የክብረ በዓላቸው ቀን |
|---|---|---|
| ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ | ከ10-77 1117ዓ.ም. ለ40 ዓመታት | ጥቅምት 19 እረፍቱ፣ መስከረም 13 ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ ሰኔ 20 የጨረሰበት |
| ቅዱስ ሐርቤይ /ገብረ ማርያም/ | ከ1117-1157 ዓ.ም. ለ40 ዓመታት | የካቲት 16 እረፍቱ |
| ቅዱስ ላሊበላ | ከ1157 1197 ዓ.ም. ለ40 ዓመታት | ታህሳስ 29 ልደቱ፤ ሰኔ 12 እረፍቱ፤ ቃል ኪዳን የተቀበለበት በየዓመቱ የደብረ ዘይት ዕለት ይከበራል:: |
| ቅዳስ ነአኩቶ ለአብ | ከ1197 1237 ዓ.ም. ለ40 ዓመታት | ህዳር 21 ልደቱ ህዳር 2 የተሠወረበት ቀን |



www.ethiopianorthodox.org

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በታተመው «የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና ዛሬ» በተሰኘው መጽሐፍ ላይ በኢትዮጵያ የሚከበሩ ቅዱሳን ስም ዝርዝር ተገልጿል ገለፃው የተነሡበትን /የነበሩበትን/ ዘመን ብቻ አስቀምጧል። የዚህ መጻሐፍ አዘጋጅ ከላይ ከተጠቀሰው መጽሐፍ ያገኛቸውን እና በመካከለኛው ዘመን የቆነሱትን ቅዱሳን ስማቸውን ከሌላ በመሰብሰብ የተነሡበትን ዓ.ም ገልጸ ከማስፈር የክብረ በዓላቸውን ቀን የተወሰኑትን ለማስቀመጥ ተሞክሯል። አንባብያን የሁሉም ክብረ በዓል ለማግኘት ብዙ ጥሬአለሁ ሆኖም የተወሰኑትን ለማግኘት ቢቻለም የተቀሩትን የነበሩበትን ዘመን ብቻ አስቀምጪዋለሁ።

**ማሳሰቢያ፤** ወደፊት የእነዚህንና በዚሁ መጽሐፍ በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ላይ የተመለከትናቸውን አባቶች ሐዋርያዊ ተልዕኮአቸውን፤ የመሠረቷቸውን ገዳማት፤ ያደረጉትን አስተዋጽኦ፤ በሌሎች የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተመራማሪዎች ሊቃውንት ይጻፋል ብዬ ተስፋ አድርጋለሁ።





# ምዕራፍ ስድስት

## ስድስተኛው ወርቃማ ዘመን
[ከ1624 - 1698 ዓ.ም.]

በዚህ ወርቃማ የታሪክ ዘመን የምናተኩርባቸው ነገሮች ሁለት ሲሆኑ፤ ይህም የዐፄ ፋሲልና የሀፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ዘመን ነው። ዐፄ ፋሲል በሚሲዮናውያን ላይ ጠንካራ እርምጃ ወስደዋል። ይህም ከኢትዮጵያ እንዲወጡ አድርጓቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ የጎንደርን ከተማ በመቆርቆርና አዲሷን ሳይሆን የጥንቷን የአክሱም ጽዮንን ቤተ ክርስቲያን አንፀዋል። በርከት ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን በጎንደር ከተማ ላይ ተክለዋል፣ ኢያሱ አድያም ሰገድ በዘመኑ ለሥነ ጽሑፍ ትልቅ ትኩረት በመስጠት በርካታ መጻሕፍትን እያጻፈ ለእየአብያተ ክርስቲያናቱ በነፍስ ወከፍ አድሏል፤ ይህም ዘመን «አራተኛው የሥነ ጽሑፍ ዘመን» በመባል ይታወቃል። እነዚህና ሌሎችን በዚህ ወርቃማ ዘመን የምንመለከታቸው ይሆናሉ።

### የዐፄ ፋሲል ዘመን
[1624-1659 ዓ.ም]

ዐፄ ፋሲል የጥንቶቹ ነገሥታት ሥርዓት ንግሥናን በሚፈፅሙበት በአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ዘውድ ደፍተው ነገሡ። በክብረ ነገሥቱ ላይ እንደተገለፀው ዐፄ ፋሲል እግዚአብሔር በአባቶቻቸው ዙፋን ላይ ሲያበቃቸው በመጀመሪያ «እግዚአብሔር ስሙ የሚጠራበትን ክብሩ የሚነገርበትን ቤት ልሥራ፤ እርሱ ደግሞ የእኔን ቤት ይሥራ» በማለት ከጐንደር ቤተ መንግስት በፊት የአክሱም ጽዮንን ቤተ ክርስቲያን ሠሩ።[1] የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ከግራኝ መሐመድ ወረራ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰራችው በዚህ ዘመን ነው። ዐፄ ፋሲል በ1627 ዓ.ም የጎንደርን ከተማ ቆረቆሩ።

[1] የቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ገጽ 64።



www.ethiopianorthodox.org

በጣም አስደናቂ የሆነውን ባለ ሦስት ድርብ ፎቅ በስማቸው የሚጠራውን ቤተ መንግስት አነፁ::

አብያተ መንግሥቱ በከተማዋ መሐል በሚገኘው ከፍተኛ ስፍራ ላይ የዐፄ ፋሲል ግቢ ተብሎ በሚታወቀው ሰፊ ቅጥር ውስጥ ይገኛሉ:: የግቢው ስፋት 70ሺ ካሬ ሜትር ይሆናል:: ከ17ኛው-18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ነገሥታት መካከል የስድስቱን አብያተ መንግሥታትና ሌሎች በርካታ የህንፃ ፍርስራሾችን ይዞ ይገኛል:: እነዚህም ነገሥታት:-

| የነገሥታቱ ስም | የነገሡበት ዘመን |
|---|---|
| ዐፄ ፋሲል | ከ1624-1659 ዓ.ም |
| ዐፄ አዕላፍ ሰገድ ዮሐንስ | ከ1660-1674 ዓ.ም |
| ዐፄ አድያም ሰገድ ኢያሱ | ከ1674-1698 ዓ.ም |
| ዐፄ ዳዊት ሳልሳዊ | ከ1708-1713 ዓ.ም |
| ዐፄ በካፋ | ከ1713-1723 ዓ.ም |
| ዐፄ ብርሃን ሰገድ | ከ1723-1747 ዓ.ም ናቸው:: |

የጎንደር ከተማ በ1626 ዓ.ም አንስቶ እስከ 1845 ዓ.ም ድረስ ማለት አፄ ቴዎድሮስ ሁለተኛ እስከነገሡበት የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ነበረች::[2] ይህም ከሁለት መቶ ዓመታት በላይ የሀገሪቱ መዲናና በተከታታይ ለአሥራ አራት ነገሥታት መቀመጫ ነበረች:: በተራራ መቀነት ሥር ከ5560 ከባሕር ወለል በላይ በአማካይ 2200 ሜትር ከፍታ ላይ የምትገኘው ጐንደር የአየር ንብረቷ ወይናደጋ እንዲሁም ዓመታዊ የዝናብ መጠኗ 1172 ሚ.ሜ ሲሆን ከአዲስ አበባ 748 ኪ.ሜ፣ ከባሕር ዳር 182 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች:: በጎንደር 44 አብያተ ክርስ ቲያናት በተለያዩ ጊዜያቶችና ምክንያቶች ተተክለው ነበር:: ተካዮቹ 4 ዓይነት ናቸው::

1. ነገሥታት፤
2. መኳንንት፤
3. ባላባት፤
4. አገሬው፤

[2] በ1678 ዓ.ም የጎንደርን ከተማ የጐበኘ የአርመን ጳጳስ በዚያን ዘመን 60 ሺህ ሕዝብ ነበረባት ካለ በኋላ፣ ከቱርክ ከተሞች /በተለይ ከኢስታንቡል/ እጥፍ እንደምትሆን ተናግሯል ሲል መምህር በለጠ መርዕድ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ባዘጋጁት «የቀዳማይ ኢያሱ አንደኛ ታሪክ» ገጽ 61 ላይ ገልጸዋል::





| ታቦቱ | ተካይ | ሁኔታ |
|---|---|---|
| ፊት አቦ | ዐፄ ፋሲል | ጣልያኖች ምሽግ አድርገውት ስለነበር ታቦቱ ከደብረ ምጥማቅ ተመድቧል |
| ፊት ሚካኤል | ዐፄ ፋሲል | የ6ቱ አብያተ ክርስቲያናት የእቃ ቤት ስለነበረች ይህን ስም ይዛለች |
| ግምጃ ቤት ማርያም | ዐፄ ፋሲል | በትልቁ ቤተመንግሥት /ፋሲል ግንብ/ ማለፊያ ወይም መውጫ ስለነበር እልፍኝ ተብሏል:: እልፍኝ ተያያዥ ቤት ማለት ነው /መውጫና መግቢያ/ |
| እልፍኝ ጊዮርጊስ | ዐፄ ፋሲል | መጀመሪያ ዐፄ ፋሲል ሠሩት የሚባል ነው የ4ቱ ጉባኤያት መምህራን ከዚያን ጊዜ-አሁን አሉበት |
| ጎንደር መድኃኔዓለም | ዐፄ ፋሲል | ከግብፅ የሚመጡት ጳጳሳት ከጐንደር ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የሚቀመጡበት ቦታ ነው |
| አቡን ቤት ገብርኤል | ዐፄ ፋሲል | በቤተ መንግሥት በአንደኛው ጽንቁላል ግንብ ውስጥ የነበረ የንጉሥ ስዕል ቤት ነበር በኋላ ቀርቷል |
| ኩራተ ርዕሱ | ዐፄ ፋሲል | ቀጥሩ ከ44ቱ አብያተ ክርስቲያናት ቢሆንም ቦታው ሩቅ ነው:: |
| ጠዳ እግዚአብሔር አብ | ዐፄ ዮሐንስ /ጻድቁ/ | |
| አባ እንጦንስ | ዐፄ ዮሐንስ /ጻድቁ/ | |
| ደብረ ብርሃን ሥላሴ | ዐፄ አድያም ሰገድ ኢያሱ | ደብረ ብርሃንን ከመሥራታቸው በፊት የሚጸልዩበት ደብር ነበር:: |
| አደባባይ ተ/ሃይማኖት | ዐፄ አድያም ሰገድ ኢያሱ | በ1880 ዓ.ም በደርቡሽ ወረራ ስለተመዘበረ ታቦቱ በአጣጣሚ ሚካኤል ተደብሷል |
| ሠለስቱ ምዕት | ዐፄ ቴዎፍሎስ | |
| ጎንደር በዐታ | ዐፄ ዮስጦስ መናኜ መንግሥት /ተክለሃይማኖት/ | |
| አጣጣሚ ሚካኤል | ዐፄ ዳዊት | |
| አቡነ ኤዎስጣጤዎስ | ዐፄ ዳዊት | በ1880 ዓ.ም በደርቡሽ ወረራ ስለተመዘበረ ታቦቱ በአጣጣሚ ሚካኤል ተዳብሏል |
| ቅዱስ ሩፋኤል | ዐፄ በካፋ | |
| ደፈጫ ኪዳነ ምሕረት | ዐፄ በካፋ | |
| ደብረ ፀሐይ ቁስቋም | እቴጌ ምንትዋብ | |



www.ethiopianorthodox.org

| ታቦቱ | ተካይ | ሁኔታ |
|---|---|---|
| መጥምቁ ዮሐንስ | ራስ ወልደ ልዑል | |
| በአታ ለማርያም | ዐፄ ተክለ ሃይማኖት | |
| ቅዱስ ቂርቆስ | ዐፄ ተክለ ሃይማኖት | |
| ጴጥሮስ ወጳውሎስ | ዐፄ ተክለ ሃይማኖት | |
| ወልደ ነጎድጓድ ዮሐንስ | ዐፄ ተክለ ሃይማኖት | |
| አባ ጀሌ ተክለ ሃይማኖት | ራስ ወንድ ወሰን | |
| ፈንጠር ልደታ | ዐፄ ተክለ ሃይማኖት | |
| ደብረ ምጥማቅ ማርያም | ዐፄ ተክለ ሃይማኖት | |
| አባ አቢየ እግዚእ | ራስ ገብሬ | |
| ቅዱስ ፋሲለደስ | ዐፄ ሰሎሞን | የተተከለው ዐፄ ፋሲል ባሠሩት ግንብ ውስጥ ነበር በጠላት ወረራ ዘመን ኢጣልያኖች ሰፈር ካደረጉት ጀምሮ ታቦቱ ተነስቷል |
| ቀሐ ኢየሱስ | የወይኔ ሰይሌ | |
| አርባዕቱ እንስሳ | አገሬው | ጠፍ ሆኖ ከአልፍኝ ጊዮርጊስ ተዳብሏል |
| ጐንደሮች ጊዮርጊስ | አገሬው | |
| ጐንደሮች ማርያም | አገሬው | |
| አባ ሳሙኤል | ዐፄ ሰይፈ አርዕድ | በጠላት ዘመን ጠፍ ሆኖ ታቦቱ ከአዘዞ ተ/ሃይማኖት ተዳብሎ ነበር አሁን ራሱን ችሎ ተሠርቷል |
| ብላ እጅግ ቅ/ሚካኤል | ወይኔ ሰይኔ /ዐፄ/ | |
| አበራ ጊዮርጊስ | ዐፄ ሠርፀ ድንግል | |
| አደራ ሚካኤል | አገሬው | ጠፍ ሆኖ ከአዘዞ ተ/ሃይማኖት ተዳብሏል |
| ጓራ ዮሐንስ | አገሬው | ጠፍ ሆኖ ከአዘዞ ተ/ሃይማኖት ተዳብሏል |
| ወራንገብ ጊዮርጊስ | ወይኔ ሰይኔ | |
| አሮጌ ልደታ | አገሬው | ጠፍ ሆኖ ከአዘዞ ተ/ሃይማኖት ተዳብሏል |
| ድባ ሐዋርያት | ወይዛዝርት | |
| ዋላጅ አማኑኤል | ወይዛዝርት | |
| ሎዛ ማርያም | አልታወቀም | |
| ምንዝሮ ተ/ሃይማኖት | አልታወቀም | |
| አዘዞ ተ/ሃይማኖት | ዐፄ ሱስንዮስ | |

ምንጭ - አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁ.5 1981 ዓ.ም ገፅ 157-159::
- መርስኤ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ጐንደርን የመጐብኘታቸው ታሪክ 1939 ገፅ 104-106::





ከጎንደር ውጭ የተሠሩት ዋናው ሊጠቀስ የሚገባው የአክሱም ጽዮን ቤተክርስቲያን ነው:: ይህን ቤተ ክርስቲያን በፊት ጉዲት አቃጠለችው፤ ሀፄ ድልነአድ አሰርቶት የነበረ ውን ግራኝ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አቃጥሎት ሳይሰራ ቆይቶ ነበር:: ከላይ እንደ ገለጥኩት ዐፄ ፋሲል በአራት መአ ዘን ቅርፅ ሦስት መቅደስ አድርጐ አሠራው የቤተ ክርስተያኑ አሰራርና የተጠቀመበት የህንፃ መሣሪያ ከጎንደር ፋሲለደስ ግንብ ጋር ይመሳሰላል:: ይህ ቤተ ክርስቲያን በደህና ሁኔታ እስከ ዛሬ ድረስ ይገኛል::

ዐፄ ፋሲል በዘመነ መንግስታቸው ሃይማኖትን በተ መለከተ ጠንከር ያለ እርምጃ ወስደዋል:: ይህም በአባታቸው በሀፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግስት የኢትዮጵያን ሃይማኖት በሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለመቀየር ከፍተኛ ደም መፋ ሰስ ተካሒዶ ነበር:: ለጊዜው ቢሆን ንጉሥ ሱስንዮስን ቀስጠ ዋቸው ስለነበር በገዛ ሕዝባቸው ላይ በእነሱ ስብከት ተሰበው ፈጅተዋቸዋል:: በዚህ መሠረት ሱስንዮስ ካረፍ በኋላ ልጃ ቸው ፋሲል ሲነግሱ፤ በሚሲዮናውያኑ ላይ የወሰዱት እርምጃ ቢኖር በጠቅላላቸው ከኢትዮጵያ እንዲወጡ አድርገዋቸዋል:: ዐፄ ፋሲል በሃይማኖት አሳቦ የሚመጣ ማንኛውም ኃይል ካለ ንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ እንዳይገባ ምፅዋን ይጠብቁ ከነበሩት ከቱርክ ፓሻዎች [ቱርኮች ምፅዋን ይጠብቁ የነበሩትን ገዢዎቻቸውን ፓሻዎች ይሏቸዋል] ጋር ተዋዋሉ:: ይህን ርምጃ ለመውሰድ የተገደዱበት ምክንያት ስለ ሁለት ነገሮች ነው:: ይህም:-

1. በተዋህዶ ሃይማኖት የሚያምኑ የቤተ ክርስቲያን አባል እንደመሆና ቸው መጠን ሃይማኖታቸው ስለሚያስገድዳቸው ሲሆን፤
2. ከእርሳቸው በፊት ሕዝቡ በሚሲዮናውያን ስለተከፋፈለ ሕዝቡ እንዳ ይከፋፈል በነበራቸው ብሔራዊ ስሜት ነው::

ይህ ሁለተኛው ተግባራቸው በጣም አስመስግኗቸዋል:: የቤተ ክርስቲያን አባቶችም ሆኑ ታሪክ ጸሐፊዎች እንደ ሚናገሩት ኢትዮጵያ እነዚህን የመሳሰሉ መሪዎች በዘመኗ



www.ethiopianorthodox.org

ባይኖራት ኖሮ የደቡብ አፍሪካና የሮዴሽያ /ዚምባብዌ/ እጣ ይደርስባት ነበር።[3] ዐፄ ፋሲል የኢየሱሳውያንን መጻሕፍት ሰብስበው ካቃጠሉ በኋላ የኦርቶዶክስ መጻሕፍት እንዲስፋፉ አድርገዋል። ከዚህም ሌላ መጻሕፍት በጥሩ ብዕር እያጸፉ ለእየአብያተ ክርስቲያናቱ በነፃ እንዲታደሉ ትዕዛዝ ሰጥተዋል በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ ወደ ሀገራችን የመጡትን የሕግ መጻሕፍት አስጽፈው አሰራጭበዋል። በአባይ ጣና እንዲሁም በታላላቅ ወንዞች ምክንያት የመገናኛ ችግር ለደረሰበት ሰው ሁሉ ድልድይ እየሰሩ እንዲገናኙ ከማድረጋቸውም በላይ በር ከት ያሉ አብያተ ክርስቲያናትንም በግንብ እያሰሩ ከውስጥ ንዋየ ቅድሳት፣ ከመጻሕፍት ጋር ለተገልጋዩ ክርስቲያን ማቅ ረብ የዘወትር ተግባራቸው ነበር።

ዐፄ ፋሲል እስከ አሁን ከምናውቃቸው የኢትዮጵያ ነገሥታት ሁሉ ረጅም አመት ከነገሡት መካከል አንዱ ናቸው። የግዛታቸው ዘመን 36 ዓመት ይደርሳል። ከዚህ በኋላ ጥቅምት 10 ቀን 1660 ዓ.ም አርፈው አዘዞ ተቀበሩ። በኋላ አፅማቸው ፈልሶ የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት ባሰራው የመስታወት ሳጥን ተደርጎ ዳጋ እስጢፋኖስ ተቀም ጧል። [በዚሁ መፅሐፍ ገፅ 139 ተመልከት] ከሳጥኑ ትልቅነት ለመረዳት እንደሚቻለው ዐፄ ፋሲል ሰውነታቸው ግዙፍ የነበሩ ሰው ናቸው። ታሪካቸውም በፓሪስ ታትሟል።[4]

## ዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ
## [ከ1674 - 1698 ዓ.ም]

በዚህ ክፍለ ዘመን በሥልጣን ላይ የቆየው ኢያሱ አድያም ሰገድ ገና ከወላጆቹ ጋር ሳለ የቅዱሳት መጻሕፍ ትን ቃል በሚገባ ስላጠና እግዚአብሔርን ፈሪ ሰውን አክባሪ ነበር። ኢያሱ የመንግስት አስተዳደር ብቻ ሳይሆን መንፈ ሳዊነት ያልጐደለው ሰው ስለነበር በውጭ አገር ጸሐፊዎች ሳይቀር ተመስግኗል። በዘመነ መንግሥቱ የቅብዐትን እምነት

[3] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ ገጽ 56።

[4] መርሐ ልቡና ገጽ 92።





ፈፅሞ አስወግዶ የተዋህዶን ሃይማኖት ከፍ ለማድረግ የሚቻ ለው ቅዱሳት መጻሕት ሲበዙና ሊቃውንትም በአንድ ቦታ ላይ እየተገናኙ እርስ በርሳቸው ሲነጋገሩ መሆኑን ያምን ነበር። በዚህ መሠረት ለመጻሕፍት ከፍ ያለ ትኩረት አድር ጓል ይህ ዘመንም «አራተኛው የሥነ ጽሑፍ ዘመን» በመባል ይታወቃል።

ፍትሀ ስጋዊና መንፈሳዊ ተብሎ በሁለት የተከፈለ ውን ፍትሐ ነገሥት ከግዕዝ ወደ አማርኛ አስገልብጦ ሁሉም እንዲያነበው አድርጓል። ከዚህ ሌላ በዘመኑ የብሉይ የሐዲስ ሊቃውንት፤ የመጽሐፈ መነኮሳት፤ ትርጓሜና የዜማ፤ መጻሕ ፍትም በዕናዕል በክበሮ በመቋሚያ እየተቀነባበሩ በአገልግ ሎት ላይ እንዲውሉ ያደረገው ኢያሱ ነው። ሊቃውንት የመጻሕፍት ትርጓሜ የላይ ቤትና የታች ቤት ስያሜ የሰ ጡት በዚህ ዘመን መሆኑ ይነገራል። ይህም ሊሆን የቻለው አራት አይና፤[1] የተባሉ መምህር ኤስድሮስ የሊቅነት ምስክር መማር ብቻ ሳይሆን መመርመር ለመመርመርም ማንበብ ያስፈልጋል በማለት ሰውየው አይነ ስውር ሲሆኑ ሦስት መቶ መጻሕፍትን እዳነበቡ ይተርክላቸዋል። በዚህም የቀድሞውን ትርጓሜ መጻሕፍትን በማንበብ አድሰዋል። ስለዚህ እስከ ዛሬ ድረስ የመምህር ኤስድሮስ ትርጓሜ እየተባለ የጠመመው የቀናበት፣ የጐደለው የሞላበት የእርሳቸው ትርጓሜ ነው።

በዚህ መሠረት ይህን ያህል መጽሐፍ ለማንበብ በመ ንፈሳቸው የተገደዱት ቀደም ብለው ያወጧቸው ብዙ ደቀ መዛሙርት ነበሩ። እነርሱም በየአገሩ ተበትነው ሲያስተምሩ ሳለ፤ እርሳቸው መጻሕፍትን ለማንበብ ወደ ጣና ደሴት ገቡና ከላይ የገለጥናቸውን ብዙ መጻሕፍትን አንብበው ምስጢር በበለጠ አደላድለው ከተመለሱ በኋላ ደቀ መዛሙርቶቻቸው የቀረን ነገር አለና ኑ እንደገና እንመርምር፣ እንማር ብለው ቢጠሯቸው ብዙዎች የመምህራቸውን ቃል አክብረው ሲመጡ

[1] አራት አይና ማለት፤ የብሉይ፣ የሐዲስ፣ የሊቃውንትን እና መጽሐፈ መነኮሳትን አጠ ቃሎ ትርጉማቸውን የሚያ ውቅ ምሁር /ሊቅ/ ማለት ነው ይህም የ4 ጉባኤ መምህር ይባላል አራት አይና የተባለውም መጠሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠሩበት መምህር ኤስድሮስ ናቸው።



www.ethiopianorthodox.org

ጥቂቶች ግን «ንሕነሰ ኢተወለድነ እምዝሙት» [እኛስ አንተ አባታችን ሳትሰስን» አዲስ ትርጉም ሳታመጣ] የተወለድን ነን እንደገና ወደ ትምህርት ቤት አንገባም ሲሉ መለሱላቸው።

ስለዚህ ብዙዎች በአዲሱ እቅድ ሲያጠኑ ጥቂቶች ግን በዚያው ፀኑ ስለዚህም ሁለት አይነት ትርጓሜ ቤት ሊፈጥር ቻለ። ይኸውም ዋላይ ቤትና የታች ቤት የተባለው ነው። የላይ ቤት የተባለው ትርጓሜ መምህራቸው ቢጠሯቸው አንመጣም ብለው ትርጓሜያቸውንም አናሻሽልም እንደገናም አናጠናም ያሉት መምህራን ትርጉም ነው። ይኸውም አብዛኛው የጎጃም ትርጉም የተባለው ባለብዙ ሐተታ ነው። የታች ቤት ትርጉም የሚባለው ደግሞ እንደገና ከመምህራቸው ጋር በመወያየት ትርጉም ያሻሻሉ ምስጢር ያደላደሉ ሰዎች ትርጉም ነው። እርሱም የጎንደር ትርጉም የሚባለው ነው። ዛሬም ጉባኤው ሰፍቶ የሚገኘው እርሱው ነው።[2]

በእርግጥ የመጻሕፍት የአንድም ትርጓሜ ስልት በአገራችን መቼ እንደተጀመረ እስከ አሁን ግልጥ ሆኖ አይታወቅም። ሊቃውንት እንደሚሉት ከሆነ ግን መጻሕፍት አሪት ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ ሲተረጐሙ የርሱም ጥንታዊ የአንድም ትርጉም አብሮ እንደገባ ይታመናል። ከዚህም ሌላ ከሕገ ኦሪት ጋር ሊቃውንተ ኦሪት በንግሥተ ሳባ ጊዜ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር አብረው ወደ ኢትዮጵያ ስለመጡ እነሱ ሲተረጐሙት ሲያስተምሩት ኑረዋል የማለት ግምት ይሰጣል። በእርግጥም ኦሪት በጥንት ዘመን ተተርጉማ በአገራችን ቋንቋ ይሠራባት ነበር የሚለው ታሪክ እውነተኛ ሆኖ ተቀባይነትን ካገኘ፣ ሊቃውንተ ኦሪትም ወደ አገራችን መግባታቸው እርግጥ መሆኑን አምነን ከተቀበልን መጻሕፍትም

---

[2] ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት ገጽ 213-214።

ለላይ ቤትና ለታች ቤት የትርጓሜ ሥልት የተሠጠው ሥያሜ ይህ ብቻ አይደለም። ሌሎችም ምክንያቶች ይቀርባሉ። ይኸውም የጉንደሩ ግምጃ ቤት ማርያምና ባሕታ ማርያም አብያተ ክርስቲያናት አቀማመጥ ተመርኩዞ የመጣ ስያሜ ነው፤ ባህታ በዝቅተኛው ቦታ ስለምትገኝ በዚችው ቤተክርስቲያን ቅፅር የሚሠጠው የመጻሕፍት ትርጓሜ ይሁን አቋቋም ታች ቤት ሲባል፤ ግምጃ ቤት ቤተክርስቲያን ከባሕታ ከፍ ባለ ቦታ ስለምትገኝ በግምጃ ቤት የሚሠጠው የመጻሕፍት ትርጓሜና አቋቋም ላይ ቤት እንደተባለ ቀረ እየተባለ ይተረካል።





ሲተረጉሙ መኖራቸው ከቶ የሚያጠራጥረን ሊሆን አይችልም። ይኸውም ከሆነ አሪታውያን መጻሕፍት ቀደም ብለው ሲነበቡ በአንድም ትርጉም ስልት ሲተረጐሙ ኖረዋል በኋላም በዚያው መልክ ቀጥለዋል።

በክርስትናም ጊዜ ደግሞ እንደገና መጻሕፍተ ብሉያትና መጻሕፍተ ሐዲሳት ከዕርዕ ወደ ግዕዝ በቀጥታ በተተረጐሙ ጊዜ የአንድም ትርጓሜ ስልት አብሮ ወደ አገራችን እንደገባ አንድም የትርጓሜውንም መጻሕፍ እንደ አብነት አድርገው አብረው እንዳስገቡት ይታመናል።[3*] ይህ የሚያመለክተን በጎንደር ዘመነ መንግሥት መጻሕፍቱ መተርጐም የጀመሩበት ዘመን አይደለም በህፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ከላይ የተገለጠው የትርጓሜ ስልት ግዕዙ በአማርኛ አንድምታ የተተረጐመበት ዘመን ነው። ከዚያ በፊት ግዕዙ በግዕዝ እየተብራራ ሲተረጐም ኖሯል።

በዚህ በአራተኛው የሥነ ጽሑፍ ዘመን በትርጓሜ የተዘጋጁ መጻሕፍት፣ ለማህሌት የሚያገለግሉ ዚቆች እየተጻፈ ለየአድባራቱ የተዳረሱት በዐፄ ኢያሱ ጊዜ ነው። ኢያሱ ፊደል ቆጥረው ካላነበቡ ሊቅነት አለመገኘቱን ተረድቶ ፊደል አስቆጥረው ንባብ ለሚያስነብቡ መምህራን ከፍ ያለ አክብሮት ስለነበረው፣ የንባብ መጻሕፍት በጥሩ ብዕር እያጻፈ ለአንባብያን እንዲያቀርቡ ያስደርግ ነበር። ከዚህ ጋር ሊዘነጋ የማይገባው በዘመኑ ለነበሩ መምህራን ይህን መድበላቸው ነበር:-

1. ለፊደል ቆጣሪ እንጀራ ወጥ፣
2. ለዜማ ተማሪ እንጀራ ወጥ ከጠላ ጋር፣
3. ለቅኔ ተማሪ እንጀራ ወጥ ከጠጅ ጋር፣
4. ለመጻሐፍ ተማሪ ከእነዚህ የበለጠ ቤት ሰጥቶ፣

---

[3] ዝኒ ከማሁ ገጽ 213።

[*] ስለ ትርጓሜ አመጣጥ ዓይነት ባሕል... የተሟላ መረጃ ለማግኘት «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በ2000 ዓመት» በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ከገጽ 174-109 ውስጥ መጋቤ ብሉይ ስይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ያቀረቡትን ጽሑፍ መመልከት ይገባናል። እስከዛሬ የአንድምታ አመጣጥ ታሪክ ከሚተረከው የበለጠ ዳብሮ የተዘጋጀ ጥናት ስለሆነ ደስ ያሰኛል። በዚያውም የጥናቱን አቅራቢ ዕውቀት ለሚገባ ያሳያል።



www.ethiopianorthodox.org

ልብስ ቀለብ አውጥቶ በሚገባ ይንከባከባቸው ነበር::[4] ተራ ቁጥር 4 የሚያመለክተን ለሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎችና ለሙያው ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እንደ ነበር ነው::

አፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ግላዊ ሕይወቱ ሲበዛ ክር ስቲያናዊ ስለነበር፤ ከዚህ በተጨማሪ የዜማ ፍቅር ስላለው ካህናቱን /ባለሙያዎችን/ በሚገባ ይንከባከብ ነበር:: በተለይ ለአብነት መምህራን የተለየ ትኩረት ነበረው::

<table>
<tr><th colspan="2">በኢያሱ ጊዜ የተጻፉ መጻሕፍት ዝርዝር</th></tr>
<tr><td>ስንክሳር</td><td rowspan="7">ስንክሳርና ፍትሐ ነገሥት ምንም እንኳ በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን ከአረቢኛ ቢተረጐምም የበሰጠ አዳብሮ አሻ ሽሎ ያሠራው ኢያሱ ነው::</td></tr>
<tr><td>ፈውስ መንፈሳዊ</td></tr>
<tr><td>ጠቢበ ጠቢባን</td></tr>
<tr><td>ማኅበረ ማዕምራን</td></tr>
<tr><td>ዜና እስክንድር</td></tr>
<tr><td>ፍትሐ ነገሥት</td></tr>
<tr><td>መልክአ ሥላሴ</td></tr>
</table>

## በዘመኑ የነበሩ ታላላቅ መምህራን

በዚያን ዘመን ከነበሩት የጎንደር ሊቆች አንዱ ክፍለ ዮሐንስ የሚባል ነበር:: ይህ ሊቅ ቅኔ የሚያስተምርበት ሥፍራ ከደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ካለው ወይራ ውስጥ ነበር:: አንድ ቀን ፀዬ ኢያሱ ቤተ ክርስቲያን ተሳልሞ ሲመለስ መጻሕፍት ሲያስተምር ለማየት ባጠገቡ ሲያልፍ በቅኔ አሳቡ ልቡ ተመስጦ ሲያስተምር ለማ የት ባጠገቡ ሲያልፍ በቅኔ አሳብ ልቡ ተመስጦ ሳያየው ሳይነሳ ቢቀር በወርቅ ዘንግ ራሱን ነካ አደረገው ዘወር ብሎ አይቶ ተነስቶ እጅ ነስቶ እንዲህ ሲል ወዲያው ተቀኘ:-

በእስጢፋኖስ አእባን እመ የኀልቁ፤
ዘበጠኒ ኢያሱ በወርቁ፤

[4] ያሬድና ዜማው ገጽ 247::





እስጢፋኖስን አይሁድ በድንጊያ ደብድበው ስለገደ ሉት ደንጊያዎች በእስጢፋኖስ ላይ ቢያልቁ ኢያሱ በወርቁ መታኝ ማለት ነው:: ሌላ ታሪክ ደግሞ ለክፍለ ዮሐንስ እንደ ስጦታ እንዲቆጠር ወርቅ ወርውሮ ንጉሥ ኢያሱ ስለመታው ነው ይህን የተቀኘው ይላል::[5] ሊቁ ክፍለ ዮሐንስ ከጎንደር አድባራት ለይቶና መርጦ ኑሮውን በደብረ ብርሃን ሥላሴ ያደረገበት ምክንያት ነበረው:: ይህም:-

- ✣ ቦታው ከከተማ ውጭ በመሆኑ ስለጸጥታው፣
- ✣ መናኝ ባሕታዊ ነበርና ለጸሎት እንዲመቸው፣
- ✣ ስጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ክብር ያገኘበት ቦታ ስለሆነ፣
- ✣ በሞት በተለየ ጊዜ መካነ መቃብሩ እዚሁ መሆኑን በመንፈስ ቅዱስ ስላወቀው፣

በእነዚህ ምክንያቶች ቦታውን መርጦታል:: ይህ ሊቅ አምስት የጎንደር ነገሥታትን እንዳሳለፈ ይነገራል:: እነዚህም ዐፄ ኢያሱ /አድያም ሰገድ/፤ ዐፄ ዮስጦስ /ፀሐይ ሰገድ/፤ ዐፄ ዳዊት /አድባር ሰገድ/፤ ዐፄ በካፋ /መሲሀ ሰገድ/፤ እና ዐፄ ቴዎፍሎስ ናቸው:: እነዚህ ሁሉ ነገሥታት ሊቁ ክፍለ ዮሐንስን እንደ ዐይናቸው ብሌን ጠብቀውታል:: በጣታቸው እንዳለው ወርቅና እንቁ ይመለከቱታል::[6] ሌላው በዚህ ክፍለ ዘመን ከነበሩት ሊቅ አንዱ የንጉሡ ባለሟልና የጎጃም ተወላ ጅና የጣና ቂርቆስ መነኩሴ አባ ስብሐት ለአብ ይጠቀሳሉ:: እኚህ አባት «መልክዐ ሥላሴን» የደረሱ ናቸው በመልኩ ውስጥ ኢያሱን ያነሳል:

በርእሰ ኢያሱ አንብሩ አክሊለክሙ ሞገሰ፤
በስምክሙ አሐዱ እስመ ያመልክ ስሉሠ፤
ወበስምክሙ ሐነፀ መቅደሰ::

አባ ስብሐት ለአብ ነሐሴ 3 ቀን 1964 ዓ.ም አርፈው ንጉሡ አስከሬናቸው ጣና ቂርቆስ ተወስዶ እንዲያርፍ አድር ጓል::[7] የፀዬ ኢያሱ አድያም ሰገድን ታሪክ ደህና አድርጎ በጽሑፍ ላይ ያሰፈረው ስለ ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ያጠ

[5] የኢትዮጵያ ታሪክ ከልብነ ድንግል እስከ ቴዎድሮስ ገጽ 182::

[6] ትርጓሜ ቅኔ ፈለገ ሕይወት ገጽ 180-186::

[7] የሕይወት ታሪክ በኀሩይ ወ/ሥላሴ ገጽ 23::



www.ethiopianorthodox.org

ናው ኢጣልያዊው ምሁር ኮንቲሮስኒ ስለ ኢያሱ እንዲህ ብሏል:: «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትመራበትን እምነት በመከተል ስለ መንፈሳውያን መጻሕፍት የጠለቀ ስሜት የነበረው በጦር ሜዳ ጀግንነቱን ከፍ ያለ መሆኑ...» አጉልቶ ጽፏል::[8] ከዚህ በተጨማሪ በስጋዊ አመራር በመንፈሳዊ ተግባር ከፍ ያለ ችሎታ ስለነበረው በኢትዮጵያ የሚገኙትን የዝሆን ጥርስ፣ የጎሽ ቀንድ ጧርቅ እጣን... የመሳሰሉትን በመላክ እርሱ ጨርቃ ጨርቆችን ይቀበል ነበር:: ይህ ግንኙነቱ ለመንፈሳዊ ጽሑፎች በአገር ውስጥ ለመስፋፋታቸው ሳይረዳው አይቀርም::

## ደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን

ከጐንደር ከተማ በስተ ምሥራቅ በኩል የሚገኝ ቤተ ክርስቲያን ነው:: የተሰራው በዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ በ1674 - 1698 ዓ.ም ዘመነ መንግሥት ነው:: ትክክለኛው ግምት ቤተክርስቲያኑ የተመሰረተበት በ1886 ዓ.ም ነበር:: በዚሁ ዓመት መቃረቢያ ተሰርቶ ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ:: በበዓሉ ላይ አዲስ ተሹሞ የመጣው ግብፃዊ ጳጳስ አቡነ ማርቆስና በዘመኑ ለሁለተኛ ጊዜ የተሾሙት እጨጌ ፀጋ ክርስቶስ ተገኝተዋል:: ዐፄ ኢያሱ በፈረስ ላይ ተቀምጦ ታቦቱን አጅቧል:: ወደ መቃረቢያው ሲደርስ ከፈረሱ ወርዶ ታቦቱን ተሸክሞ ከመቃረቢያው አገባው:: በዚህን ጊዜ የተገጠመው የአማርኛ ግጥም:-

ወዴት ሄዶ ኖሯል ስሞነኛው ቄሱ፤
ታቦት ተሸከመ ዘውድ ትቶ ኢያሱ፤
የተሸሸገውን ያባቱን ቅስና፤
ገለጠው ኢያሱ ታቦት አነሳና፤
አየነው ኢያሱን ደብረ ብርሃን ቆሞ፤
ከኪሩቤል ጋር ሦስቱን ተሸክሞ፤
ሰውነቱን ትቶ መልአክ ሆነ ደሞ፤
ሥላሴን ቢሸከም ኢያሱ ገነነ፤
ከአራቱ ኪሩቤል አምስተኛ ሆነ:: ተብሎ ተገጥሞለታል::[9]

---

[8] ትንሣኤ ቁጥር 28::

[9] አማርኛ የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁጥር 10 ገጽ 40፤ ከልብነ ድንግል እስከ ቴዎድሮስ ገጽ 247





በዚህ ደብር ለመጀመሪያ ጊዜ የተሾመው አለቃ ቀውስጦስ ይባላል:: የመጀመሪያ የደብሩ የማዕርግ ስም ሊቀ ካህናት ነበር:: ወዲያው ተለውጦ መልአከ ብርሃን ሆኗል:: ቀውስጦስ ያረፈው በ1716 ዓ.ም በ85 ዓመት ዕድሜው ነበር:: የተቀበረው እዚያው ደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ነው:: ታቦተ ሕጉ በመቃረቢያ ከገባ በኋላ ወዲያው የዋናው ቤተ ክርስቲያን ሥራ ሕንፃ ተጀመረ:: ሥራው ሁለት ዓመታት ያህል ፈጀ:: በ1688 ዓ.ም ታቦቱ ከመቃኞ ወደ አዲሱ ቤተ ክርስቲያን ተዛወረ:: የዐፄ ኢያሱ የዘመኑ ታሪክ እንደሚያስረዳን የደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የተጀመረው በነገሠ በ20ኛው ዘመነ መንግሥት ነበር::

| ኢያሱ ያሠራቸው አብያተ ክርስቲያናት | | |
|---|---|---|
| 1 | አደባባይ ተክለሃይማኖት | ጐንደር |
| 2 | በረንኮ ማርያም | ወገራ |
| 3 | ጉቢያ ኢየሱስ | ቆላድባ |
| 4 | መረዋ አባ ኪሮስ | ቆላድባ |
| 5 | ደቀዋ ኪዳነ ምሕረት | ዳባት |
| 6 | ይገንዳ ተክለሃይማኖት | ዘጌ ተራራ አራራት |
| 7 | ክብራን ገብርኤል* | ጣና ደሴት |

ምንጭ: «የኢያሱ 1ኛ ዜና መዋዕል ጥናት»፤ በለጠ መርዕድ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ

* ክብራን ገብርኤል በዐፄ አምደ ጽዮንና በዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት የተመሠረተ ቢሆንም ድጋሚ ኢያሱ 1ኛ በአዲስ መልክ አሠርቶታል::

ዐፄ ኢያሱ የመንግስቱ ፍፃሜ በተቃረበበት ወቅት የሥላሴን ቤተ ክርስቲያን በስዕል አስጊጦታል:: የደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የብሉይና የአዲስ ኪዳን ታሪክ የሚገልጥ ባለብዙ ስዕል ያለበት ቤተ ክርስቲያን ሲሆን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በብዛት የስዕል ክምችት የሚታይበት ይህ ቤተ ክርስቲያን ነው:: በደህና ሁናቴ ላይ ያለው የደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን



www.ethiopianorthodox.org

ስዕሎች የሳሉት ኃይለ መስቀል ወለዱ የተባሉ አባት ናቸው። ስዕሎቹ ራሳቸው ከዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ጋር የጠበቀ ግንኙነት አላቸው።

ለስዕሎች የሚሆኑ ቀለማት የሚበጠበጡት በሽቱ ስለ ነበር ደስ የሚል መአዛ እንዲኖራቸው አድርጓል። ከዚህ በተ ጨማሪ ዐፄ ኢያሱ ለበረከቷ ብሎ ስዕሎቹና ቤተ ክርስቲያኑ ሲሰራ ሱባኤ ገብቶ እያለቀሰ እንባው በጠርሙስ ተጠራቅሞ የስዕሎቹ ቀለማት እንዲበጠበጥባቸው አድርጓል ሲሉ በዚያው የሚኖሩ አንድ አባት ገልፀዋል [የኢትዮጵያ ሬድዮ «ኢትዮ ጵያን እንቃኛት» ሐምሌ 22 ቀን 1994 ዓ.ም እለተ ሰኞ ምሽት ላይ የተላለፈ]

ይህ የሚያስገነዝበን ቅዱሳት ስዕሎች በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዚህ መልክ የመንፈሳዊ ሕይወት መስዋዕትነት የተከፈለባቸው ሲሆኑ፤ እነዚህን አባዝቶ ምእመኑ እንዲጠቀ ምበት ማድረግ ሲቻል ፈፅሞ የቤተክርስቲያን ባሕል ያልተ ከተሉ ስዕሎች በምእመናኑ እጅ እየገባና በአንዳንድ የከተማ አብያተ ክርስተያናት ተሰቅሎ እያየነው ነው። ከዚህ አልፎ ተርፎ «የባሕል ወረራ» በከፍተኛ ሁኔታ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየተስፋፋ መጥቷል። ቅዱሳት ስዕሎች ተዘንግተው ምዕራባዊ ባሕል «ሐውልት» ቀርጾ እስከ ማስገ ባት ተደርሷል። ከላይ እንዳየነው ዐፄ ኢየሱ አድያም ሰገድ በሱባኤ ያነባው እንባ ለሐውልት ማቆሚያ የሚሆን ሲሚንቶ ያስቦካበት ሳይሆን፤ ፍፁም ኢትዮጵያዊነትና ኦርቶዶክሳዊነ ትን የተላበሱ፣ የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት የጠበቁ ለቅዱ ሳት ስዕሎች መሳያ የሚሆኑ በራሷ ልጆች ከተለያዩ እፅዋት የቀመሙበትን ቀለም ለበረከት እንዲበጠበጥበት አድርጓል። ታዲያ የአሁኑ የባሕል ወረራ በቤተክርስቲያን ውስጥ መስፋ ፋት ተጠያቂው ማን ነው? እነዚህ ነገሥታት የቤተ ክርስቲ ያን ትውፊት እንዲጠበቅ ያነቡት እንባ ቢያንስ ሊያሳዝነን ይገባል፤ ካሳዘነን ደግሞ ዝምታው ይወገዳል።

ወደ ታሪኩ እንመለስና በ1685 ዓ.ም የኔዘርላንድ ንጉሥ ሁለት ደውሎችን ለዚሁ ቤተ ክርስቲያን በስጦታ እን





ደላኩ በታሪክ መጽሐፍ ተፅፎ ይነገራል።[10] ታቦተ ጽዮንን አይተዋል ከሚባሉ ሁለት ሰዎች መካከለ አንዱ እንግሊዞ ችንና ዐፄ ቴዎድሮስን ለማስታረቅ /ለመሸምገል/ የመጣ አርመናዊ ጳጳስ ጢሞቴዎስ የሚባል የኢየሩሳሌም ነዋሪ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ዐፄ ኢያሱ አድያም ስገድ እንደ ሆነ ዶክተር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ አማርኛ የቤተ ክርስ ቲያን መዝገበ ቃላት በተባለው የታይኘ ጽሑፋቸው ላይ አስፍረዋል።[11]

ዐፄ ኢያሱ በታሪኩ ውስጥ በጣና ሐይቅ ዙሪያ ከሚገ ኙት ገዳማት አንዱ የሆነው ክብራን ገብርኤልን በጣም ይወድ ነበር። አብዛኛውን ጊዜ ወደ ዘመቻ ሲሔድ መጀመሪያ እግሩ ክብራንን ረግጦ ብፅአት ያደርግ ነበር፤ ቅ/ገብርኤልን የሚወደው ከልጅነቱ ጀምሮ ጠባቂ መልአኩ ስለሆነ ነው። አንድ ጊዜ ኢያሱ የገብርኤል እለት ወሩ ሰኔ ላይ አንዲት አውሬ ተጣላችውና ከፈረሱ ጣለችው ከዚያው በቀንዷ ብሽ ሽቱን ወጋችው ይኸውም ለሞት አድርሶት ነበር። በዚሁ በእለተ ገብርኤል ቀን የንጉሡ ነፍሱ ተረፈች። ይህን ተአምር ንጉሡ ተመለከተና በጣም ደስ አለው።

በሊቀ መላዕክት በቅዱስ ገብርኤል በተራዳኢነቱ ኃይል እየተደሰተ ወደ ሰፈሩ ገባ። ከዚህ በኋላ ንጉሡ የራሱን ዘው ድ አነሣና አስቀጠቀጠው ወርቁንም አስመዘነው ሚዛኑ 74 ወቄት ሆነ። ወደ ክብራን ገብርኤል አስልኮ «በዚህ ወርቅ የሊቀ መላዕክትን ገብርኤልን ቤተ ክርስቲያን አሠሩበት» አላቸው መነኮሳቱም ወርቁን ተቀብለው ለንጉሡ ጸለዩ። እስከ ዛሬ የሚገኘውን በቀይ በሀ ድንጋይ የተሰራውን ክብ ቤተ ክርስቲያን ያሠራው ዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ እንደሆነ በጣና ሐይቅ ዙሪያ ያሉትን ገዳማት በተመለከትንበት ክፍል አይተናል ዐፄ ኢያሱ ክብራን ገብርኤልን የቤተሰቡ መካነ መቃብር አድርጎት ነበር።

[10] የአማራ ክልል የቱሪስት መስህብ ሀብቶች አጭር ቅኝት ገጽ 83።
[11] ቀጥር 10 ገጽ 176።



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ሰባት

## ሰባተኛው ወርቃማ ዘመን

## ክፍል አንድ

## በዐፄ ዮሐንስ፣ በዐፄ ምኒልክ፣ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ፣ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

## [ከ1863 - 1922 ዓ.ም]

ዐፄ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ አባ በዝብዝ ካሳ የተባሉት በአቡነ አትናቴዎስ እጅ ተቀብተው ዮሐንስ 4ኛ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ሐምሌ 7 ቀን በ1863 ዓ.ም. አድዋ ሥላሴ ላይ ዘውድ ጫኑ:: ከዚህ በኋላ በጥንቱ ሥርዓት አክሱም ጽዮን ላይ «ንጉሠ ጽዮን» ተባሉ ዐፄ ዮሐንስ እጅግ ሲበዛ መንፈሳዊ ንጉሥ እንደነበሩ ታሪካቸው ያስረዳል:: ሥራቸውም ይመሰክራል:: ይህንንም በዘመነ መንግሥታቸው የሠሩትን ታሪክ በሁለት መድበን መመልከት ያስፈልጋል::

### 1. በሀገር ውስጥ የሠሯቸው

#### 1.1 የእምነት ልዩነት መጥፋት

በመጀመሪያ ያተኮሩት በካህናት መካከል የነበረውን የእምነት ልዩነት ለማጥፋት ነበር:: በዚያን ጊዜ ሁለት የእምነት ወገኖች ነበሩ:: ክርስቶስ ሁለት ልደት [ተዋሕዶ] የሚሉና ሦስት ልደት [የጸጋ ልጅ] የሚሉ:: የመጀመሪያዎቹ የኢትዮጵያ የዋና እምነት ወገኖች ሲሆኑ:: ሁለተኞቹ ደግሞ ቀደም ሲል የነበረው የቅብዐት እምነት ቅጥያዎች ነበሩ:: በሸዋ ከወሰን ሰገድ አንስቶ የሦስት ልደት ትምህርት ተንሠራፍቶ ነበር:: ነገሩን በጉባኤ ለመፍታት ሀፄ ዮሐንስና በዘመኑ የሸዋ ንጉሥ የነበሩት ምኒልክ ስለተስማሙ ቦሩ ሜዳ [ለደሴ ቅርብ ስፍራ] ላይ የሃይማኖት ጉባኤ እንዲደረግ ተወሰነ:: ይህም በአጋጣሚ ሳይሆን ሆን ተብሎ የተደረገ ነበር የቦታው ምርጫ በኋላ እንደምናየው ለሁለተኛው ዓላማቸው መንደርደሪያ እንዲሆን ታስቦ ነው::





በዚህ ጉባኤ ላይ የደብር አለቆችና የገዳማት አበምኔቶች አንድም ሳይቀር ለግንቦት 21 ቀን 1870 ዓ.ም. ቦሩ ሜዳ እንዲገኙ አዋጅ ተነገረ:: ማንም ሳይቀር የሚመለከታቸው ሁሉ ተሰብስበው ቦሩ ሜዳ ሄዱ:: በዘመኑ ጳጳስ አልነበረም:: ከፍ ብሎ የተጠቀሱት ሀፄ ዮሐንስን ቀብተው ያነገሡ ግብፃዊ ጳጳስ ሰኔ 23 ቀን 1867 ዓ.ም. አርፈው አድዋ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ላይ ተቀበሩ:: በዚህ ምክንያት ጳጳስ ለማስመጣት ሀፄ ዮሐንስ እየተላላኩ ነበር:: ሀፄ ዮሐንስ የሃይማኖትን ልዩነት ከቤተ ክርስቲያን ለማጥፋት ዕሑ ፍላጐት ስለነበራቸው የተከሰተውን ልዩነት በጉባኤ ለመፍታት የተነሱት ከዚህ የተነሳ ነበር::

ግንቦት 21 ቀን 1870 ዓ.ም ዐፄ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ «ዳግማዊ ኒቂያ» በተባለው በቦሩ ሜዳ ጉባኤውን ከፈቱ:: የሁለት ልደት አፈ ጉባኤዎች ሊቀ ካህናት ኪዳነ ወልድ፣ መምህር ግርማ ሥላሴ፣ መምህር አካለ ወልድ፣ ከሁሉም ይልቅ በማያሻማና በተጨባጭ ሁኔታ የሁለት ልደትን ትምህርት ያቀረቡት መልአከ ብርሃን ወለደ ዮሐንስ ናቸው:: አቀራረቡ የሰመረ፣ ኃይለ ቃሉ የከረረ በመሆኑ ጸሐፌ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ በዐፄ ምኒልክ የዘመን ታሪካቸው እንዳለ አስገብተውታል::

የሦስት ልደት ወገኖች ደግሞ አለቃ ህብተ ወልድ፣ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ፣ ዋልድቤ እንግዳ ዙራንቤ እንግዳ ነበሩ:: አቋቋማቸው ራሱ ወሳኝነት ነበረው:: ሦስት ልደቶች ከግራ፣ ሁለት ልደቶች ከቀኝ ነበሩ:: ይኸውም ንጉሠ ነገሥቱ በአጋጣሚ ያደረጉት ሳይሆን ሆን ብለው ነው:: ዐፄ ዮሐንስ በዚሁ እምነት ያሉ እንደመሆናቸው የእነዚያን ወገን በግራ ሊያቆሙ ችለዋል:: ጉባኤው በተዋህዶ ወይም በሁለት ልደቶች አሸናፊነት ተጠናቀቀ:: አንባብያን በጉባኤው ላይ የቀረ



www.ethiopianorthodox.org

በው ጥያቄና መልስ በኢትዮጵያ ታሪክ በተለያየ ክፍል ስለ ተጻፈ ያንን መመልከት ጠቃሚ ነው::[1] ጉባኤው ካበቃ በኋላ ሁለቱ ነገሥታት ወደ ደብረ ሊባኖስ አምርተው ገዳሙን ከተሳለሙ በኋላ ቤተ ክርስቲያኑን በአዲስ እቅድ በአማረ ሁኔታ እንዲሠራ ዐፄ ዮሐንስ የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን ቃል ገቡ::

## 1.2 አብያተ ክርስቲያናትን መልሶ መገንባትና ኢአማንያንን ማስጠመቃቸው

ዐፄ ዮሐንስ የደብረ ሊባኖስን ገዳም በአዲስ መልክ ለማሰራት ቃል ከገቡ በኋላ ወደ ጎንደር አልፈው ግንበኞችንና አናፂዎችን ልከው በዚያው ዓመት ተጀመረ:: ዐፄ ዮሐንስ ይህን ቤተ ክርስቲያን ሲያሠሩት 18 ጉልላት ነበረው ይባላል:: ቀደም ሲል እንደተገለፀው የሃይማኖት ጉባኤ ወሎ ውስጥ መጠራቱ ያለ ምክንየት አይደለም:: ምክንያቱም የእስልምና እምነት የተስፋፋበትና ጥንት የክርስቲያን አገር ስለ ነበር ነው:: ይህንኑ የሚያስረዱ የገሀድ ማስረጃዎች ተቆፍረው የወጡ ነበሩ:: ስለዚህ ጉዳይ ጸሐፌ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ እንዲህ ይላሉ:-

«...ከዚህ በኋላ በ1874 ዓ.ም የደብረ ነጎድጓድ፤ በለገሐዲ፤ የአትርኖስ ማርያምና፤ ታዐካ ነገሥትን፤ መካነ ሥላሴን ጥንት በኖራ የተሠሩትን አብያተ ክርስቲያናት በግራኝ ጊዜ የተቃጠሉትን እያስቆፈሩ ግንቡን አስወጡት የግምቡም ቁመት ሰባት ስምንትም ክንድ ሆነ:: ነገር ግን ከቀን ብዛት የተነሣ መሬቱ አጥብቆ ውጦታልና እስከ መሠረቱ መቆፈር አልተቻለም:: ስራውም ድንጋዩ አራት መአዘን የተጠረበ፣ የተቀረፀ እጅግ የሚያስደንቅ ነው:: ከዚህም ብዙ ነዋየ ቅድሳት ወጣ የወሎም ሰው ይህን ባየ ጊዜ እውነትም የክርስቲያን አገር መሆኑን ተረዳ...»[2]

---

[1] ታሪክ ነገሥት በዳግማዊ ምኒልክ ገጽ27፤ መጽሐፈ ቅኔ /ዝክረ ሊቃውንት/ ገጽ 27-28 መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ገጽ 154-162::

[2] ታሪክ ነገሥት ዘዳግማዊ ምኒልክ ገጽ 100::





የአፄ ዮሐንስ መሠረታዊ ሀሳብ ይህን ጥንት ክርስቲያን የሆነውን አገር ወደ ቀደመው ሃይማኖት መመለስ አለበት ነበር:: ስለዚህ ይማሙን መሐመድ አሊን ክርስትና አንስተው ስሙን ሚካኤል አሉት ይህም ንጉሥ ሚካኤል የልጅ ኢያሱ አባት ነው:: እንዲሁም የወረይሉን ባላባት አባ ዋጠውን ክርስትና አንስተው ኃይለ ማርያም አሉት:: ዐፄ ዮሐንስ ሕዝቡን እያሳመኑ ወደ ክርስትና የሚመልሱ መምህር ግርማን ሾሙ:: ንጉሥ ምኒሊክም የታወቁትን ታላቁን መምህር አካለ ወልድን ሾመው ቦሩ ሜዳ ላይ አስቀመጧቸው:: ሁለቱም መምህራን ብዙዎችን ወደ ክርስትና መልሰዋል::

## 1.3 ወንጌልን ማስፋፋታቸው

በዚህ ዘመን አፄ ዮሐንስ ክርስትና በሚገባ እንዲስፋፋ ፅኑ ምኞት ነበርና የጳጳሳት ቁጥር ወደ አራት ከፍ እንዲል የግብፅ ቤተ ክርስቲያንን ጠይቀዋል:: እንዲህ አይነቱ ጥያቄ ከላስታው ንጉሥ ከሐርቤይ ቀጥሎ ስላልነበረ የግብፅ ቤተ ክርስቲያንን አስደንግጧት ነበር:: ምክንያቱም ይህ ጥያቄ ባይመለስ ሀፄ ዮሐንስ ፊታቸውን ወደ ሌሎች እህት አብያተ ክርስቲያናት ለማዞር ወስነው ነበር:: የሆነው ሆኖ ጥያቄው ተቀባይነት አግኝቶ በ1873 ዓ.ም 4 ጳጳሳትን አባ ጴጥሮስን፣ አባ ማቴዎስን፣ አባ ማርቆስንና አባ ሉቃስን ሹመው ወደ ኢትዮጵያ ላኩ:: እነዚህ ጳጳሳት በ1875 ዓ.ም ከዋናው ጳጳስ ከአቡነ ጴጥሮስ በቀር አቡነ ማቴዎስን ለንጉሥ ምኒልክ፣ አቡነ ሉቃስን ለንጉሥ ተክለ ኃይማኖት ዘጎጃም፤ አቡነ ማርቆስን ደግሞ ለቤጌምድር ደልድለዋቸው ነበር:: አፄ ዮሐንስ ባላቸው መንፈሳዊ ቅንአት ወንጌል በኢትዮጵያ በደንብ እንዲስፋፋ እነዚህን 4 ጳጳሳት ቢያስመጡም በኋላ ግን ሁሉም በሞት ሲለዩ እንደበፊቱ አንድ ጳጳስ ይመጣ ጀመር::

ከላይ የጠቀስናቸው ከግብፅ የመጡት አራት ጳጳሳት ዐፄ ዮሐንስ በ80 ሺህ ብር ገዝተው ነበር ያስመጧቸው:: ይህን የመሰለውን የችግር ዘመን የኋላ ሊቃውንት በተገኘው



www.ethiopianorthodox.org

አጋጣሚ ቁጭታቸውን ከመግለፅ አልቆጠቡም:: መንፈሳዊ ንግድነቱንም ሕገ ወጥ መሆኑንም ጭምር ጠቅሰዋል:: ከእነ ዚህም መካከል ደስታ ተክለ ወልድ ባዘጋጁት «ገበታ ዋሪያ የንባብ መማሪያ» በተሰኘው መጽሐፋቸው ገፅ 40 ላይ በግጥም መልክ ከአለቃ ኪዳነ ወልድ የተገኘውን በከፊል እንመልከት:-

፭

በሰማንያ ሺህ ብር አራት ጳጳስ፤
ገዝተው እንዳስመጡት ዐፄ ዮሐንስ፤
ጳጳስና ክህነት በጦቢያው መንግሥት፤
የንግድ እቃ ሆኖ እንዲሸጥለት፤
እራሱን በሌዊ አኛን በይሁዳ፤
መስሎ አነፃፅሮ ሱቁን ሲያሰናዳ፤
በእራተኛው አንቀፅ ቀለም ቀንዱን ተክሎ፤
ኢይሰየሙ ሲል ኢያጳጵስ ብሎ፤
ፈራሽ ሰው ሰራሽ ሕግ ስለ ጠፋባችሁ፤
ሠልስቱ ምዕትን ለምን ታማላችሁ::
ከእኛም አንዱን መሾም በ1ኛው ሰላማ፤
ዝምሮት ነበረ አትናቴዎስማ፤
አላገኘም እንጂ መሳይ ተከታይ፤
ዘመዶች ታስረው በፍቅረ ነዋይ:: በማለት ገልጠዋል::

የመጨረሻዎቹን ሁለቱን ስንኝ ስንመለከተው ግብፃ ውያን ጳጳሳት ያለ እጅ መንሻ ሊመጡና ልጆቻቸውን ሊጐበኙ፣ ሊያስተምሩና ሐዋርያዊ ግዴታቸውን ሊፈፅሙ ያልቻሉ መሆናቸውን ያመለክታል:: 20ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ ቅዱስ አባታችን አቡነ ሰላማን አብርሃ ወአፅብሐ ጵጵስና እንዲቀበል በላኩት ጊዜ ያለምንም እጅ መንሻ ሹሞ መላኩን የግጥሙ ጸሐፊ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ጨምረው አስታውሰው ጠቅሰውታል::

## 1.4 የሚሲዮናውያን መባረር

ከውጭ ወደ አገር የሚገቡ ሚሲዮናውያን ጋብ ያሉት በዚህ ዘመን ነበር:: ሁሉንም ሚሲዮናውያን ሰብስበው ምን ልታደርጉ ወደ ኢትዮጵያ መጣችሁ? አሏቸው:: እነዚህም ወንጌልን ልንሰብክ ነው ብለው መለሱላቸው:: ንጉሡም





ወንጌል አንድ ነው፤ እግዚአብሔርም አንድ ነው፤ እኔም ሕዝቤን ለመስበክ የሚበቁ ጳጳሳትና ቀሳውስት አሉኝ ለማን ልትሰብኩ ትፈልጋላችሁ? ቢሏቸው እነሱም በዚህ አገር ለሚ ኖሩ ይሁዲዎችና እስላሞች ብለው በድጋሚ መለሱላቸው:: ዐፄ ዮሐንስም ወደ ኢትዮጵያ ስትመጡ የአይሁዶች አገር ኢየሩሳሌም የእስላምን አገር ሊቢያን፤ ሳውዲ አረቢያን፤ የመንን፣ ትታችሁ እንደምን አልፋችሁ መጣችሁ! አሁን እኔ የአገሬን ሕዝብ የእጅ ሥራ ጥበብ የሚሰሩ ስጋጃ ሠሪ ዎች፣ አናጢዎች፣ ብረት ቀጥቃጮች የሆኑትን እቀበላለሁ እንጂ እናንተን አልፈለግም አገሬን ልቀቁልኝ ብለው ገሚሶ ችን በምፅዋ፣ ሌሎችን ደግሞ በመተማ በኩል አስወጧቸው::[3] ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሚሲዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ መግባት አቁመው ነበር:: ህፄ ዮሐንስ አገራቸውን በጣም የሚወዱ ስለነበር እንዲህ ብለዋል:- *«እንደ ዳዊት በአይነ ሕሊናዬ እያገላ በጥኩ የምደግማትን ኢትዮጵያን ሲነኩብኝ ደሜ ይፈሳል:: የሚገዙ ትን መሬት ብቻ ኢትዮጵያ ብለው የሚጠሩ የአገሬ መኳንንት ከጠ ባብ ሀሳባቸው ወጥተው እንዲት ታላቅ ኢትዮጵያን መኖሯን ማወቅ አለባቸው»* በማለት ገልፀዋል:: ከዚህ በላይ የተገለፀው አራት አበይት መንፈሳዊ ተግባራት በአገር ውስጥ ያከናወኗቸው ናቸው::

## 2. በውጭ ሀገር ያከናወኗቸው

ከቀድሞ የሀገራችን ነገሥታት መካከል በኢየሩሳሌም ላለው ርስታችን ትኩረት ከሠጡት መካከል ህፄ ዮሐንስ አንዱ ናቸው:: ይኸም በዘመናቸው ከክርክር ነፃ የሆነች ቦታ ገዝተው ቤተ ክርስቲያን አሠርተ ዋል:: ህፄ ዮሐንስ ይህችን ቤተ ክርስቲያን ያሠሯት ከቱርክ ጋር ተዋግተው በምርኮ ያገኙትን ስድስት ሣጥን የእንግሊዝ ወርቅ በ1872 ዓ.ም በኢየሩሳሌም ገዳም ላሉት ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ልከው የኢትዮጵያ ጥንታዊነት ካላቸው አብያተ ክርስቲያናት አሠራር የምታንጸባርቅ ቤተ ክርስቲያን በወቅቱ የገዳማቱ አበ ምኔት በነበሩት በመምሕር ወልደሠማያት ትጋት አሠሩ::

[3] የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ቴዎድሮስ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ገጽ 64::



www.ethiopianorthodox.org

እያሠሩት የነበረው ቤተ ክርስቲያን ሥራ አልቆ ጣሪያው ሲቀር በ1881 ዓ.ም መጋቢት 1 ቀን አረፉ:: ዐፄ ዮሐንስ ሲሞቱ የቤተክርስቲያን ማሠሪያ ገንዘብ አለቀ:: በዚህ ምክን ያት መምህር ወልደ ሰማያት ከተገዛው መሬት ላይ ሩቡን ያህል በ9ሺ ብር ሸጠው በ3 ሺህ ብር ቤተክርስቲያን አስጨ ርሰው በተረፈው 6ሺ ብር በ1883 ዓ.ም የመንበረ ሊቀ ጵጵስናውን ቤት ገዝተዋል::[4] ዐፄ ዮሐንስ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ መናንያን ይልኩአቸው ከነበሩ ደብዳቤዎች ለአብ ነት ያሕል የሚከተለው ቀርቧል::

> *«በስመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሀት መልዕክተ ዘስዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ይድረስ ሀበ ኵሎሙ ማኅበረ ዘኢትዮጵያ እለ ሀለው በኢየሩሳሌም እንተ ይዕቲ ዴር ሡልጣን መናንያነ ዓለም ርቱአነ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት! እንዴት ሰነበታችሁ እኔ ከሠራዊቱ ጋር በእግዚአብሔር ቸርነት በእምነ ጽዮን አማላጅነት በእናንተ ጸሎት አምላከ ቅዱሳን ይክበር ይመስገን ይህና ነኝ ምህረቱ ለዘላለም ነውና ከጥንት ቦታ ግዙ ማለቴ የኢትዮጵያ ሰዎች ንጉሥ የላቸውም ለማኞች ናቸው፣ ከአርመንም ከሌላውም ሁሉ እየለመኑ ይኖ ራሉ እየተባላችሁ ስድባችሁ ቢጠና በዚህ ቀንቼ ነው እንጂ ለእኔ ለልጄ ለተንቤን ለእንዳርታ ሰው ይሆናል ብዬ አይደለም ቦታውን እናንተን ያልመሠለ ሰው አይቀመጥባት አታስቀርቡ እንዲሁ ሺህ ብር ሰድጄላ ችኋለሁ ለችግራችሁ ሁሉ ጉዳይ አድርጉት አይዟችሁ አትደንግጡ ጉዳይ ቢበዛብኝ ነው፣ ደግሞ እንደቀድሞ አስድላችኋለሁ የቤተ ክርስቲያኑ ነገር ሁሉ እግዚአ ብሔር በፈቀደው ጊዜ ይሰራል»[5]*
>
> *ተጻፈ አድዋ ከተማ*
> *ጥር 1 ቀን 1877 ዓ.ም*

[4] ቅዱሳት መካናት በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን ዲ/ን ስሎሞን ዮሐንስ::
[5] የኢትዮጵያ ስልጣኔ ገጽ 102::





# ክፍል ሁለት

## በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን [ከ1882 - 1903]

ከዐፄ ዮሐንስ 4ኛ እረፍት በኋላ በሀገራችን የነገሡት ዐፄ ምኒልክ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አድርገዋል:: እንደ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ አፅማቸው ያረፈበት ታዕካ ነገሥት ባሕታ ለማርያም፣ ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ዳግማዊት ጽዮን አዲስ ዓለም ማርያም፣ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የታነፁት በእሳቸው ዘመን ነው:: የዘመናዊ ሥልጣኔ ፈር ቀዳጅም ስለነበሩ ሀገሪቱ የውጭ ሥልጣኔ እንድትቀበል አድርገዋል:: አሁን የምናያት የኢት ዮጵያ ስልጣኔ መሠረት ዐፄ ምኒልክ ነበሩ::

የፖስታ አገልግሎት፣ የምድር ባቡር፣ ቴሌፎን፣ መኪና፣ የባንክ አገልግሎት፣ ሆስፒታል፣ በተለይ ዘመናዊ ትምህርት ቤት... የተጀመሩበት ወቅት ስለነበር በኢትዮጵያ ታሪክ ትልቅ ሥፍራ ይሰጣቸዋል:: ዐፄ ምኒልክ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ያላቸው አይነተኛ ሥፍራ የዐፄ ቴዎድሮስንና ዐፄ ዮሐንስን ሕልምና ትልም ገሀድ ማድረጋቸው ነው:: እንደ እሳት በሚንቀለቀለው በቴዎድሮስና በዮሐንስ የተፀነሰ ውን የአንድነት፣ የሥልጣኔ እንዲሁም ኢትዮጵያ ታላቅ ራሷን የቻለች ነፃ ሀገርና ነፃ እምነት /ሃይማኖት/ ያላት ሀገር መሆኗን ዐፄ ምኒልክ ተቀብለው ለፍሬ ማብቃታቸው ነው:: ስለዚህ የዐፄ ምኒልክ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲ ያን ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱም ወርቃማ ዘመን ነው ማለት ይቻላል::



www.ethiopianorthodox.org

## የዐፄ ምኒልክ አስተዋፅኦ በቅዱሳት መካናት

ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ በኢየሩሳሌም የሚገኘውን ቅዱሳት መካናት እንዲጠበቅ እንዲፀና ያደረጉት ለየት ባለ ዘመናዊ መንገድ ነው:: ይኸውም ሁለት መቶ ሺ ብር ልከው በኢየሩሳሌም በክሪዲልዮን ባንክ እንዲቀመጥና ወለድ ወለዱ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት እንዲጠቀሙበት አድርገዋል:: የተናገሩትም ይህን ያንፀባርቃል: «ከኢትዮጵያ ገንዘብ ለመላክ አይመችም ብዬ ነው ይህን ገንዘብ በባንክ እንዲቀመጥ ያደረኩት፣ በኢየሩሳሌም በቅድስት ሀገር በኢትዮጵያ መንግሥት ገዳም በኦርቶዶክሳዊት እምነት ፀንተው ለሚኖሩ ለኢትዮጵያ መናንያን መነኮሳት ለልብስና ለምግብ እርዳታ እንዲሆን ይርጋ» ብለዋል::[6]

በዚህ ብቻ ሳይወሠኑ ግብፃውያን በዴር ሡልጣን ይዞታ ላይ መነኮሳቶቻችን እንዳይወጡ እንዳይገቡ በር ስለ ተዘጋባቸው አብርሃም ልጁን ይስሐቅን ሊሠዋ ባቀረበበት አንፃር በሥተ ምሥራቅ አንድ ቤት አስፈርሰው ሌላ በር በመክፈት በዚያ የሚኖሩ አባቶች መግባት መውጣት ችለዋል:: ዐፄ መኒልክ ደብረ ገነት ገዳም ውስጥ አንድ የ6 ሰዎች መኖሪያ የሆነ ፎቅና ምድር ያለው ቤት ሠርተው ስላበረከቱ ገዳማውያኑ ቤቱን እያከራዩ ይጠቀሙበታል:: እንዲሁም ገዳሙ የሚተዳደርበት ደንብ ልዩ ልዩ ንዋየ ቅድሳት በየጊዜው እያበረከቱ መነኮሳቱን አፅናንተዋል:: ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱም አሁን የእስራኤል መንግሥት የህፃናት ህክምና መስጫ መሥሪያ ቤት ያደረገውን ፎቅና ምድር ቤት አሠርተዋል:: እንዲሁም በንግሥት እሌኒ መንገድ አሁን የእስራኤል መንግሥት ሬድዮ ጣቢያ እና ማዘጋጃ ቤት፣ የበጐ አድራጐት ት/ቤት የሆኑትን ሁለት ፎቅ ሕንጻዎች አሠርተዋል:: በተጨማሪ ንዋየ ቅድሳት፣ አልባሳት ለቤተ ክርስቲያኑ አበርክተዋል::

[6] የቅዱሳት መካናት መስታወት::





# ክፍል ሦስት

## በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን /ከ1909-1922 ዓ.ም/

በዚህ በጠቀስነው ዘመን በኢትዮጵያ የነገሡት የዐፄ ምኒልክ ልጅ ዘውዲቱ ነበሩ:: የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ካህናት እጅግ የተከበሩበት ዘመን በመሆኑ «ዘመነ ካህናት» በመባል ይታወሳል:: በቤተ መንግሥት ብዙውን ጊዜ ሹመት ሽልማት የሚሰጠው ለካህናት ነበር:: ይህ ዘመን ለየት የሚያደርገው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዘመናዊ አስተዳደር መመራት የጀመረችበት ነበር:: ይህም በ1918 ዓ.ም መስከረም 8 ቀን «መንፈሳዊ ጉባኤ» የተባለ የቤተክህነት መሥሪያ ቤት ተቋቁሞ ሥራውን ጀመረ:: ይህ መሥሪያ ቤት ኃላፊው እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ /በኋላ አቡነ ሳዊሮስ/ የተባሉ አባት ነበሩ::

ይህ መንፈሳዊ ጉባኤ ብዙ የቤተ ክርስቲያን ችግሮችን እንደፈታ ሰነዶች ያስረዳሉ:: መንፈሳዊ ጉባኤው በጠላት ወረራ ዘመን ችግሩን ተቋቁሞ አልፈረሰም:: እንዲያውም 72 አባላት ያሉት የምርጫ ኮሚቴ አሰባስቦ አቡነ አብርሃምን እሳቸው ከሞቱ በኋላ አቡነ ዮሐንስን /ሐዲስ ተክሌን/ ሊቀ ጳጳስ አድርጐ በችግሩ ዘመን ሾሟል:: ጠላት ኢትዮጵያን ለቆ ከወጣ በኋላ የቤተክርስቲያን ሙያ ያላቸውን ምሁራንን በአባልነት አካቶ እንዲሠሩ አድርጓል:: ይህ መንፈሣዊ ጉባኤ የተለያዩ ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅሙ ደንቦችን አውጥቷል:: በጣም የሚታወቀው የሥራው ውጤት በ1934 ዓ.ም መጋቢት ወር የወጣ ደንብ ሲሆን፣ የመጽሐፍ ርዕስ «የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደንብ» የሚል ሆኖ 12 አንቀጾች አሉት::

ብሔራዊ ሲኖዶስ በሀገራችን ከመቋቋሙ በፊት ይህ መንፈሣዊ ጉባኤ የጐላ አስተዋፅኦ አድርጓል:: ለዛሬው



www.ethiopianorthodox.org

የቤተ ክህነት መሥሪያ ቤት መወለድ ምክንያቱ እሡ ነበር:: ይህ ሁሉ ሲሆን መሥሪያ ቤቱ በታላቁ ቤተ መንግሥት ቅፅር ውስጥ ነበር:: ጽሕፈት ቤቱ ከቤተ መንግሥት ከወጣ በኋላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት ተባለ::[7] እንግዲህ በ20ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመን ወደተሻለ ምዕራፍ ለመሸጋገር እርምጃ የጀመረችበት ጊዜ ስለነበር በወርቃማ ዘመናት ውስጥ ይካተታል:: በዚህ ዘመን የተከናውኑትን አበይት ሦስት ነገሮች እንመለከታልን:-

## 1.1 ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን

በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ትኩረት ከተሠጠባቸው ተግባራት አንዱ የአምልኮ ቦታ /አብያተ ክርስቲያናት/ ማሳነፃቸው ነው:: ይህም በዘመነ መንግሥታቸው 35 የሚደርሡ አብያተ ክርስቲያናትን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አሳነፀው አበርክተዋል:: እነዚህም:-

| የቤተክርስቲያኑ መጠሪያ | የሚገኝበት ቦታ |
|---|---|
| ታዕካ ነገሥት ባዕታ | አዲስ አበባ |
| መንበረ ፀሀይ ማርያም /እንጦጦ/ | አዲስ አበባ |
| ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም /ቀጨኔ/ | አዲስ አበባ |
| ደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል | አዲስ አበባ |
| ደብረ ሳሕል ቅዱስ ሚካኤል /የካ/ | አዲስ አበባ |
| ማኅደረ ስብሐት ልደታ | አዲስ አበባ |
| ቀራንዮ መድኃኔዓለም | አዲስ አበባ |
| ሐመረ ኖህ ኪዳነ ምህረት/ እንጦጦ/ | አዲስ አበባ |
| መንበረ ንግሥት ቁስቋም | አዲስ አበባ |
| ጽርሐ አርያም ቁስቋም | አዲስ አበባ |
| ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ | አዲስ አበባ |
| ደብረ ናዝሬት ቅዱስ ዮሴፍ | አዲስ አበባ |

[7] የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደንብ 1934 ዓ.ም ፤ ፍንጭ ፍተሻ 1998፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍል 2፣ በዚሁ መጽሐፍ አዘጋጅ የታተመ የፓትርያርክነቱ መንበር እንዴት ተገኘ? 2000 ዓ.ም፣ የሚሉትን መጽሐፎች ይመለከቷል::





| | |
|---|---|
| ደብረ ገሊላ አማኑኤል | አዲስ አበባ |
| ደብረ ኃይል ራጉኤል | አዲስ አበባ |
| መናገሻ ማርያም | መናገሻ |
| መናገሻ ቅዱስ ማርቆስ | መናገሻ |
| ሰላ ድንጋይ ቅዱስ ማርቆስ | ተጉለት |
| ፋሌ መድኃኔዓለም | |
| ወሎንኮሚ ቅዱስ ማርቆስ | |
| ደብረ ጽሙና ተክለ ሐዋርያት | አደአ በርጋ |
| ደብረ በግዕ ሕፃን ሞዐ | ጠራ |
| ኢቲሳ ገዳም | |
| አብዮ ገዳም | |
| ቦሩ ሥላሴ | ወሎ |
| ጅማ መድኃኔዓለም | ጅማ |
| ወረይሉ ቅዱስ ጊዮርጊስ | ወረኢሉ |
| ልደታ | ካቢ በደጃዝማች ናደው ጉልት ላይ |
| ደብረ ብርሃን ኢየሱስ | ጐንደር |
| ደብረ ታቦር ኢየሱስ | ጐንደር |
| ቅዱስ ገላውዴዎስ | ጐንደር |
| ወጨጫ ማርያም | |
| ደብረ ዑራኤል | ጫንጮ |
| በረኸ ቤተ ክርስቲያን | |
| ሩፋ ቅዱስ ሚካኤል | |
| ጃር ሥላሴ | |
| ቅዱስ ጊዮርጊስ | ተጉለት በጉልታቸው ላይ |

እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የዘመን ታሪካቸው መዝግቦልን ያቆየን ሲሆን፣ ይህ የንግሥት ዘውዲቱ ዘመን በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ከታነፀበት ከሌሎች ነገሥታቶች የንግሥና ዘመን ቀዳሚውን ሥፍራ ይይዛሉ፤ በአዲስ ዓለም በመናገሻ ማርያም፣ በእንጦጦ ማርያም፣ በቅዱስ ጊዮርጊስ፣ በታዕካ ነገሥት በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በሚገኙ ሙዚየሞች የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በርካታ ቅርሶች ይገኛሉ፤ የሰጧቸው ስጦታዎች፣ የግል መገልገያ እቃዎች ይታያሉ፣ የንግሥቲቱ አፅም ከአባታቸው ከዐፄ ምኒልክ ጋር በባዕታ ገዳም ምድር ቤት ውስጥ በክብር ተቀምጦ ይታያል::



www.ethiopianorthodox.org

## 1.2 ሢመተ ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን

የንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት የተለየ የሚያ ደረገው በዘመናቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያውያን ጵጵ ስና ለመቀበል መቻላቸው ነበር። በ1919 ዓ.ም ግብፃዊው የኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ አቡነ ማቴዎስ በሞቱ ጊዜ፤ የኢትዮ ጵያ ቤተ ክርስቲያን ከልጆቿ መካከል ጳጳስ መሾም አለባት የሚለው ሀሳብ እየተጠናከረ ሔዶ ነበር። በዚህ መሠረት ይህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ ተቀባይነትን አግኝቶ፤ በትምህርት በምግባር የበሠሉ 5 አባቶች ተመርጠው ከእነ ዚህ ውስጥ አራቱ ግንቦት 2 ቀን 1921 ዓ.ም በአዲስ አበባ ተነስተው በባቡር ወደ ጅቡቲ ሄደው እንደገና ግንቦት 5 ቀን በመርከብ ተሳፍረው ወደ ካይሮ ሄዱ።

እዚያው ካይሮ 15 ቀን ከቆዩ በኋላ ግንቦት 25 ቀን በዚያው ዓመት በእለት እሁድ በእስክንድርያው ፓትርያርክ በአቡነ ዮሐንስ 19ኛ አንብሮተ እድ:- ጴጥሮስ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ሚካኤል ተብለው ተሰይመው ተሾሙ። ሰኔ 21 ቀን 1921 ዓ.ም ወደ ሀገራቸው ተመለሡ። የጳጳሳቱ ስምና ሀገረ ስብከት የሚከተለው ነበር:-

| የበፊት ስማቸው | የሢመት/የጵጵስና/ ስማቸው | የተሾሙበት ሀገረ ስብከት |
|---|---|---|
| መምህር ደስታ | አቡነ አብርሃም | የሸዋ ሀገርን ይዘው ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ |
| መምህር ወልደ ኪዳን | አቡነ ይስሐቅ | የጉጃምና የጎንደር ጳጳስ |
| መምህር ኃ/ሚካኤለ | አቡነ ጴጥሮስ | የምስራቅ ጳጳስ |
| መምህር ሐዲስ | አቡነ ሚካኤል | የኢሊባቡርና የከፋ ጳጳስ |
| እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ* | አቡነ ሳዊሮስ | የደቡብ ኢትዮጵያና እጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ |

* ከእነዚህ ውስጥ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በጤና መጓደል ምክንያት ወደ ግብፅ ሳይሔዱ ቀርተው ነበር። በ1922 ዓ.ም በታህሳስ ወር የእስክንድርያው ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ 19ኛ፣ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት መጥተው ነበር። ለጵጵስና ታጭተው ሳሉ ነገር ግን ወደ ግብፅ ያልሔዱትን እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ጥር 1 ቀን 1922 ዓ.ም በዳግማዊ ምኒልክ መታሠቢያ ባሕታ ለማርያም ገዳም ቅዳሴ ቀድሰው የጵጵስና ቅብዓት ቀብተው አቡነ ሳዊሮስ ብለው ሾመዋቸዋል።





## 1.3 የቅዱሳት መካናት ይዞታ ማስጠበቃቸው

በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ያለንን ይዞታ እንደ ቀድሞ ነገሥታቶቻችን ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱም የበኩ ላቸውን አስተዋፅኦ አበርክተዋል። ለምሳሌ በደብረ ገነት ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን በተለይ በባላቸው ሥም አንድ የደውል ቤት አሠርተዋል። በዚህ ሳይወሠኑ በኢየሩሳሌም ከተማ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የታሪክ ይዞታ መርጃ እንዲሆን ትልቅ ህንፃ ሠርተው ህንፃውም አሁንም እየተከራየ ጥቅም ከመስጠቱም በላይ የኢትዮጵያ መንግሥት ቆንስል ጽ/ቤት በዚሁ ህንፃ ውስጥ ነበር። በተጨማሪ ለማኅበረ መነ ኮሳቱ መልዕክት እየላኩ ያፅናኗቸው ነበር። ከደብዳቤያቸው አንዱ:-

> *«ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘኢትዮጵያ ወለቱ ለዳ ግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት፤ ይድረስ ለማኅበረ ኢየሩሳሌም እስ ሀለው በዴር ሡልጣን፤ ወበ ደብረ ነገት፤ አባቶቼ ጤናችሁን እንደምን ናችሁ። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። ስለ ችግራችሁም ሁለት ሦስት ጊዜ የላካችሁት ወረቀት ደረሰን። እግ ዚአብሔር በዚህ በአባቴ በዳግማዊ ምኒልክ መንግ ሥት ለመንገሥ ካበቃኝ ቀን ጀምሮ ሳልጠይቃችሁ መቅረት የመንገዱ መጥፋትና የጦርነቱ ብርታት ነው እንጂ በእናንተ የምጨክንበት ልቡና ኖሮኝ አይደ ለም። አሁንም ይኸው ለማኅበሩ በመምህር ማህፀንቱ እጅ አንድ ሺ ዳውላ እህል በያይነቱ፤ 1ሺ የእንግሊዝ ወርቅ ልኬላችኋለሁ፤ አባቶቼ በጸሎታችሁ አስቡኝ። ለወደፊትም እጠይቃችኋለሁ»*[8]
>
> ሰኔ 8 ቀን 1910 ዓ.ም፣
> አዲስ አበባ ተጻፈ

በአጠቃላይ የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህን ጉላ ያለ ወርቃማ ታሪክ የተመዘገበበት ዘመን ነው።

[8] የታሪክ መሥታወት ገጽ 421 ቅዱሳት መካናት በኢየሩሳሌም /ዶር ሡልጣን/ በዚሁ መጽሐፍ እዘጋጅ የታተመ።



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ስምንት

## ስምንተኛው ወርቃማ ዘመን

## ክፍል አንድ

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን

### ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን

#### ① መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የቀድሞዎችን ደጋግ ነገሥታት አርአያ በመከተል ገና ከደጃዝማችነታቸው ጀምሮ በአልጋ ወራሽነታቸው ጊዜና ከነገሡም በኋላ በዘመናቸው የተደረሰበትን የሕንፃ ጥበብ ሥራ ላይ በማዋል በየቦታውና በየጊዜው ታላላቅ ካቴድራሎችና ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን አሳንፀዋል:: ንጉሠ ነገሥት ከተባሉ በኋላ ካሠሯቸው አብያተ ክርስቲያናት መካከል መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ አንዱ ነው:: ታህሳስ 15 ቀን 1924 ዓ.ም የመሠረቱን ድንጋይ ጥለው ሥራው በጥሩ ሁኔታ ተጀምሮ ለፍፃሜ ሊደርስ ጥቂት ሲቀረው ጠላት በ1928 ዓ.ም. አገራችንን ስለወረረ ቢቋረጥም በ1933 ዓ.ም. ንጉሠ ነገሥቱ ከተሰደዱበት አገር በድል አድራጊነት ሲመለሱ፤ ሥራው እንደገና ቀጠለ:: በቅልጥፍና እንዲካሄድ ስለተደረገ በሚገባ ተጠናቆ ጥር 7 ቀን 1936 ዓ.ም. ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ::

መታሰቢያነቱ በ5ቱ የጠላት ወረራ ዓመታት ለተዋጉት አርበኞች እንዲሆን ከማድረጋቸውም ጋር ቅዳሴ ቤቱ ሲከበር የአርበኞችን አፅም አሰባስበው በታላቅ ሰልፍና በልዩ





የጸሎት ሥነ ሥርዓት በተዘጋጀለት ቦታ አስገብተዋል:: በዚህ ቀን ባደረጉት ንግግር «እጅግ ከፍ ያለው የዓለም ሁሉ ገዥ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያና ለሕዝባችን፤ ለእኛና ለአርበኞቻችን በየጊዜው ካደረገልንና ወደ ፊትም ከሚያደርግልን የችሮታ ሥራዎች አንደኛውን ዛሬ ስለፈፀመልን ልናመሰግነው ይገባናል:: ለንጉሠ ነገሥት ቤተ ዘመዳችን የእረፍት ቦታ እንዲሆን በመሠረትነው የክብር ቦታ በሥራቸውና በመስዋዕትነታቸው ውለታቸውን ልንመልስላቸው የተገባቸው አገልጋዮች ደንበኛ የርስት ተካፋይ እንዲሆኑ ፈቀድን:: የሚገባቸውን ፈፅመው ማረፋቸውን ስንመሰክርላቸው የአፅማቸው ፊት የክብር ሰላምታ እንሰጣለን» ብለዋል::

ካቴድራሉ በሚሰጠው ቀልጣፋና ዘመናዊ አገልግሎት እየተሳበ የሚመጣው ሕዝበ ክርስቲያን ቁጥር በየጊዜው እያደገ በመሔዱ ይህንኑ በአግባቡ ለማስተናገድ እንዲቻል ሦስት ጊዜ እንዲሰፋ ተደርጓል:: በመሆኑም አሁን ባለበት ደረጃ የቤተ ክርስቲያኑ ወለል ስፋት ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ 36 ሜትር ሲሆን፤ ከሰሜን ወደ ደቡብ 26 ሜትር ቁመቱም መካከሉ 35 ሜትር ነው:: ይህን ያህል ስፋት ያለው የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በመካከለኛው ክፍል የአጋዕዝተ ዓለም ሥላሴ፤ በስተቀኝ በቅድስት ድንግል ማርያም፤ በስተግራ በቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ የተሠየሙ 3 መንበሮች አሉት::

በውስጥም በውጭም ባለው ስፋት ምክንያት ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ በዓላት የሚከበሩት ብፁዓን ኤጲስ ቆጶሳት፣ ቅዱሳን ፓትርያርኮች የሚሾሙበት ለታላላቅ የሃይማኖት መሪዎችም አቀባበል የሚደረግበት ካቴድራል ነው:: ንጉሠ ነገሥቱ በወታደራዊው መንግሥት በኃይል ከሥልጣን ከወረዱና ከተገደሉ በኋላ አፅማቸው ተደብቆ ከኖረበት ቦታ ወጥቶ በክብር እንዲያርፍ የተደረገው እርሳቸው ባሠሩት በዚሁ ካቴድራል ነው::



www.ethiopianorthodox.org

## ② ምስካየ ኀዙናን መድኃኔዓለም ገዳም

የዚህ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት ታሪክ የሚነሣው ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጠላት ወረራ ዘመን በእንግሊዝ አገር በስደት ከኖሩበት ዘመን ጀምሮ ነው:: ንጉሡ በለንደን ከተማ ሳሉ በኢየሩሳሌም ይገኙ ከነበሩት ከእጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ዘንድ ልከው የመድኃኔዓለምን ጽላት በማስወሰድ አንድ መካነ ጸሎት /የጸሎት ቦታ/ መሠረቱ:: ያቺም መካነ ጸሎት በስደት ያለች ኦርቶዶክሳዊት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተብላ ትጠራ ነበር:: በ1933 ዓ.ም. ሚያዝያ 27 ቀን ግርማዊነታቸው በድል አድራጊነት ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ በስደት የነበረው የመድኃኔዓለም ታቦት ግርማዊት እቴጌ መነን ከእንግሊዝ አገር ወደ አዲስ አበባ በገቡበት ነሐሴ 23 ቀን 1933 ዓ.ም. አብሮ አዲስ አበባ ገባ:: ከዚያ በኋላ ቤተ ሳይዳ ተብሎ ይጠራ በነበረው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል ግቢ በታነፀው ቤተ ክርስቲያን ምስካየ ኀዙናን መድኃኔዓለም ተብሎ ሚያዝያ 27 ቀን 1935 ዓ.ም. ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ::

በዚህ ቤተ ክርስቲያን የሚካሄደው ጸሎት ከለንደን ጀምሮ በአማርኛ የተዘጋጀ ስለነበር የአዲስ አበባ ምእመናንን በብዛት ስቦ ነበር:: በዚህ ምክንያት ተገልጋዩ ሕዝብ እየበዛ ስለሄደ የተፈሪ መኮንንና የእቴጌ መነን ት/ቤት ተማሪዎችም እሑድ እሑድ ከዚህ ቤተ ክርስቲያን የማይለዩ ስለነበር በመጥበቡ አሁን በሚገኝበት ቦታ ላይ በ1940 ዓ.ም. ሚያዝያ 27 ቀን በግርማዊነታቸው ሌላ የመሠረት ድንጋይ ተጣለ:: አሁን በአገልግሎት ላይ የሚገኘው ምስካየ ኀዙናን መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን መሠረቱ በተጣለ በሁለት ዓመቱ ሥራው ተፈፅሞ ሚያዝያ 27 ቀን 1942 ዓ.ም. ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አገልግሎቱን በመስጠት ላይ ይገኛል::





## ③ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ቤተ ክርስቲያን

በሰሜን ምዕራብ ሸዋ ስላሌ ህገረ ስብከት የሚገኘው የደብረ ሊባኖስ ገዳም በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከኖሩት ከዐፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የታወቀ ሲሆን ቤተ ክርስቲያኑን በቀድሞ ጊዜ ዓፄ ይኩኖ አምላክና አፄ ይስሐቅ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ አፄ ዮሐንስና አፄ ምኒልክ በጥሩ ሁኔታ አሠርተውት ነበር:: ነገር ግን የተሠራበት መሬት አፈሩ የሚሸሽ በመሆኑና ሕንፃው በመስነጣጠቁ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ይህን አይተው በአዲስ እቅድ ለመሥራት እንደነገሡ የገቡትን ቃል ኪዳን በመጠበቅ ፈቃደ እግዚአብሔር ሲሞላ አሁን ያለውን መሠረተ ጽኑ ሕንፃ አሠሩ::

ግርማዊነታቸው የዚህን ሕንፃ መሠረት የጣሉት ግንቦት 24 ቀን 1952 ዓ.ም. ሲሆን ሥራው በሥራ ሚኒስቴር ተቆጣጣሪነት በሚገባ ተጠናቆ ስላለቀ ኅዳር 9 ቀን 1955 ዓ.ም. ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ:: የተለያዩ ሥራዎችን ጨምሮ የፈጀው ገንዘብ በዚያን ጊዜው ዋጋ ብር አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ሦስት ሺህ አንድ መቶ ስማኒያ አምስት ከሰላሳ ሳንቲም ነበር:: ከዚህ ሌላ ስጦታን በተመለከተ ለዚህ ገዳም:-

1. ግምታቸው ሰባ ሺህ ብር የሆነ የፋርስ ምንጣፎች ሥጋጃዎች በያይነቱ፤
2. ወርቀዘቦና ሙካሽ ሥራ ልብሰ ተክህኖ ለ7 ልዑካን የሦስት ጊዜ ቅያሪ፤
3. ልዩ ልዩ ነዋየ ቅድሳትን ንጉሠ ነገሥቱ ሰጥተዋል::

## ④ ርዕሰ አድባራት ወገዳማት አክሱም ጽዮን

አክሱም ጽዮን የኢትዮጵያ ቅድስት ከተማ ናት:: የኦሪትም ሆነ የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በዚች ከተማ በኩል ነው:: በዚህም ምክንያት ነገሥታት ሁሉ አክብረዋታል:: ህጓንና ሥርዓቷን ጠብቀውላት ኖረዋል:: ሲያያዝ በመጣው ታሪክ እንደሚገኘው በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን



www.ethiopianorthodox.org

የመጣችው ታቦተ ጽዮን በጥንቱ ዘመን በአክሱም አቅራቢያ በሚገኝ ቦታ በምኩራበ አሪት ነበረች:: ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ ግን አብርሃና አፅብሐ የመጀመሪያይቱን ቤተ ክርስቲያን አሳነፁ፣ ይህቺ ቤተክርስቲያን 12 የመቅደስ ክፍሎች እንደነበሯት ይነገራል::

በኋላ ግን በ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ካህናቶች ውስጥ እንዳሉ ዮዲት የተባለች ጨካኝ ሴት አቃጠለችው፤ ዮዲት ያቃጠለችውን አንበሳ ውድም /910 ዓ.ም/ አሰራት፤ ይህ ንጉሥ ያሠራትን በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የቅርስ ጠላት የነበረው ግራኝ መሐመድ አቃጠለው፣ ግራኝ ያቃጠለውን ዐፄ ፋሲል /1659-1624/ ዓ.ም አሰሯት:: ዐፄ ፋሲል ያሰሯት እስከ አሁን አለች:: አክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን 3 ጊዜ የመታነፅ 2 ጊዜ የመቃጠል እድል ገጥሟታል::

አሁን ያለውን ቤተ ክርስቲያን ያስሩት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ናቸው:: የመስረቱን ድንጋይ መስከረም 12 ቀን 1945 ዓ.ም አኖሩ:: በተጣለው መሠረት ላይ የሚከተለው ጽሑፍ ሰፍሮበት ነበር:: *«በአባቶቻችን ነገሥታት መዲና በአክሱም ለእመቤታችን ቅድስት ጽዮን ማርያም ይህን አዲስ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ መሠረት ጥለናል:: ይህ ቤተ ክርስቲያን እጅግ ዘመናዊ ሕንፃ እንዲሠራ ፈቅደናል ለቤተክርስቲያኑ ሥራ 1 ሚሊዮን 3 መቶ ሺህ ብር መድበናል:: የጥንቱ ሕንፃ ለጥንታውያን ነገሥታት፤ መታሰቢያነቱን እንደያዘ እንዲኖር ትተነዋል:: የበፊቱ ሴቶች እንዳይገቡበት ክልክል ነበር፤ አሁን ግን በአዲሱ ቤተ ክርስቲያን ሴቶች ገብተው እንዲገለገሉበት ፈቅደናል»* ይላል::[1]

መሠረቱ ከተጣለበት ጊዜ ጀምሮ ሥራው የሚቃናበትን፣ ኘላኑ የሚዘጋጅበትን ዘዴ ካስጠኑ በኋላ ሥራውን በቅርብ የሚከታተል ራሱን የቻለ ኮሚቴ አቋቋሙ፣ በአይነቱ ልዩ የሆነው የቤተክርስቲያኑ ሥራ ብዙ ጊዜ ስለ ወሰደ ሕንፃው ተጠናቆ የተመረቀው ጥር 29 ቀን 1957 ዓ.ም ነበር:: በዚህ የምረቃ በዓል ላይ የታላቋ ብሪታንያ ንግሥት ኤልሳቤጥ ተገኝተው ነበር::

---

[1] አዲሲቱ ኢትዮጵያ ገጽ 53::





በዐፄ ፋሲል የተሰራው የጥንቱ ቤተ ክርስቲያን እስከ አሁንም ለሴቶች የተከለከለ ነው:: [ይህ የሆነው የጥንቱን ቤተ ክርስቲያን ዮዲት ስላቃጠለችው ነው] ግርማዊነታቸው ግን አዲሱ ካቴድራል ለሴቶችም ለወንዶችም መገልገያ እንዲሆን አድርገዋል:: በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ አዲስ ለተሠራው ካቴድራል ግምቱ ስማኒያ ሺህ ብር የሆነ ልብሰ ተክህኖና ንዋየ ቅድሳት የተሰጠ ሲሆን ካህናቱም ልዩ ልዩ የማዕረግ ልብሶችን ተሸልመዋል:: በዚህ ዘመናዊ ካቴድራል ሥራ የጥንቱ የአክሱም ታላቅነት ተገልጧል:: የቤተ ክርስቲያኑ ስፋት፣ የስራው ጥብቀት፣ የእቅዱ ማማር፣ የሥጦታውም ብዛት ታላቅነቷን የሚያንፀባርቅ ነው:: በመሆኑም ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የአክሱምን ገናናነት ያደሱ ገናና ንጉሠ ነገሥት ናቸው:: የአክሱም ቤተክርስቲያን ከተመረቀች በኋላ በጥር 30 ቀን 1957 ዓ.ም የሚከተለውን ታሪካዊ ንግግር ስለአክሱም ተናግረዋል:- *«...አክሱም ሥልጣኔ የገባበት ታላቅ የኢትዮጵያ በር ናት:: የፊደላትና የቅርፃ ቅርጽ አቅድ የተገኘው በአክሱም ዘመነ መንግሥት ነው:: አክሱም የግሪክና የባቢሎን ሥልጣኔ ከኢትዮጵያ ሥልጣኔ ጋር በማቀነባበር ዕውቀትን በሰፊው የተሸመተባት ቦታ ናት:: አክሱም የሃይማኖት መዲና በመሆንዋ ያለማቋረጥ ሕገ እግዚአብሔር የተነገረባት ከተማ ናት:: አክሱም የክርስትና ፀሐይ የወጣባት የኢትዮጵያ ምሥራቅ ናት:: አክሱም በኦሪትም በሐዲስም ተከብራ የኖረች የኢትዮጵያ ነገሥታት ታላላቅ ሥራቸውን የሠሩባትና ግዳጃቸውንም የፈፀሙባት ሕያው ታሪክ ያላት ታላቅ አገር ናት...»* ብለዋል::

## ⑤ ደብረ ኃይል ቁልቢ ገብርኤል

ይህ ደብር የተመሰረተው በልዑል ራስ መኮንን ሲሆን ገባሬ ተአምራት በመሆኑ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ የውጭ ዜጎችም በብዛት እየተገኙ በዓሉን በሚገባ ሲያከብሩ ከተአምራቱ ሲሳተፉ ይታያሉ:: ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተገልጋዩ ሕዝብ በየአመቱ እየጨመረ ከመሔዱ አንፃር የቤተክርስቲያኑን ጥበት አይተው ሰፊ ቤተ ክርስቲያን እንዲሰራ አዘዙ:: በትዕዛዙ መሠረት ኘላን ተሠርቶ 8 መቶ ሕዝብ ሊይዝ በሚችል ሁኔታ በ1957 ዓ.ም በ4 መቶ 23



www.ethiopianorthodox.org

ሺህ ብር ተሰራ:: በአካባቢው ተወዳዳሪ የሌለው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ነው:: እነዚህን በመጠኑ ከታሪካቸው ጋር አብረው ቀርበዋል::

## በተለያዩ ክፍለ ሀገር ያሠሯቸው ሕብያቷ ክርስቲያናት

### በበጌምድርና ስሜን ሀገረ ስብከት

| | |
|---|---|
| አብረንታንት አባ ሳሙኤል ቤተ ክርስቲያን | በ1958 ዓ.ም |
| መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን | በ1952 ዓ.ም |
| አደባባይ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን | በ1953 ዓ.ም |
| ዋልድባ /ዳልሻህ/ ቤተ ክርስቲያን | በ1952 ዓ.ም |
| ማኅበረ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን | በ1952 ዓ.ም |
| ሳይኮ ኪዳነምሕረት ቤተ ክርስቲያን | በ1956 ዓ.ም |
| ሰቋር ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን | |

### በአዲስ አበባ

| |
|---|
| የመናገሻ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን /አሁን ምዕራብ ሸዋ |
| የጉለሌ ቅዱስ ሚካኤል /ደብረ መዊዕ/ ቤተ ክርስቲያን |
| የደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን |
| የቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ቤተ ክርስቲያን |
| ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚፀልዩበት መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን |

### በሸዋ ሀገረ ስብከት

| |
|---|
| ዜና ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን |
| የናዝሬት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን /አሁን ምስ.ሸ/ |
| የደብረ ዘይት ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን /አሁን ምስ.ሸ/ |
| የአምቦ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን /አሁን ምዕ.ሸ/ |
| ምድረ ክብድ ዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ |

### ቀድሞ የኢትዮጵያ ክፍል በነበረችው በኤርትራ

| |
|---|
| ምፅዋ ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን |
| አሥመራ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን |
| አሥመራ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን |
| መንደፈራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን |





### በሐረርጌ ሀገረ ስብከት

| |
|---|
| ሐረር አደሬ ጢቆ መካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን |
| ኤጀርሳ ጓሮ ኪዳነምሕረት ቤተ ክርስቲያን |
| ዓለማያ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን |
| ሐረር ጥምቀተ ባሕር ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን |

### በወለጋ ሀገረ ስብከት

| | |
|---|---|
| ነቀምት ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን | በ1958 ዓ.ም |
| አሶሳ ቅድስተ ማርያም ቤተ ክርስቲያን | በ1947 ዓ.ም |
| ደምቢ ደሎ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን | በ1949 ዓ.ም |

### በወሎ ሀገረ ስብከት

| |
|---|
| ደብረ ቤቴል ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን |
| አሰብ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን |

### በትግራይ ሀገረ ስብከት

| |
|---|
| ደብር ዓባይ አባ ሣሙኤል ቤተ ክርስቲያን |

ከእነዚህም ሌላ ሙሉ እድሳት ያስደረጉላቸው በቆርቆሮ ያስ ከደኗቸው፣ ደብር ያደረጓቸው የገደሟቸው አብያተ ክርስቲ ያናት በጣም ብዙ ናቸው::

## ክፍል ሁለት

## ስምንተኛው የሥነ ጽሑፍ ዘመን ቅዱሳት መጻሕፍትን በማሳተም የንጉሠ ነገሥቱ ባለውለታነት

የህዬ ገብረ መስቀል ዘመን ባለፈው እንደተመለከት ነው ቅዱስ ያሬድ የተነሳበት ዘመን ነበር በዚያ ላይ ተስአቱ ቅዱሳን ከስብከተ ወንጌል አገልግለታቸው በተጨማሪ ሥነ ጽሑፍን እንዳስፋፉ ተመልክተናል:: ይህ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው የሥነ ጽሑፍ ዘመን ነበር፤ በመቀ ጠል በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ስንደርስ ደግሞ ንጉሥ



www.ethiopianorthodox.org

አምደ ጽዮን ለሥነ ጽሑፍ መስፋፋት ከፍ ያለ ትኩረት ሰጥቶ ነበር በዚህም የተለያዩ የሊቃውንት መጻሕፍትን ወደ ግዕዝ ሲያስተረጉም በአገር ውስጥ ደግሞ ብዙ መጻሕ ፍት ተደርሰዋል ይህ ሁለተኛው የሥነ ጽሑፍ ዘመን ነበር፤ ወደ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ስንመጣ ደግሞ ሥነ ጽሑፍን በሚገባ ያስፋፋና ያጠናከረው የመምህሩን የአባ ጊዮርጊስን ፈለግ በመከተል በድርሰቱ ሙያ ላይ ራሱ የተሰማራው ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ነበር፤ ይህ የሥነ ጽሑፍ ዘመን ሦስተኛው ሲሆን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን የሥነ ጽሑፍ የበላይነትን እንድትይዝ የተደረገበት ዘመን ነው:: በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በጎንደር ውስጥ ከነገሡ ነገሥታት ውስጥ ዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ሥነ ጽሑፍን በተመለከተ ትልቅ ትኩረት ሰጥቷል፤ ከሌሎች የሥነ ጽሑፍ ዘመን ትንሽ ለየት የሚያደርገው ለመጻሕፍት መምህራን ልዩ እንክብካቤ ያደርግ እንደነበር ተመልክተናል ዘመኑም አራተኛው የሥነ ጽሑፍ ዘመን መሆኑን አይተናል::

የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት አምስተኛውና የመጨረሻው የሥነ ጽሑፍ ዘመን ነው ማለት ይቻላል:: ንጉሠ ነገሥቱ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እድገት ካደረጉት አያሌ ጥረት አንዱ ቅዱሳት መጻሕፍትን፡ በቁም ጽሕፈት በብራና እንዲጻፍ፤ ማተሚያ ቤተ በማቋቋም ቅዱሳት መጻሕፍት በግዕዝና በአማርኛ እየታተሙ እንዲቀርቡ ያደረጉት ታላቅ ተግባር ነው:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅድመ ክርስትና የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ድህረ ክርስትናም የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት፤ እንዲሁም የሊቃውንት ድርሰቶች ባለቤት መሆንዋ የሚታወቅ ነው:: ቅዱሳት መጻሕፍቱ በመጀመሪያ ከተጻፉበት ቋንቋ የተተረጎሙትና የተጻፉት በጊዜው የህዝቡ ሁሉ መግባቢያና ብሔራዊ ቋንቋ በነበረው በግዕዝ ነበር::

ከጊዜ በኋላ ግን የአማርኛ ቋንቋ እያደገ በመምጣቱ የሕዝቡ መግባቢያና ብሔራዊ ቋንቋ በመሆኑ ግእዝ በቤተ ክርስቲያንና በሊቃውንት ዘንድ ብቻ እንጂ በሕዝቡ ዘንድ የማይታወቅ ሆነ:: በዚህም ምክንያት ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ





ኃይለ ሥላሴ ገና አልጋ ወራሽ ከነበሩበት ጊዜ አንስተው ለዚህ ለቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም ጽሕፈትና ሕትመት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ከንጉሠ ነገሥት ሥራቸው ጋር አመራር እየሰጡ ቅዱሳት መጻሕፍት ከግዕዝ ወደ አማርኛ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች እንዲተረጎሙና እንዲጻፉ እንዲታተሙ አድርገዋል:: ይኸውም በመጀመሪያ በ1910 ዓ.ም በቤተ መንግሥታቸው የመጻሕፍት ማደራጃ ክፍል አቋቋሙ በዚህ ክፍል:-

- ቀለም የሚያሹ፤
- ብራና የሚያወጡ፤
- የቁም ጽሕፈት፤
- የሐረግና የሥዕል ባለሙያዎች፤
- ከግዕዝ ወደ አማርኛ የሚተረጉሙ የትርጓሜ ሊቃውንትን፤

አሰባስበው ቅዱሳት መጻሕፍት በብራና በግዕዝና በአማርኛ እየተጻፉ ለየገዳማቱና አድባራቱ እንዲሰጡ፤ በቤተ መዘክርም እንዲገኙ አድርገዋል:: በዚህም ታላቅና መንፈሳዊ ተግባራቸው ታላቁን ክርስቲያን ንጉሥ ቆስጠንጢኖስን መስለውታል:: ቆስጠንጢኖስ የማተሚያ መሣሪያ ባልተሰራበት ጊዜ የነበረ በመሆኑ ቅዱስ ወንጌል ለአብያተ ክርስቲያናት እንዲዳረስ በአደረገው የአሠራር ስልት ሃምሳ ያህል አርባዕቱ ወንጌል አስጽፎ ለአብያተ ክርስቲያናት እንዲዳረስ አድርጎ ነበር:: [አውሳብዮስ]

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴም በአንድ በኩል መጻሕፍት ከግዕዝ ወደ አማርኛ እየተረጎሙ በብዛት እንዲጻፍና የግዕዝ ቋንቋ የማያውቁ ኢትዮጵያውያን በአማርኛ ለማንበብ እንዲችሉ አብያተ ክርስቲያናትም በግዕዝና በአማርኛ በተጻፉ መጻሕፍት እንዲገለገሉ በሌላ በኩልም የቀለም ማሸት፤ የብራና ማውጣት፤ የቁም ጽሕፈት፤ የሐረግና የሥዕል ሙያ፤ እንዲጠናከር ያደረጉት ታሪካዊ ጥረት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሲጠቀስ የሚኖርና የማይዘነጋ ነው:: በአንድ አንድ ጥንታውያን ታላላቅ አድባራትና ገዳማት ካልሆነ በቀር በየአድባራቱና ገዳማቱ የማይገኙ መጻሕፍት በመጀመሪያ ከያሉበት እየተፈለጉ በግዕዝ ተጽፈው እንዲገኙ አድርገዋል::



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ግዜ ከገዳማቱ እየተጻፉ ከመጡት መጻሕፍት ለአብነት ያህል መጥቀስ ቢያስፈልግ:-

1. መጽሐፈ ሐዊ ከጣና ደሴት፤

2. አንድምታ ትርጉም ነው::

፸

በዚህ ሁኔታ እየተዘጋጁ ከተጻፉ በኋላ ቅድሚያ እየ ተሰጣቸው መታተም የሚገባቸው መጻሕፍት በቅደም ተከ ተል ታትመዋል:: ሌሎች ደግሞ በግእዝና በአማርኛ በብራና እየተጻፉ ሐረግ እየተጣለባቸው ሥዕል እየተሳለባቸው፤ እየ ተጠረዙ፤ እየታፈፉና እየተደጎሱ፤ በታላላቅ ገዳማትና አድባ ራት አገልግሎት እንዲሰጡና በቤተ መጻሕፍት መወዘክርም እንዲቀመጡ የተደረጉ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንዲሁም ልዩ ልዩ ገድለ ቅዱሳን የቁጥርና የታሪክ መጻሕ ፍት እጅግ ብዙዎች ናቸው:: ንጉሠ ነገሥቱ በዚህ ሁኔታ ሊቃውንቱን ካሰባሰቡና ከአቀራረቡ በኋላ እርስ በርሳቸው እንዲተዋወቁ ካደረጉና የቁም ጽሕፈቱንና የትርጉሙን ሥራ ከአጠናከሩ በኋላ የሕትመት መኪና በገንዘባቸው በመግዛ ትና ማተሚያ ቤት በማቋቋም ቅዱሳት መጻሕፍትን የማሳ ተም ሥራን ጀመሩ:: በመጀመሪያ በሙሉ ንባብና በአን ድምታ ትርጓሜ የታተሙ መጻፍት:-

- የዮሐንስ አፈወርቅ ድርሳንና ተግሳፅ፤
- ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም፤
- አሥራ አራቱ መጻሕፍተ ቅዳሴ፤
- አምስቱ መጻሕፍተ ሰሎሞን፤
- ኪዳንና ትምህርተ ህቡዓት፤
- አረጋዊ መንፈሳዊ፤
- አርባዕቱ ወንጌል፤
- መጽሐፈ ሲራክ፤
- ፊልክስዮስ፤





በነጠላ ትርጉም፤ የታተሙ መጻሕፍት ደግሞ:

- ተአምረ ማርያምና ማር ይስሐቅ
- አስራ አራቱ መጻሕፍት ቅዳሴ፤
- የተለያዩ የጸሎት መጻሕፍት፤
- መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ፤
- ፍትሐ ነገሥት፤
- ዳዊት፤ የመሳሰሉት ናቸው::

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የብሉይና የሐ ዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉም በግዕዝና በአማርኛ ተጽፈው መገኘት ያለባቸው መሆኑን በማሰብ የኢትዮጲያ ቤተ ክርስ ቲያን የምትቀበላቸውን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ያካተተ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በነጠላ ትርጉም በቁም ጽሕፈት እንዲጻፍ አደረጉ:: ይኸው ሥራ በ1924 ዓ.ም ጀምሮ በ1927 ዓ.ም ሊጠናቀቅ ችሏል:: በነጠላ ትርጉምና የቁም ጽሕፈት ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ለህትመት ሳይቀርብ የኢጣልያ ፋሽስት መንግሥት አገራችንን ስለወረራት የህት መቱ ሥራ ለጊዜው ዘግይቶ ነበር::

በኋላ ግን ግርማዊነታቸው በስደት እንዳሉ ዝግጅቱ በሙሉ ስለደረሳቸው «ባክስተን» በተባለ የክርስቲያን ማኅ በር አማካኝነት በእንግሊዝ አገር በፎቶ አፍሴት እንዲታተም አድርገውት ታትሟል:: ወደ ኢትዮጵያም ገብቶ በአድባ ራቱና ገዳማቱ እንዲሁም በግለሰቦች እጅ ሁሉ ይገኛል:: ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት ወደ አገራ ቸው ከተመለሱ በኋላ ቀደም ሲል የተጀመረው የቅዱሳት መጻሕፍት ህትመት እንዲቀጥል ይልቁንም ከግዕዝ ወደ አማርኛ ያስተረጎሙት የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን መጻ ሕፍት ከእናቱ ከእብራይስጥ ከግሪኩ መጻሕፍት /ቴክስት/ አንዳንድ የቃል ልዩነት አለ ስለተባለ አንድ የሊቃውንት ጉባኤ አቋቋሙ:: በዚህም ጉባኤ 7 ኢትዮጵያውያን ሊቃው ንት 3 የውጭ አገር ሊቃውንት ይገኙባቸው ነበር:: ይህ ዝግጅት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸውን የብ



www.ethiopianorthodox.org

ሉይ ኪዳን መጻሕፍት ያካተተ ሲሆን በ1947 ዓ.ም በብርሃ ንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታትሞ ወጥቶ በሥራ ላይ ውሏል።

የግርማዊ ቀዳማዊ ህዜ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግ ሥት የቅዱሳት መጻሕፍት ኅትመት ሥራ እጅግ ተጠናክሮ የታየበትና የቤተ ክርስተያናችን የትርጓሜና የዜማ ትምህ ርት መጻሕፍት በብዛት ተታተሙበት የሊቃውንቱም የመማ ርና የማስተማር የሥራ ክብደት የተቃለለበት ነው። ሊቃው ንት በየደረጃቸው በትርጉምና በቁመ ጽሕፈት ለመሥራት በአንድ ላይ መሰባሰባቸው እርስ በርሳቸው እንዲተዋወቁ ዕው ቀትም እንዲለዋወጡ ምሥጢራተ መጻሕፍትንም በስፋት እንዲገልጡ ረድቷል። ይህም የንጉሠ ነገሥቱ የቁም ጽሕፈት ሥራን የማቋቋምና የቅዱሳት መጻሕፍት ህትመትን የማፋጠን ሒደት ጥንታዊ ቅርስን ለማበርከትና ጠብቆ ለማቆየት እጅግ ረድቷል። ይኸውም፡-

1. የቁም ጽሕፈት ሥራ በራሱ የመንፈሳዊ ተግባረ እድ ቅርስ ስለሆነ ይህም፡-
   - የቀለም ማሸት፤
   - የብራና ማውጣት፤
   - ብራና ደምጦ ብዕር ቀርጾ የመጻፍ፤
   - የጥራዝ፣ የድጎሳና የቶታን ማስገባት ሥራዎች እንዳይረሱና እንዳይጠፉ እየተሰራባቸው እንዲስፋፉና በቅርስነትም እየተ ጠበቁ እንዲቆዩ አድርጓል።
2. ቀደም ሲል ተፅፈው በአንዳንድ ታላላቅ ገዳማትና አድባራት ካልሆነ በቀር በሁሉም የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የማይገኙ መጻሕፍት ከሚገኙት እየተፈለጉና እየተጻፉ በአብያተ ክርስቲያናትና በቤተ መዘክር እንዲገኙ በመደረጉ ቀደም ያሉት በቅርስነት እንዲጠበቁ አዳዲሶች አገልግሎት እንዲሰጥባቸውና እየቆዩም በቅርስነት እንዲ ጠበቁ ሆነዋል።
3. የቅዱሳት መጻሕፍት ኅትመትም ለቅርስ አጠባበቅ የሚያበረክተው ድርሻ ከፍተኛ ነው። ይኸውም ቅዱሳት መጻሕፍት በግዕዝና በአማ ርኛ እየታተሙ ሲወጡ አብያተ ክርስቲያናት እነዚህን የታተሙ መጻሕፍት በቀላሉ አያገኙ በመገልገል የነበሯቸውን የብራና መጻሕ ፍት በቅርስነት ጠብቆ ለማቆየት በከፍተኛ ሁኔታ ጠቅሟል።

እነዚህ ሁሉ ግርማዊ ቀዳማዊ ሀዜ ኃይለ ሥላሴ ለኢ ትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ተልዕኮ መሟላት፣ ለኢ ትዮጵያውያን መንፈሳዊና ማኅበራዊ እድገት ምን ያህል





ይጥሩ እንደነበር ያስረዳሉ። ይህ የቅዱሳት መጻሕፍትን የት ርጉም፤ የቁም ጽሕፈትና የህትመት ሥራን አጠናክሮ ቅዱ ሳት መጻሕፍትን የማበርከት ጉዳይ ንጉሠ ነገሥቱ ለኢትዮ ጵያ ቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ እድገት ካደረጓቸው በርካታ ዐበይት ተግባራት አንዱ ክፍል በመሆኑ ዘመኑ የመጨረሻ ውና 5ኛው ወርቃማ የሥነ ጽሑፍ ዘመን ነው። ትውልዱም ይህን ሊያውቀውና ሊረዳው ይገባል። በዘመኑ የነበሩት ሊቃውንት ብዙውን ህሳባቸውን በሥነ ጽሑፍ ከመግለጣቸ ውም በላይ ንጉሠ ነገሥቱም የድርሰት ሙያ እንዲስፋፋ ያበረታቱ ነበር። ይህ የሥነ ጽሑፍ ዘመን፡-

- ✞ ባሕላዊውን ሳይለቅ ከዘመናዊ የተዋሀደበት፤
- ✞ ለቅዱሳት መጻሕፍት የበለጠ ትኩረት የተሰጠበት፤
- ✞ ዘመናውያን ሊቃውንት ህሳባቸውን በጽሑፍ የገለጡበት፤
- ✞ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የድርሰት ሙያን ያስፋፉበት፤
- ✞ ተረስተው የነበሩ የብራና ጽሑፎች ወደ አማርኛ የተተረ ጐሙበት የሥነ ጽሑፍ ዘመን ነው።

# ክፍል ሦስት

## መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች መስፋፋትና ስብከተ ወንጌል መጠናከር

### መንፈሳዊ ትምህርት ቤት

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት መንፈሳዊ ትምህርት ቤት አድርጋ ትጠቀምባቸው የነበሩት ጥንታው ያን ገዳማት ናቸው እነ አባ ጊዮርጊስን ያፈራው ሐይቅ እስ ጢፋኖስ ደብረ ደብረዳሞ፣ ደብረ ሊባኖስ፣ ዲማ ጊዮርጊስ፣ ደብረ አልያስ...፤ ዋና ምስክር ናቸው። እነዚህ የመሳሰሉ ገዳማት ብዙ ብሔራዊያን ሊቃውንት የወጡባቸው ሲሆን፤ በውስጣቸውም የሚሰጡት ትምህርቶች በርካታ መሆናቸውን ለማወቅ «ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት» የሚለውን መጽ



www.ethiopianorthodox.org

ሐፍ መመልከት ይጠቅማል::[2] የትምህርት ሚኒስቴር እስከ ተቋቋመበት ጊዜ ድረስ የኢትዮጵያን ትምህርት ትመራ የነበረችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ናት። ከላይ የጠቀስናቸው ገዳማት መንፈሳዊ ትምህርት ብቻ ሳይሆን ፍፁም ኢትዮጵያዊ ባሕልንም ጨምረው ነበር ያስተምሩ የነበሩት፤ ተማሪዎችም በአገር ፍቅር ስሜት የተቃጠሉ ኢትዮጵያዊነትን በእጅጉ እንዲጠብቁ ጭምር በትምህርቱ ውስጥ ይጠቃለል ነበር:: የሆነው ሆኖ ስለዚህ ገዳማት ባለፈው ክፍል ተመልክተናቸዋል::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘመናዊ ትምህርት ቤት የቋቋመችው በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ነው:: በወቅቱ የነበረው መንፈሳዊ ጉባኤ [አሁን ቤተ ክህነት] ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ለቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ እንዲሆን የተፈቀደደው መሬት ከጎጃምና ከጎንደር በስተቀር ከሌሎች ጠቅላይ ግዛቶች የሚሰበሰበው የትምህርት ታክስ ለመንፈሳዊ ትምህርት ማስፋፋት እንዲውል ግንቦት 25 ቀን 1941 ዓ.ም በቁጥር 2ሺ 158/8 በተጻፈ ደብዳቤ ለገንዘብ ሚኒስቴር ትዕዛዝ ስጥተዋል:: ከዚህ ገቢ ከመቶ ሃያው እጅ እየተነሳ ለብቻው ተቀምጦ ግርማዊነታቸው ለመንፈሳዊ ጉዳይ የሚያዙበት እንዲሆን ተደርጓል::

የትምህርት ታክስ በቀጥታ ለመንግስት በሚከፍሉት በጎጃምና በጎንደር ለሚገኙት የታላላቅ አድባራትና ገዳማት የዜማ፣ የቅኔ፣ የትርጓሜ መጻሕፍት መምህራን ከትምህርት ሚኒስቴር በጀት ደመወዝ እንዲከፈላቸው አድርገው ነበር:: ንጉሠ ነገሥቱ ለመንፈሳዊ ትምህርት እድገት ባላቸው ጽኑ ፍላጎት እንደዘመናዊ ትምህርት ደረጃ አግኝቶ ከንባብ ቤት እስከ ትርጓሜ መጻሕፍት ድረስ በሰባት ክፍል ተከፍሎ እንዲሰጥ አድርገዋል:: ይኸውም ደረጃ:-

[2] በሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም የተዘጋጀ::





1. የሊቃውንት መጻሕፍት ትርጓሜ ት/ቤት፤
2. የብሉያት መጻሕፍት ትርጓሜ ት/ቤት፤
3. የሐዲሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ት/ቤት፤
4. የመጽሐፈ መነኮሳት ትርጓሜ ት/ቤት
5. የንባብና የጽሕፈት ት/ቤት፤
6. የዜማ ት/ቤት፤
7. የቅኔ ት/ቤት፤ ነው::

## የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ

ይህ ከፍተኛ የትምህርት ማዕከል አሁን ወዳለበት ቦታ ከመዛወሩና ደረጃውም ወደ ኮሌጅነት ከፍ ከማለቱ በፊት ትምህርቱ የተጀመረው በገነተ ልዑል ቤተ መንግስት ውስጥ ነበር:: ግርማዊነታቸው በጠላት ወረራ ምክንያት ከተሰደዱበት እንደተመለሱ እውቀት በበለጠ እንዲስፋፋ በተለይም ካህናት በህዝቡ ዘንድ ተሰሚነት ስላላቸው እነሱ እውቀታቸውን ሲያሻሽሉ ለሕዝብ የተሻለ አገልግሎት ይሰጣል ብለው በማስብ ትምህርት ቤት እስኪዘጋጅ ድረስ ቤተ መንግሥታቸውን ትምህርት ቤት አድርገው በቶሎ ደርሰው አገርንና ቤተ ክርስቲያንን በበለጠ ያገለግላሉ ተብለው የተገመቱትን ሊቃውንት ሰብስበው መምህር መድበው የእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲማሩ አድርገዋል:: የቋንቋውን ትምህርት ጀምረው እስከ መጨረሻው ከተከታተሉት ሊቃውንት መምህር መልዕክቱ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የተባሉት የኢትዮጵያ ሁለተኛ ፓትርያርክ ነበሩበት::

ከተወሰነ ጊዜ በኋላም በጀት ፈቅደው የውስጥና የውጭ አገር መምህራን እንዲቀጠሩ አድርገው አሁን መንፈሳዊ ኮሌጅ እየተባለ የሚጠራውን የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በመክፈት በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት የተጀመረው ትምህርት እንዲቀጥል አደረጉ:: በዚህ ግዜ ትምህርት ቤቱ በሁለት የተከፈለ ነበር:: አንደኛው የቀሳውስት ክፍል ሲሆን አስቀድመው ለቀሰሱና ከፍተኛ የሆነ ትምርህት ለሚፈልጉ የተከፈተ የሦስት ዓመት ጥናት የሚደረግበት ነበር:: ሁለተኛው የዲያቆናት ክፍል ሲሆን ከአሁኑ አን



www.ethiopianorthodox.org

ደኛ ደረጃ ትምህርት ጋር የሚመሳሰል ስምንት ዓመት የሚፈጅ ነበር:: በተጨማሪም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ዶግማ፣ ቴዎሎጂ፣ ዜና አበውና ዜማም እንዲማሩ ይደረግ ነበር::

ይህ ት/ቤት በ1945 ዓ.ም. ወደ ሁለተኛ ደረጃ፤ በ1953 ዓ.ም. ወደ ኮሌጅ ደረጃ በማደግና በዚሁም ዓመት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ አካል በመሆን ከተመሠረተበት ከ1935 ዓ.ም. እስከ 1970 ዓ.ም. ድረስ በቆየባቸው ጊዜያት በርካታ አገልግሎት ከሰጠ በኋላ በወቅቱ የነበረው ወታደራዊ መንግሥት እንደ ሌሎች የቤተ ክርስቲያኗን ንብረት ይህንንም ወርሶ መንፈሳዊ ትምህርት እንዳይሰጥበት ተደርጐ ነበር:: በ1987 ዓ.ም. እንደገና ተከፍቶ ሥራውን በመቀጠል ደቀመዛሙርትን በዲግሪና በዲኘሎማ እያስመረቀ ወጣት ምሁራንን በማበርከት ላይ ይገኛል:: ንጉሠ ነገሥቱ ለዚህ ኮሌጅ የነደፉት ዓላማ እንደገና ተግባራዊ መሆን ጀምሯል:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ ካሏት ተቋማት ከሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤትና መቀሌ ካለው ከሣቴ ብርሃን ከፍተኛ መንፈሳዊ ኮሌጅ ቀዳሚ እንደመሆኑ መጠን ወርኃዊ መጽሔት፣ ወርኃዊ ጋዜጣ፣ በውስጡ የምርምር ክፍል ተመስርቶ በበለጠ ሕይወት የሚያገኝበትን መንገድ ማመቻቸት ይገባል:: ኮሌጁ በአሁኑ ጊዜ ወደ ዩኒቨርሲቲ ለማደግ በመራመድ ላይ ይገኛል::

## የቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የቅድስት ሥላሴን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት እንደከፈቱ ሁሉ ግርማዊት እቴጌ መነንም የሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስን ት/ቤት በ1935 ዓ.ም. በራሳቸው መሬት ላይ ከፈቱ:: የዚህ ትምህርት ቤት መከፈት ዋና ዓላማው በጠላት ወረራ ወቅት ጉዳት የደረሰባቸውን ወጣቶች ሰብስቦ ለመርዳት ሲሆን የመጨረሻ ግቡ ግን እነሱንም ሆነ ሌላውን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት





ለማሰልጠን ነበር:: በዚሁ ዓላማ መሠረት ብዙ የቤተ ክርስቲያን አልጋዮችን በበቂ መንፈሳዊ ዕውቀት እያሰለጠነ በማውጣት ለቤተ ክርስቲያኒቱ ታላቅ ድጋፍ ሆኗል::

የትምህርት ቤቱ ደረጃ ለብዙ ጊዜ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ሆኖ ከቆየ በኋላ ከ1950 ዓ.ም. ጀምሮ ሙሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመሆን ወጣቶች እንደሌላው የመንግሥት ትምህርት ቤት ሁሉ ትምህርታቸውን አጠናቀው ለ2ኛ ደረጃ መግቢያ ፈተና እየቀረቡ በሚገባ ስላለፉ ወደ ቅድስት ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እየተዛወሩ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ስለተደረገ መንፈሳዊ ኮሌጅ ሌላ መጋቢ ትምህርት ቤት አገኘ::

ትምህርት ቤቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ከዘመናዊ ትምህርት ጐን ለጐን ብሉያት ሐዲሳት ሲሰጡበት የኖረ ነው:: አሁንም እውቅ የብሉይና የሐዲስ መምህራን ስላሉበት በስብከተ ወንጌል የበሰሉ ምሩቃንን እያስመረቀ ያወጣል:: ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ሰዋሰው ብርሃን ትምህርት ቤት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴና ግርማዊት እቴጌ መነን በቀየሱትና በተመኙት ዓላማ፣ በኋላም ቤተ ክርስቲያኒቱ በአዲስ መልክ እንዲደራጅ ባደረገችው ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ደረጃ አገልግሎቱን በማበርከት ላይ ይገኛል::

## ስብከተ ወንጌል መጠናከር

ከጥንት ጀምሮ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓብይ ተግባር ሆኖ የኖረው የወንጌል ትምህርት እያደር በተጠናከረ ሁኔታ እየተስፋፋ የመጣው በተለይም በዘመናዊ አቀራረብ ስልትና ዘዴ መስጠት የተጀመረው በግርማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ነው:: ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ዘመናዊና መንፈሳዊ ትምህርት ተቀናጅቶ የሚሰጥባቸው ትምህርት ቤቶችን በማቋቋማቸው ከእነዚህ እየተመረቁ የሚወጡት ሰባክያን ለዚሁ ተግባር መመደብ በመቻላቸው ነው::



www.ethiopianorthodox.org

ሰባክያን እየበዙ ሲሄዱ የሚሰጡት የወንጌል ትምህርት በዐፀደ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ተወስኖ እንዳይቀር ሠራተኛው ሕዝበ ክርስቲያንም በያለበት ሆኖ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት እንዲችል በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ ከሃምሳዎቹ ዓመታት አጋማሽ ጀምሮ የወንጌል ትምህርት በኢትዮጵያ ሬድዮ ጣቢያ መስጠት ተጀመረ። ይህም የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች በቋሳሳቅ በዓላት ከሚሰጡት ቡራኬና ቃለ ምዕዳን ሌላ ነው። በመርሐ ግብሩ መሰረት ዘወትር ጧት ለ15 ደቂቃ ዕለቱን፣ ወቅቱን የተመለከተ ጸሎትና ትምህርተ ወንጌል ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን ሲተላለፍ፤ በዐቢይ ጾምና በጾመ ፍልሰታ ግን ጧት ብቻ ሳይሆን ማታም ይኸው ትምህርት ይተላለፍ ነበር።

ከስብከቱም ጋር ያሬዳዊ ዜማ ይተላለፍበት ነበር። ይህ ኘሮግራም ይመራ የነበረው በጠቅላይ ቤተ ክህነት የስብከተ ወንጌል መምሪያ አማካይነት ነበር። ለማንኛውም መንፈሳዊ ሥራ ቅድሚያ የሚሰጡት ንጉሠ ነገሥቱ የኢትዮጵያ ሬድዮ ጣቢያ በተቋቋመበት ጊዜ ምግበ ነፍስ በቃለ እግዚአብሐር በጸሎት እንዲከፈት ማድረጋቸው ታሪክ ዘግቦ ይገኛል።

የብሥራተ ወንጌል ሬድዮ ጣቢያም የካቲት 19 ቀን 1955 ዓ.ም ሲቋቋም እንደዚሁ በጸሎት እንዲከፈት አድርገዋል። ምንም እንኳ ጣቢያው በሌላ የእምነት ድርጅት የተቋቋመ ቢሆንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም እንድታስተምርበት ንጉሠ ነገሥቱ ስለፈቀዱ በየዕለቱ የ30 ደቂቃ ኘሮግራም ተሰጥቷት በወታደራዊው መንግሥት እስከ ተዘጋበት ጊዜ ድረስ ሰፊ ትምህርት አቅርባበት እንደነበር መረጃዎች ያስረዳሉ።

ለዚህ ኘሮግራም ሰባክያንን ቀጥሮ ሥራውን በኃላፊነት ይመራ የነበረው ከግርማዊነታቸው ልዩ ካቢኔ በጀት ተመድቦለት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሥር የተቋቋመው ሐዋርያዊ ድርጅት ነበር። በዚህ ድርጅት የድርሰትና የማስታወቂያ ክፍል የሚዘጋጀው ትምህርት ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን፣ ሃይማኖትን፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክና ሌሎችንም ተዛማጅ የትምህርት ርዕሶች ያካተተ ሲሆን የስርጭቱም ሰዓት በየቀኑ ከአዲስ አበባ ውጭ ላለው ሕዝብ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ከዓርባ ደቂቃ እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት ከሃምሳ አምስት ደቂቃ ድረስ ሲሆን ለአዲስ አበባ ሕዝብ ደግሞ ከምሽቱ ሦስት ከሩብ እስከ ምሽቱ ሦስት ሰዓት ተኩል ነበር።





የሐዋርያዊ ድርጅትና የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሰባክያነ ወንጌል ከመደበኛው ሥራቸው በተጨማሪ በሥራ ቀናት ጧት ጧት በየትምህርት ቤቱ እየተገኙ የወጣቱን ሞራል የሚገነባ ለማኅበራዊና መንፈሳዊ ሕይወቱ መመሪያ የሚሆን ትምህርት ይሰጡ ነበር። በወንጌል ትምህርት የሕዝቡ ሞራል እንዲታነፅ እምነቱ እንዲጠነክርና ለአገሩ ታማኝ ዜጋ እንዲሆን ንጉሠ ነገሥቱ በወንጌል መስፋፋት በኩል ትልቅ ትኩረት አድርገዋል። ይህን ዘመን ወደ ኋላ መለስ ብለን በአይነ ህሊናችን ስንቃኘው የቤተ ክርስቲያናችን የወንጌል ስርጭት እድገት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ መሆኑን ነው። ወታደራዊው መንግሥት በአጭሩ ቀጨው እንጂ በዚህ ሁኔታ ቀጥሎ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችን ብቃት ያላቸውን ሰባክያነ ወንጌል በገፍ ታመርት ነበር።

# ክፍል አራት

## የውጭ ግንኙነትን ማሳደግ

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በውስጥም በውጭም በስፋት ተደራጅታ ትምህርተ ወንጌል እንድታዳርስና ምእመናንን እንድታበዛ ከፍተኛ አላማ እንደነበራቸው በተደጋጋሚ ተመለክተናል። ይህንም ዓላማቸውን ከግቡ ለማድረስ፡-

- ⇨ በአፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ፤
- ⇨ በአውሮፓና በአሜሪካ፤
- ⇨ በካሪቢያን ደሴቶች፤



www.ethiopianorthodox.org

ስለ ኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን መቋቋም ያልተቆጠበ ጥረት አድርገዋል። ግርማዊነታቸው ከ1928 እስከ 1933 ዓ.ም በባት ኢንግላንድ በስደት በቆዩበት ወቅት ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ሌሎችም ተከታዮቻው የሚጸልዩበት ቤተ ጸሎት እንዲዘጋጅ አድርገው ነበር። ዘወትር የሚጸልዩና ምስ ጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚፈፅሙ 5 መነኮሳት ካህናትም ነበሯቸው። የተሟሉ ንዋያቷ ቅድሳትም ተዘጋጅተው ተወስ ደው ነበር። ይህም ድርጊት የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በእንግሊዝ አገር ለማቋቋም⁄መሠረት ሆኖ ቆይቷል። ንጉሠ ነገሥቱ ከድል በኋላ በ1933 ዓ.ም በጎረቤት አገር ሱዳን ካርቱም የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን እንድትቋቋም መመሪ ያና ትእዛዝ ከመስጠታቸው ጋር ለሕንፃው ማሰሪያ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ለግሰዋል።

ከ1945 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1959 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በኒውዮርክ በካሪቢያን ደሴቶች ማለት በትሪኒዳድ፣ በቶቤጎ፣ በባርቤዶስ፣ በጊያና፣ በጃማይካና በቬርሙዳ፣ በበርጂን፣ አይላንድስ፣ በሴንት ቶማስና፣ በሴንት ኪትስ ደሴቶች ከአሥር ያላነሱ አብያተ ክርስቲያናት በግርማዊነታቸው ፈቃድና ትዕዛዝ አቋቁመ ዋል። በእነዚህ ደሴቶች ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መቋ ቋም መነሻ ምክንያት የሆኑት የራሳቸው ተወላጆች ነበሩ። ከጥቁር ሕዝብ አገሮች ሁሉ ነፃ ሕዝብና ነፃ ቤተ ክርስቲያን ያሏት ነፃ ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ስለሆነች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን እምነት ለመከተል ስለፈለጉ ነው። በተለይም የትሪንዳድና የቶቤጐ መንግሥታት በአገራቸው ለምትቋቋመው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ግንባታ ሰላሳ ሄክታር መሬት ሰጥተዋል።

በ1965 ዓ.ም በሎንደን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ህዶ ቤተ ክርስቲያን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም በግርማ ዊነታቸው ፈቃድና ትዕዛዝ ተመሰረተች ዛሬም ይህቺ ቤተ ክርስቲያን በሎንደን ለሚኖሩ የኢትዮጵያ ምእመናንና እም ነቷን ለሚከተሉ ሌሎች ሕዝቦችም ሐዋርያዊ ተልእኮ በመስ ጠት ትገኛለች። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስ





ቲያን በዓለም ያለች እንደመሆንዋ መጠን ስለሌላው ዓለም ማወቅ ማየትና መስማት ስለራስዋም ለሌላው ማሳወቅ የተራ ድኦ የሰላም ግንኙነትና የመሪዎች የጉብኝት ልውውጥ ማድ ረግ እንደሚገባ ግርማዊነታቸው አርቆ በማሰብ የውጭ ግን ኙነትዋ እንዲጠናከር አድርገዋል። እንዲህ አይነት ግንኙነት አዲስ ሳይሆን ንግሥተ ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም ሔዳ ከንጉሥ ሰሎሞን ጋር ከመገናኘትዋ ጋር ተመሳሳይ ነው። በዚሁ መሠረት:-

1. በ1961 ዓ.ም የሮማንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓት ርያርክ ጁስቲንያን ግርማዊነታቸው ባደረጉላቸው ጥሪ መሠረት የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ጎብኝተዋል። ከዚያ በፊት ግን ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በ1956 ዓ.ም የሮማንያን ቤተ ክርስቲያን ጎብኝተዋል። ያን ጊዜም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲጎበኙላቸው ግርማዊነታቸውን ስለ ጠየቁ ጥቅምት 25 ቀን 1961 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ ቴዎፍ ሎስ የቅዱስ ፓትርያርኩ እንደራሴ የሮማንያን ቤተ ክርስቲያን እንዲጎበኙና ስለ ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት እንዲወያዩ ማድረጋቸው፤
2. በጥር 1958 ዓ.ም የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ፔሜን በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፈቃድ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ኢትዮጵያን ጎብኝተዋል። ስለሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት መግለጫ ወጥቶ በመሪ ዎች ተፈርሟል።
3. በ1956 ዓ.ም የመላው አፍሪቃ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ሲመሰረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መስራች አባል እንድትሆን መፍቀዳቸው፤
4. በ1963 ዓ.ም በግርማዊነታቸው ፈቃድ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ማዕከላዊ ኮሚቴ አራተኛ ስብሰባን አስተናግዳለች።
5. በ1940 ዓ.ም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ተሳትፋለች።



www.ethiopianorthodox.org

## የአምስቱ እህት አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ /ስብሰባ/ በአዲስ አበባ መስተናድ

*«የሃይማኖት ጋሻ ብቸኛ ኦርቶዶክሳዊ ንጉሠ ነገሥት»*
*[ማር አግናጢዮስ ያዕቆብ የአንፆኪያ ሶርያ ፓትርያርክ]*

በ431 ዓ.ም በኤፌሶን ከተደረገው ጉባኤ ወዲህ መጀመሪያ የሆነውን ኦሬንቲያል ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አብያተ ክርስቲያን የቅዱሳን ፓትርያርኮች ጉባኤ አዘጋጅና አስተናጋጅ በመሆን ከፍተኛ የውጭ ግንኙነት ተልዕኮ ፈፅማለች:: ይህ ታሪካዊ ጉባኤ በአዲስ አበባ እንዲደረግ በእግዚአብሔር ኃይል ቀስቃሽነትና አነሳሽነት በክርስቲያናዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ነበሩ:: ለዚሁ ጉባኤ በኦሬንቲያል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ አንድ ምዕራፍ ተከፍቶለት የግርማዊነታቸው ስም እንደ ቆስጠንጢኖስ ሲዘከር ይኖራል::

## የጉባኤው መስተንግዶ ቅድመ ዝግጅት

ይህ ጉባኤ በአዲስ አበባ ኢትዮጵያ እንዲስተናገድ ምክንያት የሆኑ ነገሮች የታሪክ ፍንጭ እንደሚገልፁት አንዳንድ እህት አብያተ ክርስቲያናት ሊቃነ ጳጳሳት በሃይማኖት ስብሰባ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መልዕክተኞችን ሲያገኙም ሆነ በልዩ ልዩ ምክንያት በቅድስት አገር ኢትዮጵያ ሲያልፉ የተዋህዶ ኦርቶዶክሶችን መሰብሰብ እንደሚያስፈልግ ለግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በጣም ያሳስቡ እንደነበር ይገልጣል::

ይህን ከግምት በማስገባት ንጉሡ ነገሥቱ የኘሮግራም ኮሚቴ፣ የጽሕፈት ቤት ኮሚቴ፣ የአስተናጋጅ ኮሚቴ በመሰየም ከእነዚህ ኮሚቴዎች መካከል የመጀመሪያው በሐረር ሊቀ ጳጳስና የፓትርያርኩ እንደራሴ በሆኑት በብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የሚመራ ነበር:: የጉባኤው መጀመሪያ ቀን ከቀጠሮ ወደ ቀጠሮ ይተላለፍ ጀመር:: የመጀመሪያው ቀጠሮ ለጥር ወር 1954 ዓ.ም ነበር:: ነገር ግን ይህን ጥሪ የግርማዊት እቴጌ መነን ዕረፍት ሰርዘው:: ሁለተኛው ጥሪ ለመስቀል 1956 ዓ.ም /እ.ኤ.አ/ መስከረም 25 እስከ ጥቅምት 1 ቀን 1964 ዓ.ም ነበር:: ነገር ግን በዚህም ግዜ የአጸኪያው ፓትርያርክ ሚመተ ጵጵስና ሊሰጡ ወደ አንድ ቦታ የሚሔዱበት ጊዜ ነበርና ተላለፈ:: ሦስተኛው ቀጠሮ ደግሞ ለመስከረም ወር 1957 ዓ.ም /እ.ኤ.አ መስከረም 11-21 ቀን 1965 ዓ.ም/ እንዲሆን ተወሰነ:: በዚህ ግዜ ደግሞ ቀዳማዊ ሀዬ ኃይለ ሥላሴ የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች በኦፌሲዬል ይጎበኙ ስለነበር ተላለፈ:: ስለዚህም አራተኛና የመጨረሻው ቀጠሮ ተደረገ ይኸውም ጥር 3 እስከ 15 ቀን 1957 ዓ.ም /እ.ኤ.አ ደግሞ ጥር 11 እስከ 21 ቀን 1965 ዓ.ም ነበር::/

ከዚህ በኋላ የጉባኤው ተሳታፊዎች ፓትርያርኮች ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ አግናጥዮስ ሣልሳይ የአንጾኪያ ፓትርያርክ፤ ብፁዕ ወቅዱስ ባስኪን ቀዳማዊ የመላው አርመን ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ካቶሊኮስ፤ ብፁዕ ወቅዱስ ኮሬን ቀዳማዊ የታላቂቷ ቤተ ኪልቂያ ካቶሊኮስ፤ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ አውገን ቀዳማዊ የምስራቅ ካቶሊኮስ /ሕንድ/ ከእነ ተከታዮቻቸው በጊዜ ቀጠሮአቸው አዲስ አበባ ገቡ:: ሲገቡም ሀዬ ኃይለ ሥላሴ በብፁዕ ወቅዱስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሥም ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስና ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣኖች ዓለም አቀፍ አውሮኘላን ጣቢያ ድረስ ሔደው ተቀብለዋቸዋል:: የእስክንድርያው ፓትርያርክ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ የቀቡ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ 6ኛ አዲስ አበባ የገቡት ስብሰባው በተጀመረ ማግስት ነው::

በዚሁ አጋጣሚ እዚህ ላይ ሳልገልፅ የማላልፈው እስከዚህ ግዜ ድረስ ኢትዮጵያን ከጎበኙ ወይም ደግሞ ካዩ የእስክንድርያ ፓትርያርኮች መካከል አቡነ ቄርሎስ 6ኛ አራተኛው አባት ናቸው:: የመጀመሪያው በይምርሐነ ክርስቶስ ዘመነ መንግሥት /በ1077-1117 ዓ.ም/ የአባይ ወንዝ የግብፅ እስላሞችን ለመጉዳት ተገድቦ ነበር:: በወቅቱ የእስክንድርያ ፓትርያርክ የነበሩት አቡነ ሚካኤል 4ኛ በ1092 ዓ.ም /68ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ መሆናቸው ነው /ለመሸምገል ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ነበር:: የመጡበት ዋና



www.ethiopianorthodox.org

አላማ የአባይ መገደብ እስላሞች ብቻ ሳይሆኑ ክርስቲያን ወንድሞቻችሁ ጭምር በውሀ ጥም ስለሚያልቁ ውሀውን ልቀቁልን ብለው ንጉሠ ነገሥቱን ማለት ቅ/ይምርሐነ ክርስቶስንና ሕዝቡን ተማፅነው እንዲለቀቅ አድርገዋል። ፓትርያርክ ሚካኤል ወደዚህ ሽምግልና እንዲመጡ የገፋፏቸው የግብፅ ሱልጣኖች ሳይሆኑ አይቀርም። [የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ታሪክ ገፅ 35]

ሁለተኛው ደግሞ ዐፄ ቴዎድሮስ በነገሡ በ5ኛው ዓመት በ1852 ዓ.ም 110ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስ 4ተኛ መጥተዋል። የመጡበት ምክንያት:- ከኢትዮጵያ ወደ እስክንድርያ የሚሔዱ ኢትዮጵያውያን አገራችን እዩልን እያሉ በየጊዜው ስለሚነግሯቸው፤ ሀፄ ቴዎድሮስ ከቱርኮች ጋር ተጣልተው ስለነበር ለማስታረቅ፤ በተጨማሪ ካይሮ ያለውን የቅ/ማርቆስን ቤተ ክርስቲያን ለማደስ አስበው ስለነበር እርዳታ ለመጠየቅ መጥተዋል። ታሪክ ባቆየን መሰረት እኚህ ፓትርያርክ የመታሰር እድል ገጥሟቸዋል። የታሰሩበት መክንያት ከላይ እንደገለጥነው ከመጡበት አንዱ ምክንያት ዐፄ ቴዎድሮስን ከቱርኮች ጋር ለማስታረቅ ነው። ዐፄ ቴዎድሮስ ኢየሩሳሌም በቱርክ እስላሞች ተይዛ ስለነበር እነሱን ለማስለቀቅ ከፈተኛ የሆነ ስሜት ነበራቸው ከዚህ የተነሳ ኢትዮጲያን ከበው ከነበሩ ቱርኮች ጋር በየጊዜው ይጣሉ ነበር። ይህን የፓትርያርኩን የሽምግልና ጥያቄ ሲቀርብላቸው በመናደድ «እርስዎ የሃይማኖት አባቴ ሆነው እንዴት ከቱርክ እስላም ጋር የእርቅ ጥያቄ ያቀርባሉ» በማለት ፓትርያርኩ ከእነሱ ጋር ቢወግኑ ነው በማለት ማረፊያ ቤት እንዲገቡ ተደረገ። በኋላ ሊቃውንቱና ሕዝቡ ይህ የአገራችንና የቤተ ክርስቲያናችንን ክብር የሚነካ ስለሆነ ይፈቱ በማለት አስፈትተው የጠየቁት ገንዘብ ተሰጥቷቸው ወደ ግብፅ በሰላም ሊመለሱ ችለዋል። [የኢ.ኦ. ተ.ቤ.ክ ታሪክ ገፅ 66]

ሦስተኛው ደግሞ 113ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ዮሐንስ 19ኛ በ1922 ዓ.ም መጥተው ነው። እዚህ በመጡበት ወቅት በ1921 ዓ.ም 5 አባቶች ለጵጵስና ተመርጠው 4ቱ ግብጽ ሔደው ሲሾሙ 5ኛው እጨጌ ገ/መንፈስ ቅዱስ በጤና መጓደል ምክንያት ቀርተው ስለነበር ለእርሳቸው ማዕረገ ጵጵስና ሰጥተው አቡነ ሳዊሮስ ተብለዋል። [የፓትርያርክነቱ መንበር እንዴት ተገኘ? ገጽ 22]





አራተኛው ደግሞ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በነገሱበት ዘመነ መንግስት ቄርሎስ 6ኛ የተባሉት መጥተዋል። የመጡበት ምክንያት ከላይ በርዕሱ እንደተጠቀሰው በ1957 ዓ.ም ለ5ቱ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ነው። እኚህ ፓትርያርክ ለመጀመሪያው የአገራችን ፓትርያርክ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኙትርክና ማዕርግ የሰጡ ናቸው።

ከዚህ በኋላ አሁን በመንበረ ማርቆስ ላይ የተቀመጡ 117ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ 3ኛ መጥተዋል። መረጃዎች እንደሚጠቁሙን በግርማዊ ቀዳማዊ ሀፄ ኃይለ ሥላሴ ጋባዥነት በ1965 ዓ.ም በመስከረም ወር ውስጥ ለሚከበረው የደመራና የመስቀል በዓልን ምክንያት በማድረግ በክብር ጠርተዋቸዋል። በተጨማሪ በ2ሺ ዓ.ም ከሚያዝያ 3-5 ከቤተ ክርስቲያናችን በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት በይፋ ጐብኝተዋታል። ኢትዮጵያን ካዩ የእስክንድርያ ፓትርያርኮች መካከል ሁለት ጊዜ የመጡት አቡነ ሺኖዳ ብቻ ናቸው።

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ 3ኛ ጉብኝት የሚያስገነዝበን ነገር ቢኖር ከአቡነ ቄርሎስ 6ኛ በፊት የመጡ ፓትርያርኮች እነሱ በአባትነት እኛ በልጅነት ደረጃ ነበር ጉብኝቱ፤ አሁን ግን በእኩልነት ማለት በእህት አብያተ ክርስቲያናት ደረጃ ነው የተቀበልናቸው። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የራሷ ፓትርያርክ ነበራትና።

ወደ ስብሰባው እንመለስና ስብሰባው ጥር 15 ቀን 1957 ዓ.ም ከጠዋቱ በአራት ሰዓት በአፍሪካ አዳራሽ ተከፈተ። ሲከፈትም ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ከአልጋ ወራሻቸው ጋር እንዲሁም ብፁአን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ቅዱሳን



www.ethiopianorthodox.org

ፓትርያርኮች፣ ሚኒስትሮች፣ ኮር ዲፕሎማቲኮች የእነኚሁ አብያተ ክርስቲያናት መልዕክተኞችና የውጭ የልዩ ልዩ እምነት ወኪሎች የአገር ውስጥ ጋዜጠኞች በተመልካችነት ነበሩ:: በአከፋፈቱ ሥነ ሥርዓት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ አግ ናጥዮስ ሣልሳይ ቡራኬ በኋላ የንጉሠ ነገሥቱ የመክፈቻ ንግግር ተሰምቷል:: እንዲሁም ፓትርያርኮቹ በሱራስት፣ በአርመንኛ፣ በእንግሊዝኛ በአማርኛ የተሰጡ መልሶች ተደምጠዋል::

በዚህ ታላቅ ጉባኤ ሁለት ፓትርያርኮች፣ ሦስት ካቶ ሊኮሶች፣ አንድ የፓትርያርክ እንደራሴ አቡነ ቴዎፍሎስ ማለት ነው፣ ከአምስት ልዩ ልዩ ነገድ የሆኑ ከአምስት አህ ጉር የመጡ አራት ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ነገር ግን በአንዲት ተዋህዶ ሃይማኖት የሚያምኑ 35 ተከታዮቻቸው የአሉበት ይህ ስብሰባ የአ10 ቀናት ጉባኤ ተካሒዷል:: ይህ ጉባኤ ባካሔዳቸው ስብሰባዎች 6 ትልልቅ አርዕስት በአፅን ኦት አጥንቷቸዋል::

እነዚህም:-

1. ቤተ ክርስቲያንና ዘመናዊ ዓለም፤
   - ⇨ ስለወጣቶች፤
   - ⇨ የሰውን ልጅ ከቤተ ክርስቲያን ሕይወት ጋር ስለ ማዋሐድ፤
   - ⇨ የቤተ ክርስቲያን ሕይወትና ስለ ቤተሰብ ኑሮ፤
   - ⇨ የክርስትና ትምህርት፤
   - ⇨ የምንኩስና ኑሮ፤
   - ⇨ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፤
   - ⇨ ስለ ቤተ ክርስቲያን ቀን አቆጣጠር ጉዳይ አጥ ንቷል::፤
2. በመንፈሳዊ ትምህርት አሰጣጥ ስለመተባበር፤
   - ⇨ የመንፈሳዊ ትምህርት ይዞታ፤
   - ⇨ የጋራ ሥርዓተ ትምህርት፤
   - ⇨ የመተባበር ዘዴዎች፤
   - ⇨ ወደ ውጭ አገር ሔዶ ስለመማር፤
   - ⇨ ስለመንፈሳዊ ትምህርት መጻሕፍት ተዘርዝረዋል::





3. በስብከተ ወንጌል ሥራ ስለመተባበር፤
   - ⇨ ስለ ሐዋርያዊ ተግባር መሠረታዊ ዓላማ፤
   - ⇨ ስለ ጸሎትና ሐዋርያዊ ሥራ፤
   - ⇨ ስለ ሐዋርያዊ ሥራ መንፈሳዊን ኑሮን ስለማጠ ንከር፤
   - ⇨ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ላሉ ስለሚደረግ ስብከተ ወንጌል፤
   - ⇨ ስለ ስብከተ ወንጌል ዘዴዎች፤
   - ⇨ ስለሰባክያን ማሰልጠን ጉዳይ ተጠንቷል::

እነዚህ መሠረታዊ ጉዳዮች የታዩ ሲሆን ሌሎችም ስለ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት፤ ስለጉባኤው ጽ/ቤት መቋቋምና ስለዓለም ሰላም ጉዳዮች ተወያይቷል:: በጽሕፈት ቤቱ በኩል ሁለት አባሎች ያሉበት አንድ ቀዋሚ ኮሚቴ አቆመ:: ሁለተኛ ጽ/ቤቱ ጊዜያዊ በሚል ቅዕል ተሰጥቶት በአዲስ አበባ እንዲሆን አደረገ:: ሦስተኛ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልካም ፈቃድ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ጽሕፈት ቤቱ ቋሚ ሆኖ ለሥራው የሚያስፈልገውን ወጭ በአባሎች አስተዋፅኦ ገንዘብ እስኪሆን ድረስ የኢትዮ ጵያ ቤተ ክርስቲያን እንድትችል ተደረገ::

በዚህ ታሪካዊ ጉባኤ የነበሩትን ፓትርያርኮች በመወ ከል ፓትርያርካዊ ንግግር ያደረጉት የአንጾኪያ ሶርያ ኦር ቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ፓትርያርክ ማር አግናጥዮስ ያዕቆብ ስለ ግርማዊ ቀዳማዊ ሀዬ ኃይለ ሥላሴ እንደሀ ብለዋል *«ግርማዊ ቀዳማዊ ሀዬ ኃይለ ሥላሴ በዚህ ታሪካዊ ጉባኤ መከፈቻ እለት የግርማዊነትዎን ንግግር ስናዳምጥ በ325 ዓ.ም በተደረገው የኒቂያ ጉባኤ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ያደረገው የጉባኤ መከፈቻ ንግግር ትዝ ይለናል:: ቤተ ክርስቲያናችን ለብዙ ዘመናት በዚህ መልክ አልተሰበሰቡም:: ነገር ግን እግዚአብሔር በአገልጋዩ በግርማዊ ቀዳማዊ ሀዬ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ አንድንሰበሰብ ፈቀደልን:: የክርስትና ሃይማኖት ጋሻ የሆኑት ቀዳማዊ ሀዬ ኃይለ ሥላሴ እኛን ለማሳሰብ ማበረታታትን ኦርቶዶክሳዊ እም ነትንና ጥበብን ባያሳዩን ኖሮ ይህ ሁሉ ሲሆን ባልቻለም ነበር:: የግርማዊ ቀዳማዊ ሀዬ ኃይለ ሥላሴ መሰረት ያለው እምነት፣*



www.ethiopianorthodox.org

እውቀትና ትህትና ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር መስጠታቸው በአንድነት እንድንሰበሰብ አነሳስቶናል፡፡ ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ አንድ ብቸኛ ኦርቶዶክሳዊ ንጉሠ ነገሥታችን ናቸው» በማለት ተናግረዋል አድንቀዋል፡፡

የማላካራ ሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ፓትርያሪክ ማር ባስልዮስም ስለ ግርማዊነታቸው ታላቅነት «ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለኦርቶዶክስ እምነት ጋሻ እንደሆኑ የሁላችንን አሳብ ምናገርበት ጊዜ እመካለሁ» ብለዋል፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ በቅዱሳን ፓትርያርኮች እንደተባለላቸው ነበሩ፡፡[3] ስለጉባኤው ታላቅነት የግብፁ ፓትርያርክ የሚከተለውን ተናግረው ነበር:- «በዚህ ጉባኤ ገና ከጥንት ጀምሮ ጌታ ኢትዮጵያን የባረካት መሆኑን ተመለከትኩ የአባይ ወንዝ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ የሰው ዘር ሕይወትን ለመስጠት ከተራሮችም ቁልቁል ይፈሳል፡፡ እንደዚሁም ከዚህ በኢትዮጵያ ተራሮች ላይ ከሆነው ጉባኤ የኦርቶዶክስን ሕዝብ ሊያጠነክር ያለ ብርሃን ሕሊና /ኢንስፕሬሽን/ ቁልቁል ይፈሳል» ብለዋል፡፡ በጉባኤው መክፈቻ ዕለት ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ያደረጉት የመክፈቻ ንግግር ከፊሉ ይህን ይመስላል፡፡

«. . .ንጉሠ ነገሥት ከሆንበት ጊዜ ጀምሮ ልንፈጽማቸው ከሚገቡን ግዴታዎች አንደኛው በእምነት አንድነት ሲኖራቸው በሀገር ርቀት የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትን ማገናኘት እንደሆነ አምነን በአምላክ እርዳታ ይህን ለመፈጸም ይህችን ዕለት ስንጠብቅና የእግዚአብሔርን ቅዱስ ፈቃድ ደጅ ስንጠና ነበር፡፡ ቀድሞውንም ከአንድ እስከ ሦስት የተደረጉ የጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች ሁሉ ጠሪዎቹ የቁስጥንጥንያ ክርስቲያናውያን ነገሥታት ነበሩ፡፡ በዚህም እኛ ለቤተ ክርስቲያን በገባነው ቃል ኪዳን ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ያገኘነው በእምነት የሚመስሉትን አብያተ ክርስቲያናት አገናኝቶ በኅብረት እንዲሠሩ ማድረግ ነበር፡፡ የገባነው ቃል ኪዳን በዛሬው ዕለት ሲፈጸም በማየታችን እድግ በጣም ደስ ብሎናል. . . በጥንት ዘመን የቤተ ክርስቲያን እምነት አንድ በነበረበት ጊዜ ሀገራችን በቢዛንታይን ነገሥታት ጋር የቅርብ ግንኙነት ነበራት፡፡ የክርስቲያን አንገርና ክርስቲያን ያልሆኑ ገዢዎች ቀንበር ተጭኖባቸው በነበረበት ጊዜም በብዙ የሚቆጠሩ የሃይማኖት ስደተኞችን አስጠግታለች. . . ወደ ሀገራችን እንኳን ደህና ገባችሁ የምንላችሁ በጣም ደስ እያለን ነው፡፡ የእናንተ መምጣት ጥንታዊ የሆነውን ቅዱስ ስሜት ይዞልን መጥቷል. . .»[4]

በወቅቱ ከተገኘው መረጃ መሠረት 5ቱን እህት አብያተ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን መጠሪያ ስማቸው፤ የመሪው መጠሪያ፤ የቤተ ክርስቲያኑ መስራች፣ የአማንያኑን ብዛት፤ የመንበረ ፓትርያርኩ ያለበት ከተማ ከዚህ በታች በሰንጠረዥ መልክ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡

| የቤተ ክርስቲያኗ መጠሪያ | የጠቅላይ መሪው መጠሪያ | የቤተ ክርስቲያኗ መስራች ቅዱስና ክርስትና የታወጀበት ዘመን | የአማንያን ብዛት | መንበረ ፓትርያርኩ ያለበት ከተማና አገር |
|---|---|---|---|---|
| የግብፅ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን | የአስክንድርያው ፓፓና የመንበረ ማርቆስ ፓትርያርክ | ቅዱስ ማርቆስ 49 ዓ.ም ገደማ | 4 ሚሊዮን | ካይሮ |
| የአንጾኪያ አርቶዶክስ ቤተክርስቲያን | የአንጾኪያና የመላ ምሥራቅ ፓትርያርክ | ቅዱስ ጴጥሮስ 37 ዓ.ም ገደማ | 5 መቶ ሺ | ደማስቆ /ሶርያ/ |
| የአርመን አርቶዶክስ ቤተክርስቲያን | ሀ/ በኤችሚያዜን የአርመኖች ጠቅላይ ካቶሊኮስ | ቅዱስ ጎርጎሪዎስ ካሣቴ ብርሃን 301 ዓ.ም ገደማ | 4 ሚሊዮን 500ሺ | ኤችሚያዜን /አርመን/ |
| | ለ/ በታላቅዋ ቤተ ኪልቅያ የአርመኖች ካቶሊኮስ | | | አንቲሊያ /ቤይሩቶ ሊባኖስ/ |

[3] ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የንጉሡን እፅም በክብር ሲያርፍ ያታተመ መጽሔት፡፡

[4] የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የውጭ ግንኙነት ትናንትና እና ዛሬ በዓለም መድረክ ገጽ 28-29





www.ethiopianorthodox.org

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የምሥራቅ የሶሪያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን /ሕንድ/ | የምሥራቅ ካቶሊኮስ | ቅዱስ ቶማስ ሐዋርያ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን | 1 ሚሊዮን 500 ሺህ | ኩታያም /ኬራላ ደቡብ ህንድ/ |
| የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲየን | የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ | ቅዱስ ፍሬምናጦስ በ430 ዓ.ም | 12 ሚሊዮን | አዲስ አበባ ኢትዮጵያ |

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያዘጋጀችውና በንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፈቃድ የተከናወነው ይህ ጉባኤ ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን ከምትቀበላቸው ከ3ቱ ጉባኤያት በተጨማሪ አራተኛው ጉባኤ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ከኤፌሶን ጉባኤ በኋላ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኙት በዚህ ግዜ ስለሆነ ነው። ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እድገትና ልማት ከፈጸሙት ተግባር ዋናውና ተራርቀው የነበሩትን እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት አቀራርበው፣ ከቤተ ክርስቲያናችን ጋር ማስተዋወቃቸው ነው።

# ክፍል አምስት

## በኢኩሙኒካል ግንኙነት ባለሙያዎች

ክርስቲያኖች የጋራ ጠላት ሲነሳባቸው የሚወያዩበት መድረክ ሕብረት ኢኩሙኒካል ይባላል። ይህ ዛሬ ሥም ይውጣለት እንጂ በየመን የሚኖሩ የናግራን ክርስቲያኖች በአየሁዳውያን ችግር ሲገጥማቸው በዘመኑ የነበረው የኢትዮጵያ ንጉሥ አፄ ካሌብ አማካኝነት ታድጓቸዋል። ይህ የኢኩሙኒካል መንፈስ ነበር።





በቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የበለጠ የውጭ ግንኙነት የዳበረበትና መሠረት የተጣለበት ነበር ማለት ይቻላል። ከዘመነ ክርስትናም በፊት በሕገ ኦሪት አምለኮተ እግዚአብሔርን በሚፈጽሙ ሕዝበ እግዚአብሔር መካከል በኢየሩሳሌም ማዕከልነት ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ይካሄድ ነበር። ይህም የንግሥተ ሳባ የኢየሩሳሌም ጉብኝት፣ በዘመነ ክርስትና ደግሞ ኢትዮጵያዊው ጃንደርባ የኦሪቱን እምነት ለመፈጸም ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ አድርጓል። እነዚህ ለውጭ ግንኙነት መሠረት ናቸው።

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ፍሬምናጦስ ወደ እስክንድርያ ሔዶ ጵጵስና መቀበሉ፣ የዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት፣ ከላይ የገለፅነው አጼ ካሌብ ወደ የመን /የናግራን ክርስቲያኖችን/ ለመታደግ መዝመት፣ በ20ኛ ክፍለ ዘመን ላይ ደግሞ መንበረ ጵጵስና በኢትዮጵያ እጅ ለማስገባት ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያደረገቻቸው ውይይቶች፣ ሁሉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አሁን ለተስፋፋው የውጭ ግንኙነት ወርቃማ ታሪኳ ነው።

ለዚህ ደግሞ በመንግሥት በኩል ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ያደረጉት ውለታ ከፍተኛ ነው። ከቤተክርስቲያን መሪዎች ደግሞ ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ያደረጉት እንቅስቃሴ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን በመላው ዓለም አስተዋውቀዋል። ጠንካራና በሳል መሪ በመሆናቸውም በተለይ የፓትርያርክነቱ መንበር ከግብፃውያን እጅ በማላቀቅ እልክ አስጨራሽ ውይይት በማካሔድ እንዲሳካ ካደረጉ መካከል ቀዳሚውን ሥፍራ ይይዛሉ።

ቤተ ክርስቲያናችን በረዥም ጊዜ ታሪኳ ውስጥ በውጭው ዓለም አምብዛም አትታወቅም። ከ1938 ዓ.ም ጀምሮ ቤተክርስቲያናችን ከምዕራቡ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር ለማስተዋወቅና ታሪካዊ ቦታዋን እንድትይዝ ለማድረግ አባ ቴዎፍሎስ ያልተቆጠበ ጥረት አድርገዋል። እንደውም አንዳንዶች ነፃይቱን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን «የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን» በማለት ሲፈርጇት ሌሎች ደግሞ በህገራ



www.ethiopianorthodox.org

ችን የሚያዩትን አሪታዊ ባሕሎች እንደ እምነት በመውሰድ «ከአሪታዊ ልምድ ያልተላቀቀች» በማለት ያለ ስሟ ስም ይሠጧት ነበር።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ወደ ኢኮሙኒካል መድረክ ብቅ ካሉበት በ1938 ዓ.ም ጀምሮ በነበራቸው ተሰሚነት ትክክለኛ ገጽታዋን በመግለጽ የተሳሳተ አመለካከታቸውን እንዲያርሙ አድርገዋቸዋል። በውጭ ያሉትም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ለዘመናት ያካበተቻቸውን የሥነ ጽሑፍ፣ ኪነ ጠበብ፣ የሥነ መለኮት ማዕከላት ወደር የሌላቸውን የሀገራችንን የትምህርት ሚኒስቴርነቱን ቦታ ይዘው የነበሩ ገዳማትና አድባራት፣ የቅኔና የዜማ ማዕከላትን እንዲጐበኙ በማድረግና መሠረታዊ እምነቷን በማስረዳት በይበልጥ እንዲገነዘቡ አድርገዋል።

ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምሥረታ ጀምሮ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ስለነበሩ አባላቱን በየጊዜው እየጋበዙ የእምነቷ መገለጫ የሆኑትን ታላላቅ በዓላትን ማለትም ልደትን፣ ጥምቀትን፣ ትንሣኤን፣ እና ደመራ /መስቀል/ ሕዝበ ክርስቲያኑ እንዴት እንደሚያከብሯቸው እንዲመለከቱ ይጋብዙዋቸው ነበር። በ1950ዎቹ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ የነበሩትን ዶ/ር ብሌክን በጥምቀት በዓል ጋብዘዋቸው ስለነበር ከዋዜማው ጀምሮ የተመለከቱትን እንዲህ በማለት አድንቀዋል «ቅዱሳት መጻሕፍትን አዘውትሬ አነባለሁ ነገር ግን በዚህ ቦታ ተገኝቼ የተመለከትኩት ሥርዓትና ትርጉም ተገንዝቤው አላውቅም። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለመላው ዓለም ክርስቲያኖች የምታስተምረው ብዙ እሴት እንዳለ ለመገንዘብ ችያለሁ። ይህ ሠፊና ጥልቅ ትርጉም ያለው የአምልኮተ እግዚአብሔር መገለጫ የሆነው ባሕላችንም ስለሆነ አጥብቀን ልንይዘው የገባል» ሲሉ ገለፀዋል።





# አስደናቂው የአቡነ ቴዎፍሎስ ንግግር ለግብፃውያን

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በሌላው ዓለም ያደረጓቸው ጉዞዎች የሌላውን ዓለም ቤተ ክርስቲን ጠንቅቀው የመመልከት እድል ስለገጠማቸው በውጭ ግንኙነትም በሳል ስለሆኑ ይህን አምቅ ኃይላቸውን ቤተ ክርስቲያናችን የፓትርክናውን መንበር እጇ ለማስገባት ባደረገቻቸው ታላላቅ ወሳኝ ውይይቶች ላይ ግብጻውያነ አስኪገረሙ ድረስ የሚከተለውን ተናግረዋል።

*«ቅዱስ ማርቆስ የሁላችን አባት ነው እስክንድርያም የሁላችን እናት ናት፤ ከዚህ መሠረታዊ እምነት ተነስተን ነው እኛ ኢትዮጵያውያን «ማርቆስ አባቱ እስክንድርያ እናቱ» የምንለው። በመሠረቱ ቅዱስ ማርቆስ ግብፃዊ አልነበረም። ወደ እስክንድርያ የሔደውም ስደተኛ ወገኖቹን እስራኤላውያንን ለማስተማር ነበር። እስክንድርያም ቢሆን ከግብፃዊነቷ ግሪካዊነቷ ያመዝንባታል፤ የፍልስፍና መዲና በመሆን እውቅና ያገኘችው በግሪኮች ነው የሠየሟትም ግሪኮች ናቸው። ይህም ይታወቅ ዘንድ ዛሬ ግሪኮች በእስክንድርያ ፓትርያርክ አላቸው። ይህም ግሪካዊነቷን ይጠቁማል ፤...የአንድ አባትና እናት ልጆች የወላጆቻቸውን ንብረት እኩል የመካፈል መብት በህግ የተጠበቀ ነው፤ ...የክርስትና ዜና ወደ ኢትዮጵያ የደረሠው ግብፅ ከመድረሡ በፊት ነው... ለእባ ሰላማ የጵጵስና ማዕርግ ክህነት የሠጠው ቅዱስ አትናቴዎስም ቢሆን እስክንድርያ ውስጥ መኖሩን እንጂ የትውልድ ሀገሩ ሮማ ይሁን ግሪካዊ፤ ወይም ኮፕት አልያም ደግሞ አይሁዳዊ በውል አይታወቅም። የግብፅ ፓፓ የግብፅና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ አባት ይሁን ከተባለ ምርጫው በዘር ላይ የተመሠረተ መሆን የለበትም ብላ የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ታምናለች... በእናንተ በኩል ይህ ፈፅሞ የማይሞከር መሆኑን ደጋግማችሁ ትናገራላችሁ፤ ሁላችንም እንደምንገነዘበው በአንድ ነገር ላይ ሁለት እውነታ ሊኖር አይችልም ስለዚህ ያለን አማራጭ አንድ ብቻ ነው። ይሕም*



www.ethiopianorthodox.org

*አንደኛው በእኛ በኩል የተነሣውን ቅን አመለካከት በተግባር መተርጐም እና ሁላችንም በየበኩላችን የየራሳችን ፓትርያርኮች መምረጥ የምንችል መሆኑን በፀጋ መቀበል አለብን»*

ይህን የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ቃል የሰሙ ግብፃውያን በአዳራሹ የነበረ ሰው ሁሉ አይኑን ተክሎ ቅዱስነታቸውን ይመለከት ነበር። በዚህ ጊዜ የደነገጡ ግብፃውያን የሚመልሱት ስላጡ «ያሻይ ሰአት» ደርሷል በሚል ሰበብ አደራሹን ለቀው ወጡ። ራሳቸው ግብፃውያን ጳጳሳት «የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታላቅ ሰው አፍርታለች» በማለት መስክረውላቸዋል። /ተኮናኙ ኮናኝ ገጽ 57-59/።

ከቅዱስ አባታችን አቡነ ቴዎፍሎስ አነጋገር እንደ ምንረዳው የውጭ ግንኙነታቸውና የሌሎችን አብያተ ክርስቲያናት የአስተዳደር መዋቅር መመልከታቸውና መጐብኘታቸው ቤተክርስቲያናችን ከግብፅ ጋር ላለው አለመግባባት መፍትሔ እንዳመጣላቸው ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በወቅቱ ታካሂደው ለነበረ የውጭ ግንኙነት የንጉሠ ነገሥቱ ድጋፍ አልተለያትም። ዛሬም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ የውጭ ግንኙነቷን አስፋፍታለች። የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን አርማ ባነሳው የመንፈስ ልጃቸው አማካኝነት ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችን ወደ ዓለማቀፍ መድረክ ብቅ በማለት ተገቢውን ቦታ ይዛ ተገኝታለች።[5]

[5] አምስተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ «የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ኘሬዝዳንተ» ሆነው ሲመረጡ ከቢአኤ ጋዜጠኞች ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ላይ ይህ እድል አሥር ጊዜ ለአቡነ ቴዎፍሎስ ይገባ ነበር። ከመሠረቱ ጀምሮ የደከሙት እሳቸው ሲሆኑ ዛሬ ለእኔ መፈፀሙ ክብሩም ለቤተክርስቲያን ነው በማለት ተናግረዋል።





# ክፍል ስድስት

## የፓትርክና መንበር መገኘት

ቀዳማዊ ሀዬ ኃይለሥላሴ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያላትን ግንኙነት ሳታቋርጥ በዘዴና በጥበብ ለ1600 ዓመታት ያህል በአስክንድርያ ተፅእኖ ስር የወደቀችውን ቤተ ክርስቲያናችንን ራሷን ችላ የምትንዝበትን መንገድ ገና በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት እንደራሴ ሆነው ግብፅን ሲጐበኙ መሠረት ጥለውበት ነበር። ይህንንም ራሳቸው በጻፉት የሕይወት ታሪካቸው ላይ እንዲህ ብለዋል።

«...ፓትርያርኩ አቡነ ቄርሎስ ስለ እኛ ክብር ማርቆስ ቤተክርስቲያን ቅዳሴና ጸሎት ለማድረግ ማሰባቸውን አስታወቀውን ነበርና ወደ ቤተክርስቲያን ሄድን፣ ፓትርያርኩም የሽምግልና ድካማቸውን ታግሠው በመንበሩ አጠገብ በዙፋናቸው ተቀመጠው ጸሎት ቡራኬ አደረጉልን... እኛ የሃይማኖት አባትነታቸውን ለማክበር የወርቅ አክሊልና የወርቅ መስቀል፣ የወርቅ መቋሚያ፣ በወርቅ የተጠለፈ ግምጃ ቀሚስና ካባ ላንቃ አምጥተንላቸው ነበርና... አክሊሉን ደፍተው ካባ ላንቃውን ለብሠው የወርቅ መስቀሉን በቀኝ እጃቸው የወርቅ መቋሚያ በግራ እጃቸው ይዘው በማየታችን ደስ አለን»[6]

ይህ ጉብኝት ቀዳማዊ ሀዬ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከተወላጆቿ መካከል የራሷ ጳጳስ እንዲኖራት ለማድረግ መሠረት የጣሉበት ነበር። ይህም በተግባር በ1921 ዓ.ም ግንቦት 25 ቀን አምስት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በአቡነ ዮሐንስ 19ኛ ተሾሙ እንደገና በየጊዜው ውይዳት እየተደረገ በድጋሚ ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም አምስት ኢትዮጵያውያን አባቶች በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ እጅ ተቀብተው ተሾሙ። ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን

[6] ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ ገጽ 66-67።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ፍላጐቷ በጊዜው ባይሟላለትም በንጉሥ ነገሥቱ ጥረት የራሷ የሆነ ሊቀ ጳጳስ እንዲኖራትና ይህ ሊቀ ጳጳስ በፓትርያር ክነት ማእርግ ከፍ እንዲል ከፍተኛ የሆነና እልክ አስጨራሽ ውይይት ከእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ጋር ተደርጓል::

በዚህ መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜ ጥር 6 ቀን 1943 ዓ.ም የመጨረሻው ግብፃዊ የኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ ሥላሪፉ በአቡነ ዮሳብ ከተሾሙት ከ5ቱ ጳጳሳት መካከል አቡነ ባስል ዮስ ስለተመረጡ ወደ ካይሮ ሄደው በአቡነ ዮሳብ እጅ የሊቀ ጵጵስናው ስያሜ ጸድቆላቸው ተሾመዋል:: ከዚህ በኋላ ነው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ወደ ወሳኝ ምዕራፍ የተሸጋ ገረችው:: ይኸውም ኢትዮጵያዊውን ሊቀጳጳስ በፓትርያርክ ነት ማዕርግ ከፍ ለማድረግ ከእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ጋር ወሳኝ የሆኑ ውይይቶችን አድርጋለች:: በዚህ መሠረት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የራሷን ፓትርያርክ ለማግኘት ችላለች::

የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ፈቃደኝነቷን ስትገልጥ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ይህን ታላቅ የምስራች ስላገኙ ግብፅን ለመጐብኘት ፈቃደኛ በመሆን ካይሮ ገቡ:: ንጉሠ ነገሥቱ ካይሮ ሲሄዱ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ ወሳኝ መዕራፍ ላይ ያደረሠ ታሪካዊ ጉብኝት ነበር:: ሰኔ 21 ቀን 1951 ዓ.ም የኢትዮጵያዊው የብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሢመተ ፕትርክና ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በተገኙበት በአቡነ ቄርሎስ 6ኛ እጅ በግብፅ ምድር ተከናወነ::

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይህን ማዕርግ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እንድትጐናጸፍ የ31 ዓመት ዲፕሎማሲያዊ ጥረት አድርገዋል:: ይህንንም እዚያው ካይሮ እያሉ የሢመተ በዓሉ ዕለት ገልፀዋል *«በአፍሪካ መካከል የክርስቲያን ደሴት ሆና የኖረች የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የሚገባትን ትልቅነትና ክብር እን ድታገኝ በዘመናችን ደከመንበታል፤ ድካማችንን ባርኮ ይህን ፍሬ እንዲያፈራ ሳደረገልንና ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ለኢትዮጵያ የተገኘበ ትን ይህን ቀን ለማየት ሳበቃን ለልዑል እግዚአብሔር መስጋናችንን እናቀርባለን...»* በማለት ገለፀዋል::





ከአቡነ ባስልዮስ እረፍት በኋላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በታሪኳ የተለየ ክብር አግኝታለች:: ይኸውም ከእስክንደርያ ቤተክርስቲያን ጋር በተደረጉት ውይይት ሁሉ አብረው በመሆን ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረጉት አቡነ ቴዎ ፍሎስ ሁለተኛው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ መሆናቸው ነው:: ይህ የእሳቸው ፓትርያርክ ሆኖ መሾም ልዩ ያደረገው በኢትዮጵያ ምድርና በኢትዮጵያውያን እጅ ግንቦት 1 ቀን 1963 ዓ.ም መሾማቸው ነው:: ይህም የመጀ መሪያው አባት ያደረጋቸዋል:: በአጠቃላይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እድለኛ ንጉሠ ነገሥታት ናቸው:: በቅዱስ ሐርቤይ እና በአፄ ዮሐንስ 4ኛ ይህ ጉዳይ ቢሞከርም ፍፃሜ ያገኘው በቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሥለሆነ እድለኛ ያስኛቸዋል::[7] በአጠቃላይ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚከተለውን አበርክተዋል::

1. ለብዙ ጊዜ በአገር ርቀት ተለያይተው የኖሩትን የምሥ ራቅ አብያተ ክርስቲያናት (Orantal Church) መሪዎች ኢትዮጵያ ላይ አገናኝችው ያልታሰበ ኅብረት ፈጥረዋል:: ይህ በአሁኑ ክፍለ ዘመን ከአንድ የፓለቲካ መሪ የማይ ጠበቅ ከፍተኛ ሐዋርያዊ ተልእኮ በመሆኑ አድራጎቱ ለቤተ ክርስቲያን ኃይልና በረከት ሆኖ ሁልጊዜ ሲታሰብ ይኖራል::
2. በወራሪ ስጋት ጥንታውያን ቅርሶቹዋን ሁሉ ደብቃ ትኖር የነበረችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በጸሎት ቤት በኩል ዝቅተኝነት እንዳይሰማት በማሰብ የሰሎሞንን ቤተ መቅደስ የሚያስታውስ ዘመናዊ ቤተ እግዚአብሔር አሠርተው አበርክተዋል:: ይኸውም የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ነው::
3. የሃይማኖት መጻሕፍት በብዛት እንዲታተሙ በመፍቀዳ ቸው ቤተ ክርስቲያን ብራና ዳምጣ፣ ብዕር ቀርፃ ለአንድ

[7] የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያው ፓትርያርክ ስመርስኤጎዘን ወልደቂርቆስ 1951 ዓ.ም እና የፓትርያርክነቱ መንበር እንዴት ተገኘ በዲያቆን ስሎሞን 2000 ዓ.ም ዮሐንስ የተጻፉትን ይመለከቷል::



www.ethiopianorthodox.org

መጻሕፍት ዓመትና ከዚያም በላይ ከመድከም ዘመናዊ የሕትመት መሣሪያ በማስመጣት የተቀላጠፈ ሥራ እንድትሠራ አድርገዋታል፡፡

4 ለ1ሺ 600 ዓመታት ያህል በባዕድ ሥልጣን ሥር ወድቃ የኖረችውን ቤተ ክርስቲያን የ31 ዓመታት ዲፕሎማሲያዊ ትግላቸው ለማዕርገ ፓትርያርክነት አብቅተዋታል፡፡

5 በጠላት ኃይል የተደመሰሰ፣ የፈረሱ፣ የጠፋ አብያተ ክርስቲያናትን አሳድሰዋል፡፡

# ዘጠነኛው ወርቃማ ዘመን?

**ተፈጸመ**





# ዋቤ መጻሕፍት


- ሀብተ ማርያም ወርቅነህ /ሊቀ ሥልጣናት/፤ *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት* 1963 ዓ.ም ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ፡፡
- ሉሌ መልአኩ፤ *የቤተ ክርስቲያን ታሪክ* ለ3ኛ ጊዜ ተሻሽሎ የታተመ 1989 ዓ.ም ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት አዲስ አበባ
- ሐዲስ የሻነው /ዶክተር/፤ *ፍንጭ ፍተሻ* 1998 ዓ.ም አዲስ አበባ፡፡
- መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ /ብላታ/፤ *ሔሮዱቱስ 1ኛ መጽሐፍ* /ትርጉም/ ጥቅምት 23 ቀን 1948 ዓ.ም አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ፡፡
- መሪ ራስ ኤ.ኤም በላይ፤ *ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ትንሣኤ ታሪክ* 1983 ዓ.ም ቦሌ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ፡፡
- መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት፤ *የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የውጭ ግንኙነት ትናንትና ዛሬ በዓለም መድረክ* 1987 ዓ.ም አዲስ አበባ፡፡
- *መጽሐፈ አርጋኖን፤* ዘአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ 1959 ዓ.ም አዲስ አበባ፡፡
- *መለከት መጽሔት፤* 1ኛ ዓመት ቁጥር 1፡፡
- መንግሥቱ ለማ፤ *መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ፣* 1959 ዓ.ም ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ፡፡
- ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል /ባላምባራስ/፤ *ዝክረ ነገር፤* 1962 ዓ.ም አዲስ አበባ፡፡
- ምክረ ሥላሴ ገ/አማኑኤል /ቀሲስ ዶክተር/፤ *የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ በምድር ላይ* /ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ/ 1ኛ መጽሐፍ፣ 2000 ዓ.ም አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ፡፡
- ___________፤ *በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግእዝ ቋንቋ፣* 2000 ዓ.ም ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ፡፡
- ሰሎሞን ዮሐንስ /ዲያቆን/፤ *የፓትርያርክነቱ መንበር እንዴት ተገኘ፣* 2000 ዓ.ም ካሉ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ፡፡
- ___________፤ *ቅዱሳት መካናት በኢየሩሳሌም፤* 2000 ዓ.ም
- ስርግው ሐብለ ሥላሴ /ዶክተር/፤ *አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት* ቁጥር 1 እና 2፣ 1969 ዓ.ም አዲስ አበባ፡፡
- ___________፤ *አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት* ቁጥር 6 እና 12፣ 1981 ዓ.ም አዲስ አበባ፡፡




www.ethiopianorthodox.org

- __________፤ *አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት* ቁጥር 10 እና 12 1982 ዓ.ም አዲስ አበባ።
- __________፤ *አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት* ቁጥር 7 አዲስ አበባ።
- __________፤ *ማኅደረ መዝገብ ዘኢትዮጵያ፣* ቁጥር 1 1986 ዓ.ም አዲስ አበባ።
- __________፤ *ሕይወት በቤተ ክርስቲያን፣* ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ቤተ መጻሕፍት የሚገኝ የታይፕ ጽሑፍ፣ 1987 ዓ.ም አዲስ አበባ።
- ብርሃነ መስቀል ደስታ /ደጃዝማች/፤ *ዜና ላልይበላ፣* 1951 ዓ.ም ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
- በላይ ግደይ፤ *የኢትዮጵያ ሥልጣኔ* 1981 ዓ.ም፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
- __________፤ *ገንዘብ ባንክ መድኀን በኢትዮጵያ፣* 1983 ዓ.ም ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
- *ትንሣኤ መጽሔት*፤ ሐምሌ 1972 ቁጥር 34።
- __________፤ 1972 ዓ.ም ቁጥር 28።
- __________፤ ኅዳር 1972 ዓ.ም ቁጥር 74።
- __________፤ መስከረም 1976 ዓ.ም ቁጥር 72።
- __________፤ ጥቅምት 1979 ዓ.ም ቁጥር 107።
- __________፤ ኅዳርና ታኅሣሥ 1982 ዓ.ም ቁጥር 139።
- __________፤ ጥርና የካቲት 1982 ዓ.ም ቁጥር 140።
- ኅሩይ ወልደ ሥላሴ /ብላቴን ጌታ/፤ *የታሪክ ማስታወሻ* 1915 ዓ.ም።
- __________፤ *ነቅዐ ንፁሕ ዜና ሐዋርያት* 1923 ዓ.ም፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
- __________፤ *ዋዜማ* /በማግሥቱ የኢትዮጵያ ነገሥታትን በዓል ለማክበር/ 1921 ዓ.ም ጎሕ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አሥመራ።
- ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ /ሊቀ ካህናት/ M.A፤ *ታሪክ ነገሥት አብርሃ ወአፅብሐ፣* 1989 ዓ.ም ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ።
- አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ /ሊቀ ጠበብት/፤ *መጽሔተ አሚን፣* ሚያዝያ 30 ቀን 1946 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
- __________፤ *መርሐ ልቡና* ሚያዝያ 1 ቀን 1945 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።







- አያልነህ ሙላቱ፤ *የሥነ ጽሑፍ ቅኝት፣* 1977 ዓ.ም አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ።
- አድማሱ ጀንበሬ /መልአከ ብርሃን/፤ *መጽሐፈ ቅኔ* /ዝክረ ሊቃውንት/ ጥቅምት 1 ቀን 1963 ዓ.ም፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
- በቤተ ክህነት ታሪክና ድርሰት ዝግጅት፤ *መርሐ ምዕመናን፣* ጥር 6 ቀን 1946 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
- በስደስ ያለች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፤ *አራተኛ ክፍል የቤተ ክርስቲያን ጸሎት ሁለተኛ ድርሰት፣* 1966 ዓ.ም ኢየሩሳሌም።
- ተስፋ ወልደ ሥላሴ /አባ/፤ *እስከ ማዕዜኑ ተሐነክሱ በክሌሆን ጌጋያቲክሙ* የካቲት 7 ቀን 1952 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ።
- ተክለጻድቅ መኩሪያ፤ *ከጣኦት አምልኮ ወደ ክርስትና፣* 1941 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ።
- __________፤ *የግራኝ አሕመድ ወረራ፤* 1966 ዓ.ም ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ።
- __________፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ አክሱም ዛጉዬ፤* 1951 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
- __________፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ /ናፓታ መሮዌ/* 1ኛ መጽሐፍ የካቲት 1 ቀን 1965 ዓ.ም ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
- __________፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ* 8ኛ እትም 1964 ዓ.ም ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
- ታዕካ ነገሥት ባዕታ ለማርያም ገዳም፤ *መስቀል ገብረ ሕይወት* 1961 ዓ.ም ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
- ታደስ ወልዴ /ቀኛዝማች/፤ *የእቴጌ ጣይቱ ብጠል አጭር የሕይወት ታሪክ* 1980 ዓ.ም ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፤ አዲስ አበባ።
- ታዬ /አለቃ/፤ *የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፣* 1964 ዓ.ም ሴንትራል ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።
- ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፤ *የቅዱስ ያሬድ ታሪክና የዜማው ምልክቶች* ግንቦት 15 ቀን 1959 ዓ.ም አዲስ አበባ።
- __________፤ *እድገትና ነፃነት በኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣* ጥቅምት 15 ቀን 1944 ዓ.ም አዲስ አበባ።




www.ethiopianorthodox.org

- __________፤ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ነሐሴ 1986 ዓ.ም አዲስ አበባ::
- __________፤ *አዲሲቱ ኢትዮጵያ*፣ ሚያዝያ 15 ቀን 1945 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ::
- ከበደ ተሰማ /ደጃዝማች/፤ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ 1962 ዓ.ም አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ::
- ክፍያለው መራሒ /ቄስ/፤ *የቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ ኢትዮጵያ ሥልጣኔ*፣ 1986 ዓ.ም አዲስ አበባ::
- ኪዳነወልድ ክፍሌ /አለቃ/፤ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፣ 1948 ዓ.ም አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ::
- __________፤ *መዝገበ ፊደል* 1957 ዓ.ም አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ::
- ኪዳነማርያም ገ/ሕይወት /መምህር/፤ *ስለ ዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ርስትነት መብታችሁን ጠብቁ*፣ ነሐሴ 10 ቀን 1953 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ::
- ኪዳነማርያም ጌታሁን /መምህር/፤ *ጥንታዊው የቆሎ ተማሪ*፣ የካቲት 15 ቀን 1980 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ::
- ክንፉ ኪዳኔ /አዝማች/፤ *የአክሱም ጥንታውያን ገንዘቦችና የአሠሯቸው ነገሥታት*፣ 1960 ዓ.ም በትሪንጋሊ ማተሚያ ቤት አሥመራ::
- *ዐጼ ኃይለሥላሴና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን* መጽሔት የንጉሡን በክብር ሲያርፍ የወጣ፣ ጥቅምት 23 ቀን 1992 ዓ.ም አዲስ አበባ::
- ዘመድኩን በቀለ፤ *ቅዱሳት መካናት በኢትዮጵያ*፣ ክፍል አንድ 1992 ዓ.ም አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ::
- *ዜና ቤተ ክርስቲያን* ልዩ እትም መስከረም 10 ቀን 1966 ዓ.ም አዲስ አበባ::
- ዜና ቤተ ክርስቲያን 24ኛ ዓመት ቁጥር 38፣ 54፣ 58፣ 1961 ዓ.ም አዲስ አበባ::
- *ዜና ቤተ ክርስቲያን* ሐምሌ 1991 ዓ.ም አዲስ አበባ::
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ፣ *የዛሬዋ ኢትዮጵያ የቅዱሳት መጻሕፍትና የሥነ ጥንት ኢትዮጵያ ናት*፣ 1991 ዓ.ም ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ::
- *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ*፣ 2000 ዓ.ም አዲስ አበባ::
- የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት፤ *የቅዱሳት መካናት መስታወት*፣ 1973 ዓ.ም አዲስ አበባ::







- *የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት አሥር ዓመት የሥራ እርምጃ*፣ 1965 ዓ.ም ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ::
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ዝግጅት፤ *ትንሣኤ የሃያ አምስት ዓመታት መንፈሳዊ እርምጃ*፣ 1964 ዓ.ም አዲስ አበባ::
- *የአማራ ክልል የቱሪስት መስህብ ሀብቶች አጭር ቅኝት*፣ 1991 ዓ.ም አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ::
- *የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አብያተ ክርስቲያናት የመሪዎች ጉባኤ የሰጣቸው ውሳኔዎች*፣ 1958 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ::
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት፤ *የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ*፣ 1990 ዓ.ም ንግድ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ::
- *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ትናንት ዛሬ እና ነገ በዓለም መድረክ*፣ ሐምሌ 5 1989 ዓ.ም አዲስ አበባ::
- ደስታ ተክለወልድ፤ *ገበታ ዋሪያ የንባብ መማሪያ*፣ 3ኛ መጽሐፍ 1928 ዓ.ም በቅዱስ አላዛር ማተሚያ ቤት ድሬዳዋ::
- ጎርጎርዮስ /ሊቀ ጳጳስ/ M.A፤ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ* 1991 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ::
- __________፤ *የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ*፣ 1978 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ::
- ገብረዮሐንስ ገብረማርያም M.A፤ *ክርስትና በኢትዮጵያ* ክፍል አንድ የካቲት 1988 ዓ.ም አዲስ አበባ::
- ገብረሥላሴ ወልደአረጋይ /ጸሐፌ ትዕዛዝ/፤ *ታሪክ ነገሥት ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ* 1956 ዓ.ም አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ::
- ግርማ ኤልያስ *አክሱማዊት ፋና ወጊ*፣ 1991 ዓ.ም ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ አዲስ አበባ::
- ጥዑመ ልሳን ካሳ /ርዕሰ ደብር/፤ *ያሬድና ዜማው*፣ 1981 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ::




www.ethiopianorthodox.org